በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2010/2011 ኦዲት ዓመት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ግንቦት / 2011
አዲስ አበባ

ማውጫ

ተ/ቁ		ገጽ
1	መግቢያ …………………………………………………………………..	1
2	የ2010/2011 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም ………..	5
3	የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች ………………………………………	17
4	የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ………	53
5	የክዋኔ እና የአካባቢያዊ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሳቦች ……………………………………………	59
6	የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ………………………	213
7	ልዩ ኦዲት ……………………………………………………………	222
8	የ2010/2011 ኦዲት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ……..	224

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2010/2011 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች

ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም

1 መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55/1 እና አንቀጽ 101/4 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን በማንገብ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣

- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

1.1. <u>የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ስርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመ/ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያድረግ ይችላል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እንዳአስፈልጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤

- አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኃን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ ይህን ሂሳብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፣ መዘክሮች፣መዝገቦች ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥ ነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አያያዝ፣አጠባበቅ፤ የሂሳብ አያያዝና ንብረት አስተዳደር በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈለጊውን ምክር ይሰጣል፤
- ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ጋር የፌዴራልና ክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤
- ከክልል የኦዲት መ/ቤቶችና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

1.2. የሪፖርቱ ዓላማ

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 በአንቀጽ 13/1 እስከ 4 መሠረት በ2010/2011 የኦዲት ዓመት ባከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2010 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ የ2010/2011 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች መሰረት ያደረጉት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የ2010 በጀት ዓመት ሒሳብ ኦዲት፤ የክዋኔ ኦዲቶች፣ የአለም ባንክ እና ሌሎች የልማት አጋር ድርጅቶች የሚሰጡትን የመሰረታዊ ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግስት በገባው ውል መሠረት በብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን

ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤት እና በመ/ቤታችን የተከናወኑ የልዩ ኦዲት ሥራዎችን ነው፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሣቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ስራም የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፤ የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት መሠረት በማድረግ እና በኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2010/2011 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የ2010/2011 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ኦዲት ዕቅድና አፈፃፀም፤ ዋና ዋና የድጋፍ ስራዎች ክንውን ሪፖርት፤ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፤ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ ቀርቧል።

በሁለተኛው ክፍል የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የአካባቢና የክዋኔ ኦዲት፤የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤ እንዲሁም መንግሥት ከዓለም ባንክ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ

ፕሮግራም (PBS III) ኦዲት እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም(Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የማረጋገጥ ሥራዎች የተከናወኑ እና በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን የ(PBS III) ሂሳብ ኦዲት ውጤት ያጠቃልላል፡፡

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶችና በመንግስት እና በልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የኦዲት ውጤትን የሚመለከት ነው፡፡

2 የ2010/2011 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ አምስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ የካቲት /2010 እስከ ጥር 30/2010፤ በዚሁ መሠረት በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 182 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 176 መ/ቤቶችንና 46 ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውን እና የመንግስት አጠቃላይ ገቢን ወጪ ሂሳብ ኦዲት በመ/ቤታችን አማካይነት፣ የተቀሩትን ስድስቱን ደግሞ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል የታቀደ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 176 መ/ቤቶች መካከል የአንድ ዩኒቨርሲቲ ኦዲት በወቅታዊ ፀጥታ ችግር በመቋረጡና አንድ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ሂሰቡን ዘግቶ ማስመርመር ባለመቻሉ የ174 መ/ቤቶችና 46 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ መንግሥት የ2010 በጀት ዓመት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትም በመከናወኑ በአጠቃላይ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸም 98.87% ሆኗል፡፡ በዚህም ከመ/ቤታችን ቁጥጥር ውጭ በሆነው ምክንያት የ2010 የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሽፋን ቀደም ባሉት ዓመታት ከነበረበት 100% ወደ 98.87% ዝቅ ሊል ችሏል፡፡

የኦዲት ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2008 እና 2009 በጀት ሂሳብ ኦዲት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2008	2009	2010
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	27	25	25
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	73	87	89
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	5	8	11
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	53	53	49
የኦዲት ስራው የተቋረጠ			1
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ	-	-	1
ድምር	158	173	176

2.2 <u>የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ ክትትል ተደርጓል፡፡

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ጥር1/2010 እስከ የካቲት 30/2011 ዓ.ም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 65 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 170 በድምሩ 235

(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 226 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.3 <u>የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ</u>

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል በመወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታተቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ይከናወናል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2010-2011 የኦዲት ዓመት (Audit Calendar) በሁለቱ ክዋኔ ኦዲት ደይሬክቶሬቶች ከየካቲት/2010 እስከ ጥር 30/2011 የሚጠናቀቁ 24 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክዋኔ ክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች አፈጻፀም ሲታይ በእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው፤ 20 የአዳዲስ ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላኩ፤ 3 የክዋኔ ልዩ ኦዲት ስራው ተጠናቆ ኦዲት ሪፖርቶች የተላኩ ሲሆን፤ በ 5 ቀደም ባሉት ክዋኔ ኦዲቶች ላይ የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር ላይ የክትትል ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት የክትትል ኦዲቱን ሲጨመር ከ93.33% በላይ መሆኑን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 20 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶችና የ5 የክትትል ኦዲት ሪፖርቶቹ ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶች በአጭሩ ቀጥሎ ከገጽ 61 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.4 አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካል ተልኮል፡፡ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከተጠቀሱት ጥቂት ስሕተቶች በስተቀር ሂሳቡ የፋይናንስ ገጽታውን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያል የሚል ሲሆን፤ የኦዲት ሪፖርቱ በገጽ 54 ቀርቧል፡፡

2.5 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተም የ2010/2011 ኦዲት ዓመት በ264 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ደረጃ)፣ ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋዊ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በኦዲት ዓመት የ231 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ተልኳል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤቱ ከመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲት በተጨማሪ የወረዳዎች የፍትሃዊ የሃብት ተጠቃሚነት የ“Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service” ፕሮግራም ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ መለኪያዎችን የማረጋገጥ ጥያቄዎች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሲቀርብ የማረጋገጥ ሥራው ያካናውናል፡፡ በዚሁ መሰረት የ10 ክልሎች የ”ESPES” ኦዲቶች፤የፌደራል መንግስት የፋይናንስ እና በጀት አስተደደር ማኑዋል ማዘገጀቱን ማረጋገጥ፤ የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ም/ቤት የፋይናንስና በጀት ቋሚ ኮሚቴ አባላት በበጀት፣ በወጭ አስተዳደር እና በኦዲት ክትትል ላይ ስልጠና መውሰዳቸውን ማረጋገጥ እና የፌዴራል መንግስት ለክልል መንግስታት የሚመደበው በጀት ጭማሪ ማሳየቱን (ፐር ከፒታ) ማረጋገጥ በሚሉ 3 የማረጋገጫ ኦዲቶች ተጠቃልሎ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

2.6 ልዩ ኦዲት

በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት ጥያቄ 25 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 14 ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቀው ሪፖርቱ ለጠያቂ አካል የተላከ ሲሆን ሌሎቹ የተቀሩት 11 ኦዲቶች በመሠራት ላይ ናቸው፡፡

2.7 የኦዲት ጥራትና ሌሎች የኦዲት ሥራዎች

በመ/ቤቱ የሚከናወኑ ኦዲቶች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን ጠብቆ እንዲሠሩ የዚህ ዓመት ዕቅድ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የኦዲት ጥራት የሥራ ክፍልም ይህንኑ መሠረት በማድረግ የቅድመ እና የድህረ ኦዲት ቁጥጥር ሥራዎችን ለማከናወን አቅዷል፡፡ የኦዲት አገልግሎት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአሰራር ሂደት፣ የላቀ መሪነት እና የላቀ መልካም ግንኙነትና ቅንጅት ያለዉ ተቋም ለማድረግ የታቀዱት ስትራቴጅክ ዓላማዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ኦዲቱ በISSAI እና በAFROSAI-E Regularity Audit Manual (RAM) መሰረት መከናወኑን በማረጋገጥ ነው፡፡

በመሆኑም በመ/ቤቱ የጥራት ማረጋገጥ ክለሳ ሥራን በተለያዩ የኦዲት ደረጃዎች /phases/ ያሉትን በ6 የቅድመ ኦዲት /Pre engagment audit/፣ 12 የስትራቴጅክ እቅድ /Strategice plan/፣ በ12 ኦዲት ሥራዎች ደረጃዎች ላይ በዝርዝር እቅድ ደረጃ ላይ የቅድመ ኦዲት ሪፖርት እና የኦዲት ሪፖርታቸዉ ወጪ በተደረጉ 6 የኦዲት ሥራዎች ላይ የድህረ ኦዲት ሪፖርት (Post-Issuance) በሪፖርት ደረጃ (Conclusion and Reporting phase) በድምሩ 36 የጥራት ማረጋገጥ ክለሳ ሥራ ለመስራት የታቀደ ሲሆን አፈጻፀሙም በዕቅዱ መሠረት 36 ሥራዎችን በማካናወን የዕቅዱን (100%) ተሰርቷል፡፡

በተቋሙ የኦዲት ጥራት ዳይሬክቶሬት እና በAFROSAI-E peer review ጥራት ማረጋገጥ ሪፖርት መሰረት በስትራቴጂክ እቅድና በዝርዝር እቅድ ላይ የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች መተግበራቸውን ለመከታተል ታቅዶ የክትትል ሥራው ከላይ የስትራቴጂክና የዝርዝር እቅድ በተከናወነባቸው መ/ቤቶች ላይ ክትትሉ ተከናውኗል።

3 ሌሎች ዋና ዋና የዕቅድ ክንውኖች

3.1. የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

የለውጥ ሥራዎችን በተመለከተ ካለፈው በጀት ዓመት ጀምሮ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ወጤት ተኮር ሥርዓትን ተከትለው ማቀድ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን በመ/ቤትና በሥራ ክፍሎች ደረጃ የተዘጋጁትን ዕቅዶች ቆጥሮ እያንዳንዱ ፈፃሚ ጋር በማድረስ ረገድ የሚንጠበጠቡ ጉዳዮች የሚታዩ በመሆኑ ሊጠናከሩ የሚገቡ ሥራዎች አሉ፡፡ በሌላ በኩል የተሠሩ ሥራዎችን አፈፃፀም በውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት መመዘን የተጀመረ ቢሆንም ተገኘ የሚባለውን ውጤት በየዕለቱ በተፈፀሙ ተግባራት ማስረጃ በማስደገፍ ረገድ አሁንም ቀሪ ሥራዎች ይታያል፡፡ በመሆኑም ለብዙ ጊዜ እተሞከረ ያለውን የአውቶሜሽን ሥርዓት ከጨፍ በማድረስ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ዕየተሠራ ይገኛል፡፡

የውስጥም ሆነ የውጭ የመልከም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍና ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚመለከተውን ወስዶ እየሠራበት ሲሆን አንዳንዶቹ ችግሮች ሙሉ በሙሉ የተወገዱ ቢሆንም ተመልሰው ብቅ እንዳይሉ ከለውጥ ሥራው ጋር በማቀናጀት ዘላቂ አሠራር ተዘርግቶላቸው በመደበኛ እንዲሠራባቸው እየተደረገ ይገኛል፡፡

3.2. ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

በዚህ ረገድ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና እንዲፈጽሙ ቼክሊስት ተዘጋጅቶ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ በተለይ በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲት የሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በዕቅድ ውስጥ ተካቶ በጥልቀትም ባይሆን እየታየ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል በመደበኛነት ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት እንደዚሁም የኤ. አይ. ቪ. ኤዲስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች እየታጀቡ በመ/ቤቱ እየተከበሩ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በየሁለት በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ የነፃ ትምህርት ዕድል በማፈላለግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት እንደተደረገው ሁሉ በዚህም ዓመት 8 ለሚሆኑ ተጨማሪ ሴት ሠራተኞች ዕድሉ የተመቻቸ ቢሆንም አራት ሠራተኞች ብቻ ዕድሉን ተጠቅመው በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

3.3. <u>የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱንና የሠራተኛውን አቅም ከመገንባት አንፃር የተለያዩ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

እንደሚታወቀው የመ/ቤታችን የማሠልጠኛ ተቋም አንዳንድ ቀሪ ተግባራቶች ቢኖሩም ተጠናቅቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ ዋንኞቹ ቀሪ ሥራዎች ከመዋቅርና የሰው ሀይል ምደባና ቅጥር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነኚህ በሂደት የሚጠናቀቁ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቀደም ሲል የተዘጋጀውን ሞጁሎች በመጠቀም የሠራተኞቻችንን ክህሎት ለማሳደግ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በተለያየ ዙር ወደ 296 የሚሆኑ ሠራተኞችን በማዕከሉ ለማሠልጠን ተችሏል፡፡

ሁሉንም የመ/ቤቱ ሥራዎቻችን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ታልሞ ከብሪታኒያ መንግሥት (DFID) በተገኘ የ 2,000,000 የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ከሀምሌ 2009 ጀምሮ ሲሠራ የነበረው የዳታ ማዕከል ግንባታ ተጠናቅቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም ከመንግሥት በተመደበ ብር 10,970,523.72 የአዲሱ ህንፃ ግንባታ አካል ሆኖ በመንግሥት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጅክት ጽ/ቤት በኩል ሲከናወን የነበረው የኔትወርክና ተጓዳኝ ሥራዎችም ቢዘገይም በአሁኑ ወቅት ተጠናቅቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ እነኚህ ሁለቱም ፕሮጅክቶች ሁሉንም የመ/ቤታችንን ሥራዎች በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ያለምነውን ዓላማ በማሳካት ረገድ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ከመሆኑም በላይ ወጪ በመቀነስ፣ የሥራ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነትን በማጎልበት ተልዕኮአችንን በተሻለ ደረጃ እንዲናሳከ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሠራ የነበረው የኦዲት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የአማካሪ ድርጅት ቅጥር ሥራ ረዥም ጊዜ የወሰደ ቢሆንም በቅርቡ የግዥው ሂደት ተጠናቅቆ በአማካሪ ድርጅቱና በገንዘብ ሚኒስቴር መካከል

በሚያዝያ 2011 ውል የተፈረመ ሲሆን በያዝነው ግንቦት ወር ሥራውን ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ሲቀረፅ የአራት ዓመት ዕድሜ እንደሚኖረው የታሰበ ቢሆንም አሁን የቀረው አንደ ዓመት ብቻ በመሆኑ የታሰበውን ያክል ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ባይታሰብም የምንችለውን ያክል ለመጠቀም ጥረት የምናደርግ ይሆናል፡፡

3.4. የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 645 እና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 314 በድምሩ 959 ሠራተኛ ነው፡፡ የኦዲት ሥራው በየካቲት ወር 2010 ሲጀመር 423 ኦዲተሮችና 214 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 637 ሠራተኛ በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 87 ኦዲተሮችና 18 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 105 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን በዚሁ ዓመት ውስጥ 12 (ከድጋፍ 2 እና ከኦዲት 10) ሠራተኞች በጡረታ 1፣ በሞት 1፣ በዲሲፕሊን 50፣ ኦዲተሮችና 22 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 72 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን በአጠቃላይ በኦዲት ዓመቱ 86 የሚሆን የሰው ኃይል ከመ/ቤቱ ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 451 የኦዲት ባለሙያዎች (296 ወንዶችና 155 ሴቶች)፣ 206 የድጋፍ ሰጪ (92 ወንዶችና 114 ሴቶች) ሠራተኞች በአጠቃላይ 657 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 305 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት ምክንያት ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

3.5. የ2010 በጀት ዓመትና 2011 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

በ2010 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 124,242,770.86 በጀት ተፈቅዶ የነበረ ቢሆንም በተደጋገሚ ወጥቶ ባልተሳከው ጨረታ ምክንያት ከሚያዝያ 30 ቀን 2010 በፊት ብር 47,170,312.25 ገንዘብ ሚኒስቴር ለሌሎች መ/ቤቶች እንዲያስተላልፍ ተደርጎ ከቀሪው ብር 87,072,458.61 ውስጥ ብር 79,566,825.75 ወይም 91% ሥራ ላይ የዋለና ያልተሰራበት ብር

7,505,632.86 (9%) የነበረ ሲሆን፣ ለ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው መደበኛ ብር 84,464,860.00 ለካፒታል ብር 17,000,000.00 በድምሩ ብር 101,464,860.00 ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2011 ሥራ ላይ ለማዋል የታቀደው የዘጠኝ ወር በጀት ብር 64,537,446.59 ሲሆን በዘጠኝ ወር ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 58,080,831.23 ወይም 89.99% ሆኗል፡፡

3.6. መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

በኦዲት ተደራጊዎች በኩል አሁንም ያልተሻሻሉና በጊዜ አጠቃቀማችን ጭምር ተፅዕኖ እያስከተሉ ያሉ ጉዳዮች በኦዲተሮቻችን የሚጠየቁትን ማስረጃዎች በወቅቱ ያለማቅረብ ወይም ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፤ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገና ለኦዲተሮች ሌላ ስምሪት ከተሰጠ በኋላ በኦዲት ወቅት ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት በርካታ ሠነዶችን መ/ቤታችን ድረስ ጭነው ማምጣት፣ ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት ናቸው፡፡ እነኚህ ጉዳዮች አንዳንዴ ሆን ተብሎ እየተፈጠሩ ኦዲተሮቻችንን ጫና ውስጥ በመክተት በተለይ በኦዲት ማጠናቀቂያ ወቅት ትኩረት እንዲያጡና ተገቢውን ጊዜ ሰጥተው ሠነዶቹን እንዳይመረምሩ ጭምር የሚሠሩ ሥራዎች በመሆናቸው ህጉ የሚፈቅደውን አግባብ ተከትለን እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት በየዓመቱ ተመሳሳይ ችግር የሚፈጥሩ ኦዲት ተደራጊዎች ህግና ሥርዓት ተጠብቆ ሠነዶችና መዝገቦች ኦዲተሮች በጠየቁበት ጊዜ በወቅቱ ሊያቀርቡላቸው ይገባል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን፤ የሀገር መከላከያ፤ የገቢና ጉምሩክ ቅርንጫፎችንና ሌሎች ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ የፌዴራል መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ኦዲተሮቻችን ከሌለው የመንግሥት ሠራተኛ በተለየ ሁኔታ ዓመቱን በሙሉ የሚቆዩት መስክ ላይ ነው፡፡ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመስክ የሚከፈላቸው የቀን ውሎ አበል ወጪያቸውን ሊሸፍን ባለመቻሉ ኦዲተሮቻችን አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሥራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ ለሁለትና ሦስት ቀናት ብቻ መስክ ቢሄዱ ችግሩን እንደምንም ሊቋቋሙ ይችላሉ ተብሎ ሊታሰብ ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ዓመቱን ሙሉ መስክ ስለሚቆዩ ችግሩ እጅግ ግዙፍ ነው፡፡

መንግሥት ይህንን ልዩ የሆነውን ሁኔታ ተገንዝቦ ለችግሩ መፍትሄ እንዲሰጠን ብንጠይቅም እስከ አሁን ያልተፈታ በመሆኑ ም/ቤቱ ይህንን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶት እንዲፈታልን በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ሌላው በዚህ ዓመት ያጋጠመን ችግር በወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ ኦዲተሮቻችን ሥራዎቻቸውን በአቀድነው ጊዜ ሠርተው ማጠናቀቅ አለመቻለቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን ከእኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነው ምክንያት ኦዲት ልናደርጋቸው ካልቻልነው ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች በስተቀር ጊዜውን ገፋ ብያደርግብንም ሠራተኞቻችን ባሳዩት ከፍተኛ ቁርጠኝነት የዓመቱን ዕቅድ ማሳካት ተችሏል፡፡

ማጠቃለያ

የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች (አንዱ በወቅታዊ የፀጥታ ችግር ሌላኛው ሂሰቡን ሊዘጋ ባለመቻሉ) በስተቀር በሌሎች የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በታቀደው መሠረት ተከናውኗል፡፡ ነገር ግን ከመ/ቤታችን ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት የሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች ሂሳብ ኦዲት ስላልተጠናቀቀ የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ክንውን መቶ በመቶ መፈፀም አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሽፋኑ ካለፉት ዓመታት ወደ ኋላ ተንሸራትቶ 98.87% ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 24 አዳዲስና 6 የክትትል ኦዲት በድምሩ 30 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 23 አዳዲስና 5 የክትትል በድምሩ 28 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም በአንደ የክትትል ኦዲት አንሶ የተፈጸመ ቢሆንም የዕቅድ አፈፃፀሙ አምና ከነበረበት 92.86% ወደ 93.33% ተሻሽሎ ተገኝል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ264 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ231 (87.5%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲት ዕቅድ ክንውን በዚህ ደረጃ እንዲያንስ የሆነበት ምክንያት በርካታ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች ከተለያየ አካላት በመቅረባቸውና የሰው ሃይሉን ለነኚህ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሥራዎች አዛውሮ እንዲሠራ በመደረጉ ነው፡፡ ከመደበኛው ኦዲቶች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በርካታ ልዩ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን ከፍሎቹ ተጠናቅቀው ለሚመለከታው አካል የተላኩ ሲሆን ቀሪዎቹ አሁንም በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤት መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ባለፉት ዓመታት የታዩትን የአሠራር ግድፈቶችን በማረምና የተዘረገውን የመንግሥት የፋይናንስ፣ ግዢ እንዲሁም የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ተከትለው በመሥራት ረገድ አሁንም አብዛኛዎቹ በሚጠበቀው ልክ ለውጥ እያሳዩ አይደለም፡፡

ስለሆነም እነኚህ የኦዲት ግኝቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው እርምጃ ተወስዶ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይህንን ያላደረጉ ተቋማት ደግሞ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱና አጠቃላይ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ28 ጥራዝ፣ አስተያየት ሊሰጥባቸው ያልተቻለ የ11 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርትና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው የ49 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ለየብቻ ተዘጋጅተው ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን የም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተውና ተመርምረው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትልና ግፍት ሊደረግ ይገባል፡፡

እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በ2010 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲትም ወቅት በዋንኛነት የኦዲት ግኝት ሆነው የቀጠሉት ከጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የውዝፍ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ ወይም አለመወራረድ፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚከናወኑ ግዥዎችና እንደዚሁም ከህግና ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ አላግባብ የሚፈጸሙ የጥቅማ ጥቅምና ሌሎች ክፍያዎች፣ አላግባብ በብልጫ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣ ከውል አስተዳደር ጋር የሚታዩ ግድፈቶች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተደጋጋሚ ግድፈቶች፣ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ጉድለቶች፣ የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር ተያየዞ የሚታዩ ክፍተቶች እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ

የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረጉት የክዋኔ ኦዲቶች በርካታ ሊዘረጉ ሲገባ ያልተዘረጉ የየመ/ቤቶቹን ቅልጥፍናና ውጤታማነት እንዲሁም ለተልኮ ስኬት አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩ የህግ እና የአሠራር ሥርዓቶች ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ከተልዕኮ ስኬት አንፃር በርካታ የአፈፃፀም ጉድለቶች ታይቷል፡፡

በመ/ቤታችን የሚደረጉ የፋይናንስና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ጉድለቶችንና ክፍተቶችን ብቻ የሚናገሩ ሳይሆን የማሻሻያ አስተያየቶች ጭምር የሚያካትቱ በመሆኑ በአግባቡ ቢተገበሩ የኦዲት ተደራጊዎችን አሠራርና አፈፃፀም በማሻሻል ለተልዕኮአቸው ስኬት ዓይነተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደረጊዎች የሚሰጡት የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቅሙት ራሳቸው እንደሆነ ተገንዝበውና አምናው ተቀብለው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

እስከ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊዎች በዚህ መልኩ አምነው ተገቢውንና በቂ እርምጃ እየወሰዱ ባለመታየቱ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይችሉ የነበሩ የኦዲት ግኝቶች በየዓመቱ ተደጋግመው እየታዩ በመሆኑ በየደረጃው ያሉ አካለት ማለትም የተከበረው ም/ቤት፣ የሚኒስትሮች ም/ቤት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሁም መ/ቤቶቹ ተጠሪ የሆኑባቸው ተቋማትና የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አግባብ የሆነውን የተጠያቂነት እርምጃ እንዲወስዱ እንዲያደርግ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ሕጋዊነት ኦዲት
ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

መ/ቤታችን በ2009/2010 የኦዲት ዓመት በ174 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና በ48 ቅ/ጽ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ ባቀደው መሰረት የ173 መ/ቤቶችና የ44 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን በኦዲቱ የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ክፍል የሚነሱ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች አብዛኞቹ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1) የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ 3 መ/ቤቶች ብር 960,832.66 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 102,532.99 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-2/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-3/ሀ-ሰ እና አባሪ-4፣4/1 እና አባሪ-5 እና 5/1 ተመልክቷል፡፡

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ2 መ/ቤቶች ብር 694,110.02 መሆኑ፤
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ3 መ/ቤቶች ብር 7,131,997.25 መገኘቱ፣
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 525,637,742.86
- በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው በ2 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ት/ቤቶች ብር 411,532.99 መሆኑ ፤
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ3 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 214,749,495.37 መገኘቱ እና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,150,445.75 መደበኛ ሚዛን ያልሆኑ- (መክፈቻ ሚዛን) (ክሬዲት ባላንስ) ያለው የጥሬ ገንዘብ የተገኘባቸው፤
- የተጣራ ሃብት ሂሳብ 5601 የመነሻ ምዝገባ ያልተደረጋላቸው በ1 መ/ቤት ብር 67,785.40 እና በ1 መ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ (4101) የመነሻ ሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገባቸው ብር 10,037.61 መኖሩ፤

- ዓመታዊ ቆጠራ ባለመካሄዱ በሰኔ 30/2010 ሂሳብ ሪፖርት ላይ በካዝና የሚታይ ጥሬ ገንዘብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር495,016.36፤
- በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ያልተካተተ በ1 መ/ቤት ብር 74,913,188.22፣
- የባንክ ማስታረቂያ ሚዛን በትክክለኛ የሂሳብ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የማጠቃለያ ሂሳብና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፤ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2 የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1. <u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ129 መ/ቤቶች እና በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,252,562,207.37 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-6 እና አባሪ-6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	2,316,439.51
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	809,921,206.58
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	1,269,686,923.83
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,394,657,718.74
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	410,241,540.57
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	365,738,378.14
ጠ/ድምር	ብር	4,252,562,207.37

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 763,279,769.15፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 2,356,252,611.41፤ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 524,990,497.56 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 168,604,776.56 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 439,424,322.50 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡ በተጨማሪም በ8 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,298,391,518.67 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቢ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 608,731,337.69፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 441,828,292.09፤የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,520,418.09፤የቀድሞ የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር282,965,014.42፤ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር256,674,976.65 ፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 250,218,048.94፤ ፤ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 169,647,495.93 ፤የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 160,457,088.68፤ ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 153,255,211.99 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር114,611,493.86፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 111,362,647.02፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 108,079,052.31 እና ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር102,777,501.69 ይገኙበታል፡፡ የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብም፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 1,203,900,478.44፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 33,064,845.86 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 23,412,458.30 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2. <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ(Abnormal balance) የሚታይባቸው፤ በ10 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 52,054,783.31 መሆኑ፣
- በአንድ መ/ቤት ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 9,712,330.24 መኖሩ፤
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት ተሰብሳቢ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 361,743,928.36 መገኘቱ፤
- በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በተጣራ ሀብት የተመዘገበ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 60,574.43

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ ሠ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4 የገቢ ሂሳብ

4.1 <u>በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር

302,835,172.76 ፤በሌሎች በ59 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤት ብር 54,615,686.58 በድምሩ ብር 357,450,859.34 የንግድ ትርፍ ግብር፤ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 15 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 53,033,612.64 ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-9 እና 9/1 እስከ አባሪ - 9/3 እና 9/4 ተመልክቷል/

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	302,835,172.76
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	13,058,191.32
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	9,848,324.35
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	18,717,284.32
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	2,324,341.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	10,667,544.72
ጠ/ድምር	ብር	**357,450,859.34**

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- የሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 129,320,116.87 ፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,103,121.15፤ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,515,511.90፤ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 25,685,575.29 እና የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 15,699,207.46 ሲሆን ፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 12,625,775.80፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 10,666,140.00 እና በፌዴራል የቴክ/ሙያ ትም/ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 5,723,497.08 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣

- የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ፤
- በግብይት ዋጋ(FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ(marine insurane) ወጪ ባለመደመሩ፣
- እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው
- የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ ፣
- በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ ባለመካተቱ፣
- በትክክለኛ የቀረጥና ታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ እና ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸው አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ በመደረጋቸው
- በ2009 ዓ.ም በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ልዩነት ያለው በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ፣
- ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር በመኖሩ፣
- ዕቃው በዲክላራሲዮን ላይ በተመዘገበበት ቀን በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ባለመሰላቱ፤
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት የሽያጭ ገቢያቸውን ባለማስታወቃቸው እና በመሳሰሉት ሲሆን፤
- በሌሎች መ/ቤቶችም ከፈጸሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት በ16 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በ3 መ/ቤቶች ከውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ውዝፍ የአገር ውስጥ ግብር መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 7,670,055,993.73 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,323,297,368.69፣በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የፍ/ቤት ውሳኔ ክትትል ምዝገባ መካከል የታየ ልዩነት፣ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,312,069,929.97፣ በቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን ለዋና መ/ቤት ያቀረቡ የተባሉ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም ግብር ከፋዮቹ በዋና መ/ቤት የክትትል መዝገብ ላይ ዝርዝራቸው ያልገኘ የግብር ዕዳ ውሳኔ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 481,837,038.37፣ የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታን በተመለከተ ዋና መ/ቤት ውሳኔው በፍርድ ቤት ክትትል ላይ ያለ መሆኑን መረጃውን የያዘ ሲሆን፣ ቅ/ጽ/ቤች ግን በዕዳ ክትትል መዝገባቸው ላይ መዝግበው ያልያዙ በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 6,895,954,886.08፣ ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ መጠን በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር109,687,117.26 መኖሩ እና በጉምሩክ አስመጪዎች የቀረበ አቤቱታ ለዋና መ/ቤት የቀረበና አቤቱታ ተገቢው ውሳኔ ሳያገኝ የቆየ የቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 6,699,429.01 በመኖሩ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-8 እና 8/1 እና 8/1 ሀ - ረ ተመልክቷል/

በተጨማሪም የሱቅና የቢሮ ኪራይና በሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ፤ ወለድና ቅጣት በ4 መ/ቤቶች ብር 3,634,488.76 ፤ የመንግስት ነፃ ሕክምና መብት ተጠቃሚ ከሆኑ ኃላፊዎች ያልተቀነሰ የሕክምና መዋጮ በ4 መ/ቤቶች ብር 16,081.84 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ፤ በአንድ መ/ቤት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ ብር379,831.22 እና የአሜሪካ ዶላር 156,536.17 መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ አባሪ 9.1 እስከ 9.4 ተመልክቷል፡፡

ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,452,745,400.00፤ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 991,128,073.20፤ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 549,978,782.00፤ ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 484,094,194.69፤ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 411,555,324.63 ፣ እና ድሬ ዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር188,798,632.61 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 89,033,639.59 ወጪው በዝርዝር የቀረበ ባለመሆኑና ተቀባይነት ያለው ወጪ

ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የገቢው ሁኔታ በዝርዝር ሳይገለጽ ከገቢ ላይ የተቀነሰ ወጪ መጠን ዝርዝር ወጪው ሳይገለጽ ከገቢ የተቀነሰው የወጪ መጠን ብር 64,680,345.98፣ በሌሎች 4 ቅጽ/ቤቶች የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣ ብዛታቸው 399 የሆኑ ዲክለራሲዮን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ያልቀረበው በገንዘብ መጠን ብር 748,971,389.57 ፣እንዲሁም ዕቃ ወደ አገር ለማስገባት በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ቀረጥና ታክሳቸው ግን በቅ/ጽ/ቤቱ ሳይሰላ የቆየ፣በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 50,616,773.33፣በ7 መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን/ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 12,533,320.71 እና በሌሎች 1 መ/ቤት ብር12,900.00 በተመኑ መሠረት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ ወጪው በዝርዝር የቀረበ ባለመሆኑና ተቀባይነት ያለው ወጪ ስለመሆኑ በዝርዝር ሳይገለጽ ከገቢ ላይ የተቀነሰ ወጪ መጠን፣ የተሟላ መረጃና ዲክላራሲዮን ባለመቅረቡ፣ ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፣ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች 40 ግብር ከፋዮች እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 34 ግብር ከፋዮች በድምሩ 74 ግብራቸውን ያላሳወቁ በመሆኑ፣ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም፣ ስለመክፈላቸው/ ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በገቢ ያልተመዘገበና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተተ የገቢ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች ፡-

ብር 157,466,831.46 የገቢን ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች፤ በሶስት መ/ቤቶች በብር 18,041,754.71 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ፤ በ1 መ/ቤት ብር 153,729.19 አለአግባብ በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ እና በሌላ 1 መ/ቤት ደግሞ ብር177,440.00 በድጋሚ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-11 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	3,497,452.96
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	11,467.00
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	132,174,723.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	21,783,188.30
በድምር	ብር	**157,466,831.46**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በ3 መ/ቤቶች ብር 2,390,798.60 በትክክለኛው/በተገቢው ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ፤ተገኝቶል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የተሰበሰበው ገቢና ከወጪ ቀሪ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች</u>

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜውና በሰኔ 30/2009 የሚታየው

ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ማጠቃለያ ብር 81,037,046.82 ለማዕከላዊ ግምጃቤት ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብና በ4 መ/ቤቶች ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ብር 3,389,765.45 በድምሩ ብር 84,426,812.27 ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ አባሪ-12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፣ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፣የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ በ4 ቅ/ጽ/ቤ/ቶች 74 ድርጅቶችመገኘታቸው፣
- ዕቃ ወደ አገር ለማስገባት በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን በወቅቱ ቀረጥና ታክሳቸው ያልተሰላ ወይም ያልተሰረዙ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ግምት መሰረት የብር 50,616,773.33 ቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ በተለያዩ አካላት አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር ብር 11,329,996,797.00 መኖሩ፣
- ግብር ከፋዮች ላቀረቡት የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታው በዋና መ/ቤት ውሳኔው ተሰጥቶበት በቅ/ጽ/ቤቶች ግን ቅሬታቸው ውሳኔ ያላገኘ ተብሎ የተያዘ የብር 1,312,069,929.97 የግብር ዕዳ ውሳኔ መኖሩ፣

- በቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን ለዋና መ/ቤት ያቀረቡ የተባሉ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም ግብር ከፋዮቹ በዋና መ/ቤት የክትትል መዝገብ ላይ ዝርዝራቸው ያልተገኘ የግብር ዕዳ ብር 481,837,038.37 መኖሩ፣
- የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታን በተመለከተ ዋና መ/ቤት ውሳኔው በፍርድ ቤት ክትትል ላይ ያለ መሆኑን መረጃውን የያዘ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤች ግን በዕዳ ክትትል መዝገባቸው ላይ መዝግበው ያልያዙ የብር 6,895,954,886.08 ሂሳብ መኖሩ፣
- ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ 109,687,117.26 መኖሩ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ8/1(ሀ-ሠ፣ አባሪ9/ለና አባሪ10ሀናለ ይመልከቱ/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4.7 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለገቢ ማመንጫነት ከሰራቸው ቤቶች ውስጥ ከኪራይ ገቢ መሰብሰብ ሲገባው ለተለያዩ ባለሀብቶች በነጻ ወይም ያለ ምንም ክፍያ የተሰጠ መሆኑን እና ከዩኒቨርስቲው መብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደው የገንዘብ መጠን ወይም የገቢ መሰረተ ግምት፣ የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነትና አገልግሎቱን በመስጠት ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ የገቢ ዕድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም

እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣

- ዩኒቨርስቲው የሚሰበስበው ገቢ በሚመለከተው አካል የገቢ ተመን /ታሪፍ ሳይወሰን የሚሰበስብ መሆኑን፣ የገቢ ዕቅድ የማያዘጋጅ (የሌለው) መሆኑን እና በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን፣
- በዩኒቨርሲተው ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>**በመቱ ዩኒቨርስቲ፣**</u>

- በሂሳብ መደብ 1489 በድምሩ ብር 6,200.00 የውስጥ ገቢ መሰብሰብ ከነበረበት ግዜ (ወቅት) ዘግይቶ የተሰበሰበ መሆኑን እና የውስጥ ቁጥጥሩ ክፍተት ያለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- ከሙያና ትምህርት ተቋሞች የሰበሰበውን ገቢ ብር 294,886.00 በሂሳብ መደብ 1443 መመዝገብና ሪፖርት ማድረግ ሲገባው በሂሳብ መደብ 1441 ምዝገባው የተከናወነና ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

<u>**በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፣**</u>

- ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ ላይ ለግቢው ማህበረሰብ ለሻይ ቡና አገልግሎት በተዘጋጁ አምስት (5) ቦታዎች ላይ አለአግባብ ገቢ ለመሰብሰብ ሥልጣን ባልተሰጣቸው በተማሪዎች ህብረት በነጭ ወረቀት የሚሰበሰብ መሆኑን እና የገቢውም መጠን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑን፣

<u>**አዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፣**</u>

- የተከታታይ ትምህርት አጠቃላይ ወጪው የሚሸፈነው አገልግሎቱን ከሚያገኙት ተማሪዎች በሚሰበስበው ገቢ መሆን ሲገባው ብር 166,714.00 የተከታታይ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተባበሩ ኃላፊዎችና ትምህርቱን ላስተማሩ መምህራን ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣

- በግቢው ውስጥ አምስት (5) ማህበራትና ግለሰቦች ኪራይ ሳይከፈሉ፣ እንዲሁም የመብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን

4.8 የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፡-

ብር 54,049,425,657.14 (23%)

ለ/ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

ብር 191,588,705.98 (38%)

ከዕቅዱ በታች ወይም በዕቅዱ መሰረት ያልተሰበሰ ገቢ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ ተመልክቷል፡፡

5 የወጪ ሂሳብ

5.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች ብር 413,280,996.45 ማስረጃ ሳይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	9,889,552.79
አቅም ግንባታ መ/ቤት	"	142,840,824.60
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	19,133,218.94
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	241,417,400.12
በድምር	**ብር**	413,280,996.45

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው፣ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 134,472,633.18 ፤የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 129,001,549.44፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 53,772,357.80፤የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 95,100,095.07፤ ወቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 41,937,315.62 እና የቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 13,456,488.42 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

5.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ63 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 1,475,867,250.28 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	850,678,819.23
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	1,916,979.53
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	103,645.21
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	85,007,096.62
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	516,299,420.06
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	21,861,289.63
በድምር	ብር	1,475,867,250.28

ሆኖ ተገኝቷል ።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፤ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 842,885,505.51፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 356,715,318.54፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 129,587,507.28፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,381,996.90፤ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 18,952,906.73፤ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,663,770.37፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 9,329,585.59 እና የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩትብር 8,805,060.25 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሚይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ፤ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

5.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ በ77 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 145,676,300.91 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	2,777,149.94
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	394,192.73
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	44,848,365.62
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	94,092,844.08
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	1,125,120.38
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,438,628.16
በድምር	**ብር**	**145,676,300.91**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 73,982,403.47፤ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር10,569,744.81፤አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,960,196.57፤ ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,671,634.60 ፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,507,155.91 ፤አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,196,212.00 እና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር6,001,671.53 እና ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,317,438.53 ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት በሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ በ8 መ/ቤቶች በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 122,920.11 እና በሌሎች በ8 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 13,904,355.05 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ፤

እንዲሁም በ29 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር41,703,125.15 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-19/1 እና አባሪ-19/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ወደ መንግስት ካዝናተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 3,266,061.85 እና በ55 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 28,865,144.17 በጠቅላላው ብር 32,141,202.02 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5.5 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ100 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች፡-

ብር 956,822,601.96 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	580,832,851.55
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	7,925,158.76
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,490,558.78
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	91,694,070.66
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	129,735,606.19
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	133,144,356.02
በድምር	ብር	956,822,601.96

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡-ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 802,199,221.84፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 5,937,639.38 ፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገበው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 78,267,524.87 ፣ የዋጋ ወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 18,393,839.63 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 52,024,352.94 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 556,832,185.29፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 67,943,833.03፣ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 43,360,623.00 ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,697,650.65፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 17,927,784.00 ፣ ወራቤ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,574,142.14፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,663,136.22 ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ብር 15,415,976.04 እና ወቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,956,353.16 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ በ11 መ/ቤቶች የብር 21,628,420.99 መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

5.6 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ20 መ/ቤቶች በብር 2,006,431,091.87 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ6 መ/ቤቶች ብር 1,361,059,364.44 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1/ሐ ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	174,050.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	1,939,546,380.97
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	5,113,574.43
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	35,020,535.36
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	26,576,551.11
በድምር	ብር	2,006,431,091.87

ከዚህም ውስጥ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,928,982,791.60 ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,020,535.36፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,442,455.35፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 10,151,406.77 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ወይም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ካላቀረቡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፣ የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

ብር 1,311,908,803.11 እና የጤና ሚኒስቴር ብር 23,969,464.20 እና የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር22,173,426.52 ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 186,009,704.35 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 28 ተመልክቷል/

የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፤ ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 116,821,986.39፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 41,573,161.15 ፤በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ብር 15,437,979.87 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 6,078,078.54 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎችም በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ86 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 252,767,992.68 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	6,215,275.76
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	7,261,257.66
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	24,640,359.14
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	41,897,945.59
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,950,444.23
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	158,802,710.30
በድምር	ብር	**252,767,992.68**

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል፤- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 71,281,322.37 ፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 53,540,259.43፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,442,455.35፤ በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 14,303,722.18 እና የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 7,819,589.91 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.9 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ34 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 257,621,118.90 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2010 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	73,116,748.19
የፋይናንስንኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	66,690,494.85
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	,253,819.67
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,560,056.19
በድምር	ብር	257,621,118.90

ሲሆን፤ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት ዓመቱ ለተገኘ አገልግሎት ወጪውም በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 65,725,429.61 የወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/ ከዚሁ የሂሳብ ሪፖርት ጋር በተያያዘ በ12 መ/ቤቶች ብር 5,092,228.55 በድጋሚ የተመዘገበ

የወጪ ሂሳብ እና በ4 መ/ቤቶች ብር 591,780.44 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤ በ3 መ/ቤቶች ብር 389,549.42 በማነስ የተመዘገበ እና በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 120,193.48 ያልተመዘገበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ፤ለአመዘጋገብ ስህተቶቹ አስፈለጊው ማስተካከያ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.11 <u>ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤</u>

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለት በ1 መ/ቤት ብር 18,629,844.49፤ በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ1 መ/ቤቶች ብር 9,001,699.77፤ የግንባታ ሥራዎች ክፍያ ከ 30% በላይ ብር 1,270,586.85 ጭማሪው (38.84%) ተከፍሎ መገኘቱ፤

- ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፤በ1 መ/ቤት ብር 5,106,668.90፤

- በ4 መ/ቤቶች ብር 114,959,683.05 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርትፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤

- በግንባታ አማካሪ ድርጅት ባልተዘጋጀና ባልጸደቀ የክፍያ ሰርቲፍኬት የተከፈለ ክፍያ በ1 መ/ቤት ብር 36,238,839.25 ወጪ መሆኑ፤

- ለሕንጻ ተቋራጮች የብረትና ሲሚንቶ ቅድሚያ የተሰጠ ቢሆንም የመከታተይ ሌጀር ያልተዘጋጀ በ1 መ/ቤት ብር 53,130,865.05 መገኘቱ፤

- በውላቸው መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶች፤ በ3 መ/ቤቶች ሳይጠናቀቁ የተቋረጡ 12 የግንባታ ፕሮጀክቶች፤(በገንዘብ መጠን ብር 265,681,830.82) የሆኑ፤ እና በግንባታ ሂደት ያሉ ግን ከማጠናቀቂያ የውል ጊዜያቸው በላይ የዘገዩ በ7 መ/ቤቶች 55 የግንባታ ፕሮጀክቶች እንደሚገኙ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-20/1 እስከ አባሪ-20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከሪ ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን፤ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ፤የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ አሰፈለጊው እርምጃ እንዲወሰድና የዘገዩት እንዲጠናቀቁ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

5.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ19 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 25,367,673.85 ፤በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 4,172,688.00 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ እና በ17 መ/ቤቶች በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ

የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር 17,670,108.12 መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ-33/ለ ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

5.13 <u>የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ10 መ/ቤቶች የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜያቸው የዘገየ 55 ፕሮጀክቶችና በ2 መ/ቤቶች የግንባታ ሂደታቸው የተቋረጠ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ20/5 ተመልክቷል/ በተጨማሪም፤

- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቀው ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ወይም አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ግንባታዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ37 እስከ 188 ቀናት የዘገዩ መሆኑን፣
- **በመቱ ዩኒቨርሲቲ** ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት የፈርኒቸር ዕቃዎች ግዥ ብር 14,765,020.84 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ የውሉ አንድ አካል ሆኖ በግልፅ በውሉ ያላስቀመጠ በመሆኑ በውል ክፍተት ምክንያት የጉዳት ካሳ ለማስላትና ለመጠየቅ የማያስችል መሆኑን፣
- **አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ**፣ ያስገነባቸውን ግንባታዎች (ህንፃዎች) እንደቋሚ ንብረት በመዝገብ የማይመዘግብ መሆኑን፣

- በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው (በተቀመጠለት) የጊዜ ገደብ መሰረት ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣
- በድምሩ ብር 2,291,218.30 የሚያወጣ ሲሚንቶ በተቋራጮቹ በቀረበ መረጃ ብቻ የተቀነሰ ለመሆኑ እና በእያንዳንዱ ተቋራጭ የተወሰደው የሲሚንቶ ዕዳ በተሰብሳቢ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) የማይያዝ (የማይመዘገብ) መሆኑን፣

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣ የግንባታ ውል ሲዘጋጅ የዩኒቨርስቲውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ሁኔታዎች በውል እንዲካተቱ፣ በቅድሚያ የሚሰጡ ስሚንቶና ሌሎች ዕቃዎች በተሰብሳቢ ሊያዙና በወቅቱ እንዲወራረዱ መደረግ የሚገባው እና ሕንጻዎች በተሰጣቸው ቁጥር መሠረት በንብረትነት መመዝገብ እንደሚገባቸው አሳስበናል፡፡

6 የተከፋይ ሂሣብ

6.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ88 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,301,454,860.35 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	231,874,492.83
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	40,868,202.31
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	198,572,016.98
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	709,413,407.68
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	105,230,484.85
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	15,496,255.70
ድምር	**ብር**	1,301,454,860.35

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 230,432,305.20፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 304,489,394.63 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 232,452,595.52 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 7,968,195.76 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 526,112,369.24 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡

በተጨማሪም በ9 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 385,575,238.97 በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 445,781,634.00፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 213,767,213.72፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 125,843,637.00፤ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 107,026,553.84፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ብር 59,896,212.41፤ መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 58,638,207.92 እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 45,228,032.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተከፋዩን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 218,576,198.26፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 48,305,103.58 እና ምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ብር 61,164,814.07፤አዲስ አበባ ኤርፖርት ብር 24,455,940.54 እና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 15,472,158.61 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

6.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተከፋይ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 192,046.79 መገኘቱ፤
- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 3,126,737.51 መገኘቱ፣ (አባሪ-27/1)

- መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ(ዴቢት ሚዛን) የተከፋይ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 114,823.52 መገኘቱ፤
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ12 መ/ቤቶችና በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 64,634,272.14 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 325,344,429.30 ተገኝቷል፡፡

/ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

7 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

7.1 <u>ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ</u>

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ53 መ/ቤቶችና 10 ቅ/ጽ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 312,314,378.22 ፣ የውስጥ ገቢ ብር 10,676,983.96 እና ከካፒታል በጀት ብር 208,375,565.99 በድምሩ ብር 531,366,928.17 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	9,047,293.14
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		585,176.68
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	300,402,340.56
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	186,028,562.22
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		7,750,358.94
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	27,553,196.63
ጠ/ድምር	**ብር**	531,366,928.17

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 111,987,647.53 ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 79,615,377.18፤ የፌ/ቴክኒክና ሙያ ት/ትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 76,710,149.04፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 38,598,157.84 ፤የወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 35,664,551.36፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 29,063,652.11፤ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 26,797,772.27 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 23,487,495.67 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ17 መ/ቤቶች ብር 17,670,108.12 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 26,195,153.19 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የበጀት ዝውውር የፈፀሙ እና በ3 መ/ቤቶች ብር 66,929,084.32 ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበን ሂሳብ በጀት ሳያስፈቅዱ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ156 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 6,480,797,414.15፣ የውስጥ ገቢ ብር 99,029,157.37 እና ካፒታል ብር 8,250,647,805.65 በድምሩ ብር 14,830,474,377.17 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	2,274,735,273.31
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	452,252,633.56
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,052,896,011.44
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	3,783,581,128.68
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	3,304,106,362.84
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,962,902,967.34
ጠ/ድምር	ብር	**14,830,474,377.17**

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,814,291,032.86 ፣ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 1,678,256,147.22፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 785,140,206.00፤ አዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 573,497,035.94፤ የቀድሞው የስትራቴጂ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ብር 536,591,781.98፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 506,085,595.77፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 452,252,633.56 ፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 444,208,233.70 ፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 419,859,663.02፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 417,400,462.94፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 353,343,805.89 እና ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 320,079,284.82 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

8 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.2 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል፡፡/

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	45	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	35	3
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	17	3
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	19	4
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	35	4
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	62	4
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	80	13
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	36	2
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	24	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው:- 157 የተለያዩ ተሸከሪካሪዎችና 24 ሞተር ብስክሌቶች ሲሆን፣ በ4ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት ያልተገለጸ	1	11
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር2,956,884.52 ይገኙበታል)	28	
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፣	2	
የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ፣ ዋጋቸው ብር 20,346.01 እና 1 ታብሌት ኮምፒዩተር፣ 18 የላቦራቶሪ ዕቃዎች	2	1
በዱቤ ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ንብረት(ዋጋቸው ብር210,220.76 የሆነ)	1	
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	6	6

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በእያንዳንዱ የኦዲትሪፖርት በዝርዝር እና ዋና ዋናዎቹም በየዘርፍ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.3 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	29/ 3ቅ*	174	41
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	37	373/4	42
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	7/ 1ቅ*	11	28/63*
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	26	300	21
የሻንሲ ቁጥር የሌላቸው	1	1	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	2/ 1ቅ*	31	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	3	2	1

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው/ጌጅ/ የማይሰራ	4	11	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	4	10	11
በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ	2	3	
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	3/ 1ቅ*	14	2

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች * ሌሎች- ቦክሰር፤ጂያንሺ፤ዚንግሽ፤ ትራክተር

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ቀ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው፤ በኃለፊዎች ተወስደው ያልተመለሱትም ተመላሽ እንዲደረጉ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

በ2009 በጀት ዓመት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ108 መ/ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት የተሰጠበት ብር 228,717,664.13 ውስጥ ተመላሽ የተደረገ ብር 12,536,323.36 እና በሁለት መ/ቤቶች ተመለሽ ተደርጎል ቢባልም ያልተረጋገጠ ብር 13,697,724.66 ብቻ ሲሆን ቀሪው ብር 216,225,140.67 በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልተወሰደበትና ተመለሽ ያልተደረገ መሆኑ ተውቋል፡፡ አሁንም ትኩረት እንዲሰጥበቸው ያህል ፤ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

የገቢ ሂሳብን በተመለከተም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና በስሩ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 198,199,027.59 በኦዲት ተገኝቶ እንዲሰበሰብ አስተያየት ከተሰጠበት በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት መሰብሰቡ የተረጋገጠ ብር 59,966,560.87 ብቻ ሲሆን ቀሪው ብር 138,232,466.72 በኢዲት አስተያየቱ መሰረት አልተሰበሰበም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤

ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፤በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. የገቢ ሂሳብ

1.1 ከገቢ እቅድ በታች የተሰበሰበ የኢንቨስትመንት ገቢ

በ2010 በጀት ዓመት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት ገቢ በታቀደው መሰረት የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት አመቱ ከስድስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተገኘው ገቢ ከገቢ እቅዱ ጋር ሲነጻጸር ከንውኑ በብር **4,679,310,831.49** (52%) አንሶ ተገኝቷል፡፡

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	በአመቱ የታቀደ ገቢ	ገቢ የተደረገ	ያልተሰበሰበ ገቢ	
				በገንዘብ	በ%
1	ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር	126,670,000.00	97,295,678.41	29,374,321.59	23%
2	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	8,099,000,000.00	3,750,000,000.00	4,349,000,000.00	54%
3	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	377,740,000.00	284,557,120.19	93,182,879.81	25%
4	ከብሔራዊ ትንባሆ ድርጅት	126,307,000.00	70,000,000.00	56,307,000.00	45%
5	የመንግስት ቤቶች ኪራይ	154,000,000.00	2,553,369.91	151,446,630.09	98%
	ድምር	**8,883,717,000**	**4,204,406,168.51**	**4,679,310,831.49**	**52%**

1.2 በገቢ ዕቅድ ሳይካተት የተሰበሰበ ገቢ

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል5 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2ሀ መሰረት አመታዊ በጀት ሲዘጋጅ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ሊይዝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በ2010 በጀት አመት ውስጥ ከመንግስት ኢንቨስትመንት ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ እንዲሁም ከውጭ ሀገር ብድርና እርዳታ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ሙሉ በሙሉ አስቀድሞ በገቢ በጀት ዕቅድ የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በገቢ ሂሳብ መደብ 1461 ከሞኤንኮ ኩባንያ ብር 16,294,785.45
- በገቢ ሂሳብ መደብ 1461 ሜድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት የመንግስት ኢንቨስትመንት ባለመሆኑ በገቢ ዕቅድ ሳይካተት የተሰበሰበ ብር 19,538,457.33

በድምሩ ብር 35,833,242.78 ከመንግስት ኢንቨስትመንት ገቢ የተገኘ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ የገቢ በጀት ዕቅድ ሳይያዝ የተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.3 በገቢ ዕቅድ ተይዞ ያልተሰበሰበ ገቢ

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 10 ለ የሂሳብ መግለጫው የሂሳብ አያያዝ ስርአቱን፡የአገር ውስጥ ገቢ በጀት ከተሰበሰበው ጋር ገቢ እና እርዳታ የታወጀ በጀት ከተስተካከለው በጀት እና ከወጪው ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ በየገቢ አርዕስቱ ተለይቶ በዕቅድ የተያዘው ገቢ በዕቅዱ መሰረት የተሰበሰበ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ከታቀደው ዕቅድ በታች ብር 68,047,613,855.99 የተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.4 የ2009 በጀት ዓመት ትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ የገቢውን ትክክለኛነት ሳይረጋገጥ የተሰበሰበ ሂሳብ

በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 ክፍል 6 አንቀጽ 28 ቁጥር 2 እና ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 730/2004 አንቀጽ2(1) ከተመለከቱት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮኖቻቸው ሙሉ በሙሉ በመንግስት ከተያዙ አክሲዮን ማህበራት የተጣራ ትርፍ እንዲሁም ሽያጭ የሚገኝ ገቢ እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በመንግስት ከተያዙ አክሲዮን ማህበራት የተጣራ ትርፍ እንዲሁም ሽያጭ የሚገኝ በሂሳብ ሪፖርቱ መሰረት ገቢ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ ከተለያዩ 3 ድርጅቶች፤

- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ብር 3,000,000.00
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር 97,295,678.48
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 3,750,000,000.00

በድምሩ ብር 3,850,295,678.48 የበጀት ዓመቱን ትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ሳይቀርብ ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

1.5 ከሚድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት የተገኘ ገቢ

ሚድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት ከወርቅ ምርት ላይ ብር 19,538,457.33 ገቢ ያደረገ ቢሆንም ያመረተውን ወርቅና ከሽያጭ የተገኘውን መጠን የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ባለመቅረቡ የመንግስት ድርሻው ሊሰበሰብ በሚገባው ልክ ስለመሰብሰቡ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

1.6 ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገቢ፣የሊዝ ክፍያ፣ ከተዛወሩ ድርጅቶች የብድር ተመላሽ እቅዱ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ

በ2010 በጀት ዓመት ውስጥ ቀደም ብለው ከተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ገቢ፣ በበጀት ዓመቱ ከሚሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገቢ፣ከተሸጡ ድርጅቶች የሊዝ ክፍያ ፣ከልማት ድርጅቶችና ወደ ግል ከተዛወሩ ድርጅቶች የብድር ተመላሽ በድምሩ ብር 4,236,900,000.00 ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም የተገኘው ገቢ ብር 2,654,550,000.000 ብቻ በመሆኑ የገቢ እቅዱ ከክንውኑ ጋር ሲነጻጸር ብር 1,582,350,000.00 የሚያንስ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.7 ከመልሶ ማበደር ያልተሰበሰበ የብድር ወለድ ገቢ

መንግስት ከውጭ ሀገር በብድር ያገኘውን ገንዘብ በመልሶ ማበደር ስምምነት መሰረት ለልማት ድርጅቶች የሚያበድር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተበዳሪዎች ከመንግስት የተበደሩትን ገንዘብ በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ያልተከፈለ ዋና ገንዘብ	ያልተከፈለ ወለድ	ቅጣት	ጠቅላላ ድምር
1	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	33,067.45	-	-	33,067.45
2	ብረታ ብረትና ኢ.ጂነሪንግ ኮርፖሬሽን	-	29,335,600.00	10,179,334.68	39,514,934.68
	ድምር	33,067.45	29,335,600.00	10,179,334.68	39,548,002.13
	ከ2004 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2010 የልተከፈለ				
1	ብረታ ብረትና ኢ.ጂነሪንግ ኮርፖሬሽን	-	29,666,890.02	-	29,666,890.02
2	ወንጂ ስኳር ፋብሪካ	383,276,899.80	24,038,524.71	10,599,967.08	417,915,391.59
3	ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ	561,062,331.21	252,129,643.58	11,679,177.98	824,871,152.77
4	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ	833,139,589.88	573,596,704.53	22,010,693.43	1,428,746,987.84
5	ስኳር ኮርፖሬሽን	244,811,956.58	72,874,220.75	17,832,297.04	335,518,474.37
6	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል	-	793,720,418.00	-	793,720,418.00
	ድምር	2,022,290,777.47	1,746,026,401.59	62,122,135.53	3,830,439,314.59
	ጠቅላላ ድምር	**2,022,323,844.92**	**1,775,362,001.59**	**72,301,470.21**	**3,869,987,316.72**

በድምሩ ብር 3,869,987,316.72 የብድር ወለድ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 <u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 7 እንደተገለጸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውስጥ ቁጥጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ሳያቋርጥ ክትትል ማድረግና አግባብነት በሌላቸው፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማና ስኬታማ ባልሆኑ ግኝቶች ላይ ወቅታዊና ተገቢ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ላይ ከተመለከተው ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 4201(ተንጠልጣይ ሂሳብ) በ96 መ/ቤቶች ብር 130,942,631.00
- በሂሳብ መደብ 4203 (ከደመወዝ ላይ ተቀናሽ ቅድመ ክፍያ) በ130 መ/ቤቶች ብር 227,108,457.80
- በሂሳብ መደብ 4204 (ለማህበራዊ ልማት ዘርፍ ፕሮግራም የሚውል ቅድመ ክፍያ ብር 9,113,771.22
- በሂሳብ መደብ 4207 (ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት ላይ የሚታሰብ የካፒታል ወጪ) ብር 38,763,484.38
- በሂሳብ መደብ 4208 (ለክልሎች የሚሰጥ ቅድመ ክፍያ) ብር 2,539,996,583.58
- በሂሳብ መደብ 4209 (ለበጀት ተቋሞች ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች) ብር 1,285,132,913.46
- በሂሳብ መደብ 4210 (በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ቅድመ ክፍያ) ብር 8,610,440,316.19
- በሂሳብ መደብ 4211 (ለግዢ ቅድመ ክፍያ) ብር 540,426,806.29
- በሂሳብ መደብ 4271 (ለገበሬ ማህበራት) ብር 730,472.48
- በሂሳብ መደብ 4272 (ለህብረት ስራ ማህበራት)ብር 20,786,447.36
- በሂሳብ መደብ 4273 (ለግለሰቦችና እና የግል ድርጅቶች) ብር 358,491,976.21
- በሂሳብ መደብ 4274 (ሌሎች) ብር 4,924,641,907.88

በድምሩ ብር 18,686,575,767.85 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

2.2 ያልተተካ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

በፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ኦዲት ሲደረግ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4202 ላይ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር **8,169,401.13** መኖሩ ታውቋል፡፡ በጉድለት ከሚታየው ጥሬ ገንዘብ ውስጥ ብር **7,535,863.54** በ11 መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ መሆኑ ጉድለት መሆኑ ታውቋል፡፡

3. ተከፋይ ሂሳብ

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መከፈሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ላይ በሰኔ 30/2010 ዓ.ም. በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 317,292,603,215.74 ለባለጥቅሙ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 5002(ልዩ ልዩ ተከፋዮች) ብር 9,245,865,592.58
- በሂሳብ መደብ 5003 (የጡረታ መዋጮ ክፍያ) ብር 1,807,561,867.78
- በሂሳብ መደብ 5006 (ከተከፋ ሂሳብ ቅድመ ክፍያ) ብር 100,431,607.16
- በሂሳብ መደብ 5007 (ወጪ መጋራት) ብር 954,663.96
- በሂሳብ መደብ 5026 (ለክልሎች ወይም ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተከፋይ ብር 2,026,841,972.35
- በሂሳብ መደብ 5028 (በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋዮች) ብር 2,081,374,545.41
- በሂሳብ መደብ 5058(የተጨማሪ እሴት ቀረጥ ተያዥ) ብር 2,124,058,271.03
- በሂሳብ መደብ 5059 (የተጨማሪ እሴት ቀረጥ) ብር 1,168,760,703.92

በድምሩ **18,555,849,224.19** በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የፌዴራል መንግስት የሂሳብ መግለጫዎች እስከ ሰኔ 30/2010 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፤ እንዲሁም በሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የተዘጋጁ በመሆናቸው በእኛ አስተያየት አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የክዋኔ እና የአካባቢያዊ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

እና የማሻሻያ ሃሳቦች

1.2.1.1. በገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም

❖ **የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ ጥናቶችና ግምገማዎች በተመለከተ**

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት የፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት ጥናት፣ የቅድመ ግምገማ ሪፖርት (Feasibility, pre-feasibility appraisal) ሊያረጋግጥ ይገባል::

2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት የፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት ጥናት፣ የቅድመ ግምገማ ሪፖርት (Feasibility, pre-feasibility appraisal) የማረጋገጡን ስራ እየተገበረ ባለመሆኑ በ290 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ተደጋጋሚ የጊዜ እና የገንዘብ መጠን/በጀት ክለሳ በመደረጉ ምክንያት ብር 44,272,740,000.00 ወጪ ያስከተሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በውሃ መስኖና ኢነርጂ (የቀድሞው የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ) ሚኒስቴር ስር ያሉ/የነበሩ 18 ፕሮጀክቶች ብር 32,090,120,000.00 ወይም 72 በመቶ የሚይዙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣**

ለፕሮጀክቶች በጀት ከመመደቡና ከመልቀቁ በፊት የአዋጭነት ጥናት መከናወኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

3. 16 የመንግስት ፕሮጀክቶች አዋጪነት ጥናት ሳይደረግባቸው በመጀመራቸው ብር 246,571,379.10 ወጪ ከወጣባቸው በኋላ የተቋረጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

❖ **ፕሮጀክቶች በተዘጋጀላቸው የጊዜ ሰሌዳ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣**

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በተዘጋጀላቸው የጥናት ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊጀመሩና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቃቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በተዘጋጀላቸው የጥናት ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊጀመሩና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቃቸውን እያረጋገጠ ባለመሆኑ፤ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች፡- ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት 75 ፣ ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት 208 ፤ ከ 3 ዓመት እስከ 5 ዓመት 54 እንዲሁም ከ 5 ዓመት በላይ 32 በአጠቃላይ 369 ፕሮጀክቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

6. የተለያዩ 54 ፕሮጀክቶች የተፈቀደላቸው የገንዘብ መጠን ክለሳ ሳይደረግ፣ 26 ፕሮጀክቶች ብር 1,541,240,000.00 ለፕሮጀክቶች ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ ተፈፅሞባቸው የተጠናቀቁ እና 28 ፕሮጀክቶች ብር 1,598,000,000.00 ለፕሮጀክቶች ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ ተፈፅሞባቸው ያልተጠናቀቁ ሲሆኑ በድምሩ ብር 3,139,240,000.00 ተጨማሪ ወጪ ያስከተሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **አስፈፃሚ መ/ቤቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚልኩትን የፕሮጀክት ሪፖርት በተመለከተ፣**

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ሕግና ሥርዓቱን የተከተለ የፕሮጀክቶች ወቅታዊ የሂሳብና የፊዚካል ሪፖርቶች ክንውን በተሟላ መረጃ የተደገፉ እና ሊለኩ የሚችሉ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

8. ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርቡ የፕሮጀክቶች ወቅታዊ የሂሳብና የፊዚካል ሪፖርቶች ክንውን ሕግና ሥርዓቱን የልተከተሉ፤ በተሟላ መረጃ ያልተደገፉ እና ሊለኩ የማይችሉ 280 ፕሮጀክቶች ተገኝተዋል፡፡

❖ **ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክቶችን የግንባታ ሒደት የሚያሳይ ሪፖርት መቅረቡን በተመለከተ**

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክቶችን የግንባታ ሒደት በየወቅቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት መቅረቡን በማረጋገጥ እና ፕሮጀክቱ ያለበትን ደረጃ ክትትል በማድረግ በጀት ሊለቅ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክቶችን የግንባታ ሒደት በየወቅቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት መቅረቡን እና ቀደም ብሎ የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ሳያረጋግጥ በጀት የሚፈቅድ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የፕሮጀክት ፕሮፋይልን በተመለከተ**

10. ፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ትግበራ ውጤት ያለውን ሂደትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ (ፕሮጀክት ፕሮፋይል) በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሊዘጋጅ ይገባል እንዲሁም የተያዙት መረጃዎችም በየጊዜው በመተንተን ሊጠናቀርና ለሌሎች ለወደፊት ለሚሠሩ ፕሮጀክቶች ግብአት እንዲሆኑ ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጩ ይገባል፡፡

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ትግበራ ውጤት ያለውን ሂደትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ (ፕሮጀክት ፕሮፋይል) የሌለው መሆኑ፣ እንዲሁም የተያዙ መረጃዎችም በየጊዜው በመተንተን የማያጠናቅር መሆኑና ለሌሎች ለወደፊት ለሚሠሩ ፕሮጀክቶች ግብአት እንዲሆኑ ለሚመለከታቸው አካላት የማያሰራጭ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ የተመለከቱትን ዋና ዋና ግኝቶች ለማስተካከል ያግዛሉ ተብለው የተቀመጡ የማሻሻያ ሃሳቦች፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት በተጠናከረ መልኩ የፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት ጥናት እና የቅድመ ግምገማ ስራ ተከናውኖ እንዲሁም ሊፈጸም የሚችል የትግበራ ዕቅድ ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ መቅረቡን ሊያረጋግጥና በጀት ሲለቀቅም አስቀድሞ በቀረበው ዕቅድ መሰረት መሆኑን

ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ የአዋጭነት ጥናት ሳያስጠኑ፣ በበቂ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ የፕሮጀክት ዕቅድም ሆነ በጀት የሚያቀርቡ ተቋማትም ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክቶችን የግንባታ ሒደት ቀደም ብሎ የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም በየወቅቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት መቅረቡን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ክትትል በማድረግ በጀት መልቀቅ ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር በተመደበው በጀት እና የጊዜ ሰሌዳ ተጠናቀው የታለመላቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ የተጠናከረ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በተፈቀደው ዕቅድ፣ የጊዜ ሰሌዳና በጀት የማይተገብሩ አካላት በሙሉ በየደረጃው ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮጀክቶችን የግንባታ ሒደት ቀደም ብሎ የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም በየወቅቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ባዘጋጀው ወጥ የሆነ ሪፖርት የሚቀርብበት ቅጽ (Format or Template) መሰረት በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ከሪፖርቱ ጋር ተያይዘው የሚላኩ ዝርዝር መረጃዎች ሕግና ሥርዓቱን የተከተሉ ወቅታዊ የሂሳብና የፊዚካል ሪፖርቶች ክንውን በተሟላ መረጃ የተደገፉ እና ሊለካ በሚችል መልኩ እንዲያቀርቡ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል አለበት፡፡ ይህ የአሰራር ሥርዓት በሚፈለገው መንገድና የጊዜ ገደብ ሪፖርት የማያቀርቡ የፕሮጀክት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ተጠያቂ የሚደረጉበት ሂደትን መጨመር አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሪፖርት አቀራረብ ሁኔታው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚታገዝበትን ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ትግበራ ውጤት ያለውን ሂደትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ (ፕሮጀክት

ፕሮፋይል) በማዘጋጀት እንዲሁም የተያዙት መረጃዎችም በየጊዜው በመተንተንና በማጠናቀር ለሌሎች ለወደፊት ለሚሠሩ ፕሮጀክቶች ግብአት እንዲሆኑ ሊደረግና ለፖሊሲ ውሳኔም ለሚመለከታቸው አካላት ሊልክ ይገባል፡፡

1.2.1.2. በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም በተመለከተ

❖ **የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አስተዳደርን (Financial Managmnet) በተመለከተ፣**

12. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የስርጭት እና ግብይት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

13. ኮርፖሬሽኑ ከቀድሞው አለ በጅምላ ከመጣ ብድር የተነሳ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ውስጥ መሆኑ ፣ ከፍተኛ ዕዳና ወለድ እየከፈለ የሚገኝ መሆኑ እና ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመስራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፤

❖ **የፍጆታ ዕቃዎች የግዥ ዘዴን በተመለከተ፣**

14. ኮርፖሬሽኑ የሚፈጽማቸውን የፍጆታ ዕቃ ግዥዎች በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን እና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

15. በኮርፖሬሽኑ ከውጭ የሚገቡ የፓልም የምግብ ዘይቶች ከኢንዶኔዥያ እና ማሌዥያ ብቻ ተገዝተው የሚገቡ መሆኑ ፤ ሌሎች የተለያዩ ሀገራት አቅራቢዎች በጨረታ ተወዳድረው እንዲያቀርቡ ዕድሉን ያላመቻቸ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

❖ **ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ**

16. ኮርፖሬሽኑ የተቀላጠፈና በዘመናዊ የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ (በተለይ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን) ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

17. ኮርፖሬሽኑ በዘርፉ የተቀላጠፈ እና በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ አለመሆኑንና ያሉት ማከፋፈያዎቹም በአዲስ አበባና በተወሰኑ ከተሞች ብቻ የተወሰነ መሆኑ ታውቋል፡፡

18. ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ አብዛኛውን የአገሪቱን አካባቢ እና ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ያላደረገ መሆኑ፤

❖ **ዕቃዎች ደረጃውን በጠበቀ መጋዘን ውስጥ እንዲከማቹ ማድረግን በተመለከተ**

19. ኮርፖሬሽኑ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ገዝቶ የሚያስመጣቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ደረጃውን ጠብቆ በተገነባ መጋዘን ውስጥ እንዲከማች ሊያደርግ ይገባል፡፡

20. ኮርፖሬሽኑ የዘይት ማስቀመጫ ለእህል እና ቡና ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን መጋዘን ለማከማቻ መጠቀም እየቻለ ደረጃውን የጠበቀ አይደለም አንጠቀምበትም በሚል ምክንያት እና ተለዋጭ መጋዘንም ቢሆን በኪራይ ባለመዘጋጀቱ፤ በኮሜትና በሞጆ ደረቅ ወደብ ውስጥ በወቅቱ ሳይራገፉ ከሶስት ወራት በላይ ላስቆጠሩ ኮንቴይነሮች ከብር 7 መቶ ሺ በላይ ለመጋዘን ኪራይ የተከፈለ ሲሆን ኮንቴይነሮቹም በተገቢው ቀን ባለመነሳታቸው /ዕቃዉን ጭነው ሳያራግፉ በግቢ ውስጥ በመቆየታቸው ከሐምሌ 2016 እስከ ጥቅምት 2016 ድረስ ብቻ ብር 1,654,215.00 ሚሊዮን ዲመሬጅ ያለአግባብ መከፈሉን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎችን በተመለከተ**

21. ኮርፖሬሽኑ የሚሰራጩ የፍጆታ ሸቀጦች የተበላሹ እና የጎደሉ ካሉ ተለይተው እና ተቆጥረው ወይም ተመዝነው ለየብቻ እንዲቀመጡ ፣ በተበላሹ እና በጎደሉ የፍጆታ ሸቀጦች በውል መሰረት የሚተኩ ካሉ እንዲተኩ ሊያደርግ ይገባል ፡፡

22. በቃሊቲ እና በሌሎች ቅርንጫፍ ማከማቻ መጋዘንና መሸጫ መደብሮች ከአንድ እስከ አራት ዓመት የተቀመጡ ጊዜ ያለፈባቸው እና ጉዳት የደረሰባቸው/ የተበላሹ የፍጆታ ዕቃዎች (ምግብና ምግብ-ነክ፣ መድሃኒት-ነክ ያልሆኑ የመዋቢያ ዕቃዎች /ኮስሞቲክ እና የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች)

ለምሳሌ፡ በመርካቶ ከብር 60,000 በላይ የሚገመቱ ፣ በባህርዳር ፣ ሀዋሳ እና በቃሊቲ ዋጋቸው የማይታወቅ ዕቃዎች መኖራቸው ተውቋል፡፡

23. ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና (minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

❖ የገበያ ጥናት ማካሄድን በተመለከተ

24. ኮርፖሬሽኑ በዋነኛነት የሚያገለግለውን የህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡በጥናቱም መሰረት እጥረት ያለባቸውን የመሰረታዊና የፍጆታ ሸቀጦችን በወቅቱ ወደ ገበያ በመግባት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን ሊያረጋጋ ይገባል፡፡

25. ኮርፖሬሽኑ በመሰረታዊ ሆነ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ የተጠናከረ የገበያ ጥናት ላይ የተመሠረተ ግብይት የማያደርግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም

- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ከመቀላቀሉ በፊት የነበረው ሂሳብ ተዘግቶ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሒሳብ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይገባል፣
- የቀድሞው አለ በጅምላ ሲቋቋም ከባንክ የተበደረው ብድር በታህሳስ 2008 ዓ.ም. ወደ ኮርፖሬሽኑ ሲቀላቀል የብድሩ ዋናው (principal) ክፍያ እፎይታ ጊዜው በሦስት (3) ዓመት በመጠናቀቁ እ.ኤ.አ ከመስከረም 2016 ጀምሮ ዕዳና ወለድ በየሶስት (3) ወሩ ብር ወደ 21 ሚሊዮን (በዓመት 84 ሚሊዮን) ኮርፖሬሽኑ እየከፈለ በመሆኑና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥና ሽያጭ ለማከናወን በየቀኑ በተመሳሳይ ወለድ ምጣኔ የሚታሰብበት ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመሆኑ ይህ ኮርፖሬሽኑ የተቋቋበትን አላማ ለማሳካት እንቅፋት በመሆኑ በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እና የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ችግሩ የሚቀረፍበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ግዥዎች ግልጽነትና ፍትሃዊነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለበት በስተቀር የፍጆታ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም ይኖርበታል፣ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት የነበረ ልምድ ተብሎ በኮርፖሬሽኑ እየተከናወነ ያለው የፓልም የምግብ ዘይት ግዥ የሚከናወንበት መንገድ በጥናት ተከልሶ ሂደቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ዋጋን ብቻ ሳይሆን ጥራትን (የህብረተሰብ ጤናንና ደህንነትን ከግምት ያስገባ) ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የዕቃ ግዢዎች የአገልግሎት መቆያ ጊዜ ቢያንስ ምን ያህል መሆን እንዳለበት በግልጽ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ የሚበላሹ ፤ጊዜ የሚያልፉቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ሊቀንስ/እንዳይኖሩ የሚያደርግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተለያየ ምክንያት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የደረሰና ያለፈ ለገበያ ሊቀርቡ የማይችሉ እቃዎችን በኮርፖሬሽኑ በተቀመጠው አሰራር መሠረት ሊያስወግድ ይገባል፣፡

- ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን እና የገበያውን ሁኔታ ለመረዳትና ተፈላጊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፣ የሚከናወነው ጥናትም ለስትራቴጂክ ዕቅድ እንደግብዓት ሊያገለግል ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት አላማን ለማሳካትና በሁሉም አካባቢዎች ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት በመዘርጋትና ከዚህ በፊት በጥናት የተለዩትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ማቆያ መጋዘኖች እና መሸጫ መደብሮች ሊያስፋፉ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

1.2.1.3. በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውጪ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ

❖ **የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች መጠናታቸውን በተመለከተ፤**

26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች ሊያካሄድ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት በዕቅዱ መሰረት አለመከናወኑ፤ በ2008 በጀት ዓመት በሶስት አገራት በቻይና፣ ሱዳን እና ህንድ የሰሊጥ ኤግዚብሽኖችና ኮንፈረሶችን ማስተባበርና እንደ አስፈላጊነቱ መሳተፍ በሚል የተያዘው እቅድ በህንድ እና በሱዳን ያልተከናወነ መሆኑን (3 ታቅዶ 1 መፈፀሙን)፤ በ2009 በጀት ዓመት በሰሊጥ የወጪ ምርት ላይ የገበያ ጥናት ማካሄድ እና በሦስት አገራት የገበያ ቅኝት ለማካሄድ የተያዘው የሥራ ዕቅድ ያልተከናወነ መሆኑን እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በቻይና እና ህንድ ዓለም አቀፍ የሰሊጥ ኮንፈረንሶች ላይ ሰሊጥ ላኪዎች እንዲሳተፉ በማስተባበር የገበያ ትስስር ለመፍጠር የተያዘው እቅድ 2 ታቅዶ 1 መሰራቱን፤በ2009 በጀት አመት የሀገሪቱን የውጪ ምርቶችን ማሳያ በአራት ቦታ በአገር ውስጥና በውጪ አገር ለመስራት የተያዘው እቅድ ያልተሰራ መሆኑን እና የወጪ ምርቶች የተወሰኑ እና በተወሰኑ የገበያ መዳረሻዎች ላይ ብቻ ጥገኛ መሆናቸውን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **በወጪ ንግድ ዙሪያ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፤**

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ዙሪያ በላኪ እና ገዢ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤

❖ **ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ጥናት በማከናወን የተለዩ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ጥናት በማከናወን ሊለይ እና የመፍቻ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

31. ይሁን እንጂ የወጪ ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት ከሚደረገው ጥረት አኳያ፤ የወጪ ንግድ ማነቆ መስፋፋቱን፤ ግልፅ የሆነ የመፍቻ ሥርዓት አለመኖሩን፤ለኤክስፖርት የኮንትሮባንድ ንግድ፤ የማኔጅመንትና የቴክኒክ አቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነት መኖሩን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

32. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎች በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋጋ አሳንሰው ሆነ አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት የሌለ መሆኑን፤ወቅታዊ የዋጋ ተመን መረጃ የማይልክላቸው መሆኑን፤ የዋጋ ተመን መረጃ የማይደርሳቸው በመሆኑ ለሽያጭ ተወዳዳሪነታቸውን የሚቀንስባቸው መሆኑን፤ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የገበያው ዋጋ መረጃ የማይደርሳቸው በመሆኑ ወቅታዊ የመላኪያ ዋጋ ባለማወቅ ውል በመግባታቸው የኮንትራት ውል የሚያፈርሱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

❖ **ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃው ተደራጅቶ ባለመያዙ በግልፅ ያለማወቅ ችግር መኖሩን እንዲሁም ለኤክስፖርት ተብሎ በማበረታቻ መልክ የሚሰጠው ብድር ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፤**

36. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

37. ይሁን እንጂ ሚ/መቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤ ታዋቂነትና ተአማኝነት ካላቸው የመረጃ ምንጮች የገበያ መረጃ ለማሠራጨት በ2008 በጀት አመት ታቅዶ እስከ 2011 በጀት አመት በሂደት ላይ በመሆኑ ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑን፤

በመሆኑም፡-

- በአገር አቀፍ ደረጃ በየአመቱ የሚታቀደው የኤክስፖርት እቅድ ከአቅራቢው ጀምሮ ሁሉንም የግል ሴክተሮች ተሳታፊ ያደረገ፣ ለዕቅዱ ተፈጻሚነት ግብአት የሚሰጡበትንና ዕቅዱን በባለቤትነት ይዘው ለትግበራው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡ይህንን በማድረግም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በአይነት፣ በብዛትና በጥራት ለማሳደግ የሚያግዝ አሳታፊ የሆነ እቅድ ሊዘጋጅ እና ለተፈጻሚነቱ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በአገሪቱ ውስጥ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች ምርቶቻቸውን ለመላክ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የላኪዎቹም ሆነ የአገሪቱ ጥቅም መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያግዝ የህግ ማዕቀፍ እና ህጉን ለማስፈጸም

የሚረዱ እና የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋሉን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ ይህንን ለመከታተል የሚያስችል ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃ ተደራጅቶና በየጊዜው ወቅታዊ እየተደረገ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሌሎች አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሊያዝ ይገባል፡፡
- አጠቃላይ የአገሪቱን የወጪ ንግድ መረጃን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፣የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት ሥርዓት ዘርግቶ መ/ቤቱም ሆነ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለድርሻዎች ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

1.2.1.4. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር አፈጻጸምን በተመለከተ

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ**

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር ፈጥሮ የጋራ እቅድ ሊያዘጋጁና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የተዘጋጀው ዕቅድ ተግባራዊ ስለመደረጉ በየጊዜው አፈጻጸሙን በጋራ ክትትልና ግምገማ ሊደርግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ

- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል የሚመለከታቸዉ የፌዴራልና የክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት እና አጋር ድርጀቶች ጋር የሚሰሩ ስራዎች ያልተጠናከረ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና ጉዳቶች (NCDI) ኮሚሽን ህዳር 2011 ዓ.ም ሪፖርት መሰረት ከባለድርሻ አካላት ጋር ዘርፈ ብዙ እቅድ የሌለ እና

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ለሚገጥሙ እንቅፋቶችን ለመቅረፍ ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፣

- በ2009 እና በ2010 ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ዘርፈ-ብዙ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ማዘጋጀት የታቀደ ቢሆንም ያልተፈፀመ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና ላይ በቂ የጤና ባለሙያዎች መኖራቸውን በተመለከተ**

40. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎችን ስፔሻላይዝድ ያደረጉትን ጨምሮ የሚፈሩበትን ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ ስለሚፈጠሩ ሁኔታዎች ለባለሙያዎቹ ሥልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

41. በኦዲቱ ወቅት ፡

- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመቆጣጠርና ህክምና አገልግሎቱን ለመስጠት እና ተደራሽ ለማድረግ በየደረጃው ያሉ የባለሙያዎች ዕጥረት መኖሩ፤
- ከተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስኳር፣ ልብ፣ መተንፈሻ አካላት እና የማህፀን ጫፍ ካንሰር ላይ ቢያንስ አንድ የሰለጠነ ባለሙያ አገልግሎቱ በሚገኝባቸው ጤና ተቋማት የስኳር 8%፣ የልብ 7%፣ የመተንፈሻ አካላት 6%፣ እና የማህፀን ጫፍ ካንሰር 33% ብቻ ባለሙያዎቹ የተሟሉ፣ በህክምና ሙያ ተመርቀው በካንሰር በሽታዎች ህክምና ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ሃኪሞች በአገሪቱ 12 ብቻ ሲኖሩ 6 ስፔሻሊስት ሃኪሞች በጥቁር አንበሳ ያሉ ሲሆን 6ቱ በክልሎች ያሉ መሆኑ፤ የህፃናት አንኮሎጂ ሃኪሞች በአገሪቱ ላይ 2 ብቻ መሆናቸው፣ 11 አንኮሎጂ ነርሶች ብቻ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መኖራቸው፤ በአማኑኤል ሆስፒታል ለፍትህ አካላት ተጠርጣሪዎች የአእምሮ ህሙማን መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጫ የሚሰጥ (ፎረንሲክ ሳይካትሪስት) ያለው 1 ስፔሻሊስት ሃኪም ብቻ መሆኑ፤

- ከበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክቶሬት 2010 አመታዊ ሪፖርት መሰረት የአይን ሞራ ግርዶሽ የሚሰሩ ባለሙያዎች ቁጥር ማነስ ለአብነት አፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ የአይን ሞራ ግርዶሽን የሚሰራ ባለሙያ አለመኖሩን የተገለፀ መሆኑ፤
- አዲስ እየተገነቡ ላሉት በሃረማያ ዩንቨርስቲ በህይወት ፋና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የካንሰር ህክምና ማዕከል እና በሀዋሳ ዩንቨርስቲ ሪፈራል ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የካንሰር ህክምና ማዕከል ባለሙያዎች ያልተዘጋጁ መሆኑን በቃለ መጠይቅ ያናገርናቸው የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ

ታውቋል፡፡

❖ በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች እየተገነቡ ያሉ የካንሰር ህክምና ማዕከላትን በተመለከተ

42. የካንሰር ህክምናን ተደራሽ ለማድረግ በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲገነቡ የታቀዱ የካንሰር ህክምና ማዕከላት በተያዘላቸው ጊዜ ግንባታቸው ተጠናቆ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡
43. በጎንደር፣ በመቀሌ፣ በሃዋሳ፣ በጅማ እና በሀረማያ (ሀረር) ዩኒቨርሲቲዎች ሆስፒታሎች ውስጥ አዲስ የካንሰር ማዕከላት ግንባታ እየተከናወነ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ደግሞ ተጨማሪ የጨረር ህክምና ለመስጠት የክፍል እደሳ ስራ ለማከናወን ሥራ እየተሰራ መሆኑ፡፡
44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

በሀረማያ ዩንቨርስቲ ሕይወት ፋና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- የካንሰር ህክምና ማዕከል ለመገንባት አፍሮ ጽዮን የተባለ የስራ ተቋራጭ ውል የገባ እና በውሉ መሰረት ግንባታዉ ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም. (December 25 2014 G.C) ተጀምሮ በ2016 G.C መጠናቀቅ ቢኖርበትም እስከ አሁን ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣
- የካንሰር ማዕከሉ ግንባታ በነዋሪዎች መንደር አካባቢ የተሰራ እና ነዋሪዎቹ ለጨረር ተጋላጭ እንዳይሆኑ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወሩ ባለመደረጋቸው ግንባታው ተጠናቆ ቢያልቅ እንኳን አገልግሎቱን ለማስጀመር እንቅፋት የሚሆን መሆኑን በቃለ መጠይቅ ባነጋገርናቸው ኃላፊዎች የተገለጸ መሆኑ፤

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- የካንሰር ህክምና ማዕከሉን ለማሰራት ከይርጋለም ኮንስትራክሽን ፒ.ኤል.ሲ ጋር ውል የተገባ እና በውሉ መሰረት ግንባታዉ በየካቲት 23 2008 ዓ.ም. (March 2/2016) ተጀምሮ በመስከረም 14 2010 ዓ.ም. (SEP 24 2017) መጠናቀቅ ቢኖርበትም ባለመጠናቀቁ ውሉን በመከለስ በየካቲት 23 2010 ዓ.ም. (March 2 2018) የማጠናቀቂያ ውል ቢገባም በተባለለት ጊዜ አለመጠናቀቁ፤

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- በተቋሙ ውስጥ ባለ አንድ ክፍል እድሳት (የግድግዳዎች እና ጣሪያ ውፍረት መጨመር፣ በር መግጠም፣ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ እና ቀለም መቀባት) ስራ በኤልስሜድ ኸልዝ ኬር ሶሉሽን ሚያዚያ 28 2008 (እ.ኤ.አ በ5/5/2016) በፊት የተጀመረ መሆኑን እና መስከረም 1 2010 (እ.ኤ.አ በ11/9/2017) ስራውን ለማጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም ለመስክ ጉብኝት እስከተሄደበት ጊዜ ድረስ ክፍሉ ውስጥ የጨረር ማሽን ተተክሎለት አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩ፣

ጅማ ዩንቨርስቲ ሆስፒታል ስር ያለው የካንሰር ማዕከል ግንባታ

- ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በ26/12/2017) በተደረገ ጉብኝት ግንባታው እንደተጠናቀቀና የተወሰኑ ማጠቃለያ ስራዎች ብቻ እንደቀረው እንዲሁም የቀሩት ስራዎች በ15 ቀን ውስጥ እንደሚጨርሱ ስምምነት ላይ መደረሱን የተገለፀ ቢሆንም ስራው እስከ አሁን ተጠናቆ አገልግሎት መሰጠት አለመጀመሩ፤

ጎንደር ዩንቨርስቲ ሆስፒታል ስር ያለው የካንሰር ማዕከል

- ጥር 1 ቀን 2010 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በ09/01/2018) በተደረገ ጉብኝት የተወሰኑ ስራዎች ብቻ እንደቀረው እንዲሁም የቀሩት ስራዎች በ3 ወር ውስጥ እንደሚጨርሱ ስምምነት ላይ መደረሱን የተገለፀ ቢሆንም ስራው እስከ አሁን ተጠናቆ አገልግሎት መሰጠት አለመጀመሩ፤

- ሁሉም የጨረር ማሽኖች አገር ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉ ቢሆንም የጨረር ማሽኖቹን ለመግጠም በጎንደር፣ መቀሌ እና ሀዋሳ የባንከሮቹ (ማሽኑ የሚተከልላባቸው) ቤቶች ግንባታ አለማለቅ እንዲሁም ጅማ እና ሃረር ኤሌክትሪክ ገመድ ዝርጋታ እና ማጠቃለያ ስራዎች አለማለቃቸው እንዲሁም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ላይ ማሽኑ የሚተከልበት ክፍል ጣሪያ ውሀ እያስገባ በመሆኑ እንቅፋት የሆነባቸው መሆኑን የጨረር ማሽኑን አስገብተው እንዲገጥሙ የተመረጡት ኤልስሜድ ኸልዝ ኬር ሶሉሽን የስራ ኃላፊዎች መግለፃቸው፤
- በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፣ በሃረማያ እና በጅማ የካንሰር ህክምን ማዕከላት የጨረር ማሽኖች ተገዝተው በግንባታ ቦታው ጥቅምት 13 ቀን 2010 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ23/10/2017) የደረሱ ቢሆንም ግንባታው እና ለማሽን ተከላው የሚያስፈልጉ ተያያዥ ስራዎች ባለማለቃቸው ተገጥመው አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ከቀረቡ መጠይቆችና በመስክ ጉብኝት ወቅት ታውቋል፡፡

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የሚያክሙ የጤና ተቋማት በማስፋፋት እና ያሉትን በማጠናከር ለተጠቃሚዎች ተደራሽ መደረጉን በተመለከተ**

45. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የሚያክሙ የህክምና ማዕከላትን በማስፋፋት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በውጭ የሚሰጠውን የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት በአገር ውስጥ እንዲሰጥ በማድረግ ዜጎች በቅርበት ህክምናውን የሚያገኙበት ብሎም የውጭ ምንዛሬ ወጪን የሚቀንስበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

46. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ሆስፒታሎች ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል እና ጎንደር ዩንቨርስቲ ሆስፒታል በውጭ የሚሰጠውን የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት በአገር ውስጥ እንዲሰጥ ለማድረግ የካንሰር፣ የልብ እና የኩላሊት ህክምናዎች መሰጠት መጀመራቸው ታውቋል፡፡

47. የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት በአገር ውስጥ እንዲሰጥ ለማድረግ ስድስት የካንሰር ማዕከላት ግንባታ እየተካሄደ መሆኑ፣

48. ይሁን እንጂ ዜጎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፡

- ህክምና ለማግኘት በአገር ውስጥ የማይሰጡ አገልግሎቶች ስላሉ ወደ ውጭ አገር ሄደው እንደሚታከሙ፣
- በአገር ውስጥ የሚሰጡት ህክምናዎች ዋጋቸዉ ውድ በመሆናቸው የመክፈል አቅም የሌላቸው ሰዎች ህክምና አገልግሎት የማያገኙ መሆኑ፣
- ከአንድ መቶ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ባለበት አገር ውስጥ የካንሰር ህክምና ላይ ኬሞቴራፒ እና የጨረር ህክምናን በተሟላ መልኩ የሚሰጠው በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብቻ ሲሆን የአዋቂዎች ካንሰር ህክምና ተደራሽ አለመሆኑ፣

በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለሚሰጡ አገልግሎቶችም፡-

- የካንሰር ህክምና አገልግሎት የሚፈልጉ ታካሚዎች አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈጅባቸው ጊዜ አዋቂዎች ለተኝቶ መታከም ከ4-5 ወር፣ ለጨረር ህክምና ከ1 አመት ከ3 ወር እስከ 1 አመት ከ6 ወር፣ ኬሞቴራፒ ህክምና ተመላላሽ ለሆኑ 2 ወር አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈጅባቸው ሲሆን፤
- በባለሙያዎቹ በትርፍ ሰዓት በሚሰሯቸው ስራ ለግል ታካሚዎች ኬሞቴራፒ ቀጠሮ የሌለውና የጨረር ህክምና ቀጠሮ 3 ወር የሚፈጅባቸው እና በግል የጨረር ህክምና ለሚታከሙ ከብር 8000 - 15000 የሚያስፈልጋቸው መሆኑ፣
- የነፃ አፅፈው የሚታከሙ ታካሚዎች የተጠቀሱትን ወረፋዎች እንዲጠብቁ መገደዳቸው፤
- ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሆስፒታል፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል (ሐረር)፣ ከሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና ከካሳንቺስ ጤና ጣቢያ የተጠየቁ 38 ታካሚ ህብረተሰቦች ውስጥ የህክምና አገልግሎቱን በሚኖሩበት አካባቢ ባለ የጤና ተቋም ማግኘት ስለመቻላቸው ሲጠየቁ ስድስት (15.7%) የሚሆኑት እንደሚያገኙ ፣ ዘጠኝ (23.6%) የሚሆኑት በከፊል እንደሚያገኙ እና ሃያ ሶስት (60.5%) የሚሆኑት ጭራሽ እንደማይገኙ መግለፃቸው ታውቋል፡፡

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምናን ጤና ተቋማት ከመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ**

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሰረታዊ ደረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምናን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጤና ተቋማት ከመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲደረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በአገሪቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ 290 ሆስፒታሎች እና 3962 ጤና ጣቢያዎች ያሉ መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን በ60 ጤና ተቋማት (18 ሆስፒታል እና 42 ጤና ጣቢያዎች) ላይ ብቻ የተሻሻለ የስኳር እና ደም ግፊት ምርመራ እና ህክምና የሚሰጥ መሆኑን፤
- በ207 ጤና ተቋማት (ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች) የማህፀን ጫፍ ካንሰር ምርመራ እና ክራዮቴራፒ ህክምና የሚሰጡ መሆኑን እና 10 ሪፈራል ሆስፒታሎች ብቻ LEEP (loop electro excision procedure) አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን የሚገልፅ መሆኑ፤
- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት በ2008 በጀት አመት በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች እንዲሁም በ2009 በጀት አመት በተመረጡ 144 ጤና ጣቢያዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ለማስጀመር ታቅዶ በሁለቱም አመት አፈፃፀም ላይ 36 የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ብቻ ስለመከናወኑ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተገለፀ መሆኑ ፤
- 2010 በጀት አመት አመታዊ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የአእምሮ ጤና አገልግሎትን በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ጤና ተቋማት አቀናጅቶ መስጠትና ማጠናከር ያልተጀመረ መሆኑ፤ ክልል ጤና ቢሮዎች ራሱን የቻለ የአእምሮ ጤና ተጠሪ ባለማስቀመጣቸዉ የተነሳ የአእምሮ ጤና አገልግሎት

እየሰጡ ያሉ የጤና ተቋማት ልየታ ተሰርቶ የቅብብሎሽ ስርአት ባለመዘረጋቱና ተቋማት አለመያዛቸዉን የተገለፀ መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት አመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ከጉሮሮ ኢንፌክሽን ጋር ተያይዞ የሚመጣ የልብ በሽታ ምርመራና ህክምናን (Rheumatic Heart Diseases (RHD)) በተመረጡ 2 ሆስፒታሎችና 6 ጤና ጣቢያዎች ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ (ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል) ጋር በመተባበር የሚካሄደዉን በጉሮሮ ኢንፌክሽን አማካኝነት የሚመጣ የልብ በሽታ መከላከል ምርመራና ህክምና ትግበራ በተመለከተ ክትትል ያደረጉ ስለመሆኑ ነገር ግን እስከ አሁን ትግበራው የልብ ምርመራ ማከናወኛ መሣሪያው (Echo machine) ባለመስራቱ ምክንያት አለመጠናቀቁ የተገለፀ መሆኑ፤

❖ **ዜጎች ፍትሃዊ እና ጥራት ያለው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉን በተመለከተ**

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ሀገር አቀፍ ገፅታ ያለው ጥናት በማድረግ ለጤና ተቋማት ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና ላይ ዜጎች ፍትሃዊና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉን ሊከታተልና ተግባራዊነቱን ሊመዝን ይገባል፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ2010 ETHIOPIAN HEALTH REFORM IMPLIMENTATION GUIDELINES፣ ETHIOPIAN NATIONAL HEALTH CARE QUALITY STRATEGY (እ.ኤ.አ ከ2016- 2020)፣ እ.ኤ.አ በ2016 የወጣውን ETHIOPIAN HOSPITAL SERVICES TRANSFORMATION GUIDELINES እና ETHIOPIAN HEALTH CENTER REFORM INTEGRATED GUIDELINES ያዘጋጀ እንዲሁም የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አገልግሎት መገኘት እና ዝግጁነትን በተመለከተ በህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት Services Availability and Readiness Assessment (SARA) በ2018 G.C ላይ የተጠና ጥናት መኖሩ ታውቋል፡፡

53. ይሁን እንጂ፣

- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና ለመስጠት የሚያስችሉ የአገልግሎት ዝግጁነትን በተመለከተ፡ የሰለጠነ ባለሙያ፣ መመሪያ፣ ወሳኝ ህክምና መስጫ መሳሪያዎች እና አስፈላጊ መድሃኒቶች መገኘት አንፃር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ይህም ከሆስፒታሎች ይልቅ ጤና ጣቢያዎች ላይ የባሰ መሆኑ፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት መገኘት ከከተማ አካባቢ እና ሪፈራል ጤና ተቋማት ይልቅ የገጠርማ አካባቢዎች እና በመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማት ላይ አናሳ መሆኑ ይህም ከማህበረሰቡ አንፃር ዝቅተኛ ተደራሽነት ያለው መሆኑ
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ጤና ቢሮዎች፣ ጤና ፅ/ቤቶች/ መምሪያዎች እንዲሁም ጤና ተቋማት ዜጎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና ላይ ፍትሃዊና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል መመሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከክልሎች ያልደረሳቸው መሆኑን የገለጹ እና ስለ አገልግሎት አሰጣጣቸው ክትትል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ በየክልሉ ጤና ቢሮ ያልተደረገ መሆኑ መግለጻቸው፤
- በኦሮሚያ ክልል ባሉ ጤና ተቋማት ጥራትን ከማስጠበቅ አንፃር ተደራሽነቱ ላይ ክፍተት ያለበት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ያነጋገርናቸው ሃላፊ የገለፁ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የጤና ፕሮግራሞችን በማስፋፋት በበሽታዎቹ የሚመጣን ጫና እና የሞት ምጣኔ መቀነሱን በተመለከተ**

54. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የጤና ፕሮግራሞችን በማስፋፋት በበሽታዎቹ የሚመጣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫና እንዲሁም የሞት ምጣኔን በሂደት ሊቀንስ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከተያዙ እናቶች በበሽታዎቹ ምክንያት የሚከሰት ያለጊዜያቸው የተወለዱ ህፃናትን ሞት ሊቀንስ ይገባል፡፡

55. በኦዲቱ ወቅት፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና አስተዳደር መረጃ ስርዓት (በኤች ኤም አይ ኤስ) መሰረት በተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ውስጥ መረጃ የተያዘላቸው (ደም ግፊት፣ ስኳር፣ መተንፈሻ አካላት፣ ጭንቀት፣ የአይን ሞራ ግርዶሽ እና ካንሰር) የተያዙ ሰዎች ብዛት በ2008 በጀት አመት 4,626,322 በ2009 በጀት አመት 5,230,727 ሲሆን በ2010 በጀት አመት ያለው መረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ANNUAL HEALTH SECTOR PERFORMANCE እ.ኤ.አ 2018 ሪፖርት መሰረት በጉሮሮ ኢንፌክሽን አማካይነት የሚመጣ ልብ በሽታ 500,000 የሚሆኑ ሰዎች የተያዙ ሲሆን ከእነሱ ውስጥ 2,000 በአመቱ የሚሞቱ መሆኑ፤

- በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና ጉዳቶች (NCDI) ኮሚሽን ህዳር 2011 (እ.ኤ.አ Nov 2018) ባወጣው ሪፖርት፡

- በኢትዮጵያ የበሽታዎቹ ጫና በህይወት ዘመን ከሚያሳድሩት ጉዳት አንፃር የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች 37.5 በመቶ መሆኑ፣

- ከተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና አደጋዎች ጫና ውስጥ በአደጋዎች 19%፣ በልብ በሽታ 17 %፣ በአእምሮ ጤና መቃወስ 16% እና ካንሰር 11% በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙ መሆናቸው፤

- በ2016 በኢትዮጵያ ከጠቅላላ በሽታዎች ሞት በተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች 43 በመቶ ሞት የተከሰተ መሆኑ፣

- ከተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና ከአደጋዎች ሞት መጠን ውስጥ የልብ በሽታ እና የካንሰር በሽታ ወደ 54 በመቶ የሚጠጋ ሞት መጠን የያዙ መሆናቸው፤ በዚህም ከ51 በመቶ በላይ ሞቶች ከ40 አመት በታች እና 63 በመቶ ደግሞ ከ50 አመት በታች የሆኑ ዜጎችን የሚቀጥፍ መሆኑን፣

- በኢትዮጵያ ገጠር አካባቢዎች የአእምሮ ጤና መቃወስ 11 በመቶ ከሌሎች በሽታዎች አንፃር የያዘ መሆኑ፣ የአይን ሞራ ግርዶሽ ለ640,000 አይን መጥፋት እና 1.25 ሚሊየን ሰዎች ደግሞ ዝቅተኛ የማየት ችሎታ እንዲከሰት ማድረጉ፤

- የደም ግፊት ስርጭት 16 በመቶ መሆኑ የደም ውስጥ ስኳር መጠን መጨመር ስርጭት ከ 3.2 ወደ 8 በመቶ የጨመረ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች 23 በመቶ ጠቅላላ ወጪ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የሚወጣ ሲሆን ኩላሊት ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ ምክንያት 10 በመቶ፣ አእምሮ በሽታ 6 በመቶ፤ ስኳር በሽታ 2 በመቶ ወጪውን የሚይዙ መሆናቸው፤
- ኢትዮጵያ ከአጠቃላይ ወጪዎቿ ለጤና 6.7 በመቶ የምትመድብ ሲሆን ከጤና ወጪዎች 10 በመቶ ብቻ ለተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የሚመደብ መሆኑ ተገልጾዋል፡፡ እንዲሁም
- በአገር አቀፍ ጤና መግለጫ ሪፖርት (NHA6th report 2017) መሰረት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና ላይ አብዛኛው ወጪ በታካሚው ላይ የወደቀ መሆኑን በዚህም በግለሰቡ 68 በመቶ ፣ በመንግስት 30 በመቶ እና በአጋር ድርጅቶች 1 በመቶ ብቻ ወጪ የሚሸፈን መሆኑን ተጠቅሷል፡፡

❖ **ሴቶችን የበለጠ ሊያጠቁ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመለየት የመከላከል እና የመቆጣጠር ስራ መሰራቱን በተመለከተ**

56. ሴቶችን የበለጠ ሊያጠቁ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመለየት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሥርዓት በመዘርጋት ሊከላከል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ የሚዘረጋውም ሥርዓት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ተደራሽ ሊሆን የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

57. በኦዲቱ ወቅት፤

- በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በጡት እና ማህፀን ጫፍ ካንሰር ላይ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች መኖራቸው፤
- የኢትዮጵያ ተላላፊ ልሆኑ በሽታዎችና ጉዳቶች (NCDI) ኮሚሽን ህዳር 2011 ሪፖርት መሰረት ሴቶች በብዛት ሊያጠቁ የሚችሉ የካንሰር በሽታዎች የጡት፣ የማህፀን እና የማህፀን በር ጫፍ ፣ ኦቫሪ ፣ የደም፣ ታይሮይድ ፣ የቆዳ፣ ጉበት መሆናቸውን መለየቱ፣

- በAnnual health sector performance 2017/18 G.C (20th ARM) ሪፖርት መሰረት በየአመቱ ከሚታዩ አዲስ 65,000 ካንሰር ታማሚዎች ሁለት ሶስተኛው ሴቶችን ሲሆኑ በብዛት በጡት እና ማህፃን በር ጫፍ ካንሰር የተያዙ መሆናቸው መታወቁ፣
- በServices Availability and Readiness Assessment (SARA) 2018 G.C ሪፖርት መሰረት በ2017 ካሉት የጤና ተቋማት የማህፃን በር ጫፍ ካንሰር ምርመራ አገልግሎት መገኘት 9 በመቶ እና አገልግሎቱ በሚገኝባቸው ጤና ተቋማት ላይ ያለው የአገልግሎት ዝግጁነትን በተመለከተ 51 በመቶ እንደሆነ ማስቀመጡ፤
- እንደ እ.ኤ.አ በ2015 በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ጤና ተቋማት ካንሰር ምዝገባ ላይ የጡት ካንሰር 32.8%፣ የማህፀን ጫፍ ካንሰር 14.7% እና ኦቫሪያን ካንሰር 6.1% የያዙ መሆኑ፤
- ኦዲቱ በናሙና በታዩ የፌዴራል፣ የክልል ጤና ቢሮዎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሥር ባሉ የጤና ተቋማት የማህፀን ጫፍ ካንሰር ምርመራ እና ወደ ካንሰር ያልደረሱት ላይ ህክምና በተወሰነ መልኩ የሚሰጥ መሆኑ፣ ሌሎች ሴቶችን በብዛት የሚያጠቁ ካንሰር በሽታዎች ላይ አለመሰራታቸው፤

❖ **ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የሚመለከቱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ**

58. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የሚመለከቱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሲቀረጹ በሚመለከታቸው አካላት እንዲገመገሙ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የተቋቋሙት ፕሮጀክቶችም በታቀደላቸው ጊዜ እና በጀት እየተከናወኑ መሆናቸውን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ፕሮጀክቶች ውጤታማነታቸው በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት ፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የሚመለከቱ የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሚመለከታቸው አካላት እንዲገመገሙ እንዲሁም

ከተከናወኑ በኋላ ውጤታማነታቸው እንዲመዘን ስለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- በኦሮሚያ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ እና በደቡብ ክልል ጤና ቢሮ በአጋር ድርጅች የሚሰሩ ፕሮግራሞች ቢኖሩም በባለሙያዎች እንዲገመገሙ አለመደረጋቸው፤ የተቋቋሙ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እና በጀት እየተከናወኑ መሆናቸውን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጋቸው እና የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ውጤታማነታቸው የማይገመገሙ መሆኑ መግለጻቸው፤

ታውቋል፡፡

❖ **ለተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እና መድሃኒቶች አቅርቦት በተመለከተ**

60. በጤና ተቋማት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት የሚያገለግሉ የህክምና መሳሪያዎችና መድኃኒቶች ለጤና ተቋማት በወቅቱ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ የሚቀርቡ የህክምና መሳሪያዎችና መድኃኒቶች ተፈላጊው ጥራት ያሚሉ መሆናቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ አቅርቦቱም ከፍላጎት ጋር ሊጣጣሙ እና ያሉት መሳሪያዎች ሲበላሹ ቶሎ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ ክትትል ሊያድርግ ይገባል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለማከም የሚያስችል የመድሃኒት ተደራሽነትን ለማሻሻል ጥራት ላላቸው የአገር ውስጥ ምርቶች የጥሩ የአመራረት ሂደት ፍኖተ ካርታ (Good Manufacturing Practices road map) ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

61. በኦዲቱ ወቅት ፡

- የአእምሮ ጤና፣ ልብ፣ መተንፈሻ አካላት እና ካንሰር ላይ ያሉ መድሃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ለማድረስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስዊዘርላንድ ከሚገኝ Novartis መድሃኒት አገልግሎት እና በኦስትሪያ ከሚገኝ ሳንዶዝ የሚባል ድርጅት ጋር እ.ኤ.አ በጥቅምት 15 2015 ላይ በተፈራረመው መሰረት እ.ኤ.አ ከታህሳስ 31 2015 ጀምሮ በቀጣይ 5 አመታት መድሃኒት ለማቅረብ የተስማሙበትን መግባቢያ ሰነድ የቀረበ ሲሆን በመግባቢያ ሰነዱ መሰረት ስለመፈፀሙ ግን ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ15/5/2011 ዓ.ም ለመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በፃፈው ደብዳቤ መሰረት የካንሰር መድሃኒቶች ተደራሽነትን ለማሻሻል ላለፉት 4 አመታት ከኤስ ዲ ጂ ድጋፍ መገኘቱን እና በዚሁ አመትም የ 4 ሚሊየን ድጋፍ በመገኘቱ የካንሰር መድሃኒቶች እንዲገዙ ትዕዛዝ ስለመስጠቱ የሚያሳይ መሆኑ፤

- ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ANNUAL HEALTH SECTOR PERFORMANCE 2018 ሪፖርት መሰረት በአገሪቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን (ካንሰር ፣ የአይን ጤና ፣ ስኳር እና ደም ግፊት) ለማከም የሚረዱ በቂ የህክምና ግብአቶች አለመኖራቸው፤

- በሀገራችን የካንሰር በሽተኞችን ለመለየትና የተለዩ በሽተኞችን ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ለህክምና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ያልተሟሉ መሆኑ፤

- በጤና ተቋማት ውስጥ ለአእምሮ ጤና አገልግሎት በቂ የሆነ የህክምና መሳሪያዎች አለመኖሩ ከማስረጃዎች የተከለሰ መሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በፌዴራልና በክልል ጤና ቢሮዎች ሥር የሚገኙ የጤና ተቋማት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት የሚቀርቡ የህክምና መሳሪያዎች ጥራት ቁጥጥር፣ አቅርቦት ከፍላጎት ጋር እንዲጣጣሙ እና ያሉት መሳሪያዎች ሲበላሹ ቶሎ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ ክትትል አለመደረጉ፤

- በጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል የህክምና መሳሪያዎች በህክምና መሳሪያ ቁጥጥር ባለሙያዎች ጥራታቸው ተፈትሸው የማይረከቡ መሆናቸው በዚህም ሁለት የትንፋሽ መተኪያ መሳሪያዎች እንደተገዙ አገልግሎት የማይሰጡ መኖራቸው እንዲሁም በአገሪቱ ለካንሰር ህክምና የጨረር አገልግሎት የሚሰጠው ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብቻ ሲሆን ለህክምናው የሚውል መሳሪያ ያሉት ሁለት ሲሆኑ በስራ ላይ ያለው 1 ብቻ ሲሆን ሌላው መሳሪያ ከተበላሸ ከ8 ዓመት በላይ የሆነውና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመጠገኑ፤

- በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ስር ያሉ 10ሩም ክፍለ ከተማ ስር ያሉ ጤና ጣቢያዎች አዲስ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሚገቡበት ጊዜ የሚፈተሸበት Acceptance checklist አለመኖር፣ የተሟላ የህክምና መሳሪያዎች እና የላቦራቶሪ ምርመራዎች አለመኖራቸዉ፤ በህክምና መገልገያ መሳሪያዎች የሚገለገሉ ሁሉም የጤና ባለሙያ ስለ አጠቃቀሙ እና ጥገናው ተገቢ ስልጠና አለመውሰዳቸው፣

- በናሙና ባየናቸው ሁሉም ጤና ቢሮዎች፣ ጤና ፅ/ቤቶች እና ጤና ተቋማት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለማከም የሚረዱ መድሃኒቶች በስፋት የሚቀራረጡ እና ለተጠቃሚው ተደራሽ እንዲሆኑ አለመደረጉ፤ ዋጋቸው ውድ የሆኑ መድሀኒቶች በበቂ ሁኔታ የማይገኙ እንዲሁም ነፃ ህክምና ተጠቃሚ ያልሆኑ ነገር ግን ውድ መድሃኒት የመግዛት አቅም የሌላቸው ታካሚዎች መድሃኒቱን ለመግዛት የሚቸገሩ መሆኑ፤

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከአገር ውስጥ መድሃኒት አምራች ኩባንያዎች ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ አንፃር የማስፈፀሚያ መርሃ ግብር ያላዘጋጀ መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2010 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም የተገለጸ መሆኑ ፤

- በ2010 በጀት አመት የካንሰር መድሃኒት አቅርቦትን መከታተል እና ብሄራዊ የካንሰር ቁጥጥር አፈጻጸም ለመከታተል የታቀደ ቢሆንም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከመድሃኒት አምራች ኩባንያዎች ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ አንፃር የማስፈፀሚያ መርሃ ግብር ባለመዘጋጀቱ ያልተፈፀመ መሆኑ፤

- የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2008-2012 ኢ.አ ላይ የመድኃኒት ተደራሽነትን ለማሻሻል ጥራት ላላቸዉ የአገር ውስጥ ምርቶች ላይ ትኩረት ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም ባለፉት ሦስት ተኩል የእቅድ ዘመኑ አመታት ተግባራዊ ለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሆስፒታል፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል (ሐረር)፣ ከሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና ከካሳንቺስ ጤና ጣቢያ ከተጠየቁት 38 ታካሚዎች ውስጥ ስለ መድሃኒት መገኘት ሲጠየቁ አስራ ሶስት (13) የሚሆኑ በመንግስት ሆስፒታሎች መድኃኒቶቹ አይገኙም ያሉ ሲሆን፤ አሥራ ሦስቱ (13) በከፊል ይገኛል፣ አስራ ሁለቱ(12) ይገኛል ብለው

የመለሱ ሲሆን የመክፈል አቅማቸውን ያገናዘበ ስለመሆኑ ሲጠየቁ፡- ሀያ አንዱ (21) መድኃኒቱ ውድ ነው የመክፈል አቅማችንን ያገናዘበ አይደለም ሲሉ፣ አስራ ሦስቱ(13) ተመጣጣኝ መሆኑን ፤ አንድ ሰው ርካሽ ነው፣ ሦስቱ (3) የነፃ ታካሚ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን የሚጠቀሙት መድሃኒት የአገር ውስጥ ይሁን የውጭ ሲጠየቁ አምስት (5) የአገር ውስጥ መድኃኒት ነው የምንጠቀመው ያሉ ሲሆን፤ ሃያ ሁለቱ (22) የውጪ አገር ነው፤ አስራ አንዱ (11) የምንጠቀመው መድኃኒት የአገር ውስጥ ይሆን የውጪ አገር አናውቅም ብለው መልሰዋል፡፡ እንዲሁም የአገር ውስጥ መድኃኒት የማይጠቀሙበትን ምክንያት ሲጠየቁ ስምንቱ(8) መኖሩን ስለማላውቅ፣ አስራ አራቱ (14) ስለሌለ፣ ሶስቱ (3) የተሻለ ፈዋሽ ነው ብዬ ስለማላስብ፣ ያሉ ሲሆን ስምንቱ (8) ደግሞ ጤና ተቋሙ የሰጠኝን መድኃኒት ነው የምጠቀመው ማለታቸው፣ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ መጠይቆች ታውቋል፡፡

❖ **በመከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስ እና ማረሚያ ቤቶች ላይ ባሉ የህክምና መስጫ ተቋማት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ**

62. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስ እና ማረሚያ ቤቶች ላይ ባሉ የህክምና መስጫ ተቋማት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍና፣ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት ፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በተመለከተ ከመከላከያ እና ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ክፍተት ያለበት መሆኑን በ2010 በጀት አመት የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክቶሬት ሪፖርት መገለጹ፣
- የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የሐረሪ ክልል ጤና ቢሮ፣ የደቡብ ክልል ጤና ቢሮ፣ የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ጤና ፅ/ቤት፣ የምስራቅ ሃረርጌ ዞን ጤና ፅ/ቤት፣ የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና ፅ/ቤት እና የሲዳማ ዞን ጤና መመሪያ በየክልላቸው ባሉ መከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስ እና

ማረሚያ ቤቶች ላይ ባሉ የህክምና መስጫ ተቋማት ትኩረት በመስጠት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጋቸውን መግለጻቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ስራ መስራቱን በተመለከተ**

64. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

65. በኦዲቱ ወቅት ፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ስራን በተመለከተ የአእምሮ ጤና ላይ ከሚሰሩ የተወሰኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተሰሩ ጅምር ስራዎች ቢኖርም ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመሆን ከችግሩ ስፋት አንፃር እና ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ለእነሱ ተብሎ ተለይቶ የተሰራ ስራ አለመኖሩ፣
- የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ እና የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ጤና ፅ/ቤት፣ የሐራሪ ክልል ጤና ቢሮ፣ የምስራቅ ሃራርጌ ዞን ጤና ፅ/ቤት፣ የደቡብ ክልል ጤና ቢሮ፣ የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና ፅ/ቤት፣ የሲዳማ ዞን ጤና መመሪያ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ስራ አለመስራታቸው፣
- በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማረጃዎችና ከቀረቡ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከል እና መቆጣጠር በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ትብብር ፈጥሮ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የጋራ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ በየጊዜው አፈጻጸሙን በጋራ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ በህክምና ሙያ ተመርቀው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ህክምና የሚሰጡ የተለያዩ ባለሙያዎች ስፔሻላይዝድ ያደረጉትን ጨምሮ በቂ ባለሙያዎች በማፍራት ለህብረተሰቡ አገልግሎት ተደራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እየተገነቡ ያሉት የካንሰር ህክምና ማዕከላት በፍጥነት ተጠናቀውና ተፈላጊው ባለሙያ ተሟልቶላቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ፣ ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገር ውስጥ በማስፋፋት ህክምና ፈላጊዎች በወቅቱ እና በመጠነኛ ወጪ ህክምናውን እንዲያገኙ በማድረግ በውጭ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት በአገር ውስጥ እንዲሰጥ በማድረግ በሽተኞችንም ሆነ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ወጪን የሚቀንስበት ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ምንነት እንዲሁም በሽታዎቹን ሊያስከትሉ ከሚችሉ መንስኤዎች ጋር ተያይዞ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በመደበኛ ትምህርት ካሪኩለም ውስጥ እንዲካተቱ፣ የበሽታው ተጋላጭነት የሚጨምሩ ባህሪያትን ለመቀነስ ህብረተሰቡ ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚያገኝበት ሁኔታ ሊያመቻች፣ ውጤታማነታቸው ላይ ክትትል እና ግምገማ ስራ በማጠናከር ተማሪዎች ስለ በሽታዎቹ እውቀት እንዲኖራቸዉ እና በበሽታዎቹ እንዳይያዙ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚያችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት መሰጠት ያለባቸው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ምርመራ እና ህክምና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጤና ተቋማት ተሟልተው እንዲሰጡ፤ የህክምና ማዕከላትን በማስፋፋት የህክምናው ተጠቃሚዎች በአቅራቢያቸው አገልግሎቱን እንዲያገኙ ፤ ሴቶችን የበለጠ ሊያጠቁ የሚችሉ የካንሰር በሽታዎች ላይ የመከላከል እና መቆጣጠር

አገልግሎቶችን በማስፋፋት የህክምናው ተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚደረግበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት በማስፋፋት በየጊዜው እየጨመረ በመጣው የበሽታዎቹ መስፋፋት ምክንያት የሚመጣውን የጤና፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ጫና እና የሞት ምጣኔ (በበሽታዎች በተያዙ እናቶች ምክንያት የሚከሰት ያለጊዜያቸው የተወለዱ ህፃናት ሞት ጨምሮ) እንዲቀንስ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልልና አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ስትራቴጂ በመቅረጽና ሥርዓት በመዘርጋት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት የሚቀርቡ የህክምና መሳሪያዎችና መድኃኒቶች ከፍላጎት ጋር እንዲጣጣሙና በወቅቱ እንዲደርስ በማድረግ ታካሚዎች ለእንግልተና ለአላፊላጊ ወጪ እንዳይዳረጉ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ያሉት መሳሪያዎች ሲበላሹ ቶሎ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ ክትትል በማድርግ በህክምና መሳሪያዎች ምክንያት የሚፈጠረውን አገልግሎት መቆራረጥና መንገላታት እንዳይኖር መደረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥራት ላላቸዉ የአገር ዉስጥ የመድኃኒት አምራቾች ትኩረት በመስጠት ጥሩ የአመራረት ዘዴ እንዲተገብሩ በማድረግ የመድሃኒቶች ተደራሽነትን ሊያሻሽል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመከላከያ ሰራዊት፣ ከፖሊስ ተቋማትና ከማረምያ ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት በሥራቸው ባሉ አባላት ሆነ በታራሚዎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ትኩረት ተደርጎ እንዲሰራ ሁኔታዎች ሊያመቻችና ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

1.2.1.5. በሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ

❖ **ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች በዓመታዊ እቅድ በማካተት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

66. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች የእስትራቴጅክ እቅዱን ወደ ዓመታዊ እቅድ በመመንዘር ሊያቅድ እና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ያከናወነውንም ስራ በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ

- በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ ፈርኒቸር፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ የስልጠና መስኮች የሚያስፈልግ የማጣቀሻ መጽሐፍት፣ ዩኒቨርስቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጓቸውን ኮምፒውተሮችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የምግብ ቤት እቃዎች፣ እንዲሁም የጀነሬተር ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ ምንም ዓይነት ግዥ አለመከናወኑ፣

- ግዥ ባልተከናወነበት በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ከ67 ፐርሰንት እስከ 85 ፐርሰንት አፈፃፀሙ እንደተከናወነ ተደርጎ የቀረበ መሆኑ፣

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 በጀት ዓመት የመግባቢያ ሰነዶችን እና መመሪያዎችን ለማዘጋጀት እቅድ ቢይዝም ከየትኞቹ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እና ምንን በተመለከተ እንደሚፈራረሙ በዕቅዱ አለመገለጹ፣ ምንን በተመለከተ እና ምን ያህል መመሪያዎች ለማዘጋጀት እንደታቀደ ያላስቀመጠ መሆኑ፤

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የአርማታ ብረት እና የሲሚንቶ ግዥ ለመፈፀም እቅድ ቢይዝም ስለሚገዛው የሲሚንቶና የአርማታ ብረት ዓይነት እና መጠን በእቅዱ ላይ ያላስቀመጠ መሆኑ፣

- በ2010 በጀት ዓመት እቅድ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ፈርኒቸሮች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ እቃዎችን ግዥ ለመፈፀም አቅዶ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ባልተከፈተበት ሁኔታ በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ 51 ፐርሰንት እንዳከናወነ ተደርጎ የቀረበ መሆኑ፤
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች ተግባራት የተከናወኑበትን ጊዜ የማያመለክቱ መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግዥዎችን ከመፈፀሙ በፊት በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን የሰበሰበ እና የገበያ ጥናት ያደረገ ስለመሆኑ፣**

68. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ግዥዎችን ለመፈፀም በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን ሊሰበስብና የገበያ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡
69. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የአርማታ ብረት እና የሲሚንቶ ግዥ ለማከናወን እቅድ ቢይዝም ስለሚገዛው የሲሚንቶ እና የብረት አይነት (ባለ 6፣ ባለ 8፣ ባለ 10 ወዘተ) እና ብዛት በዝርዝር ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በ2008 በጀት ዓመት ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያገለግል 12,440 ቶን የባለ 10 ጨምሮ የተለያየ ስፋት ያላቸው (ከእያንዳንዱ ምን ያህል ብዛት ብረት እንደተገዛ መረጃ ያልቀረበ) የአርማታ ብረት ግዥ የፈፀመ መሆኑ፣ ሆኖም በ2008 ከተገዛው ብረት እስከ ጥቅምት 2011 ድረስ ከግንባታ ተርፎ አገልግሎት ላይ ሳይውል የተከማቸ የባለ 10 የአርማታ ብረት በየግንባታ ሳይቱ ቢኖርም በ2011 ዓ.ም በድጋሚ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ውጪ በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የግንባታ ቅርንጫፍ ፕሮጀክቶችን የግዥ ፍላጎት ሳይጠይቅ ተጨማሪ ብዛቱና የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ባለ 10 የአርማታ ብረት ግዥ ፈጽሞ ለዩኒቨርስቲዎች ያሰራጨ መሆኑ፤

- በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት ዩኒቨርስቲዎች መካከል በመስክ ጉብኝት ወቅት ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ፕሮጀክት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የተከማቸ 12,263 ቤርጋ (1ቤርጋ =12 ሜትር የአርማታ ብረት) ባለ 10 ብረት እያለ እና አገልግሎት ላይ ሳይውል በ2011 ተጨማሪ 2,900 ቤርጋ ባለ10 የአርማታ ብረት ከቅርንጫፍ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፍላጎት ውጭ በግንባታ ሳይት የተራገፈ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለፈፀማቸው ግዥዎች የገበያ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በመስክ ጉብኝት በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የተቋቋመ ስለመሆኑ**

70. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡
71. የፌደራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 649/2001 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ ኮሚቴ ያቋቁማሉ በማለት ቢገልጽም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አላቋቋመም፡፡

❖ **ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚፈጸሙበትን የግዥ ዘዴዎች በመለየት በግዥ እቅድ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ፣**

72. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ሊያመላክት ይገባል፡፡
73. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች (ግልጽ ጨረታ፣ ውስን ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ፣ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣ በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ) ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ያላስቀመጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

❖ **ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብዓቶች እና ተዛማጅ እቃዎች በታቀደላቸው ጊዜ መገዛታቸውን በተመለከተ፣**

74. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች ግዥ በታቀደላቸው ጊዜ ሊፈፅም ይገባል፡፡

75. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ 11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስቻሏቸውን የትምህርት ግብዓቶች በወቅቱ ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

76. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ መፈፀምን በተመለከተ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና የማጣቀሻ መጽሐፍት ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል እስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነድ በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ፣ የላቦራቶሪ ፈርኒቸር እስፔስፊኬሽን ዝግጅት የተጠናቀቀ እና ግዥ ለመጀመር የሚያስችል ስራ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ፣ የፈርኒቸር፣ የምግብ ማብሰያና ማቅረቢያ እቃዎች እስፔስፊኬሽን በመዘጋጀት ላይ እንደሆነ፣ የኮምፒውተርና ተዛማጅ እቃዎች እስታንዳርድ እና እስፔስፊኬሽን ለማዘጋጀትም ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገ በሁለቱ በጀት ዓመታት የእቅድ ክንውን ሪፖርት የተገለፀ ቢሆንም፣

- እቃዎች እስከ ታህሳስ 2010 ያልቀረቡ መሆኑ፣
- ከታህሳስ 2010 በኋላ እስከ በጀት ዓመቱ ማብቂያ የተሟላ ባይሆንም የተማሪ መገልገያ ፈርኒቸር እና ኮምፒውተር ብቻ የቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም
- የተፈጥሮ ሳይንስ መጽሐፍት ለማቅረብ የውል ስምምነት ካደረጉት ሶስት አቅራቢዎች ሁለቱ በህዳር 2011 ማቅረብ የጀመሩ መሆኑ

ታውቋል፡፡

77. እንዲሁም

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚገዛቸውን እቃዎች ዝርዝር እና የሚያቀርብበትን ጊዜ ለዩኒቨርሲቲዎቹ በግልፅ ባለማሳወቁ እና በወቅቱ ባለማቅረቡ ዩኒቨርሲቲዎቹ በራሳቸው የመደበኛ በጀት (የብር መጠኑን

ያልገለጹት) የኤሌክትሮኒክስ፣ የፈርኒቸር፣ የመጽሐፍት፣ የኮምፒውተር፣ ኤልሲዲ ፕሮጀክተር፣ እንዲሁም ለተማሪዎች የምግብ ማብሰያ የሚውሉ እቃዎችን የገዙ መሆኑን መግለጻቸው፤

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን ለመግዛት ከ16 የውጪ አገር የላቦራቶሪ መሳሪያ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ከ2009 ጀምሮ የግዥ ስምምነት ውል የተፈራረመ ቢሆንም እስከ ኦዲቱ ማብቂያ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ያልተከፈተ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት አዲስ የግዥ ስራዎችን ማለትም የማህበራዊ ሳይንስ መጻሕፍት፣ የኢንጅነሪንግ መጻሕፍት፣ የላቦራቶሪ መሣሪያዎችና የተማሪዎች መገልገያ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ የስልጠና መስኮች የሚያስፈልግ የማጣቀሻ መጻሕፍት ግዥ ለመፈፀም ቢታቀድም እስከ ሰኔ 30 2010 ዓ.ም ያልተከናወነ መሆኑ፤ እንዲሁም በ2011 በጀት ዓመት የመጽሐፍት እና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ግዥዎች የተቋረጡ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

❖ **አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ፣**

78. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋገጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ሆነ ዩኒቨርሲቲዎቹ ሲረከቡ በስፔሲፊኬሽኑ ወይንም በናሙና መሰረት መሆኑን እያረጋገጡ ሊረከቡ ይገባል፡፡
79. ይሁን እንጅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለማድረጉ ታውቋል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፈርኒቸር አቅራቢዎች እቃዎቹን ሲያቀርቡ እቃዎቹን ለሚረከቡ ዩኒቨርስቲዎች በቴክኒክ መግለጫው መሰረት እንዲረከቡ ደብዳቤ ከመፃፍ እና የተረከቡበትን ሰነድ ከመቀበል ባለፈ በአካል ሂዶ የማያረጋግጥ እና የማረጋገጡን ስራ ለመስራት ውል የተፈራረመው የአርሲ ዩኒቨርሲቲም ለዩኒቨርሲቲዎች የገቡ የፈርኒቸር እቃዎች በቴክኒክ መግለጫው መሰረት መሆናቸውን ያላረጋገጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በቀረቡ ፈርኒቸሮች ላይ የተለያዩ ችግሮች ታይተዋል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመጋቢት 2010 ዓ.ም በቦንጋ ዩኒቨርስቲ ባደረገው የመስክ ምልከታ ለዩኒቨርሲቲው በቀረቡ የተለያዩ ፈርኒቸሮች ላይ፣

  - **በተማሪዎች ወንበር/አርም ቼር** (Tablet chair):- **የታዩ ችግሮች፡**
    - የወንበሩ አራቱም እግሮች እኩል አለመርገጥ፣
    - ብይዱ መልቀቅ እና የተወላገዱ መሆናቸው፣
    - የታሰረበት ቡሎን በናሙናው መሰረት አለመሆኑ፣
    - የአንዳንዶቹ writing board የተጣመመ መሆኑ፣

  - **የመመገቢያ እና የምግብ ቤት ወንበሮች** (Dining and Lounje chair)
    - የቀረበው ወንበር በሳምፐሉ መሰረት አለመሆን፣ ለምሳሌ የመደገፊያው ውፍረት 10 ሚሊ ሜትር መሆን ሲገባው የቀረበው በ6 ሚሊሜትር መሆኑ፣
    - የተወሰኑት ወንበሮች እግራቸው የተጣመመ መሆኑ፣
    - የታሰረበት ቡሎን በሳምፐሉ መሰረት አለመሆኑ፣

  - **ተደራራቢ አልጋ** (Double bunk bed)
    - የቀረበው አልጋ እኩል አለመርገጥ፣
    - አልጋው በተገቢው መንገድ ሊሰካካ አለመቻሉ እና ተጨማሪ የማስተካከያ ስራ ማስፈለጉ፣ ተሰኪዎቹ በአግባቡ አራቱም ማዕዘን ላይ አለመሰካት፣
    - ብይዳቸው መልቀቅ እና መገንጠል፣

- የአልጋው እግር ጎሚኖ አለመኖር፣
- ለፍራሽ ማስቀመጫ ተብሎ የመጣው ፓሊይ ውድ ከአልጋው ሳይዝ በላይ በመሆኑ የማስተካከያ ስራ መፈለጉ፤

የታዩ የጥራት ችግሮች መሆናቸው መገለጹ፤

80. በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎች ሲላኩ በቴክኒክ መግለጫ እና በናሙና መሰረት መሆናቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ስለመኖሩ ተጠይቀው

የእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች

- አቅራቢዎች ለዩኒቨርሲቲው እቃዎችን ሲያስረክቡ በቴክኒክ መግለጫ (እስፔስፊኬሽን) እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑ የሚረጋገጥበት ስርዓት አለመኖሩን፣
- ገዝቶ የላካቸውን ንብረቶች በቴክኒክ መግለጫው (specification) መሰረት እየቀረቡ መሆኑን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትል እንዳላደረገና በአካል ተገኝተው የማረጋገጥ ስራ እንዳልሰሩ የገለጹ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለዩኒቨርሲቲው የሚገዛቸውን ዕቃዎች ስፔስፊከሽን እና ናሙና አስቀድሞ ባለመላኩ የሚቀርቡ እቃዎች በትክክለኛው መስፈርት ስለመምጣታቸው ማረጋገጥ እንዳይቻል ማድረጉን የገለፁ መሆኑ፤

የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የስራ ኃላፊዎች

- አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትል እንዳላደረገ እና የፈርኒቸር እቃዎችን ስፔስፊኬሽን ቀድመው የላኩ ቢሆንም የሌሎች እቃዎችን እስፔስፊኬሽን የሚልኩት እቃዎቹን አጓጉዞ ለሚያደርስ ትራንስፖርተር መሆኑን ሆኖም እስፔስፊኬሽኑ ቀድሞ ቢመጣ የእቃዎቹን ዓይነትና ብዛት በመለየት ተደጋጋሚ ግዥ እንዳይከሰትም ሆነ ጥራቱን በተሻለ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያስችል እንደነበር የገለፁ መሆኑ፤ እንዲሁም

የወራቤ ዩኒቨርስቲ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፈርኒቸር ዕቃዎችን ለዩኒቨርስቲው ከመላኩ በፊት ሁለት ባለሙያዎች እንዲላኩ እና የዕቃዎችን ናሙና በማሳየት እና እስፔስፍኬሽን በመስጠት አረጋግጠው እንዲቀበሉ እንዳደረገ፣ ሆኖም ኮምፒውተር ገቢ ሲደረግ ዩኒቨርስቲው በራሱ ባለሙያዎች በማረጋገጥ መቀበሉን፣
- አቅራቢዎች ዕቃዎችን ለዩኒቨርስርቲው ሲያቀርቡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአካል ተገኝቶ ክትትል የማያደርግ መሆኑን፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የላካቸውን ዕቃዎች ዩኒቨርስቲው መረከቡን እና ገቢ ማድረጉን የገቢ ማድረጊያ ሠነድ ዕቃውን ከአጓጓዘው አካል (transporter) በመቀበል ብቻ የሚያረጋግጥ መሆኑን፤
- ከዚህ በተጨማሪም ከቀረቡት ዕቃዎች መካከል ጉድለት/ብልሽት ያለባቸውን አልጋና ወንበሮች የተወሰኑትን አቅራቢዎቹ አስተካክለው እንዲመልሱ መደረጉንና አንዳንድ ፈርኒቸሮችን በአጣዳፊ ሰዓት የመጡ በመሆኑ ዩኒቨርስቲው በራሱ ወጪ አስተካክሎ ጥቅም ላይ ሲያውል ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን የገለፁ መሆኑ፤

  ከዚህ በተጨማሪም የብረት እና የሲሚንቶን አቅርቦት በተመለከተ በናሙና በታዩ በወራቤ ዩኒቨርሲቲ፣ በእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ እና በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ብረት እና ሲሚንቶ በሚልክበት ወቅት የተላከውን የግብዓት ዓይነትና ብዛት የሚገልጽ ሰነድ እቃውን ከሚያጓጉዘው ሾፌር በመቀበል የመጣውን ግብዓት ከሰነዱ ጋር ተመሳክሮ የገቢ ሰነድ ተቆርጦ እንደሚመለስ ሆኖም የአርማታ ብረት አስቀድሞ በተዘጋጀ ደረጃ (grade) መሰረት መሆኑ እንደማይረጋገጥ ገልፀዋል፡፡

❖ **የተገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ተሰራጭተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተደረገ ስለመሆኑ፣**

81. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተገዙ ዕቃዎችን ለተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች በወቅቱ ሊያሰራጭ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

82. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዩኒቨርስቲዎች የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቅረቢያ እቃዎችና ጄነሬተር ግዥ ፈጽሞ በጥቅምት 2011 ዓ.ም ወደ 11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የላከ ቢሆንም ከዩኒቨርስቲዎቹ ጋር እርክክብ ያልተፈፀመ እና እቃዎቹ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

❖ **ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ያዋለ ስለመሆኑ፣**

83. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት የመንግስት የግዥ ስርዓትን ጠብቆ በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

84. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግንባታ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች አይነትና ብዛት በስራ ቅደም ተከተል በትክክል በመለየት መጥኖ ባለመግዛቱ የባለ 10 የአርማታ ብረት ለግንባታ ከሚያስፈልገው ብዛት በላይ በየግንባታ ሳይቶች ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችቶ መገኘቱ፤ ለምሳሌ በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በህዳር 2011 ዓ.ም ለሳይት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የተከማቸ በወቅቱ በተገዛበት ዋጋ መሰረት ብር 1,639,848.00 አካባቢ የሚደርስ 12,263 ቤርጋ ብረት የተከማቸ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

❖ **የፕሮጀክቱ ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ስለመሆኑ፣**

85. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ሊሆን ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓቶች አስተዳደርን በተመለከተ

- የግንባታ ግብዓቶች ወጥነት ባለው መልኩ የሚመዘገቡበት አሰራር አለመኖሩ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከ2008 ጀምሮ ለግንባታ የተገዙ ግብዓቶች ብዛት፣ ግንባታ ላይ የዋሉ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች፣ እንዲሁም በየግንባታ ሳይቱ የተከማቹ የአርማታ ብረቶች መዝገብ በተሟላ መልኩ አለመኖሩ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በነሀሴ 2009 ዓ.ም በቦንጋ ዩኒቨርስቲ ባደረገው የመስክ ምልከታ ሲሚንቶን በተመለከተ ከፍተኛ ብክነት መታየቱ፤ ዘላለም በተባለ ስራ

ተቋራጭ ሳይት ላይ ፕሪካስት ለማምረት የተዘጋጀ ባለ 6 ቁጥር እስታፋ ብረት ጥቅም ላይ ሳይውል ተጠላልፎ የተቀመጠ መሆኑ፣ የአርማታ ብረት የተከማቸበት ቦታ በአግባቡ ያልተከለለ እና በሳር የተዋጠ መሆኑ፤

- በነሀሴ 2008 ዓ.ም በወራቤ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባደረገው የመስክ ምልከታ የአርማታ ብረት የተከማቸበት ቦታ አጥር አለመኖሩ፤ ለህንፃ ግንባታ የተገዛው ሲሚንቶ የተከማቸው በግለሰብ የኪራይ መጋዘን መሆኑ እና ከመጋዘን አከራዩ ፋብሪካ ውስጥ በመሆኑ ያለው ጥበቃ የፋብሪካው እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያልነበረ መሆኑ፤ እንዲሁም በነሀሴ 2009 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባደረገው የመስክ ምልከታ ፒራሚድ በተባለ ስራ ተቋራጭ ሳይት ብዛት ያለው ባለ 14 ቁጥር ከ3 ሜትር በላይ እርዝመት ያለው ቁርጥራጭ ብረት ተከማችቶ መገኘቱ፤

  - በጂንካ ዩኒቨርስቲ በየካቲት 2010 ዓ.ም ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን አጠቃቀም በተመለከተ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተደረገ የመስክ ምልከታ የሚከተሉት ችግሮች የታዩ መሆኑ፣

    - ለተቋራጮች የግንባታ ግብዓት በሞዴል 22 ወጪ ሲደረግ በአነሰ ዋጋ ወጪ ማድረግ እና የተቋራጬን ስም በትክክል አለመፃፍ፣
    - ከተቋራጮች ተመላሽ መሆን የነበረበት አርማታ ብረት ተመላሽ አለመሆን፣
    - በብክነት ሊያዙ የማይችሉ ቁመታቸው ከ2 ሜትር እስከ 10 ሜትር የሚሆኑ ብረቶች በየስራ ተቋራጩ እጅ የሚገኙ መሆናቸው፣
    - 631 ኩንታል ሲሚንቶ ለብልሽት እና ለብክነት መዳረጉ፣
    - የአርማታ ብረቱ ከዩኒቨርስቲው ግቢ ውጪ መከማቸቱ፣
    - የዩኒቨርስቲው ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ቢሮ ከዩኒቨርስቲው ግቢ ውጭ በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆን፣

  - በቀብሪ ደሃር ዩኒቨርስቲ በሐምሌ 2009 ዓ.ም ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን አጠቃቀም በተመለከተ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተደረገ የመስክ ምልከታ የሚከተሉት ችግሮች የታዩ መሆኑ፣

- የሲሚንቶና ብረት አወጣጥን የተመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ ያልተያዙ መሆኑ፣
- የአርማታ ብረት በሰንሰለት ያልታሰረና ለቁጥጥር አስቢ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው በሚገኘው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት ገቢ ሰነድ 0044017 ላይ 200 ኩንታል ሲሚንቶ የተቀረጠ ቢሆንም ሲሚንቶ ከፋብሪካው ወጪ ያልሆነ እና ወደ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ለክፍያ ያልመጣ መሆኑ፣
- የአርማታ ብረት ከማዕከል (ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ) የተላከው 14,938.59 ኩንታል ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው በሚገኘው የግንባታ ጽ/ቤት የንብረት ገቢ ሰነድ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘው 15,988.59 ኩንታል መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት 1,050 ኩንታል ልዩነት ማሳየቱ፣
- 40 ኩንታል የሚሆን ሲሚንቶ በአያያዝ ጉድለት ለብልሽት መዳረጉ፤
- ሰነድ አያያዝን በተመለከተ ምንም ዓይነት ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፣

የንብረት አጠባበቅ እና አያያዝን በተመለከተ ከ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ሳይቶች በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት በቀረበ ቃለ መጠይቅ የአርማታ ብረት ማከማቻ ቦታ እና አጥር እንዲሰራላቸው ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘታቸውና በዚህ ምክንያት የአርማታ ብረት አላግባብ መሬት ላይ እንዲከማች እና በዝናብ ጊዜ ተሸከርካሪ የማያስገባ በመሆኑ የአርማታ ብረት አቅራቢዎችም ሆነ ስራ ተቋራጮች አገልግሎት ለማግኘት የተቸገሩ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ክትትል የተደረገ ስለመሆኑ፣**

87. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ መደበኛ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
88. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ የግንባታ ሳይቶች ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ አልፎ አልፎ የተከታተለ

ቢሆንም ክትትሉ መደበኛ አለመሆኑ እና ክትትል ባደረገባቸው የግንባታ ሳይቶች ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ፣

- በሚያዚያ 2009 ዓ.ም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ የንብረት አስተዳደር ክትትል ሲያደርግ የተለያዩ ችግሮች ቢያገኝም በድጋሚ በጥር 2010 ዓ.ም በዩኒቨርስቲው የመስክ ክትትል ሲደረግ ክትትሉ ህንፃዎች ያሉበትን ደረጃ በፎቶ ከማሳየት ባለፈ የግንባታ ግብዓት አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እንዲሁም ቀድሞ በተደረገው ምልከታ የታዩ ችግሮች ስለመቀረፋቸው የተገለፀ ነገር አለመኖሩን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

89. ይህን በተመለከተ በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ የግንባታ ማስተባበሪያ ቅርንጫ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መደበኛ ባይሆንም አልፎ አልፎ ክትትል እንደሚያደርግ እና ክትትል በሚያደርግበት ጊዜም ግብረመልስ እንዳልሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

❖ **የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ የሚካሄድበት ስለመሆኑ እና የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረግ ስለመሆኑ፣**

90. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ሊካሄድበት ይገባል፡፡ እንዲሁም የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት ሊደረጉ ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ

- በ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገባቸው መሆኑ፣
- በናሙና በታዩ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ የግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ሲሚንቶ በመጋዘን ብዙ ጊዙ እንደማይቀመጥ እና የአርማታ ብረት ግን ከ2008 ጀምሮ የተከማቸ ቢኖርም ቆጠራ ተደርጎበት እንደማያውቅ የገለፁ መሆኑ፣

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረጉበትን አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ከ27/02/2010 ጀምሮ ውሉ የተቋረጠ ቢሆንም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የመስክ ክትትል እስካደረገበት 11/7/2010 ድረስ ንብረት ወጪ እያደረገ የነበረ መሆኑን

በኦዲት ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ፣**

92. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
93. ይሁን እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ከተቋራጮች ተመላሽ የሚደረጉ ቁርጥራጭ የአርማታ ብረቶች መረከቢያ የሚሆን ሚዛን አለመኖሩ፣
- በናሙና በታዩ የዩኒቨርስቲ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለተቋራጮች ወጪ ከተደረጉ የአርማታ ብረቶች የሚተርፉ ቁርጥራጭ ብረቶች ቢኖሩም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በምን መልኩ እንደሚቀበል የተላለፈ መመሪያም ሆነ አሰራር ባለመኖሩ ተመላሽ እንዳልሆኑ በዚህ የተነሳም ቁርጥራጭ ብረቶች ለስርቆት የተዳረጉበት ሁኔታ እንዳለ እና የተቋራጮች ተደጋጋሚ ቅሬታ እንዳስከተለ የገለፁ መሆኑን

በኦዲት ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ11አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሆነ በሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጄክቶች እቅድ ሲያቅድ የሚያዘጋጃቸውን መመሪያዎች እና ሰነዶች ለይቶ ሊያስቀምጥ፣ የግዥ ዕቅድ ሲታቀድ ግብዓቱን ከሚጠቀሙ አካላት የግዥ ፍላጎት ሊያሰባስብ እና የገበያ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚገዛቸውን ዕቃዎች በአይነትና ብዛት በመለየት አስቀድሞ ሊያስቀምጥ፣ ግዥዎቹ የሚከናወኑበትን ዘዴ በግልጽ በማስቀመጥ እንዲሁም ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ ሊያመላክት ይገባል፡፡ የግዥ ዕቅዱ የሚገዙ ዕቃዎች ብዛትና አይነት ከዚህ በፊት ተገዝተው በመጋዘን/ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉትን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም በዕቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ከዕቅዱ ጋር በማነጻጸር በየጊዜው የእቅድ ክንውን ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚገዛቸው እቃዎች እንዲዘጋጁ ያደረጋቸውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎችና የግዥ ስምምነት ውሎች እቃዎቹን ለሚጠቀሙት ዩኒቨርሲቲዎች አስቀድሞ በመላክ በዝርዝር እንዲያውቁ እና እቃዎቹ በውሉ መሰረት ስለመቅረባቸው ለማረጋገጥም ሆነ ለእቃዎቹ ተገቢ ቦታ አስቀድሞ እንዲያዘጋጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ የቴክኒክ መግለጫዎች ዝግጅት ለማድረግ እና በተዘጋጁት መግለጫዎቹ መሰረት ዕቃዎቹ ስለመቅረባቸው የሚያረጋግጥ አማካሪ ቅጥርም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው የእቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም ማንዋል መሰረት በግልጽ ጨረታ ሊከናወን እና ፈቃድ ባላቸው አካላት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁምና ግዥዎች የመንግስት ህግና ስርዓት ጠብቀው መገዛታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማስተባበር ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስፈልጉ የመጽሐፍት፣ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ግብዓቶች ግዥ በወቅቱ በመፈፀም ለዩኒቨርሲቲዎቹ ሊያሰራጭ እና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን በመከታተል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን ግብ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በራሱ ባለሙያዎች እና በቀጠራቸው አማካሪዎች አማካኝነት በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተገዙ የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቅረቢያ እቃዎችና ጄነሬተሮችን ለተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች በወቅቱ ሊያስረክብ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት በሚሰራው ስራ ልክ በመለየት የመንግስት የግዥ ስርዓትን ጠብቆ በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓች ግዥ፣ ስርጭት እና አጠቃቀም ወጥነት ባለው መልኩ ሊመዘገብ፣ የግዥ እና የጨረታ ሰነዶች በተገቢው መልኩ ሊጠበቁና ሊያዙ፣ እንዲሁም በየግንባታ ሳይቱ የሚገኙ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ የግንባታ ሳይቶች ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ፣ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ እና ግብዓቶች በትክክል መመዝገባቸውን መደበኛ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥ እና ችግሮች በወቅቱ እንዲቀረፉ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች መ/ቤቱን/ ፕሮጄክቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረጉበትንና እርክክብ የሚከናወንበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክቱ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የሚመዘገቡበት፣ የሚከማቹበትና የሚወገዱበት የንብረት አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ቢደረግ ንብረቶቹን ከስርቆትና ከብክነት ለመከላከል እንዲሁም ከተቋራጮች የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ጥያዎችን ምላሽ ለመስጠት ያግዛል፡፡

9 በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድና ድልድይ ጥገና አፈፃፀምን በተመለከተ

❖ **የመንገዶችና የድልድዮች ጥገና የሚከናወነው በእቅድ ላይ በተያዘው በጀት፤ ጊዜና በሚፈለገው ጥራት መሆኑን በተመለከተ፣**

95. በየዓመቱ የታቀዱት የጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፤ ጥራትና ጊዜ ተጀምረው በወቅቱ እንዲጠናቀቁና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው የመንገድና የድልድይ የጥገና ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ያልተጀመሩ፣ በእቅድ ተይዘው በተመደበላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት ያልተጠናቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ፣ የአዳማ አሰላ አስፋልት መንገድ በ2008 ዓ.ም ድንገተኛ ጥገና ቢከናወንም መንገዱ በጎርፍ ተቆርጦ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

❖ **የመንገዶችና ድልድዮች በተፈቀደላቸው የክብደት መጠንና በሚያስተናግዱት የትራፊክ መጠን መሰረት መደበኛ ጥገና መከናወኑን በተመለከተ፣**

97. ባለሥልጣን መ/ቤቱ መንገዶችና ድልድዮች ሊያስተናግዱ ከሚችሉት የክብደት መጠንና የትራፊክ ፍሰት ልክ እንዲያስተናግዱ በማድረግ ለመንገዶቹም በመደበኛ ጥገና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ መንገዶች በየጊዜው የሚያድገውን የትራፊክ ፍሰት እና የጭነት መጠን መነሻ በማድረግ በዓመታዊ ዕቅድ በመያዝ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ያልተደረገ እንዲሁም ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት ያላቸውን መንገዶች በጥናት በመለየት በወቅቱ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፣

❖ **የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን በተመለከተ፡-**

99. የተጎዱ መንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመንገድ ቀለሞችና ምልክቶች ከመንገድ ጥገና ሥራ ጋር በእቅድ ተካተው የሚሰተካከሉት ሊስተካከሉ ወይም በአዲስ ሊተኩ ይገባል፡፡

100. የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ጋር ተካተው የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዕቅድ ያልተያዙና በኮንትራት ውል ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑ፤

❖ **የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ሁኔታ በተመለከተ፡-**

101. ባለሥልጣኑ የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ግልጽ መመሪያና መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ እንደ ሥራው ባህርይ ብቃት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መመሪያና መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

❖ **ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ውሎች ተዘጋጅቶ በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፡-**

103. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ውሎችን በማዘጋጀት ሥራዎች በውሉ መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

104. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውል መዋዋል ቢኖርበትም ያለውል የሚያሰራ መሆኑ፣

❖ **በራስ ኃይል ስለሚከናወኑ ድንገተኛ /አስቸኳይ/ የመንገድና የድልድይ ጥገና ሥራዎችን በተመለከተ፡-**

105. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

106. በኦዲቱ ወቅት ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር (አደረጃጀት) ወይንም የተዘረጋ ሥርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

❖ **በመንገዶች ላይ ጥበቃ መከናወኑን በተመለከተ፣**

107. መንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ለማድረግ የሚያግዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

108. በኦዲቱ ወቅት በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች የሚጠየቁበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣

❖ **የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፡-**

109. የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ በተዘጋጀውም መመሪያው መሰረት ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

110. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመንገዶችና በድልድዮች ላይ የሚተላለፉ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ለማስከበር አጥፊዎች በመንገዱ ላይ ባደረሱት ጥፋት ልክ ለመጠየቅ የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች የቀረቡ ሲሆን ከላይ ለተጠቀሱት ግኝቶች ችግሮቹን ለመቅረፍ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን ማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- ተገነንብተው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ወደ መንገድ ሀብት የገቡ መንገዶችና ድልድዮች እንደሚያስተናግዱት የትራፊክ ፍሰት መጠን፣ እና የሚስተናግዱት የክብደት መጠንን ከግምት ያስገባ ክትትል በማድረግና ሲገነቡ ታሳቢ የተደረጉ የአገልግሎት ዓይነትና ጊዜ እንዲሰጡ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ሊደረግ እንዲሁም መደበኛ ጥገና በሚመደብላቸው በጀት፣ ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመንገዱም ሆነ የድልድዩ የጉዳት መጠን ተባብሶ ለመንገድ ግንባታ የሚውለውን የሃገሪቱን ሀብት እንዳይሻማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶች የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚረዱ በመሆናቸው የመንገዶችም ሆነ የድልድዮች ጥገና በሚታቀዱበትም ሆነ ውል በሚገባበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸውና አብረው እንዲታቀዱ በማድረግ የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ሊደረግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ እንደየሥራው ባህሪ ብቃት ያላቸው የሥራ ተቋራጮችን ለማግኘት የሚረዳ ግልፅ የሆነ መምረጫ መስፈርትና መመሪያ በማዘጋጀት እና በሚመለከታቸው አካላት እንዲጸድቅ በማፀደቅ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በተቋራጮች አቅም ውስንነት የሚፈጠረው የሥራ ጥራትና መጓተት እንዲቀረፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ለኮርፖሬሽኑ ለሚሰጣቸው እያንዳንዱ የጥገና ሥራዎች ውል ሊዋዋልና ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ጊዜ የማይሰጡና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚፈልጉ በመሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የአደረጃጀት ወይንም ሥርዓት በመዘረጋት ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ በማመቻቸት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ

ሰዎችን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው የአካባቢ መስተዳድሮች ጋር የጋራ ግንዛቤ በመያዝ የመንገድ ሀብት የሚጠበቅበት ምቹ ሁኔታ ሊኖር ይገባል፡፡

- የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር እየተዘጋጀ ያለው ደንብ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንዲገባ በማድረግ ከክብደት ጋር ተያይዞ በመንገድ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሊቀንስ ይገባል፡፡

10 በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ("የምድብ 'ሐ'ሕንፃ") በተመለከተ

❖ **የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች ሲከናወኑ የህንጻ አዋጁ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ**

111. የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች በህንጻ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሰረት እንደማንኛውም ሕንጻ ግንባታ የፕላን ስምምነት ሊያገኝ፣ የግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትሎ ሊገነባ ይገባል፡፡

112. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎች በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይናቸው እንዲጸድቅ የማይደረግ እና የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው፣ እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ ከመሆኑም በላይ ተገቢው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌላቸው እና በሚመለከተውም የመንግስት አካል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ ታውቋል፣

❖ **የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ**

113. በከተሞች ውስጥ የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው ሊገነቡ ይገባል፡፡

114. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በከተሞች ውስጥ የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደትን ተከትለው የማይገቡ መሆኑ (ኤሌክትሮ ሜካኒካል ፕላንና ትንታኔ ፣ የአፈር ምርመራ

ሪፖርት፣ አርክቴክቸራል፣ ኤሌክትሪካል፣ እና ሳኒቴሪ ፕላን ትንታኔ ሪፖርት ሳይይቀርብ ወዘተ…የግንባታ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ)

❖ **የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ያገኘ መሆኑ**

- በከተሞች ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛው ሰው የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ሊያገኝ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከተሞች የተሰጠው የፕላን ስምምነት በከተሞቹ መሪ ፕላን ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት እየተረጋገጠ አለመሆኑ መታወቁ፣

❖ **በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካልጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ**

115. በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ የሚከታተልበትን እና የሚደግፍበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

116. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በከተሞች የተዘጋጁ የዲዛይን (ፕላኖች) እና የተገነቡ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን የሚመቹ ወይም ፍትሀዊ ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳትፎአቸውን ያካተቱ መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ የማይከታተል መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፣

❖ **በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን በተመለከተ**

117. ሚ/ር መ/ቤቱ በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡

118. ይሁን እንጂ በከተሞች የተገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሂደትን ተከትለው ያልተገነቡ በመሆኑ ህገወጥ ግንባታዎች ሴት ባክ (የተፈቀደላቸውን ወሰን) ሳይጠብቁ መገንባት፣ ከተፈቀደው ከዲዛን ውጪ ወለል መጨመር እና የግንባታ ፈቃድ ሳይኖር ግንባታ የመገንባት ሥራዎች መስፋፋታቸው ታውቋል፣

❖ **በ“ምድብ ‘ሐ’ ሕንጻ” ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን በተመለከተ**

119. ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞችና በክልሎች በ“ምድብ ‘ሐ’ ሕንጻ” ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሂደት ተከትለው እየተሰጣቸው ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

120. በኦዲቱ ወቅት በከተሞች በ“ምድብ ‘ሐ’ ሕንጻ” ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ (ለአገልግሎት ብቁ ሲሆኑ) እና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣ እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸውም ቢሆን ሂደቱን ተከትሎ ያልተሰጠ መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፣

❖ **በሕንጻ አዋጁ መሠረት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ መቋቋሙን በተመለከተ**

121. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል በሕንጻ አዋጁ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ሊያቋቁም ይገባል፡፡

122. ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ቦርዱ መቋቋሙን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ከተሞች በህንጻ አዋጁ መሠረት በሕንጻ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በከተሞች ያልተቋቋመ መሆኑ መታወቁ፣

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች የቀረቡ ሲሆን ከላይ ለተጠቀሱት ግኝቶች ችግሮቹን ለመቅረፍ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን ማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች የሕብረተሰቡ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ ለማስቻል በሕንጻ አዋጁ መሰረት እንደሌሎቹ ግንባታዎች ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የግንባታ ፈቃድ እየወሰዱ እንዲሁም ሕንጻው ለአገልግሎት ብቁ መሆኑ እየተረጋገጠ የመጠቀሚያ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ አገልግሎት እንዲገነቡ መደረግ አለበት፡፡

- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ሕግን ተከትለው በተሟላ መንገድ እየተፈጸሙ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና የግንባታ ፈቃድ ሳይወስዱ ግንባታ የሚጀምሩ ተጠያቂ መሆናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች የከተማውን መሪ ፕላን መሰረት በማድረግ የፕላን ስምምነት አግኝተው መገንባታቸውን ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡
- ተዘጋጅተው የቀረቡ የዲዛይን ጥናቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስገዳጅ የዲዛይን ስታንዳርድ በመተግበር ተደራሽ ዲዛይን (Accessible Design) እንዲሁም ሁሉን አቀፍ ዲዛይን (Universal Design) በማጣመር ተግባራዊ እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን ከተሞች እያረጋገጡ ስለመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሂደቱን ተከትለው በሕጉ መሰረትና በተሟላ መንገድ እንዲተገበር እየተደረገ ስለመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና የተጠያቂነት ሥርዓት ስለመኖሩ ሊከታተል ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ተከትለው በሕጉ መሰረትና በተሟላ መንገድ እንዲተገበር መድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ያለመጠቀሚያ ፈቃድ በከፊል አገልግሎት ለሚሰጡና ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው አገልግሎት ለሚሰጡ ሕንጻዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ ሚ/ር መ/ቤቱ በስራ ላይ ያሉ የሕንጻ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም ወደፊት የሚወጡ ሕጎች ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በግንባታ ፈቃድ፣ በግንባታ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን (ቅሬታዎች) ለመፍታት በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በሌላቸው ከተሞች ቦርድ እንዲቋቋም ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

11 በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ትግበራና አፈፃፀምን በተመለከተ

❖ ***የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ (CIP) መዘጋጀቱን በተመለከተ፣***

123. የከተማ አስተዳደሮቹ የ3 ዓመት የመሰረተ-ልማት እቅድ (*Capital Investment Plan*) ከትግበራ እቅድ ጋር አያይዘው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትል እና ሲአይፒ በወቅቱ እንዲላክ ለማፍጠን በተላለፈ ደብዳቤ ላይ በተቀመጠው ጊዜ መሠረት ሊያዘጋጁና የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ በሚተገበርበት በጀት ዓመት ውስጥ የከተማ ምክር ቤቱም ሊያፀድቅና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሊልኩ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ ከተሞች የመሠረተ ልማት ዕቅድ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 24 እ.ኤ.አ ሊያዘጋጁና በምክር ቤታቸው በማጸደቅ እንዲሁም የተከለሰው ዕቅድ እስከ የካቲት 6 እ.ኤ.አ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መቅረብ ቢኖርበትም በናሙና ባየናቸው ከተሞች የ2007፣ 2008፣ 2009 እና በ2010 ዓ.ም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አዘጋጅተው ያላቀረቡ ከተሞች መኖራቸው፣

❖ **ለጥገና የሚወጣው በጀት እና አፈጻጸሙ ከእቅዱ ከ80 ፐርሰንት አለማነሱን በተመለከተ፣**

125. የከተማ አስተዳደሩ ለጥገና (መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች፣ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች፣ የገበያ ቦታዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ወዘተ) የሚወጣውን በጀት ሊያዘጋጅና አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 በመቶ ማነስ የሌለበት ሊሆን ይገባል፡፡

126. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለጥገና ያወጡት በጀት አፈፃፀም ከእቅዱ ከ80 በመቶ በታች አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች መኖራቸው፣

❖ **የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣**

127. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

128. በኦዲቱ ወቅት አብዛኛዎቹ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜና ዋጋ እንደማይጠናቀቁ ለማወቅ መቻሉ፣

❖ **ከተሞች ከፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን በተመለከተ፣**

129. ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንድ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

130. በአንዳንድ ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ መታወቁ፣

❖ **ለፕሮጀክቶች የጨረታ ሂደት ከመጀመሩ በፊት የተሟላ ዲዛይን ስለመዘጋጀቱ፣**

131. የከተማ አስተዳደሮቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ሊያዘጋጁ እንዲሁም የተሰሩት ዲዛይኖቹ በሌላ አካል ሊከለሱና ሊረጋገጡ ይገባል፡፡

132. የአዳማ፣ የቢሾፍቱ፣ የሮቤ፣ የሐዋሳ፣ የባቱ፣ የዲላ፣ የደብረ ታቦር፣ የባህር ዳር፣ የአሰላ የከተማ አስተዳደሮች ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ማለትም Preliminary Design (Survey Data) እና የተለያዩ Drawing እንደማያዘጋጁ መታወቁ፣

❖ **ከተሞች በየዓመቱ ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ማሳደጋቸውን በተመለከተ፣**

133. ከተሞች የመሰረተ-ልማት እቅድ ላይ በተቀመጠው መሠረት ገቢ ሊሰበስቡና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ይገባል፡፡

134. የከተሞች የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ መሆንና በእቅዱ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ እና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ቢገባም ሆኖም ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት የማያሳድጉ ከተሞች መኖራቸው፣

❖ **የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናትን በተመለከተ፣**

135. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናት በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሊጸድቅ ይገባል፡፡

136. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት የሚዘጋጁትና በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ይሁንታ የሚያገኙ ፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ መሆኑ፣
- የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ቢኖሩም ሆኖም የሕብረተሰብ የመልሦ ማስፈር ጥናት ሳይከናወን እንደሚሰራ፣
- በአብዛኛው የአካባቢና ማህበራዊ ደህንናት ልየታ (Screening) ሪፖርት ሲሰራ ከዓለም ባንክ ፈንድ ለመጠቀም ብቻ ሲባል እንጂ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይቶ የማይሰራ እንደሆነና የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአንዱን ለሌላው ኮፒ ፔስት በማድረግ ሪፖርቶቹ እንደሚዘጋጁ፣

ታውቋል፡፡

❖ **የሁለተኛው የከተሞች አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች (ዩኤልጂዲፒ) ላይ በተቀመጠው ዕቅዱ መሰረት አዳዲስ የስራ እድል ስለመፍጠሩ፣**

137. በሁለተኛው የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP II) የሚሳተፉ ከተሞች አዳዲስ የስራ ዕድል እንዲፈጠር በዕቅድ ሊይዙና በዕቅዱም መሰረት ሊተገብሩ ይገባል፡፡

138. ሚኒስቴር መ/ቤቱም በዕቅዳቸው መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡ አንዳንድ ከተሞች የስራ ዕድል ለመፍጠር በበጀት ዓመቱ ካቀዱት አንፃር ግባቸውን እያሳኩ እንዳልሆነ መታወቁ፣

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች የቀረቡ ሲሆን ከላይ ለተጠቀሱት ግኝቶች ችግሮቹን ለመቅረፍ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን ማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- ከተሞቹ ማግኘት የሚገባቸውን ነጥብና ከፍተኛ ገንዘብ እንዳያጡ፣ በርካታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጀምሩና በወቅቱ እንዲጠናቀቁ እንዲሁም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲሰሩ የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ እንዲዘጋጅ ሊደረግና በወቅቱ በማጸደቅ ወደ ሥራ እመግባት አለባቸው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይሄ ስለመደረጉ ከፍተኛ ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ከተሞቹ ከፕግራሙ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረቱን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡
- በከተሞቹ የሚገኙት አብዛኛዎቹ መሰረተ ልማቶች ጥገና ስለሚያስፈልጋቸው ከተሞች ከአዳዲስ የመሠረት ልማት ግንባታዎች ጎን ለጎን ለነዚህ መሰረተ ልማት አውታሮች አይነተኛ ትኩረት እንዲሰጡና ሥራው ቀጣይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው የሲአይፒያቸውን 10% ወይም የአጠቃላይ የከተማውን ሃብት 2% ለጥገና በጀት እንዲመድቡና በየዓመቱ በእቅድ አድያያዙ መተግበር እንዲጀምና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክለሎች ጋር በመተባበር ከፍተኛ ክትትልና እገዛ ሊደርጉላቸውና ጥገናው በራስ ኃይል ወደፊት ለመስራና ዘላቂነት እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክቶቹ በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራቸው ተጠናቀው ወደ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከተሞች ተገቢውን ክትትል ሊያደርጉና ላልተገባ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ እንዳይዳረጉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህብረተሰቡም እሮሮ እንዳይነሳባቸው ፕሮጀክቶች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሁሉን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በየዓመቱ በዕቅድ በመያዝ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ከተሞቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን እንዲዘጋጁ፣ የሚዘጋጁትም ዲዛይኖች ገለልተኛ በሆነ አካል ሊከለሱይገባል፡፡ በፌዴራል ሞባይል ቡድንና ይሄን ፕሮግራም እየረዱ ባሉት አማካሪዎች ከፍተኛ ግምገማ በማድረግ ከተሞቹን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች ሳይከናወኑ ግንባታዎች እዳይከናወኑ በየደረጃው ድጋፍ፣

ክትትል እና ቁጥጥር በማደረግ የመሰረተ ልማቶቹ ሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ከፕሮግራም ፈንዱ ለከተሞች የሚለቀቀው ገንዘብ በማሳወቅ ረገድ መዘግየቶች እንዳይፈጠር፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ ዝግጅት በወቅቱ እንዲካሄድ፣ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀመሩና ሚ/ር መ/ቤቱ በዚህ ረገድ በርካታ አሜሪካ ዶላር እንዳያጣ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በወቅቱ ማከናወን ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሞች በፕሮግራሙ ላይ በተቀመጠው መሰረት በየዓመቱ ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት ባነሰ ሁኔታ የሚያሳድጉትን ከተሞች ተለይቶ የገቢ አሰባሰባቸው የሚያድግበትን የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ የሆነበትን መንስኤ አጥንቶ የሚሻሻልበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ሊያደረግላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪምከገቢ ጋር በተያያዘ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተከታታይ የአቅም ግንባታ እና ሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊጠናና ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ በማድረግ ፕሮጄክቶቹ በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጡት ተፅእኖ የሚቀነስበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- በከተሞቹ በዕቅዱ መሰረት ለነዋሪዎቻቸው ጊዜያዊና ቋሚ የስራ ዕድል በፕግራሙ አማካኝነት ሊፈጥሩና በከተሞች ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥርን ከመቀነስ አኳያ ፕሮግራሙ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲሳካ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሥራ ዕድል ለመፍጠር በፕሮግራሙ የተቀመጠው አላማ እንዲሳካ የበኩልን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በፕሮግራሙ የተሰሩ እየተገነቡ ያሉ እና የሚገነቡት የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ጥራታቸውን ጠብቀው ሊገነቡ እና ይህን በማያሟላ መልክ የሚሰሩ በየደረጃው ተጠያቂ ሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተገነቡት መሰረተ ልማቶች በየጊዜው እየተበላሹ መንግስትም አላስፈላጊ ወጪ እንዳያወጣ፣ ለጥገና የሚወጣውን

ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ለማዳን እንዲሁም የሚሰሩት የፕሮጀክት ግንባታዎች ለተፈለገላቸው ዓላማ ሳይውሉና የሚፈልግባቸውን ቆይታ ሳያከናውኑ እንዳይበላሹ እና ህብረተሰቡ በዚህ ምክንያት ቅሬታና እሮሮ እንዳያነሳ በየደረጃው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የግንባታዎቹን ጥራት ለመጠበቅ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትና በከተሞቹ ለሚገኙ ፕሮጀክቶቹን ለሚቆጣጠሩ የፕሮጀክት ኢንጂነሮችና ሌሎች ባለሙያዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር ስልጠናና የልምድ ልውውጥ በማዘጋጀት ባለሙያዎቹን ክህሎትና አቅም የሚገነባባት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

12 በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት እና የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የእንቦጭ አረም በሀይቆችና ወንዞች ላይ ያስከተለውን ስጋትና ችግሩን ለመፍታት የተዘረጋውን ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

139. ኢንስቲትዩቱ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእንቦጭ አረም በሀገሪቱ ሀይቆችና ወንዞች ላይ ከመከሰቱ በፊት ለመከላከል አረሙ የሚፈጠርበትን ሁኔታ፣ ምንጩን እና የስርጭቱን መጠን የመለየትና የመቆጣጠር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

140. በዓለም አቀፍ ሕይወታዊ ሀብት ስምምነት መሰረት አባል ሀገራት ወራሪ መጤ ዝርያዎች ወደ ሀገር ገብተው በስርዓተ ምህዳርና በዝርያዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የቅድመ መከላከል፣ መቆጣጠርና ማስወገድ ተግባራትን ማከናወን እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የሀገሪቱ ብዝሃ ህይወት ከውጪ በሚገቡ ልውጥ ሕያዋን እና ወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይበከልና ጥፋት እንዳይደርስበት ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደሚጠበቅበት የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 291/2005 አንቀፅ 6(19) እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት የመለየትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለበት በአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2015 ይደነግጋል፡፡

141. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ በአሁኑ ግዜ በሀገራችን ውስጥ በመስፋፋት ላይ ካሉ በርካታ ወራሪ መጤ ዝርያዎች መካከል አንዱና ዋንኛው የሆነውና የተለያዩ የውሃ ስርዓተ ምህዳሮችን በከፍተኛ ፍጥነት በመጉዳት ላይ ስለሚገኘው የእንቦጭ አረም ተፈጥራዊ ባህሪ (ምንጩንና የሚፈጠርበትን ሁኔታ፣ የመራቢያና የመዛመቻ መንገዶችን፣ ስለሚያደርሳባቸው ጉዳቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን የመለየትና መቆጣጠር ስራ ያላከናወነ መሆኑ፣

142. ኢንስቲትዩቱ አዲስ የእንቦጭ አረም ወረርሽኝ በሚከሰትበት ወቅት ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ኢንስቲትዩቱና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት በሚገኙ የውሃ አካላት ላይ አዲስ የእንቦጭ አረም ወረራ በሚከሰትበት ወቅት ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት ያልዘረጋ በመሆኑ በተለይ በጣና ሀይቅ ላይ የእንቦጭ አረም የስርጭት መጠኑን መቆጣጠር ባለመቻሉ ከጣና ሀይቅ ባለፈ በአባይ ወንዝ ላይ አረሙ በመገኘቱ ወደፊት በታላቁ የህዳሴ ግድብ ሜጋ ፕሮጀክት ላይ የመፈጠር እድሉ ከፍተኛ በመሆኑ ስጋት የፈጠረ መሆኑ፣

ኢንስቲትዩቱ የእንቦጭ አረም ወረርሽኝ በከፍተኛ ሁኔታ በተከሰተባቸው አከባቢዎች አረሙን ለማጥፋት የሚያስችል ሀገራዊ ዕቅድ /ፕሮግራም/ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

143. ኢንስቲትዩቱና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በናሙና በታዩ በአማራ ክልላዊ መንግስት በጣና ሀይቅ፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቆቃ ግድብና በዝዋይ ሀይቅ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት በአባያና ጫሞ ሀይቆች ላይ የእንቦጭ አረም ወረርሽኝ በከፍተኛ ሁኔታ በተከሰተባቸው አከባቢዎች አረሙን ለማጥፋት የሚያስችል ሀገራዊ ዕቅድ /ፕሮግራም/ ያላዘጋጀ ሲሆን አረሙ የተከሰተባቸው ክልሎችም ክልልዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ እንዲገቡ ድጋፉ ባለማድረጉ በህብረተሰቡ ንቅናቄ የማስወገድ ዘመቻው የሚከናወንበት ወጥ የሆነ የግዜ ሰሌዳ ባለመኖሩ እና በዓመት ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ወራ ብቻ በዘመቻ መልክ የሚከናወን በመሆኑ አረሙን ከመስፋፋት መግታት ያልተቻለ መሆኑ፣

144. ኢንስቲትዩቱ በእንቦጭ አረም የተወረሩ ቦታዎችን እንደ ስጋታቸው መጠን፣ እንዳስከተሉት ተፅዕኖ እና የሽፋን መጠን ስርጭታቸውን ሊቀንስ ይገባል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በአማራ ክልላዊ መንግስት በጣና ሀይቅ፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቆቃ ግድብና በዝዋይ ሀይቅ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት በአባያና ጫሞ ሀይቆች ላይ የተከሰተውን የእንቦጭ አረምን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን በእንቦጭ አረም የተወረሩ ቦታዎችን እንዳስከተሉት ተፅዕኖ፣ የሽፋን መጠን እና እንደ ስጋታቸው ደረጃ ስርጭታቸውን የመቀነስ ስራ ባለመሰራቱ፡-

- በአማራ ክልል በጣና ሀይቅ ላይ አረሙን በእጅና በማሽን በመታገዝ የመቀነስ ስራ እየተሰራ ቢሆንም አረሙ ባለው ተፈጥሯዊ ባህሪ በአጭር ግዜ ራሱን በእጥፍ የሚያራባ በመሆኑ በእጥፍ በማደግ ወደ 50,000 ሄክታር ወይም ከ18 ቀበሌዎች በላይ ወደ128 ኪሎ ሜትር የሚሆን የሀይቁን ዳርቻ እንደሸፈነ፣
- የኦሮሚያ ክልል በቆቃ ግድብ ላይ የተሸፈነውን የውሃ አካል መጠን በጥናት የተደገፈ ማስረጃ ማግኘት ያልተቻለ ሲሆን በዝዋይ ሀይቅ ላይ በሀይቅ ዙሪያ ካሉ ወረዳዎች በዱግዳ ወረዳ ባሉ 8 ቀበሌዎች ከ40 ሄክታር በላይ እንዲሁም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የአባያ ሀይቅ በአረም የተሸፈነው የውሃ መጠን 1780 ሄክታር በላይ ተስፋፍቶ የሚገኝ መሆኑ፣

13 በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን (በቀድሞው ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር) የውጤት ተኮር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ

❖ የውጤት ተኮር ሥርዓት ማኑዋል ዝግጅትን በተመለከተ

145. የመንግሥት ተቋማት በውጤት ተኮር ሥርዓት መሠረት ስትራቴጂን ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው የውጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ አሰራር ማኑዋል በሚኒስቴር መ/ቤቱ (በአዲሱ አደረጃጀት በኮሚሽኑ) ሊዘጋጅና ለተቋማት ሊሰራጭ ይገባል፡፡

146. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት ተቋማት መካከል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በጤና ሚኒስቴር፣ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ በፌደራል ኀብረት ሥራ ኤጄንሲ፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሁሉንም ተቋማት ነባራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ በሀገር ደረጃ ወጥነት ያለው፣ የግንባታ ደረጃዎችን ያካተተ እና የህግ ማዕቀፍ ያለው የውጤት ተኮር ሥርዓት አሰራር ማኑዋል አለመኖሩን ለተቋማቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **የተቋማት አመታዊ ዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ሪፖርትን በተመለከተ**

147. ሁሉም የፌዴራል ተቋማት አመታዊ ዕቅድና ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በተቀናጀ መልኩ በውጤት ተኮር ሥርዓት መሰረት ሊያዘጋጁና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

148. ይሁን እንጂ በሀገር ደረጃ በየዓመቱ ተቋማት አመታዊ ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ ለተለያዩ ተቋማት የሚልኩት ሪፖርት በውጤት ተኮር መሠረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ተቋማት ላይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ትምህርት ሚኒስቴር፤ ገንዘብ ሚኒስቴር፤ ጤና ሚኒስቴር፤ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤ ትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በየአመቱ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን የሚልኩት የአፈጻጸም ሪፖርት በውጤት ተኮር መሠረት ሳይሆን በቀድሞው ስትራቴጂክ ዕቅድ አስተቃቀድና አመራር (Strategic Planning and Management) መሠረት መሆኑ፤

- ከትምህርት ሚኒስቴር፤ ከጤና ሚኒስቴር፤ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር፤ ከውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፤ ከፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚላክ አመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት በውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) ሳይሆን በውጤት ላይ የተመሠረተ አመራር (Result Based Management) መሠረት መሆኑ፤

- የትምህርት ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስቴር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ (በአዲሱ አደረጃጀት ለኮሚሽኑ) የሚልኩት አመታዊ ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት በውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) መሠረት ሳይሆን የለውጥና መልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በሚል ፎርማት መሆኑን ለየተቋማቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና ከየተቋማቱ የቀረበ ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **የግቦች መለኪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ**

149. በመንግስት ተቋማት በአራቱም ዕይታዎች (በተገልጋይ፣በበጀት/ ፋይናንስ፣ በውስጥ አሰራር እና በመማማርና ዕድገት) ሥር የሚቀመጡ የግቦችን ስኬት ወይም ውጤትን ለመመዘን፣ለመለካት እና ለመከታተል የሚያስችሉ በቂ እና ተስማሚ የሆኑ መለኪያዎች ስለመሆናቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ (በአዲሱ አደረጃጀት በኮሚሽኑ) ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

150. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ በጤና ሚኒስቴር፣ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ በኢትዮ-ቴሌኮም፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲና በራሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ (በአዲሱ አደረጃጀት በኮሚሽኑ) ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በአራቱም ዕይታዎች ሥር የሚቀመጡ ግቦች ሲቀረጹ የግቦችን አፈጻጸም ሂደት (performance driver) ወይም የወደፊት አፈጻጸም ላይ ለመድረስ እና ለመገመት የሚያስችሉ መለኪዎች(Leading Indictors) እና የአፈጻጸም መለኪያዎችን(Lagging Indicators) በሚያሳይ መልኩ ለመለካት እና ለመከታተል የሚያስችል አለመሆኑን ከተቋማቱ ስትራቴጂ ዕቅድ ሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ የስልጠና ፋይዳ ግምገማን በተመለከተ

151. በፌደራል ተቋማት ስትራቴጂ ውስጥ የመማማርና ዕድገት ዕይታ ሥር የሚቀረጹ ግቦችን በተመለከተ የሰው ሀብት (Human Capital) የሰራተኞች እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ክፍተቶችን (Gap) በመለየት ስልጠና የሚሰጥ ስለመሆኑ፣ ስልጠናውም ያመጣው ፋይዳ የሚገመገምበት መለኪያዎች (Indictors) ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

152. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ተቋማት መካከል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በጤና ሚኒስቴር፣ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እና በራሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ (በአዲሱ አደረጃጀት በኮሚሽኑ) ለሠራተኞች የሚሰጥ ስልጠና የእውቀት፣ የክህሎትና አመለካከትን ክፍተት በመለየት እና ከድህረ-ስልጠና የተገኘውም ፋይዳ የሚገመገምበት አሰራር አለመኖሩን ለተቋማቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅና ከተከለሰው የተቋማቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

14 በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማእከል ሁለ-ገብ አገልግሎት አሰጣጥና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም

153. ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲ ፣ አዋጅ ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሊያቀርብ እና ሲፀድቀም ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

- በአገር አቀፍ ደረጃ የእንስሳት የጤና ፖሊሲ የሌለ ሲሆን ማዕከሉም የመተዳደሪያ ደንብ ቢያዘጋጅም ጸድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጫማሪ የላቦራቶሪ አወጋገድ ፖሊሲ ወይም መመሪያ ባለመኖሩ በአገራችን በተለያየ አከባቢ የሚገኙ እንስሳቶች ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የሚጋለጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

- የማዕከሉ ተግባር እና ኃላፊነቱን የሚገልጽ የፀደቀ የተቋቋመበት ደንብ የሌለው በመሆኑ የማዕከሉ የመፈጸምና የማስፈጸም መብት ህጋዊ ድጋፍ ከማግኘት አንጻር ተጽእኖ የፈጠረ በመሆኑም በእንስሳት ጤና ላይ እንደ ሀገር ከፍተኛ ችግር እያመጣ ያለ ሲሆን፤ ይህውም በእርድ ወቅት በሽተኛ እንስሳት እንዴት እንደሚወገዱ (የአወጋገድ ህግ ያልተዘጋጀ) መሆኑ እንዲሁም ለህብረተሰቡ ካሳ አከፋፈልን አስመልክቶ የወጣ የህግ ማእቀፍ ባለመኖሩ ፣ የላቦራቶሪ ተቋማት ምርመራ በሚያካሄዱበት ወቅት ፖዘቲቭ የሆኑትን እንስሳት የሚያስወግዱበት መመሪያ ባለመኖሩ በሽታው እየተስፋፋ የሚሄድበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ስጋ እና ወተቱን የሚጠቀሙት ላይ የጤና ችግር እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑ፤
- ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን በሚመለከት ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ማቅረቡን በተመለከተ፡
- የላቦራቶሪ ናሙና አወጋገድ ፖሊሲ (በላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት መሠረት የእንስሳት ጤና ችግሮች መፍቻ መንገዶች (የፖሊሲ አቅጣቻጫ) ባለመኖራቸው በአየር ላይ የሚንሳፈፉ ቫይረሶች እንዲስፋፉ እና በኤፍ ኤም ዲ /የአፍ እና እግር/ የመሳሰሉ በሽታዎች የአገራችንን የቤት እንስሳት በስፋት የሚያጠቁበትን እድል እንዲሰፋ ያደረገ መሆኑ፤
- በእንስሳት ጤና ላይ እንደ ሀገር ከፍተኛ ችግር እያመጡ ካሉት ውሰጥ በእርድ ወቅት በሽተኛ እንስሳት እንዴት እንደሚወገዱ ወይም የአወጋገድ ህግ ያልተዘጋጀ መሆኑ ፣
- የላቦራቶሪ ተቋማት ምርመራ በሚያካሂዱበት ወቅት ፖዘቲቭ የሆኑ እንስሳት የሚወገዱበት መመሪያ ባለመኖሩ የማይወገዱበት ሁኔታ መኖሩ፣ በሽተኛ የሆኑ እንስሳት በሽታቸው ወደሌሎች እንስሳት እንዲስፋፉ ከማድረጉም በተጨማሪ የእነዚህን እንስሳት ስጋቸውን እና ወተታቸውን የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የጤና ችግር እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በድሬ ደዋ እና በጅግጅጋ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች ከእንሳሳት ወደ ሰው እና ከሰው ወደ እንስሳት እንዲሁም ከእንስሳት ወደ እንሳስት የሚተላለፉ በሽታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ የሚገዙ

እና የሚሸጡ ህብረተሰቦችን ማስቆም የሚያስችል ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ችግር እያመጣ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

- እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ቃለ መጠይቅ ካቀረበላቸው እና ከሰነድ ክለሳ በተገኙ ማስረጃዎች የያቤሎ ክልላዊ የእንስሳት ላቦራቶሪ ፣ የአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ ፣ የድሬ ደዋ ኳራንታይን ጣቢያ ከሌላ ሀገር የሚመጡ ድንበር ዘለል እንስሳዎች በሽታዎችን ይዘው ወደ ሀገር እንዳይገቡ ለመከላከል የሚያስችል ፖሊሲም ሆነ መመሪያ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፣ እንዲሁም በድንበር አካባቢ ያሉ እንስሳቶች ከጎረቤት ሀገሮች እንስሳት ጋር አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ በመኖሩ የድንበር ዘለል በሽታ ሊመጣ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም፤ ችግሩን ለመከላከል በሀገር ደረጃ የሪፍት ቫሊ ፌቨር በሽታ ምርመራ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. ማዕከሉ የበሽታ ፍንዳታና ሌሎች መፍትሄ የሚሹ የእንስሳት ጤና ችግሮች ሲኖሩ የበሽታውን ወይም የጤና ችግሩን መንስኤ በመለየት ለተገልጋዮች በወቅቱ የመፍትሔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በያቤሎ፣ በሂርና፣ በድሬደዋ እና በጅግጅጋ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች፣ ማእከሉ የሚሰበሰባቸው ናሙናዎች ውጤት ቶሎ የማይመለስ ወይም ማዕከሉ ያስቀመጠው አማካይ የናሙና መመለሻ ጊዜ 10 ቀናት ከ21 ቀናት በላይ የሚቆይ መሆኑን ፣ናሙናው የሚጠፋበት ሁኔታ መኖሩ እና ውጤቱ የማይመለስበት ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት የበሽታው መንስኤ የማይታወቅበት ሁኔታ በመኖሩ ብዙ እንስሳት ህክምና አጥተው የሚሞቱበት ሁኔታ መኖሩ፡
- በአላጌ ቴክኒክ ኮሌጅ በበሽታ ፍንዳታ ምክንያት 65 እንስሳት መሞታቸውን፣ ከሰኔ 2015 እስከ መጋቢት 2018 ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን አርሲ ነገሌ በበሽታ ፍንዳታ ምክንያት 50 አህያዎች መሞታቸውን፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ሉሜ ወረዳ የእንስሳት ጤና መምሪያ ከእንሳሳት ወደ ሰው እና ከሰው ወደ እንስሳት እንዲሁም ከእንስሳት ወደ እንሳስት የሚተላለፉ በሽታዎች ላይ እሰካሁን ድረስ የተሰራ ስራ አለመኖሩን፡

- የአለማ ፋርሚስ ድርጅት IB (infectious bronchitis) የሚባል የዶሮ በሽታ ናሙና እንዲመረመርለት አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ያልተመረመረለት በመሆኑ ብዙ ዶሮዎችን እየገደለ እና እንቁላል እንዳይጥሉ እያደረገ ከባድ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን በ2008 **51,335** ፣ በ2009 **52,549** ፣ በ2010 **133,518** በድምሩ **237,402** ዶሮዎች ተመርምረው እርምጃ እንዲወሰድ ባለመደረጉ ከአንድ ድርጅት ብቻ (አለማ ዶሮ ፋርምስ) መሞታቸው እንዲሁም ድርጅቱ ጫጩቶቹን አስፈልፍሎ ለገበሬዎች እና ለሌሎች ድርጅቶች የሚያሰራጭ በመሆኑ እና በሽታውም በትንፋሽ የሚተላለፍ በመሆኑ የተሰራጩት ከበሽታው ጋር የሚሰራጩበት ሁኔታ በመፈጠሩ በሽታው ወደ ሌሎች ዶሮዎችም ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ፣
- በያቤሎ፣ በሂርና፣ በጅግጅጋና በድሬደዋ ክልላዊ ላቦራቶሪዎች የበሽታ ምርመራዎች ከአቅማቸው በላይ በሚሆንበት ጊዜ ናሙናውን ወደ ብሄራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ እና ጥናት ማእከል የሚልኩ መሆኑን ነገር ግን ቶሎ ምላሽ ከመስጠት አንፃር ችግር ያለ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከገበሬዎች ጋር ግጭት የሚፈጥርባቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱት ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

155. ማዕከሉ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤትን ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ለመጠበቅ የሚያስችል ብቃት ያለው የላቦራቶሪ አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ከአገር ለሚወጡና ወደ አገር ለሚገቡ እንስሳት ፣ የእንስሳት ውጤቶች እና ተዋጽዖዎች ውጤታማ እና ተዓማኒነት ያለው የበሽታዎች ምርመራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

156. ማእከሉ የላቦራቶሪ አሰራር ስርአት የዘረጋ ቢሆንም ነገር ግን ከውስጣዊና ውጫዊ ተፅጽኖዎች ለመጠበቅ የሚያስችል ብቃት ያለው አለመሆኑ፣

ለአብነትም፤-

- የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የማእከሉ የስራ ሃላፊዎች፤ ከኳራንቲኖች፤ እንዲሁም ከቁም እንስሳት ላኪ ድርጅቶች የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና ባደረጋቸው ሰነድ ክለሳዎች መሰረት የማእከሉ

የላብራቶሪ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጡ ለውስጣዊ (ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ናሙና እንዲሰበስብ ጫና የሚያሳድር መሆኑ) እና ውጫዊ ተፅጽኖዎች የተጋለጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ወደ ውጭ የሚላኩ የቁም እንስሳት በመጀመሪያ በኳራንታይኑ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የምርመራ ናሙናዎች ተቀድቶ ማዕከሉ ሊደርስ ሲገባው ነገር ግን የማዕከሉ ባለ ሙያዎች ቀጥታ የላቦራቶሪ ናሙናዎችን የባለ ሀብቶቹ እንስሳት ማቆያ ቦታ ሄደው ቀድተው የሚያመጡ በመሆኑ ከባለ ሀብቶች ጋር የጥቅም ግንኙነት ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ከማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎችና ከኳራንታይኖች እንዲሁም ከቁም እንስሳት ላኪ ድርጅቶች ከተደረገ ቃለመጠይቅ ታውቋል፡፡
- ስሪቃ በዳሶ የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት ማዕከሉ በቀን 24/02/2016 በSR/Ex58/16 በ test report No, 58/16 የመረመረውን በአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ በቀን 22/06/2008 ዓ.ም በማዕከሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ዱባይ የተላኩ ሲሆን ዋጋቸው 110,000 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ እንስሳቶች በሻርጃ /ዱባይ ጤንነታቸው የተሟላ አይደለም ተብለው በቦታው እንዲቃጠሉ የተደረገ መሆኑ፣
- አባ ኪያ ጀነራል ትሬዲንግ (በረከት ደመቀ) የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት በአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ በቀን 09-11/06/2016 በ SR/Ex267/16 test report No, 58/16 በtest report No, 267/16 በማዕከሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው 900 ፍየሎችን ወደ ዱባይ ሻርጃ የተላኩ ቢሆንም ከ900 ፍየሎች 61 ፍየሎች ብቻ ተቀባይነት ሲያገኙ ቀሪዎቹ 59,780 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ ፍየሎች ተቀባይነት ባለማግኘታቸው ወደ ሀገር የተመለሱና ለአውሮፕላን መጓጓዣ 46,970 የአሜሪካ ዶላር ኪሳራ ደረሰ መሆኑን፣
- ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪ ማዕከሉ በቀን 25-27/06/2017 በ SR/Ex259/17 በtest report No, 259/17 በማዕከሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው 2500 ፍየሎች ለ21 ቀናት በኳራንታይን ጣቢያ ውስጥ እንዲቆዩና ለአባ ሰንጋ፣ የበጎች ደስታ መሰል በሽታ፣ ፈንጣጣ እና የፍየል ሳንባ በሽታ ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት የወሰዱ መሆኑን ጠቅሶ እ.አ.አ በቀን 21/04/2017

በእንስሳት ጤና ሰርትፍኬት ቁጥር AQS-01/397/2017 ከአዳማ ኳራንታይን ጣቢያ የተሰጣቸው ቢሆንም ፣ ከ2500 ፍየሎች ውስጥ 1298 ወይም ዋጋቸው 90,860 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ የሞቱ መሆኑና በጅቡቲ የወደብ የአገልግሎት ዋጋ ብር 4,322,222.7 ላኪው እዲከፍል መጠየቁ ፤

157. ማዕከሉ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከማዕከሉ የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ከቦረና አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ ከያቤሎ ክልላዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእንስሳት ጤና ቁጥጥር ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ከድሬ ደዋ እና ከጅግጅጋ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎች የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክሜንት ክለሳወች መሰረት ማዕከሉ በአከባበው ተንቀሳቃሽ የላቦራቶሪ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣

158. ማዕከሉ በኦፕሬሽናል ማኑዋሉ መሰረት በዓመት አራት ጊዜ የበሽታዎች አሰሳና ምርመራ በማድረግ ወቅታዊ የበሽታ ጥናት ማድረግ ይጠበቅበታል፣

159. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በወላይታ ሶዶ፣ በቦረና፣ በደቡብ ክልላዊ መንግስት፣ በሉሜ ወረዳ፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን፣ በጅግጅጋ፣ በድሬደዋ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊወች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና ሰነድ ክለሳዎች መሰረት ማእከሉ በኦፕሬሽናል ማኑዋሉ በተገለፀው መሰረት በአመት አራት ጊዜ የበሽታዎች አሰሳና ምርመራ በማድረግ ወቅታዊ የበሽታ ጥናት የማያካሂድ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ማእከሉ በኦፕሬሽናል ማናዋሉ በተገለፀው መሰረት በመፈፀም በአገራችን ያለው የእንስሳት በሽታ አይነት ፤ ስርጭት እና ስፋትን በመገምገም ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግና ችግሩ ሲከሰትም አፋጣኝ መልስ ለመስጠት የሚያስችል ስራ በበቂ ሁኔታ አለመስራቱ በአገሪቱ የእንስሳት ሀብት ላይ የከፋ ችግር እዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፤

15 የግብርና ሚኒሰቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስርዓት መገምገም

160. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም በወጣው መሰረት ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነቱንና ጥራቱን በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ መመዝገቡን እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ መኖሩንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

161. በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው በላብራቶሪ ተመርምሮና ተረጋግጦ እንደማይመዘገብና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ እየተመዘገቡ ያሉት እንዲሁ ዶክመንት /ወረቀት/ በማየት ብቻ መሆኑ በተጨማሪም በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች /ድርጅቶች/ ጥራቱን የጠበቀምርትና ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ፣ የፀረተባይ ኬሚካሎች በሃገር ውስጥ ለማምረት እና ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የተደራጀና ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ ላብራቶሪ አገልግሎት የሌላቸው መሆኑንና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተገቢው ሁኔታ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት እንደሌለና ተግባራዊ እንዳላደረገ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቅሪትና ጥራት ለመቆጣጠር የሚያስችል የተጠናከረና ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የጥራትና ቁጥጥር ላብራቶሪ አለመኖሩ፣
- ኳራንቲን ጣቢያዎች በላብራቶሪ የተሟሉ አለመሆንና አለም አቀፍ እስታንዳርድን በሚጠይቀው መሰረት ተሟልተው አለመገኘታቸው፣
- ከጎረቤት ሀገራት በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ያልተመዘገቡ እና ጥራታቸው በላብራቶሪ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ እንዲሁም በኤክስፖርት ሰብሎች ላይ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ቅሪት በመገኘቱ በኤክስፖርቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣

- ወደ ውጪ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ በተገኘ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቅሪት ምክንያት በከፍተኛ ወጪ የተመረተ ምርት እንዲወገድ መደረጉ፣ ተቀባይነቱና ተፈላጊነቱ እየቀነሰ መምጣቱ፣ ለማሳያ፡- ወደ ጃፓን በተላከ የቡና ምርት ላይ የኦርጋኖ ክሎሪን ዝርያ ያላቸው ፀረ ተባይ ቅሪት መገኘቱ፣ እ.ኤ.አ አቆጣጠር ከ2014-2016 በተከታታይ ወደ ጣሊያን ለምግብነት እንዲውሉ የተላኩ ምርቶች በፀረ ተባይ ቅሪት ምክንያት ከድንበር ላይ እንዲመለሱ መደረጉ፣ ወደ አውሮፓ በተላከ ነጭና ቀይ ቦለቄ ውስጥ ለግብርና እና ለወባ ትንኝ ማጥፊያ የሚውሉ የፀረ ተባይ ቅሪት በመገኘቱ በምርቱ ጥራት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደሩ ለመግዛት መቸገራቸው በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ አለመኖሩ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ እንዲኖር ስለዘረጋው ስርዓት /ስለሰራው ስራ/ ማስረጃው ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆናቸው ማረጋገጡን በተመለከተ፤

- ሼር ኢትዮጵያ ኃ.የተ.የግል ማህበር ከተመረተ 6 ወር ያለፈው ቴፒኪ /Teppeki/ የተባለ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱ፤
- ኒዶፒያ ኦርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር Ortiva እና Folio Gold ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለያሲን ለገሰ ጆንሰን የአበባ እርሻ እና ዜድ ኬ ፍላወርስ ኃ.የተ.የግል ማህበር ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ የተሰጣቸው መደረጉ፤
- መኮቡ ኢንተርፕራዝ ኃ.የተ.የግል ማህበር Fastac R እና Stomp R የተባሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፤

- ዜድ ኬ ፍላወርስ እና ያሲን ለገሰ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኒዶፒያ ሆርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኩል 240 ሊትር ሬጀንት /Regent/ የተባለ ፀረ ተባይ ኬሚካል ከተመረተ 6 ወር ያለፈው ቢሆንም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ መደረጉን፤
- ማኮቦ ኢንተርፕራይዝ ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅት ከተመረተ 7 ወር የሆነው ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለማከፋፈል ሳይሆን ለምርምር ወይም ለሙከራ ብቻ የሚውል መጠኑን በመወሰን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ በአስገዳጅ ሁኔታዎች የሚፈቅድ ቢሆንም አስገዳጅ ሁኔታዎች አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰኑ እንደሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 4 እና ክፍል ሦስት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 4 ቢገለፅም አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ደንብና መመሪያ በሌለበት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይመዘገቡ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ሳይኖራቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ እያስገቡ መሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ቢገቡ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ጥቅም ላይ ይውላሉ በሚል ሲገቡ በሚኒስቴሩ የተፈቀደበት /የተወሰነበት/ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አለመቅረቡ፤

163. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱንና ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ መሰብሰቡን በተመለከተ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ ከጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ከብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ሚኒስቴር የተውጣጡ እና የተዋቀሩ የቦርድ አባላት እንደሚኖሩት እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ምዝገባ፣ እድሳት፣ ማገድ፣ ማሻሻል፣ ምዝገባን መሰረዝ፣ የፍቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችና ቅድመ

ሁኔታዎችን እና ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስወገድን፣ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠቃቀምን፣ አስተሻሸግን፣ መለያ አደራረግን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ ስርጭትን፣ የባዶ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መያዣዎች ማስወገድን እንዲሁም ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር ከመተግበር አኳያ ሚኒስቴር መ/ቤቱን እንደሚያማክር እና በብሔራዊ ደረጃ ከሚወከል አካል ጋር በመተባበር እንደሚሰራ በሚኒስቴር መ/ቤቱአዋጅ ላይ ቢገለፅምቦርዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ወደ ስራ አለመግባቱና በተወሰነለትጊዜም አለመሰብሰቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው መዝግቦ በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት መዘርጋቱንና አፈፃፀሙን መከታተልና መቆጣጠሩን በተመለከተ፤

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 480,000 ሊትር
- በአዲስ አበባ ግብርና ቢሮ 400 ሊትር
- በስኳር ኮርፓሬሽን 100,527 ሊትር
- በኢትዮጲያ የግብርና ስራዎች ኮርፓሬሽን 24,853 ሊትር
- በግብርና ግብዓት አቅራቢዎች ድርጅት 39,913 ሊትር
- በደቡብ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት 29,845.5 ሊትር
- በአማራብ/ክ/መንግስት 29,510 ሊትር
- በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት 105,598 ሊትር
- በትግራይ ብ/ክ/መንግስት 33,251 ሊትር
- በቤንሻንጉል ብ/ክ/መንግስት ግብርና ቢሮ 14,200 ሊትር
- ጋምቤላ ብ/ክ/መንግስት ግብርና ቢሮ 5,905 ሊትር
- ሐረር ብ/ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ 1,000 ሊትር

- በአፋር ብ/ክ/መንግስት ግብርና ቢሮ 5,120 ሊትር
- በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ 540,854 ሊትር
- በጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ማህበር 16,660
- በባይስም ኃ/የተ/የግ/ማህበር 1000
- ሲንጀንታ ኃ/የተ/የግል ማህበር 3,438
- በአጠቃላይ 1,432,074.5 ሊትር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸው፡፡

በ9 ክልሎችና በ1 ከተማ መስተዳደር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ዲዲቲ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

ተ.ቁ	ክልል /መስተዳድር/	መጋዝኖች	ብዛት	መለኪያ
1	በድሬደዋ መስተዳድር	1	4,793	ኪ/ግ
1	በአማራ ብ/ክ/መንግስት	102	287,861.60	ኪ/ግ
2	በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት	190	286,747.50	ኪ/ግ
3	በትግራይ ብ/ክ/መንግስት	30	28,953.67	ኪ/ግ
4	በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት	68	203,231.50	ኪ/ግ
5	በሐረሬ ብ/ክ/መንግስት	1	5,440	ኪ/ግ
6	በቤንሻንጉል ብ/ክ/መንግስት	17	17,433.24	ኪ/ግ
7	በአፋር ብ/ክ/መንግስት	16	16,349.60	ኪ/ግ
8	በጋምቤላ ብ/ክ/መንግስት	4	43,074	ኪ/ግ
9	በሱማሌ ብ/ክ/መንግስት	31	34,625.2	ኪ/ግ
	ጠ/ድምር	**460**	**928,509.31**	**ኪ/ግ**

165. እንዲሁም ከላይ በናሙና በተገለፁ ሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለብቻቸው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው እና በየቦታው በተበታተነና ባልተደራጀ መልኩ እንደሚገኙ በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገዱበትን ስርዓት አለመዘርጋቱ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር አለመቻሉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

16 የገንዘብ ሚኒስቴር ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም

15.1 <u>የገንዘብ ሚኒስቴር በተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም</u>

166. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 16 መሰረት ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/ 2009 የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ እና የሚመለከታቸው አካላት በስራ ላይ እንዲያውሉት ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የገንዘብ ሚኒስቴር ህጋዊ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ በወቅቱ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ባለማድረጉ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው አካላት በተዘጋጁ ፣ ባልጸደቁ እና ህጋዊነታቸውን ጠብቀው ስራ ላይ እንዲውሉ ባልተደረጉ መመሪያዎች ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ማድረጉ፡፡

167. የገንዘብ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 9 ንዕስ አንቀጽ 2/ መሰረት ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊወስን ይገባል፡፡

- የገንዘብ ሚኒስቴር ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘቡ ለተጠቃሚዎች እስከ ተሰተጠበት ጊዜ ድረስ በአዋጁ መሰረት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚተላለፍበት ደንቦችና ሁኔታዎች ያላዘጋጀ መሆኑ፡፡

168. የገንዘብ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ከባንኩ የሚደርሰውን የፈንዱ አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚደርሰው የተመረመረ የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫ እና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያላቀረበ መሆኑ፡፡

169. የገንዘብ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከባንኩ የሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ ሊፈጽም ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 6/2 መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፤ በአዋጁ ስልጣን ላልተሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡፡

15.2 <u>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም</u>

170. ባንኩ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ሊይዝ ይገባል፡፡

- ለፈንዱ ከተመደበው በጀት ብር 10,000,000,000 ውስጥ ከ9 ቢሊየን ብር ማለትም ከ 90 % በላይ ከመንግስት ወጪ ሆኖ ለክልሎች /ለተጠቃሚዎች/ እንዲተላለፍ የተደረገ ቢሆንም የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ሆነ በሌላ አካል እንዲያዝ አለመደረጉ፡፡

171. ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 11/2 መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያላቀረበ መሆኑ፡፡ እንዲሁም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትም ለተጠቃሚዎች ያሰራጩት የፈንዱን ገንዘብ ኦዲት አለማድረጋቸው እና ኦዲት እንዲያስደርጉ ያልተደረገ መሆኑ፡፡

172. በየኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅቁጥር 995/2009 ዓ/ም የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የአዋጁ አንቀፅ 9/1 እና 2 እንደሚገልጸው /የክልሉን ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በማድረግ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9/1 እና 2 /በየክልሎቹ ወጣቶች ቁጥር/ መሠረት በ2009 እና 2010 በጀት አመት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይንንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ማድረግ ሲገባው ነገር ግን ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ የተደረገው በአዋጁ ከተገለፀው ውጭ ውክልና በሰጣቸው የዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች በኩል ከመሆኑም ባሻገር የገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ገንዘቡ ወደ ተጠቃሚዎች የሚያስተላልፉበት ደንብና ሁኔታዎች ባለወጣበት እና በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው በየክልሉ በሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በተዘጋጁ ወጥነት በሌላቸው ደንቦች እና ሁኔታዎች/ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ሰነዶችና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፡፡

173. ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2/ መሰረት የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም የፈንዱን ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር አላደረገም፤ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ውክልና ከሰጣቸው ውስጥ በናሙና ባየናቸው የትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ የሀረሪ ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ሂሳብ በዋናው ኦዲተር ወይም እነሱ በሰየሙት ኦዲተር በየዓመቱ እንዲመረመር ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

174. በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር በአዋጅ 995/2009 ዓ/ም በክፍል ሁለት አንቀጽ ሰባት ኃላፊነት ቢሰጠውም፤ ባንኩ የመወከል እና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን አሳልፎ ለሌሎች አካላት የመስጠት ስልጣን ሳይኖረው ስራውን ሳይጀምረው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በውክልና ስልጣኑን የሰጣቸው መሆኑን በቀን 13/09/2010ዓ/ም የባንኩ ፕሬዚደንት በተገኙበት እንዲሁም በቀን 25/11/10 ዓ/ም

የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ከገለጹት እና በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማአ.-30/19/12 ከተጻፈ የውክልና የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

15.3 <u>የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር በተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም</u>

175. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተል፣ እንዲገመግም፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርብ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ያልሰራ መሆኑ ፡፡ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናትም ለፈንዱ የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ከ90% በላይ ወጪ ሆኖ ለወጣቶች እስከ ተሰራጨበት ጊዜ ድረስ የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ያላቀረቡ መሆኑ፡፡

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2/ መሰረት አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት ፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ያልሰራ መሆኑ፡፡

177. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ መሰረት አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲገኙ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም እንዲሁም ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ **በተቀናጀ ፣ በታቀደ ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ ያልሰራ መሆነን ለማወቅ ተችሏል፡፡

178. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የሚደርሰውን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለማቅረቡ ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣናትና ሕዝቡ የፈንዱን አፈጻጸም በምን ደረጃ እንደሚገኝ በትክክለኛ በማስረጃ የተደገፈ መረጃ እንዳያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ የተፈጠሩ ችግሮች በየአመቱ ተለይተውና በሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎች ታውቀው ከስር ከስር መፍትሂ እንዳያገኙ በማድረጉ በብድር የተሰጠው የፈንዱ ገንዘብ አመላለስ ላይ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንዲወድቅ የበኩሉን አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደረ መሆኑ፡፡

17 የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ

የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና እንዲሁም የሰልጣኝ ልማትና ተቋማት አቅም ግንባታ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነት

179. ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 199/2203 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን ሊያዘጋጅ ፣ ሊከልስ እና በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

180. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የስራ ሃላፊዎች፣ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች እና ከማሰልጠኛ ተቋማት የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና ቀርበው በተከለሱ ሰነዶች መሰረት ኤጀንሲው የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃዎችን በተሟላ ሁኔታና በወቅቱ ያላዘጋጀ እና ያልከለሰ መሆኑን እንዲሁም ያዘጋጃቸውንና የከለሳቸውን ደረጃወችም ለሴክተር መ/ቤቶች ፣ ለክልል ቢሮዎች እና ለምዘና ማዕከላት እና ለተቋማት መድረሳቸውን እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን አለመከታተሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

181. ለአብነት እንደሚመከተለው ቀርቧል፦

- ኤጀንሲው በገበያ ተፈላጊ ሆነው የሙ.ያ ደረጃ ያላዘጋጀላቸው ሙ.ያዎች ለአብነትም፦ በወለል ንጣፍ ምርት Terrazzo Tiles production ፣ በልብስ ቁልፍ ማምረት ሥራ ፣ በጠመኔ ፣ በ airfram technician level III እና በወረቀትና ሰበዝ በሚሰሩ ጌጣጌጦች ፣ በሚስማር ፣ በአጥር ሽቦ ማምረት እና በሳሙና ጌጣጌጥ እና ፕላስቲክ) ሙ.ያዎች መኖራቸው ፡፡
- ለኦሮሚያ የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮ እና የብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ፣ ለአፋር እና ደቡብ ክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ቢሮዎች ፣ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ብቃት ምዘና ማዕከል እና የማሰልጠኛ ተቋማት፦ ለሻሸመኔ ለአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ፣ ለሀዋሳ አትላስ የቢዝነስ ቴክኖሎጂ ኮሌጅ እና ለኤስ ኦ ኤስ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጅ፣ ለአዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለሰመራ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ለወ/ሮ ስኂን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ የስራ ሃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የሙ.ያ ደረጃዎች ሲከለሱ ለኮሌጆች ወቅቱን ጠብቆ የማይላክበት ሁኔታ መኖሩን ፣ የሙ.ያ ደረጃ ደብዳቤ ሳይጻፍ በሲዲ ብቻ እንደሚላክና ፎርማሊቲ የሚጎድለው መሆኑን፣ ሙ.ያ ደረጃዎች ተከልሰው ሲላኩ ስልጠና ከተጀመረ በኋላ የሚደርሱበት ሁኔታ መኖሩ፣ በተከለሰው የሙ.ያ ደረጃ ወደ ስራ ስለመገባቱ ክትትል እንደማይደረግ፣ በፌዴራሉ ኤጀንሲ የሙ.ያ ደረጃዎች ከ 3-5 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ መከለስ ቢኖርባቸውም ከተባለው የግዜ ገደብ ቀድሞ የሚከለሰበት ሁኔታ በመኖሩ የስልጠና ጥራት ችግር እንደሚፈጥር እና ተግባራዊነቱን አስመልክቶ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ላይ ውይይት ከማድረግ ያለፈ በቂ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

182. ኤጀንሲው በደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ፣ ስርዓተ - ትምህርቶች እና የስልጠና መሳሪያዎች (Teaching and Training learning material /TTLM/ እና Competency biased learning material/CBLM/ መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሰልጣኞች የሚሰጥ የስልጠና የምስክር ወረቀት በየተቋሙ የሚለያይ መሆኑን

- በደቡብ ብ/ክ/መ የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ባለሙያዎች ደረጃ 4 ለደረሱ ባለሙያዎች ብቻ ኦርጅናል የምስክር ወረቀት እነደሚሰጥና ደረጃ 1/ 2 /3 በጊዚያዊ የምስክር ወረቀት ብቻ እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑን ፣ ብቃታቸውን ላረጋገጡ ተመዛኞች ሰርተፊኬት ያለመስጠት ሁኔታ መኖሩን/በተለይ ደረጃ1 እና 2/ ፣ በአጫጭር ስልጠና አጠናቀው የሚወጡ ሰልጣኞችን የደረጃ አንድ ሰርትፍኬት የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ፣

- የሙያ ብቃት ምዘናና ሀገር አቀፍ የብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን ዘርግቶ ጊዜያዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በብቃት ማዕከላት ተዘጋጅቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሰጠቱ እና ዋናውን በሶስት ወር ውስጥ አዘጋጅቶ በማዕከላት በኩል ለተመዛኞች የማድረስ ስራ እየተስራ አለመሆኑን፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት አመታት ብቻ ስለማገልገሉ እና ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃው ከተቀየረ ባለሙያው ምዘናውን እንደገና የማይወስድ መሆኑን፣ ከ 3 ዓመት በኋላ የሙያ ደረጃ ካልተቀየረ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በየ ሦስት ዓመቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የማይታደስ መሆኑን፣ እንዲሁም ኤጀንሲው አፈፀሙን የማይቆጣጠር መሆኑን ታውቋል፡

183. በደንብ ቁጥር 199/2003አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ6 መሰረት ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት በመዘርጋት የቴ/ሙ/ት ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ ያለፉ ስለመሆኑ ሊከታተል እና አፈፃፀሙንም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኤጀንሲው የስራ ሃላፊወች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ለታዩ የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ/ ቢሮዎች ፣ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ማዕከላት እና ለቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጆች የስራ ሃላፊወች ላቀረበው ቃለ መጠይቆች እና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃወች ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓትን ቢዘረጋም የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞች በምዘና ሂደት ውስጥ

ስለማለፋቸው እንዲሁም ኤጀንሲው የምዘና ስርአቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ተከታታይነት ያለው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑን ፣

184. እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በመንግሰት እና በግል ተቋማት መደበኛ ስልጠናን ያጠናቀቁ 377,844 ሲሆኑ የተመዘኑት 155,479 ብቻ መሆናቸውን ፣ አጫጭር ስልጠና ያጠናቅቁ 834,018 ሲሆኑ የተመዘኑት ግን 177,219 ብቻ መሆናቸውን፣ በአጫጭር ስልጠና እና በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ስራ ምዘና ያለመጠናቀቅ ችግር መኖሩን ፣ የሙያ ደረጃን ለኤክስቴንሽን ድጋፍ የጥራት ማስጠበቂያ መሳርያ አድርጎ በመጠቀም ጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማትን እስከ ደረጃ አራት የማብቃት ስራ በሚፈለገው ልክ አለመሰራቱን እና ጥራትን በምዘና እንዲረጋገጥ ማድረግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱን ፣ በሬልዌይ ቴክኖሎጂ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፓኬጅ እንደ ሀገር አለመኖሩን እንዲሁም በልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ GMFA እና በአውቶ መካኒካል ዲፓርትመንት በደረጃ 5 ሙያ ምዘና የማይሰጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

185. በኤጀንሲው የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 እና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) በተቀመጠው መሠረት የማሰልጠኛ ተቋማት ተደራሽ እንዲሆኑ እና እውቅና የሚያገኙበትን መመዘኛ መመርያ ሊያወጣ እና አፈጻጸሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ቀረበው ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወረዳ አንድ ማሰልጠኛ ተቋም እንዲኖር ለማድረግ ቢታቀድም በ2010 በጀት ዓመት 158 አዳዲስ ማሰልጠኛ ተቋማት ለመገንባት የታቀደ ቢሆንም መገንባት የተቻለው 24(15%)ብቻ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ 225 እውቅና እንዲያገኙ ታቅዶ 17(8%) ብቻ እውቅና ያገኙ መሆኑን ፣ በ2010 በጀት ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ 12 እውቅና እንዲገኙ ቢታቀድም እውቅና ያገኘ ማሰልጠኛ ተቋማት አለመኖሩን
- እንዲሁም በናሙና ከታዩ ክልሎች በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 336 ወረዳዎች ውስጥ 163 ወረዳዎች ላይ ብቻ ተቋማት መክፈት እንደተቻለ

መገለጹ ፣ በደቡብ ክልል ከ135 ወረዳዎች 51 ወረዳወች ላይ ብቻ የማሰልጠኛ ተቋማትመከፈት እንደተቻለ መገለጹ፣ በአፋር ክልል እስከ ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 7 የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮሌጆችን ለመገንባት ቢታቀድም ምንም ግንባታ አለመከናወኑ በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤ የ2010 ዓ.ም. ዕቅድ አፈጻጸም መገለፁ፣

186. ኤጀንሲው ደንብ ቁጥር 199/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 13 መሰረት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት ለቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ኤጀንሲው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ድጋፍ እና ክትትል በቂ አለመሆኑን እንዲሁም በ2010 ዓ.ም. የፌ/ቴ/ሙ/ስልተና ኤጀንሲ ዕቅድ አፈፃፀም አዲስ የመደበኛ የሴት ሰልጣኝ ቅበላ አፈጻጸም በሶማሌ 42% ፣ በአፋር 35% እና በጋምቤላ 16% መሆኑን ፣ የሴቶች ተሳትፎ በመደበኛ ስልጠና ላይ በጋምቤላ ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 1314 ሲሆኑ የተመዘኑት 108 (8.2%) እና በአፋር ስልጠና ያጠናቀቁ ብዛት 503 የተመዘኑ አለመሆኑን ፣
- እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች የመደበኛና የአጫጭር ስልጠና ተሳትፎ ያጠናቅቁ ፣ የተመዘኑ እና ከተመዘኑት የበቁ አፈፃፀሙ ቤንሻንጉል ጉምዝ(0) እና ጋምቤላ(0) መሆኑን እነዲሁም የቤ/ጉ/ቴ/ሙ/ኢ/ል/ቢሮ የ2009 ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ሪፖርተ ለ120 አካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች ቅበላ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 50(41.6%) መሆኑ፣ በኦሮሚያ ክልል ከተመረጡ የግልና የመንግስት ተቋማት በአድማስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች ለአካል ጉዳተኖች ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩን /የመማሪያ ክፍሎች ፣ ሾፖች ፣ ቤተመጽሃፍት ፣ አይቲ ክፍል ፣ ማጸዳጃ ቤቶች እና ቢሮዎች ለዊልቸር ተጠቃሚ አመች አለመሆናቸውን እንዲሁም የመስማትና ማየት ውስንነት

ላለባቸው ከበር ጀምሮ ኮሪደሮች ላይ ምልክቶች አለመኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

187. ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና የማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማደራጀትና፤ በመተንተን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ዳታ ቤዝ ሊያዘጋጅና ስራ ላይ ሊያውል በየጊዜውም እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፤

- የፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ በሀገር አቀፍ ደረጃ መረጃ በማሰባሰብ ፣ በማደራጀት ፣ በመረጃ ቋት(በዳታ ቤዝ) በማጠናከር እና በየጊዜው በማሻሻል የማይዝ መሆኑን፣
- በቁልፍና አበይት ተግባራት ዕቅድ ሲታቀድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚያሳይ መረጃ አለመደራጀቱን፣ በአብዛኞቹ ተቋማት መረጃን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መለዋወጥ ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፤

18 የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት

የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን መገምገም፤

188. ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት ማስተዳደር አስፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በአገር ውስጥና በውጭ አገር በማምረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ወቅቱ የሚጠይቀውን የኢንዱስትሪ ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል ጥናት በማጥናት ችግሮችን በመለየት እና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ቅደም ተከተል (Priority) በማስቀመጥ የተሰራ ስራ አለመኖሩ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ማቅረብ ያለበት ቢሆንም ይህን በተመለከተ የተሰራ ስራ አለመኖሩ፤

189. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት በመለየት በእስትራቴጂክ ዕቅዱና በዓመታዊ ዕቅዱ በማካተት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርገና በክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት ለመለየት እና አቅጣጫ ለማመላከት የሚያስችል የፀደቀ እስትራቴጂክ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፤

ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን አስፈላጊውን ጥናት በማከናወን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመግዛት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር በግዢ የሚያቀርብ ቢሆንም በጥናት የተደገፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ አለመሆኑ፤

ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቱ ዓይነት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በማዘጋጀት እንደ ግብዓቱ ዓይነት በመለየት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ መሳሪያዎችና የመጋዘን መርጃ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተደራጀ መሆኑ፤ ለማሳያ ያህል፡-
  - ድርጅቱ የስቶር አያያዝ ችግር ያለበት መሆኑን እና መጋዘኖቹ መተላለፊያቸው ጠባብ በመሆናቸው እሳት ቢነሳ እንኳን ለመከላከል አስቸጋሪ መሆኑ፤
  - በቃሊቲ በጥጥ መጋዘን እና በሌሎች መጋዘኖች ውስጥ ከተለያዩ ቦታ የመጡ ምርቶች እንደ ጥራታቸው ደረጃ ተሰጥቶአቸው የተለያየ ቦታ ሊቀመጡ ሲገባ ተቀላቅለው የሚቀመጡና ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑ፤ የጥጥ አቀማመጡም ወለል ላይ የሚቀመጥ በመሆኑ ቅዝቃዜ ስቦ

የክብደትና የከለር ለውጥ በማምጣት የነበረውን ጥራት የሚቀንስና የሚበላሽበት ሁኔታ መኖሩን፣

- ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በቃሊታ መጋዘን የገባ በአጠቃላይ 1,367,592.622 ኪ.ግ የአርማታ ብረት በግቢ ውስጥ ያለ በቂ ጥበቃ ለብክነት እየተዳረገ መሆኑ፤
- እንዲሁም በቃሊቲ የመጋዘን ቁጥጥርና አስተዳደር ደካማ በመሆኑ እና እቃ ሲገባና ሲወጣ ተገቢ የሆነ ክትትል ባለመደረጉ በቃሊቲ መጋዘን የገቢ ሰነድ ሳይቆረጥለት የአርማታ ብረት በብልጫ የብር 1,764,617.92 (የአንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ከ 92/100 ሳንቲም) የአርማታ ብረት በቆጠራ ወቅት መገኘቱ፣ በተጨማሪም ብር 908,434.63 (ዘጠኝ መቶ ስምት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከ63/100 ሳንቲም የአርማታ ብረት በክምችት ከተመዘገበው በላይ ተሸጦ የተገኘ መሆኑ፤
- በተጨማሪም በጁላይ 7 2015 እስከ ማርች 3,2018 ድረስ የአርማታ ብረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ጨምሮ 33,386,174.36 ብር (ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ከ36/100 ሳንቲም ጉድለት መታየቱን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ ግብዓት በሚያቀርብበት ጊዜ ዱቤ ከመስጠቱ በፊት የፋብሪካዎቹን አቋምና የዕዳ አከፋፈል በተመለከተ ተገቢውን ጥናት ሳያደርግ የዱቤ ሽያጭ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩ፣ ለማሳያ ያህል በናሙና ከታዩ ፋብሪካዎች መሀከል የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ድርጅቱ የፋብሪካዎችን የመክፈል አቅም ጥናት ሳይደረግ ብድር የተሰጠ መሆኑ፣

190. ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት ለሚረከቡ ኢንዱስትሪዎች ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት ለሚረከቡ ኢንዱስትሪዎች ለሚረከቡት ግብዓት ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲያቀርቡ አልተደረገም፡፡ ይህን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ታይተዋል፡-

- ዲ ኤም ቪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ኢንዱስትሪ ያቀረበው ዋስትና በውስጥ ኦዲት ሲጣራ ያቀረበው ትክክለኛ አለመሆኑ መረጋገጡ፣

- የቆዳ ፋብሪካዎች ከድርጅት ለሚያገኙት የዱቤ ሽያጭ ተመጣጣኝ የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና እንዲያቀርቡ በወቅቱ ያልተደረገ መሆኑ፣ ሀበሻታኒግ ቆዳ ፋብሪካ፣ ሆራ ቆዳ ፋብሪካ ፣ ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ አክሰዮን ማህበር ፣ የቃል ኪዳን ሰነደ ከመፈረም ውጭ ዋስትና እንዲያቀርቡ አለመደረጉ፣

- የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፣ የባህርዳ ጨርቃ ጨርቅ ለወሰዱት ዱቤ ግዢ ዋስትና ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

- እንዲሁም የአይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ጥጥ በግዢ የሚቀርብለት ሲሆን በእነዚህ ጊዜያት ውል ከመፈረም ውጭ ዋስትና አስይዞ የማያውቅ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለየያዩ ግብዓቶች በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለያዩ ግብዓቶች ውል እንዲፈጽሙ እና በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ውጤታማ በሆነ መልኩ የማይደርግ መሆኑ እና በተቀመጠው ጊዜ በማይመልሱት ላይ ተገቢ እርምጃ በወቅቱ የማይወሰድ ሁኔታ መኖሩ፡-

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ድርጅቶች ውስጥ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዱቤ ግዥ ፈጽመው በተቀመጠው ጊዜ/ 6ወር/ ውስጥ ክፍያ ያልፈጸሙ

ድርጅቶች እስከ (የካቲት 2011 ዓ.ም) ድረስ ያልከፈሉ እና በድርጅቱም ያልተሰበሰበ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉት ተቀምጠዋል፡፡፡

- አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዱቤ ከተሸጠ ብር 390,919,000.00 (ሶስት መቶ ዘጠና ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አሰራ ዘጠኝ ሺ.ህ) ውስጥ ብር 106,568,562.19 አንድ መቶ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ.ህ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ከ19/100 ሳንቲም) የመክፈያ ጊዜው ስድስት ወር ያለፈ ያልተሰበሰበ፣

- ካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 239,503,000 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሶስት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 36,100,506.29 (ሰላሳ ስድስት ሚሊየን አንድ መቶ ሺ.ህ አምስት መቶ ስድስት ከ19/100 ሳንቲም) መክፈያ ጊዜወ ያለፈና በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

- ካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 239,503,000(ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሶስት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 36,100,506.29 (ሰላሳ ስድስት ሚሊየን አንድ መቶ ሺ.ህ አምስት መቶ ስድስት ከ19/100 ሳንቲም) መክፈያ ጊዜወ ያለፈና በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

- ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 59,697,000.00 (ሀምሰ ዘጠኝ ሚለዮን ሰድስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 1,220,662.21 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀያ ሺ.ህ ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ከ21/100 ሳንቲም) የመክፈያ ጊዜው ያለፈ፣

- ሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በዱቤ ግዢ ከፈጸመው ውስጥ ብር 2,395,261.77 (ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ.ህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ከ77/100 ሳንቲም ያልተሰበሰበ መሆኑ

- እንዲሁም ከቢ.ረ ኢንተርፕራዝ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ውስጥ ብር 101,034,000 (አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ሰላሳ አራት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 38,757 ,536.72 (ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ.ህ አምስት

መቶ ሰላሳ ስድስት ከ72/100 ሳንቲም) የመክፈያ ጊዜው ያለፈና እስከ የካቲት 2011 ድረስ ያልተሰበሰቡ ናቸው፡፡

- በተጨማሪም አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እ.እ.አ መስከረም 11/2016 በዱቤ ሽያጭ መጠኑ 497,326 ኪ.ግ የሆነ ጥጥ የመሸጫ ዋጋው በብር 35.05 በኪሎ ግራም በአጠቃላይ በብር 17,431,276.30 (አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ብር 30/100 ሳንቲም) ተገቢው ውል ሳይፈፅም በዱቤ የተሸጠለት መሆኑ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም በዱቤ ግዥ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ፈጽመው በውል በተቀመጠው ጊዜ / 5 ወር / ጊዜ እስከ የካቲት 2011 ዓ.ም ያልመለሱ የቆዳ ፋብሪካዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፣
- ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 35,993 ሚሊየን ውስጥ ብር 3,287,936.76 (ሶስት ሚለዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስድስት ከ76/100 ሳንቲም) በወቅቱ ያልተከፈለና የመመለሻ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ሃበሻ ታኒግ በዱቤ ግገር ከፈጸመው ብር 25,411,631.96 (ሃያ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ከ96/100 ሳንቲም የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ሆራ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 23,728,069.66 (ሀያ ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀያ ስምንት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ከ66/100 ሳንቲም) ያልተከፈለ መሆኑ፣
- ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 1,293,859.42 (አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ስመንት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ከ42/100 ሳንቲም) ያልተመለሰና ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ዴቨ ኢምፔክስ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግገር ከፈጸመው ብር 318,330.12 (ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ከ12/100 ሳንቲም) የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣

- ይልማ እሸቱ ቆዳና ሌጦ ንግድ ድርጅት በዱቤ ከወሰደው ብር 1,500,000(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) ውስጥ ብር 791,000 (ሰባት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ብር) በወቅቱ ያልተመለሰና የመክፈያ ጊዜው ያለፈና በወቅቱ ያልተሰበሰቡ ናቸው፡፡

  - በተጨማሪም የአርማታ ብረት በዱቤ ግዢ ፈጽመው ያልመለሱ ድርጅቶች ውስጥ፣

    - ዋይ ኤች ኤ የተባለ ድርጅት በዱቤ ሽያጭ በ2008 ዓ.ም ብር 37,341,500 (ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) የወሰደው የአርማታ ብረት ውስጥ ብር 22,160,250 (ሃያ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሺ ሁለት መቶ አምሳ ብር) ያልተከፈለና የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
    - ሃይለ ኪሮስ በዱቤ ሽያጭ ከወሰደው ብር 29,980,500 (ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሺ አምስት መቶ ብር) ውስጥ ብር 4,180,500 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሺ አምስት መቶ ብር) የመክፈያ ጊዜ ያለፈ መሆኑ፤
    - ዲ.ኤ.ቪ. ድርጅት በዱቤ ሽያጭ ከወሰደው ብር 52,337,500 (አምሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ አምስት መቶ ብር) ውስጥ ምንም ያልተመለሰ እና የጊዜ ገደቡ ያለፈ መሆኑ ከተከለሱ መስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

19 ኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ልማት እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር አፈፃፀም ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን

191. ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን የድጋፍ አገልግሎቶች በግልፅ ሊያሳውቅ እና አገልግሎቱን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ በ 2007 ዓ.ም 19 ዓይነት የአገልግሎት ድጋፎችን የያዘ የደንበኞች ቻርተር በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በግልፅ

የማሳወቅና የአገልግሎት ተጠቃሚ የማድረግ ችግር የታየበት መሆኑ ከኢንስቲትዩቱ 2008 በጀት ዓመት የ 12 ወራት እቅድ-አፈፃፀም ሪፖርት በኦዲቱ ወቅት ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

192. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦት አገልግሎትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርት እና የግብዓት ትስስር ድጋፍ ሊፈጥር ይገባል፡፡

- በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች(አንበሳ፣ጥቁር ዓባይ፣ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ የግብዓት ትስስሩ ተጠቃሚ መሆኑ ሲታወቅ የተቀሩት 7 ቱ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት ድጋፍ የማመቻቸት ሥራ ያልሰራ መሆኑን የገለፁ መሆኑ፣
- በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ገላን፣ሞጆ፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ 4ቱ (ብሉናይል፣ ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ እና ገላን) ቆዳ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያላደረገ መሆኑን የገለፁ መሆኑ፣
- እንዲሁም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብዓት ትስስርን በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት እና ከኢትዮጵያ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማህበር ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በሚገኙ የጥሬ ቆዳና ሌጦ መጋዘኖች የሚገኘውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ክምችት አስመልክቶ የመስክ ጥናት የሰራውን ሥራ መስከረም 2010 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት በተወሰኑ 12 የጥሬ ቆዳ ሌጦ መጋዘኖች ውስጥ 195000 የበግ ሌጦ፣ 58200 የፍየል ሌጦ፣ 80000 የዳልጋ ከብት ቆዳ፣ 150000 የበግ ፒክልድ ቆዳ እና 50000 የፍየል ዌት ብሉ ቆዳ በድምሩ 533200 ለቆዳ ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆን በከፊል የለፋና የጥሬ ቆዳ ሌጦ ምርት ተከማችቶ የተገኘ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ በወቅቱ

በየሚረከብ የቆዳ ፋብሪካ ባለመገኘቱ የጥራት ደረጃው የቀነሰ/ የተበላሸ 98800 የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ክምችት የተገኘ መሆኑ፣

193. ኢንስቲትዩቱ ለቆዳ እና ቆዳ ውጠየቶች ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶች ሊያከናውን፤ እንዲሁም የገበያ ማፈላለግ እና ትስስር ሊፈጥር ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ በ 2007 ዓ.ም 19 ዓይነት የአገልግሎት ድጋፎችን የያዘ የደንበኞች ቻርተር በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በግልፅ የማሳወቅና የአገልግሎት ተጠቃሚ የማድረግ ችግር የታየበት መሆኑ ፣

194. ኢንስቲትዩቱ የግብዓት (ጥሬ ቆዳ፣ ኬሚካሎች፣ አክሰሰሪዎች...) አቅርቦት አገልግሎቶችን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ጠንካራ የምርት ትስስር መፍጠሩን በተመለከተ፡

195. በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 8 ጫማ ፋብሪካዎች (አንበሳ፣ጥቁር ዓባይ፣ ፒኮክ፣ ኦኬ ጃማይካ፣ ኒው ዊንግ አዲስ፣ ፎንታኒና እና ሞደርን ዘጌ) ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ የግብዓት ትስስሩ ተጠቃሚ መሆኑ ሲታወቅ የተቀሩት 7 ቱ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት ድጋፍ የማመቻቸት ሥራ ያልሰራ መሆኑ ፣

196. በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ 9 ቆዳ ፋብሪካዎች(አዋሽ፣ ባቱ፣ ብሉናይል፣ ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ፣ ገላን፣ሞጆ፣ ባህርዳር እና ሀበሻ) ሲሆኑ፡- የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለእያንዳንዱ የሥራ ኃላፊ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ 4ቱ (ብሉናይል፣ ኢትዮጵ ቆዳ አክስዮን ማህበር፣ ኮልባ እና ገላን) ቆዳ ፋብሪካዎች ኢንስቲትዩቱ የግብዓት አቅርቦትን በማመቻቸት በአምራች ፋብሪካዎች መካከል ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ፣

197. እንዲሁም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብዓት ትስስርን በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት እና ከኢትዮጵያ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማህበር ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በሚገኙ የጥሬ ቆዳና ሌጦ መጋዘኖች የሚገኘውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ክምችት አስመልክቶ የመስክ ጥናት የሰራውን ሥራ መስከረም 2010 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት በተወሰኑ 12 የጥሬ ቆዳ ሌጦ መጋዘኖች ውስጥ 195,000 የበግ ሌጦ፣ 58,200 የፍየል ሌጦ፣ 80,000

የዳልጋ ከብት ቆዳ፣ 150,000 የበግ ፒክልድ ቆዳ እና 50,000 የፍየል ዌት ብሉ ቆዳ በድምሩ 533,200 ለቆዳ ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆን በከፊል የለፋና የጥሬ ቆዳ ሌጦ ምርት ተከማችቶ የተገኘ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ በወቅቱ የሚረከብ የቆዳ ፋብሪካ ባለመገኘቱ የጥራት ደረጃው የቀነሰ/ የተበላሸ 98,800 የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ክምችት የተገኘ መሆኑ፣

❖ **ኢንስቲትዩቱ የገበያ ጥናት ማከናወኑን፤ እንዲሁም የገበያ ማፈላለግና ትስስር መፍጠሩን በተመለከተ፡**

198. ኢንስቲትዩቱ የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ምርት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀይ እና ለማስተዋወቅ በተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች ለመግባት የሚያስችል የገበያ ልማት እስትራቴጂዎች ጥናት ከዚህ በታች የተመለከቱትን-

- በዩኒዶ የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ የአውሮፓ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ጥናት፣ ወደ አሜሪካን ገበያ ለመግባት የተዘጋጀ የገበያ ፔኒትሬሽን(መግቢያ) ጥናት፣
- በታክት ሰርቪስ ፒ.ኤል.ሲ (TACT Service P.L.C) የተጠና በጫማና በቆዳ ውጤቶች ወደ ተወሰኑ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ገበያ ለመግባት የሚያስችል የገበያ እስትራቴጂ ጥናት፣
- በኮሜሳ (COMESA) ትብብር አማካኝነት የተካሄደ የቆዳ ንዑስ ዘርፍ የገበያ ጥናት እና የእሴት ሰንሰለት እስትራቴጂ ጥናቶች ያዘጋጀ መሆኑ ከማስረጃዎች መረዳት ተችሏል::

199. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ከ2008- 2010 በጀት ዓመታት ከተዘጋጁት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ባገኘው መረጃ መሰረት የኤክስፖርት አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በ2008 በጀት ዓመት ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ኢንዱስትሪ ዘርፍ 185 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 116.35 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን ይህም የእቅዱን 62.89% ሆኖ በ 2007 በጀት ዓመት አፈፃፀም ተገኝቶ ከነበረው 132.86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጋር ሲነፃፀር የ 16.51 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (12.43%) ቅናሽ ያሳየ መሆኑ፣

- በ2009 በጀት ዓመት 272.70 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 115.46 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብቻ የተገኘ መሆኑ፣
- በ2010 በጀት ዓመት 280.53 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 133.77 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ 47.69% በመሆኑ የኤክስፖርት ገቢው በሶስቱም ተከታታይ በጀት ዓመታት እየቀነሰ መሄዱ ኢንስቲትዩቱ የተጠኑትን ጥናቶች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ክፍተት የሚታይበት መሆኑ ፡

200. የኤክስፖርት አቅምን ከፍ በማድረግ አገራችን በጫማ ረገድ ያላትን አቅም ከማስተዋወቅ አንፃር በተለይ የታወቁ ገዢዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት እና ምርቶችን በአሜሪካ ገበያ የማሰተዋወቅ ስራ ለመስራት በፕሮጀክት ደረጃ በፕሪሜትር ኮንሰልቲንግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኩል በሜድባይ ኢትዮጵያ እና በኢንስቲትዩቱ መካከል የኮንትራት ስምምነት በአራት የክፍያ ወቅት በሚፈፀም ክፍያ በጠቅላላው 500,000 የአሜሪካን ዶላር እ.ኤ.አ መጋቢት/2016 የኮንትራት ውል የተገባ ሲሆን፡-

- በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ በውሉ መሰረት(በመጀመሪያ ዓመት 4.75 ሚሊዮን ዩ ኤስ ዲ ፣ በሁለተኛው ዓመት 45 ሚሊዮን ዩ ኤስ ዲ ፣ ሶስተኛ ዓመት 127.5 ሚሊዮን ዩ ኤስ ዲ ፣ በአራተኛ ዓመት 229.5 ሚሊዮን ዩ ኤስ ዲ እና በአምስተኛው ዓመት 382.25 ሚሊዮን ዩ ኤስ ዲ ቢሆንም ከ 2009 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በፕሮጀክቱ የተያዘው የኤክስፖርት ገቢ ግብ በእቅድ በተቀመጠው መሰረት ሊከናወን አለመቻሉ የተመለከተ በመሆኑ፣ የኦዲት ቡድኑ ችግር በገጠመው ወቅት ከተመደበለት በጀት ምን ያህል ገቢ በአሜሪካን ዶላር እነደተገኘ እና በምን ሁኔታ እነደሚገኝን የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ሜድ ባይ ኢትዮጵያ ያለበት ደረጃ ከተገመገመ በኃላ የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ስለ ፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብ በደብዳቤ ቁጥር 03.2/1-4 የተጠየቀ መሆኑ፣

20 በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ አፈፃፀም ሥራ ውጤታማነትን መገምገም

❖ **ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ፡-**

201. ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋና ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ መሰረት ኮሚሽኑ የአደጋ ክስተት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን ስራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ህጎች፣መመሪያዎችና ማዕቀፎችን እንዳላዘጋጀ እና የአፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት እንዳልዘረጋና ተግበራዊ እንዳላደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን በተመለከተ፡-**

202. ኮሚሽኑ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ሊያስተባብር፣ ሊከታተል፣ ሊገመግም እንዲሁም ማንኛውንም መሪ ሴክተር መስሪያ ቤትን የማይመለከት ወይም ከመሪ ሴክተር መ/ቤት አቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ሊሰራ፣ ሊመራ እና ሊያስተባብር ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከኮሚሽኑ በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ፣ የሐረሪ፣ የሶማሌ የክልሎች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና የጌዲኦ ዞን አደጋ ስጋት ቢሮዎች የስራ ኃላፊወች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እንዲሁም በተከለሱ ማስረጃዎች መሰረት ኮሚሽኑ በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች በተከሰቱ እና ከክልሎች እና ከመሪ ሴክተር መ/ቤቶች አቅም በላይ የሆኑ ድንገተኛ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የአደጋ ምላሽና

የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ያላስተባበረ፣ ያልተከታተለ እና ያልገመገመ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የኮሚሽኑ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎችን በተመለከተ**

203. ኮሚሽኑ በአደጋ ክስተት ስራ ዙሪያ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲሁም የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስጥ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ኤች.አይቪ ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ትኩረት ስለመሰጠታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-
- ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ክትትልና ግምገማ እያደረገ እንዲሁም በመመሪያ፣ በፕሮግራምና በዕቅዶች ውስጥ ተካቶ በየደረጃው ተፈፃሚ ስለማድረጉ የሚያመላክት በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ቡድኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ አልቀረበም፡፡
- የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን በተመለከተ ለእናቶችና ለህፃናት የሚደረገው ልዩ ድጋፍ/አልሚ ምግብ/ በቂ እንዳልሆነና የእናቶችና የህፃናት ሰውነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ ከዞን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ጽ/ቤት የተገኙ መረጃዎች ያመላከቱ መሆኑንና የህፃናት ምግብ (የወተትና አልሚ ምግብ) ከሚጠየቀው የምግብ ሬሽን ጎን ለጎን ተሟልቶ አለመቅረቡን ኮሚሽኑ በመጋቢት 2010 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የተለያዩ ዞኖችና ከተሞች ባደረገው የመስክ ጥናት ላይ ታውቋል፡፡
- በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑ የስርጭት ሂደቱ ለአቅመ ደካሞች (አረጋውያን)፣ ነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች፣ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ለሚገኙ ትኩረት አድርጎ እንደሚከናወንና እርዳታ በሚሰጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በራሳቸው የመስክ ክትትል በማድረግ፣ በመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ በክልል ደረጃ እስከ ዝቅተኛው አስፈጻሚ ባለው የመንግስት መዋቅር እንዲሁም ከፌዴራል

በሚንቀሳቀስ የቴክኒክ ቡድን አማካኝነት ክትትል እንደሚደረግ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ ቢሆንም የኦዲት ቡደኑ ከክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ-መጠይቆች ከኮሚሽኑ ኃላፊዎች አስተያየት በተለየ መልኩ እንደሚከተለው ገልፀዋል፣

- የሀረሪ ክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ ዕቅድ በማቀድ እየሰራ አለመሆኑን እና የምላሽ ስራዎች እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርግ አለመሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልል እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ያደረገ ምላሽ ለመስጠት በእቅድ ተይዞ የሚሰራ ቢሆንም በተግባር በተለይም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ከማካተትና መረጃን ከመሰብሰብ አንፃር ችግሮች መኖራቸውን ከተደራሽነት አንፃርም ክፍተቶች እንዳሉና የምላሽ ስራዎች የመዘግየት ችግር እንዳለ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በተሟላ መልኩ ፓኬጆች ክልሉ ጋር የማይደርሱ መሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ስራ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ የሚሰጥ እንዲሆን እየተሰራ ቢሆንም ሙሉ ነው ለማለት እንደማያስችልና በአቅም ውስንነት ምክንያት በተገቢው ሁኔታ ተደራሽ የማድረግ ችግሮች መኖራቸውን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

❖ **ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራርን በተመለከተ፡-**

204. ኮሚሽኑ በክልሎች መካከል በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ እና የክልል የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-
- በሀረሪ ክልል የተፈናቀሉ ሰዎችን ከመቀበል ውጪ ችግሮችን ከሌሎች ክልሎች ጋር በጋራ ለመፍታት እንደ አደጋ መከላከል የተሰራበት ሁኔታ አለመኖሩንና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በሶማሌ ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር በስብሰባዎች ከመገናኘት ውጪ በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎና ተባብሮ የምላሽ ስራን ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑንና ከክልሎች ጋር በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች የመደጋገፍ እና የልምድ ልውውጥ አስፈላጊ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/ብ/ እና ህዝቦች ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር አደጋን ተባብሮ ምላሽ ለመስጠት ጅምሮች ቢኖሩም የተጠናከረ አለመሆኑን ስራው እስከ ህብረተሰቡ ድረስ ወርዶ እንዲሰራ ማድረግ እንደሚገባ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በተለይ የጎርፍ ስጋትን አስመልክቶ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ቢኖርም የተጠናከረ ባለመሆኑ ምክንያት የሶማሌ ክልል ተፈናቃዮችን በለሊት በአይሱዙ እየጫኑ አራግፈው መመለሳቸውን ማለትም ያለምንም መረጃ የተፈናቀሉትን ተረከቡን እንኳን ሳይባል ሜዳ ላይ ጥለዋቸው መሂዳቸውን የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የአደጋ ምላሽ ስራ ሰብአዊነትን ተከትሎ የሚሰራ እንጂ ድንበርን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ባለመሆኑ እንደ ክልል ተባብሮ እየተሰራ መሆኑን ነገር ግን ባለው የፖለቲካ ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ እርዳታዎችን ለማድረስ ችግሮች የሚፈጠሩ መሆኑ እና ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ አሰራር የሌለው መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

❖ **ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-**

205. ኮሚሽኑ የክምችትና የስርጭት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየደረጃው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶከመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኮሚሽኑ እና የክልል የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-
- ለእለት እርዳታ እንዲውል ለክልሎች የሚላክ ምግብ በአንዳንድ ቦታዎች በወቅቱ ያለመከፋፈል ችግር መኖሩን ከኮሚሽኑ የ2009 ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- በሶማሌ ክልል እርዳታዎች በወቅቱ የማይደርሱ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የአደጋ ምላሽ ትራንስፖርተሮች ያለ አቅማቸው ጨረታ በማሸነፍ በተፈለገው ጊዜ የማይደርስበት ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሚገኝና ችግሮችን ለመፍታት ለኮሚሽኑ በደብዳቤ አሳውቀው የማያውቁ ቢሆንም ከትራንስፖርተሮች ጋር በመነጋገር የሚፈታበት አግባብ መኖሩን የክልሉ አደጋ ስጋት የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የጌዴኦ ዞን የዕርዳታ ቁሳቁሶችን በተቀመጠው መጠን መሰረት ቆጥሮ የመረከብ ሁኔታ ደካማ መሆኑንና በ2010 ዓ.ም ለዞኑ የመጣው በቆሎ ከ100 ኪ.ግ የጎደለና ለተረጂዎች ለማሰራጨት ልኬቱ እኩልና በተቀመጠው ልክ ገቢ ያልተደረገ መሆኑንና እንዲሁም የቁሳቁስ አቅርቦት ችግር ከፍተኛ መሆኑ፤የምግብ አቅርቦቶች ወቅቱን/በየወሩ ጠብቆ እየቀረቡ አለመሆኑንና አልሚ ምግብ፤ጥራጥሬና ዘይት አሚልቶ እየተላከ እንዳልሆነ የዞኑ የአደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢና ወጪ የሚደረጉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን መጠን ለማወቅ የሚያስችል የምድር ሚዛን የማይጠቀም መሆኑና

ምዝገባ ብቻ በማከናወን ከኮሚሽኑ በሚመጡ ማዘዣዎች መሰረት ወጪ በማድረግ እየተሰራ መሆኑን እንዲሁም አስፈላጊውን የጨረታ ሰነድ ላሟሉ አጓጓዥ ድርጅቶች ቁሳቁሶችን ቆጥሮ በማስረከብ ወደ ክልሎች እንዲጫን የሚያደርግ ቢሆንም በአጓጓዥ ሹፌሮችና ክልል ላይ ካሉ የመጋዘን ተቆጣጠሪዎች(store keeper) መካከል ያለውን አሰራር ቁጥጥር የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩንና ክልሎች ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው የቅርንጫፉ የስራ ኃለፊዎች ገልፀዋል፡፡

- እንዲሁም ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮሚሽኑ በስርጭትና ክምችት መመሪያ መሰረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን በግንባር በመሄድ ክትትል እንደማያደርግና በስልክ ግንኙነት ብቻ የኦፕሬሽን ስራዎችን እንዲሰሩ እንደሚያደርግና ክትትል ባለማድረጉ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ክፍተት ለይቶ እልባት ለመስጠት እንዳልተቻለና ለስርጭትና ክምችት ስራው አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ግዥ ባለመፈፀሙ የጭነት ስራ የሚሰሩ የጉልበት ሰራተኞች የሚጠጡትና የሚታጠቡበት ውሃ በማጣታቸው ስራ የሚያቆሙበት ሁኔታ በመኖሩ በስርጭቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ የቅርንጫፉ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- ከ7ኛ ዙር ጀምሮ ለኦሮሚያና ለአማራ ክልል ከተላከው ውስጥ 7749.8 ሜ/ቶን ኦሮሚያ 6826 ሜ/ቶን አማራ ክልል በድምሩ 14575.8 ደርሶ ለተረጂው እንዳልተከፋፈለ ክልሎቹ ሪፖርት ሲያቀርቡ 617.3 ሜ/ቶን ደግሞ ኦሮሚያ ክልል እንደጠፋ ሪፖርት የቀረበ መሆኑን በኮሚሽኑ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ዳይሬክቶሬት የ2009 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡

- በደቡብ ብ/በ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት አስቸኳይ ጊዜ የምግብ አቅርቦት እና ስርጭት ሁኔታን በተመለከተ በሲዳማ ዞን ከጥር እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ የዕለት ዕርዳታ እንዲረዱ ለተፈቀዳለቸው በ11 ወረዳዎች ለሚገኙ 150,735 ተረጂዎች እስካሁን ድረስ እርዳታ ባለመቅረቡ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች በችግር ላይ መሆናቸውን ከሰኔ 19-25/2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ከክልሉ ለኮሚሽኑ ከተላከ ሪፖርት ለመመልከት ተችሏል፡፡

- በእርዳታ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ የተላከውን የእለት ዕርዳታ ድጋፍ በአማራ ክልል አንዳንድ ወረዳዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ከሰኔ 19-25/2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ተሰራጭቶ ያላለቀ መሆኑን ከክልሉ ለኮሚሽኑ ከተላከ ሪፖርት ለመመለከት ተችሏል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የኮሞዲቲ ማኔጅመንት መመሪያ (guideline) ከመጠቀም ውጭ ከኮሚሽኑ የወረደ የስርጭትና የክምችት መመሪያ እንደሌለ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

❖ **ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-**

206. ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

207. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት ኮሚሽኑ ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ እንዳላደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዋናዋና ጉዳዮች መካከል፡- ቅፅበታዊ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ወዲያውኑ እርዳታውን በማቅረብ ጊዜያዊ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ማዕከል እንዲቋቋም ማድረግ፤ ከሌሎች የስራ ክፍሎችና አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤ የቅደሚያ ማስጠንቀቂያና አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማዕከል በአስፈላጊ የኮምንኬሽን መሳሪያዎች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች መደራጀቱን በመከታተል ማረጋገጥ እንዲሁም ቅፅበታዊ አደጋዎች ሲከሰቱ በሚመለከታቸው መሪ ሴክተር መስራቤቶችን እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ ማስተባበር እንዳለበት የሚሉት የሚጠቀሱ ሲሆን በጉዳዩ ዙሪያ የሚከተሉት ዋናዋና ጉዳዮች ታይተዋል፤

- የኦሮሚያ፣ የደቡብብ/ብ/ህ እና የሶማሌ ክልል የአደጋ ስጋት እና መልሶ ማቋቋም ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ እንዳልተደረገ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም በሀረሪ ክልል ቅፅበታዊ አደጋን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት አሰራር እንደሌለ የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቅጽበታዊ አደጋ ሲያጋጥም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የተዘረጋ አሰራር አለመኖሩን አልፎ አልፎ የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ጽ/ቤቱ ብቻውን እየሰራ መሆኑን የአሰተዳደሩ የአደጋ ስጋት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል አለመኖሩን የቅርንጫፉ የስራ ኃፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
- ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በኮሚሽኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ ለእርዳታ አቅርቦት ስራ በአንዳንድ አካባቢዎች በመንገድ መበላሸት ምክንያት እርዳታው በወቅቱ እንዳይደርስ እንቅፋት መሆኑን ከኮሚሽኑ የ2009 ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ መቻሉ እንዲሁም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በመበራከታቸው ችግር ወደ ተከሰተባቸው ቦታዎች ለመድረስ የመንገድ ችግር በመኖሩ በፈጣን ምላሽ አሰጣጥ ላይ ችግር ማስከተሉን ከኮሚሽኑ የ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ አመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል፡፡
- የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ዳይሬክቶሬት በኩል ቅፅበታዊ ለሆኑ አደጋዎች የሚሰጠው ምላሽ ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ላይ አዲስ የአሰራር ሥረዓት በመዘርጋቱና አሰራሩ የኢንተርኔት አገልግሎት ስለሚያስፈልገውና የክልሎችን ጥያቄ በአፋጣኝ ለመመለስ ውስንነት የሚታይበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

❖ **ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር የዘረጋና ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን በተመለከተ፡-**

208. ኮሚሽኑ በአደጋ የተጎዱ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እንስሳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የዶክመንት ክለሳወች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ መሰረት፡-

- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር በመሆን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር (DRM Tecnical working Group) እና የግብርና ግብረ ኃይል (Agricultural Task Force) አማካይነት በሚደረገው ውይይት/ስብሰባ በማስተባበርና በመሳተፍ ድርቅ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች የተጎዱ እንስሳቶችን ከጉዳት ለመታደግ በተለይም የእንሰሳት መኖ እና መድኃኒት አቅርቦትን በሚመለከት እየሰራ እንደሚገኝ የሥራ ኃላፊዎች የህለፁ ቢሆንም፤

- በሶማሌ ክልል ለእንስሳቶች የመኖና የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ቢደረግም በቂ አለመሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

- በኦሮሚያ ክልል በዋናነት በባሌና ጉጂ አርብቶ አደሮች አካባቢ በእንስሳቶች ላይ ጉዳት የሚደርስ በመሆኑ የተጎዱ እንስሳቶችን በሙሉ ለማዳን ኮሚሽኑ በችግሩ ስፋት ልክ ተደራሽ ለማድረግ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ በተለይ በ2008 ዓ.ም ቦረና ላይ ከፍተኛ ጉዳት በእንስሳቶች ላይ በመድረሱ ካሉት አራት ሚሊዮን እንስሳቶች 50%ቱ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን የክልሉ አደጋ ስጋት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

- ለእንስሳት የሚቀርብ መኖ በኮሚሽኑ ደረጃ ስታንዳርድ ወጥቶለት እየተሰራ አለመሆኑን፣ ኮሚሽኑም የተቻለውን ያህል ድጋፍ ብቻ ሲያደረግ መቆየቱን የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡

- በኦዲት ቡድኑ በእንስሳቶች ዙሪያ ከ2008-2010 ዓ.ም ስለደረሰው ጉዳትና ስለተደረገው ድጋፍ የሚገልፅ በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ኦድቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

21 በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥ እና አፈፃፀም በተመለከተ

209. የለሁሉ አገልግሎት ዋና መነሻው የአንድ መስኮት የተቀናጀ የክፍያ አገልግሎት ስርአት መዘርጋት ሲሆን ለመነሻነትም ሶስት ዋና ዋና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ማለትም ውሃ፣ መብራት እና ስልክ በተለያየ ቦታ እና ጊዜ የሚሰጡትን አገልግሎት ወደ አንድ መስኮት በማምጣት የተቀላጠፈ፣ ምቹ፣ ጊዜ ቆጣቢ እና ተደራሽ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ ይህን አገልግሎት በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ የጋራ ትብብር በለሁሉ ማእከላት አሰራር ለማበልጸግ /Build/፣ ለማስተዳደር /operate/ በመጨረሻም ለባለቤቱ ለማስረከብ /transfer/ የተደረገ የስምምነት ውል ነው፡፡ ይህ አገልግሎት ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ታይተውበታል፡-

210. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን በመንግስት እና በግል ሽርክና (Public Private partnership PPP) ግዥ ለመፈፀም ያስፈለገበትን አግባብ ማለትም (በመንግስት ሊሰጥ ስላለመቻሉ፣ በግል ቢሰጥ ስለሚያስገኘው ጥቅም ወዘተ) በጥናት መሰረት ስለመወሰኑ፤ እንዲሁም የለሁሉ ኮንትራትን ለግል ሴክተር ለጨረታ ከማቅረቡ በፊት በመንግስት ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት እንደማይቻል የተረጋገጠ ስለመሆኑ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፡፡

- እንዲሁም ለግል ሴክተር ከመቅረቡ በፊት በመንግስት መ/ቤቶች ማለትም (እንደ ባንክ፣ ፖስታ ቤት ወዘተ) አገልግሎቱን መስጠት እንዲችሉ ባለመደረጉ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡
- የመንግስት እና የግል ሽርክና በባህሪው ከመንግስትና በግል ባለሀብቱ መካከል የሚደረግ ሽርክና በመሆኑ አገልግሎቱ በብቸኝነት (Monopoly) በግል ሴክተሩ ብቻ እንዲያዝ ከማድረጉም በላይ የለሁሉ አገልግሎት (service based) በመሆኑ ሌሎች የክፍያ አማራጮች ለመጠቀምና አገልግሎቱን ማሳደግ ያልተቻለ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ለለሁሉ ሴንተር ተብለው በተከፈቱ 34 ማእከሎች ብቻ መውሰኑ የተፈለገውን አገልግሎት ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ነገር ግን ይህ አገልግሎት

ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጥ ቢሆን በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ባሉ 422 ቅርንጫፎች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት የሚሰጥባቸው 180 ቢሮዎች አገልግሎቱን በመስጠት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከመሆንም አልፎ የአገር ሀብት (resource) በአንድነት ለተለያዩ አገልግሎቶች መጠቀም ያልተቻለ መሆኑ፣

- በተጨማሪም የለሁሉ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የክፍያ ማእከላት ኪራይ በተገልጋይ ተቋማት(utilities) ስለሚሸፈን ተጨማሪ ወጪ እያስከተለባቸው መሆኑ፣ታውቋል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ ሊኖር ስለሚችለው የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ፣ እንዲሁም የአገልግሎቱ ባለቤት የሆኑት የተገልጋይ ተቋማት(utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) አለመስራቱ ታውቋል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል ከግዥ ሰነዱ (Request for proposal (RFP)) መሰረት ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡
- በኤክስፕረሽን ኦፍ ኢንተረስት ለተመረጡ ድርጅቶች በተላከው ሌተር ኦፍ ኢንቫይቴሽን RFP ላይ ይህ ኢንቫይቴሽን አይተላለፍም ተብሎ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በኮንትራት ሰነዱ አንቀጽ 24 ላይ ውሉ ለሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ እንዲተላለፍ በማድረግ ጨረታውን ያሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኮንትራት አሳይመንቱን ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር እንዲተላለፍ የተደረገ መሆኑ፣
- ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ ምንም አይነት ባለቤትነት ድርሻ የሌለው እና ለድርጅቱም ሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ አለመሆኑ፣
- በተጨማሪም ክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር የኮንትራት አሳይመንቱን ሲቀበል ጨረታው የሚጠይቀውን የ 5 ዓመት የስራ ልምድ እና

ቢ.ያንስ 4 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የሰራ የሚሉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሳለ ኮንትራቱ ሙሉ በሙሉ ተላልፎ እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል፡፡

211. በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 45 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመንግስት መ/ቤት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ እንደማይቻል ተገልፆል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (unified billing system (UBS 1)) አሸናፊው ድርጅት ከግሎባል ኮምፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ለUBS 1 ያቀረበው ዋጋ በአንድ ግብይት (ትራንዛክሽን) ብር 1.43 (አንድ ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም) ቢሆንም በኮንትራት ሰነዱ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ድርድር በማድረግ የተዋዋለው ዋጋ በብር 2.56 (ሁለት ብር ከአምሳ ስድስት ሳንቲም) መሆኑ ታውቋል፡፡

- በተጨማሪም በውሉ መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) በብር 1.13 (አንድ ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም) እንዲጨምር በማድረግ በአጠቃላይ ለሁሉ ኮንትራት ከተጀመረበት የካቲት 2005 ዓ.ም እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ብር 70,173,000 (ሰባ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር) ተጨማሪ የኮሚሽን ክፍያ አስከትሏል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ግዢ ለ[(unified billing system (UBS 1 እና UBS 2)] ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የጨረታ መነሻ ዋጋ (Estimated price) ሳይቀመጥ መከናወኑ እና በዚሁ ጨረታ ላይ ለፋይናንሻል ውድድር አንድ ተጫራች ብቻ ያለፈ ሲሆን ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ጨረታውን እንዲያሸንፍ መደረጉ ታውቋል፡፡

212. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚሰበስቡትን የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀሙ ሲገመገም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

- የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት የካቲት ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 2010 ዓ.ም (ከ5 ዓመት በላይ) እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,472,048,746.90 (ብር ስድስት ቢሊዮን አራት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አርባ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አርባ ስድስት ከዘጠና ሳንቲም) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,198,033,890.00 (ብር ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሚሊዮን ሰላሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ብር) (49.4%) መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአዲስ አበባ በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከጥር 2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,318,693,418.68 (ብር ስድስት ቢሊዮን ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ሺ አራት መቶ አስራ ስምንት ከ ስልሳ ስምንት ሳንቲም) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,879,997,662.74 (ሶስት ቢሊዮን ስምንት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ሁለት ከሰባ አራት ሳንቲም) (61%) መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቀሌ እና ባህርዳር በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 488,227,105.02 (ብር አራት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ አምስት ከሁለት ሳንቲም) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 246,537,910.52 (ብር ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አስር ከአምሳ ሁለት ሳንቲም) (50.4%) መሆኑን ታውቋል፡፡

213. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ስለመዘርጋቱ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ታይተዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በUBS 1&2 ውል አባሪ 8 ገጽ 2 መሰረት፡-
  - security Deposit እንደ ማስተማማኛ እንዲቀመጥ ይህም በየጊዜው ዝቅተኛ ባላንስ መጠኑ እንዳይጎድል ማሻሻያ የሚደረግበት ለእያንዳንዱ UBS 1&2 ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) እንዲሆን እንዲሁም ቅጣቶች በሚኖርበት ጊዜ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወሩ ከተቀመጠው ገንዘብ እንደሚቀንስ የተገለፀ ቢሆንም በውሉ መሰረት ተግባራዊ አለመሆኑ፤
  - ለUBS 1 የስራ አፈጻጸም ዋስትና(Performance guarantee in operation period) ብር 1,800,000 (ብር አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ) ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ከትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም አለመደረጉ፤
  - ለUBS 2 የስራ ማስፈፀሚያ ዋስትና (Performance guarantee in operation period) ብር 2,200,000 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር) ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ክትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም አለመደረጉ ታውቋል፡፡
  - ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት በገለልተኛ አካል ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት ማረጋገጥ ቢኖርበትም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡
  - ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ታይቷል፡-
  - ኢትዮ ቴሌኮም ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች፣ ኢንባሲዎች እና ሌሎች ትልልቅ ተቋማትን የሚያስከፍለው በቴሌ ሾፕ መሆኑ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ኢንዱስትሪዎችን፣ ትላልቅ ተቋማትን እና የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎች አገልግሎት በራሱ ደንበኞች አገልግሎት እንደሚያስከፍል መሆኑ፤

- እንዲሁም በUBS2 ውል መሰረት አዋሳ፣ አዳማ፣ መቀሌ እና በባህርዳር ከተሞች (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት ቢዋዋልም፣ አገልግሎቱ በአዋሳ እና አዳማ ከተሞች አለመጀመሩ፣ በተጨማሪም በመቐለ እና በባህርዳር ከተሞች የውሃ ክፍያ የአገልግሎት በለሁሉ የክፍያ ማዕከል የማይከፈል መሆኑ የታቀደው የአንድ መስኮት አገልግሎት አለመተግበሩ ታውቋል፡፡

22 በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በኮሚሽኑ ለኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ/ የሚያገለግሉ

❖ **ደረጃዎች መውጣታቸውንና መተግበራቸውን በተመለከተ፤**

214. ኮሚሽኑ አግባባ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ለኢንዱስትሪ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝ እና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎችን ሊያወጣ እና ስለተግባራዊነታቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

215. የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ወይም ከፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ (Sedimentation tank) የሚወጣ የፍሳሽ ቅሪት (Sludge Cake) አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከንና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎች አለመውጣታቸው፣

216. በዚህም ምክንያት በናሙና የታዩ ፋብሪካዎች ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሳይሆኑ እና የሚያስከትሉት ጉዳት ሳያረጋግጡ በተለያየ መንገድ ዝቃጩን እያስወገዱ እና ለተለያየ ጥቅም እያዋሉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ለቦሎኬት መስሪያ(አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ)፣
- ለአትክልት ማዳበሪያነት (ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ) ፣
- በግቢያቸው ውስጥ የሚያቃጥሉ (ጸሐይ ቀለም ፋብሪካ)፣
- ወደ ወንዝ በመድፋት (ሆዶቹ፣ ሆራ፣ ዚንግዛንግ፣ ሞጆና ኮልባ ቆዳ ፋብሪካዎች)፣
- በግቢ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር (ዲ.ኤክስ ቆዳ ፋብሪካ እና ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ)፣

- በከተማ ቆሻሻ መድፊያ የሚጥሉ (ሀበሻ እና በባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች ባህርዳር እና ኢስት አፍሪካ፣ ፍሬንድ ሺፕ፣ ጆርጅ ሹ ቆዳ ፋብሪካዎች ሞጆ) ሲሆን

217. በባህርዳር ከተማ እና በሞጆ ከተማ መርዛማ ለሆኑ ቆሻሻዎች ማስወገጃ የተለየ ቦታ የሌለ፣ የደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉበት ቦታ አጥር የሌለውና ደረጃውን ያልጠበቀ ቢሆንም ምንም አይነት ማጣራት ሳይደረግለት (ሳይታከም) ወደ ከተሞቹ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ የሚጥሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ከተማ ከተለያዩ ፋብሪካዎች የሚወጣው ዝቃጭች/ቆሻሻ ምንም አይነት የማጣራት ሂደት/ሥራ/ ሳይደረግለት የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ማለትም በቆሼ/በረጲ እያስወገዱ መሆኑ፤ እንዲሁም የተጠቀሰው ቦታ ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ደረጃ እስከሚወጣለት ፋብሪካዎቹ በግቢያቸው እንዲይዙ የከተማው አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በ2010 ዓ.ም. ለከተማ መስተዳድሩ በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም ድርጊቱ ስለመቆሙና ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

218. በተጨማሪም በሰበታ ከተማ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ፋብሪካዎች ወደ ከተማዋ ቆሻሻ መድፊያ እንዳይጥሉ እና በግቢያቸው ውስጥ እንዲይዙ የተደረገ ቢሆንም የተፈቀደው ቆሻሻ መድፊያ በአጥር ያልተከለለ፣ በወንዝ ዳር ያለ እና በቀላሉ በጎርፍ እየታጠበና እየተገፋ ወደ ወንዙ በመግባት ለወንዙ ብክለት የራሱ ድርሻ መኖሩ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ወደ ውሃ አካላት እና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችን ደረጃ መውጣቱን በተመለከተ፤**

219. ኮሚሽኑ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾች ደረጃዎችን ሊያወጣ ይገባል፡፡

220. ከፋብሪካዎች የሚወጡ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችን በተመለከተ አገር አቀፍ ደረጃ የወጣ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 42 ፋብሪካዎች ውስጥ 76 በመቶ ደረጃውን

ያልጠበቀ/የተበከለ ውሃ/ ወደ ፍሳሽ መቀበያ እና ወደ ወንዞች የሚለቁ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

- በሞጆ በናሙና ከታዩት 14 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ 10 ፋብሪካዎች የመጀመሪያ ደረጃ የፍሳሽ ማከምያ መሳሪያዎች ብቻ ያላቸው ሲሆን ይህ መሳሪያ በፍሳሽ ቆሻሻዎቹ ውስጥ ያለውን በአንጻራዊ መልኩ ግዙፍ ጠጣር ነገሮችን እና ፍሳሹን ለመለያት ብቻ የሚገለግል መሳሪያ በመሆኑ በተናጠል የዚህ መሳሪያ በአንድ የቆዳ ፋብሪካ መኖር በአካባቢ ደረጃ የተቀመጡትን ከማምረቻ ተቋማት የሚለቀቁት በካይ ነገሮች ፓራሜትሮች ለማከም የማያስችል በመሆኑ እና በተቀሩት አራቱ (ዲኤክስ፣ ፊሪዳ፣ ጆርጅ ሹ፣ ዩናይትድ ቫዚን) ቆዳ ፋብሪካዎች 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ያላቸው ቢሆንም 3ኛ የፍሳሽ ማከሚያ ባለመኖራቸው ምክንያት የብክለት መጠናቸው ቢለያይም ሁሉም ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ ወደ ሞጆ ወንዝ የሚለቁ በመሆኑ በሞጆ ወንዝ ላይ ከፍተኛ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣
- በሰበታ ከተማ በናሙና ከታዩት 7 ፋብሪካዎች አራቱ (ባለዛፍ እና ብሔራዊ አረቄ ፋብሪካ፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) ወደ ሀጠበላ ወንዝ እና ወደ ፍሳሽ መስመር የተበከለ ውሃ የሚለቁ መሆናቸው፣ የተቀሩት ሦስት ፋብሪካዎችም በአሁኑ ወቅት ሴዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በብልሽት ምክንያት፣ ሀፋዳ እና ብሉ ናይል ቆዳ ፋብሪካዎች በአካባቢ ብክለት ምክንያት እስከ ብሉ ኘሪንት ያለው ምርት እንዲቆም (ካቆሙ ዘጠኝ ወር ሆኗቸዋል) የተደረገ ቢሆንም ላለፉት አመታት ወደ ሀጠበላ ወንዝ ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ በመልቀቅ ሲበክሉ መቆየታቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ከታዩት 7 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ ስድስቱ የቆዳ ፋብሪካዎች 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማከሚያ ብቻ ያላቸው በመሆኑና ይርጋለም ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ ምክንያት የአለም አቀፍ ደረጃውን ያልጠበቀ(ከ6 እስከ 9 ያሉ ፓራሜትሮች ላይ ከተፈቀደው የልቀት ደረጃ በላይ) ላይኛውና ታችኛው የአቃቂ ገባር ወንዞች የሚለቁ ሲሆን በተጨማሪም በአዲስ አበባ 90 በመቶ የሚሆኑ ፋብሪካዎች በአቃቂ ክፍለ ከተማ

ከትንሹ አቃቂ ወንዝ 50 ሜትር አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸው አቃቂ ወንዝ በከፍተኛ ሁኔታ እየበከሉ መሆኑ፣ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ያሉ ትልልቅ ፋብሪካዎች (ሞሃ ለስላሳ ፋብሪካ፣ ብሔራዊ አልኮል ፋብሪካ፣ አዋሽ ወይን ጠጅ አክሲዮን ማህበር፣ ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅትም) ያለምንም የፍሳሽ ማጣሪያ ከተፈቀደው የልቀት ደረጃ በላይ የሚለቁ መሆናቸው፣

- በኮምቦልቻ ከተማ እና በቱሁለዶሬ ወረዳ (ሐይቅ)ከታዩት አምስት ፋብሪካዎች ሦስቱ (ሁሃክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በከተማውና በወራዳው ያለው ቅርንጫፍ) 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ብቻ ያላቸው በመሆኑ እና ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሦስት ሼዶች ላይ ሙሉ ለሙሉ ሥራ የጀመረ ቢሆንም የተገነባው ማጣሪያ ሥራውን ባለመጀመሩ እና ደሴ ቄራ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ ሁሉም ደረጃውን ያልጠበቀ/ያልተጣራ ፍሳሽ አብዛኞቹ ወደ ቦርከና፣ ኢዮሌ እና የመሳሰሉት ወንዞች የሚለቁ መሆናቸው፣

- በተመሳሳይ ባህርዳር ከተማ በናሙና ከታዩት ሦስት ፋብሪካዎች ሁለቱ ማለትም አማራ ፓይፕ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ፣ ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ የመጀመሪያ ደረጃ ብቻ በመኖሩ ያልተጣራ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ውጭ በመልቀቅ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣

- በተጨማሪም በናሙና ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ ከጥቂት ፋብሪካዎች (ኢትዮ ቆዳ(ሎሚ)፣ ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ(ኮምቦልቻ)፣ ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ (በህርዳር)) በስተቀር በተቀሩት ፋብሪካዎች ከኢንዱስትሪ የሚወጣውን ፍሳሽ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት ቤተ-ሙከራ የሌላቸው እና ወደ ወንዝ ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር የሚለቀቁ ውሃዎች ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ ቀጣይነት ባለው መልኩ በቤተ-ሙከራ የማይስመረምሩ መሆናቸው የኦዲት ቡድኑ በፋብሪካዎቹ በመገኘትና በአካል በማየት፣ በናሙና ለተመረጡ የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ከላይ የታዩት አብዛኛው ወንዞች የአዋሽ ገባር ወንዞች ሲሆኑ በ2009 ዓ.ም. ከአፋር፣ ከአማራና፣ ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በአስር ዋና ዋና የአዋሽ ገባር ወንዞች ላይ ማለትም ቦርከና፣ ሚሌ፣ ከሰም፣ ሞጆ፣ ወሬርሶ፣ አቃቂ፣ ቀበና፣ ሎሜ፣ ሀጠበላና ጊንጪ በኮሚሽኑ በተደረገ የብክለት ክትትል ሪፖርት ሀጠበላ (Dissolved Oxygen 2.8 ሚ.ሊ. ግራም/ሊትር፣ Total Dissolves solids=1300 ሚ.ሊ. ግራም/ሊትር) ከሚጠበቀው ደረጃ በታች መሆናቸዉ አንድ ተፈጥሮአዊ ወንዝ ህይወትን ማኖር የሚያስችል የሚሟ የኦክስጅን መጠን በአማካኝ ቢያንስ ከ6.00 ሚ.ሊ. ግራም/ሊትር ማነስ እንደሌለበት Guideline for Surface water quality standard ላይ የተገለጸ እና ዉሃዉ የአካባቢዉን ማህበረሰብ የእንስሳት ሀብት ልማት ስራ እየጎዳ መሆኑ፣
- ቀበና (Dissolved Oxygen=3.5ሚ.ሊ.ግ/ሊ፣ Total Dissolves solids S=375ሚ.ሊ.ግ/ሊ)፤ አቃቂ (Dissolved Oxygen=3.9 ሚ.ሊ.ግ/ሊ፣ Total Dissolves solids=518 ሚ.ሊ.ግ/ሊ)ና ሞጆ(DO=2.5ሚ.ሊ.ግ/ሊ፣ TDS=317ሚ.ሊ.ግ/ሊ) ና መሰል መስፈርቶች ከደረጃ በላይ መሆን በሶስቱ ወንዞች ውስጥ እንደ ዓሳ ላሉ ዉሃ ውስጥ ለሚኖሩ እንስሳት/Aquatic animals/ ለመኖር ሊያዳግታቸው እንደሚችል፣ በተጨማሪ ከወንዞች የተወሰዱት የውሃ ናሙናዎች በቤተ ሙከራ ፍተሻ የሞጆ ወንዝ የከባድ ብረት አሰተኔ/Heavy metals/ ይዘት ካድሚየም (0.034ሚ.ሊ.ግ/ሊ)፣ ክሮሚየም (0.33 ሚ.ሊ.ግ/ሊ)፣ እርሳስ(Lead)[0.26ሚ.ሊ.ግ/ሊ) እንዲሁም የአቃቂ ወንዝ ከባድ ብረት አስተኔ(Heavy metals) ካድሚየም (0.04 mg/lit)፣ ክሮሚየም (0.52ሚ.ሊ.ግ/ሊ)፣ እርሳስ(Lead)[0.3ሚ.ሊ.ግ/ሊ) ከደረጃው በላይ መሆኑ፣
- እንዲሁም በ2010 በአስሩም ወንዞች ላይ በቤተ-ሙከራ ተመርምሮ ማንጋኒዝ 0.3 ሚ.ሊ.ግ/ሊ፣ ሰልፌት 200ሚ.ሊ.ግ/ሊ እና ክሎራይድ 250 ሚ.ሊ.ግ/ሊ በሁሉም ወንዞች ላይ ከደረጃ በላይ ሆነው መገኘታቸውን ከመረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም ወንዞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊበክል የሚችል ከፍተኛ ሽታ እንዳላቸው የኦዲት ቡድኑ በቦርከናና በሞጆ ወንዝ በአካል በመገኘት ለመረዳት ተችሏል፡፡

❖ **ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረባቸውንና ሰነዱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤**

221. ከኢንዱስትሪዎች ወይም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮች ብክለት እንዳያስከትሉ ፋብሪካዎች አስቀድመው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

222. እንዲሁም ለማምረቻ ተቋማት ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሊሆን ይገባል፡፡

- ሆኖም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መሰረት ማንኛውም ፍቃድ (ኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ) ሰጪ መሥሪያ ቤት ፍቃድ ከመሥጠቱ በፊት ከኮሚሽኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርብ መደረጉን አስመልክቶ በተደረገው ማጣራት፡-

- በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ኢንቨስትመን ቢሮ እና በ ሞጆ፣ በአዳማ፣ በባህርዳር፣ በደሴ፣ በኮምልቻ ከተሞች እና ደቡብ ወሎ ዞን ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲወስዱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣

- በተመሳሳይ በናሙና በታዩት በሁሉም ንግድ/ሥራ ፍቃድ ሰጪ ተቋማት(ንግድ ሚኒስቴር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ፣ ባህርዳርና አዲስ አበባ የንግድ ቢሮዎች) ለባለሀብቶች የንግድ ፍቃድ ወይም የሥራ የንግድ ፍቃድ ሲሰጡ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የይሁንታ ፍቃድ/የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣

- በተጨማሪም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 159/2001 መሰረት ለማምረቻ ተቋማት የሥራ ፈቃድ ሲሰጡ ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ

አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ የማይሰሩ ወይም እንዲረጋገጥ የማያደርጉ መሆናቸውን ከየመ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ በተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በናሙና በታዩት በሁሉም ክልሎች፣ ከተሞች፣ ዞንና ወረዳዎች የመንግሥት ፕሮጀክቶች ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ (አረርቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሁዛጂያን ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ደብረብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የአዳማ ኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ አራት (4) የተቀናጀ የአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (ቡልቡላ፣ ይርጋለም፣ ቡሬ እና ባህርዳር) የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሳያሰሩ ወደ ሥራ የገቡ መሆናቸው እንዲሁም ባለሀብቶች ከመንግስት ባንኮች የባንክ ብድር ሲፈልጉ ስለሚጠየቁ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ የሚያሰሩ መሆናቸውንና በናሙና በታዩት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች(ከኦሮሚያ በስተቀር) ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሌላ መልኩ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ኖሯቸው ግንዛቤው ባለመኖሩ ምክንያት ሰነዱን ማዘጋጀት ብቻ እንደ ትልቅ ግብ ስለሚቆጥሩት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ/የአካባቢ አያያዝ እቅድ ያላቸው በናሙና ከታዩት አብዛኛው ፋብሪካዎች (ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፣ ዚንግዛንግና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ፣ ኢትዮ ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ገላን ቆዳ ፋብሪካ፣ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፣ ፈሪዳ ቆዳ ፋብሪካ፣ ባለዛፍ አረቄ ፋብሪካ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ፣ ሁዛክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አባይ ጣና ምግብ ኮምፕሌክስ) ሰነዱን በፋብሪካቸው የማይገኝና ተግባራዊ የማያደርጉ ሲሆን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነዱን ወቅቱን ጠብቀው የማያሳድሱ ፋብሪካዎችም (ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ፣ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ፣ የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣) መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ያላሰሩ ከአዋጁ በፊት (የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 159/2001) የተቋቋሙ ፋብሪካዎች ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ የአካባቢ አያያዝ እቅድ አሰርተው ወደ ተግባር እንዲገቡ የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው ቢሆንም አብዛኞቹ እቅዱን ያላሰሩ

መሆናቸው፣ ለማሳያ ያህል፣ በኦሮሚያ በ2010 ዓ.ም. በ11 ከተሞች በተደረገ ቆጠራ 2150 ፋብሪካዎች ውስጥ 365ቱ/20%/ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም የአካባቢ አያያዝ እቅድ ሲኖራቸው የተቀሩት 1780/80%/ የሌላቸው መሆኑንና በአማራ ክልል በደብረታቦር በጎንደርና በቡሬ 211 ፋብሪካዎች ውስጥ 43ቱ/20%/ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ/የአካባቢ አያያዝ እቅድ ያላቸው ሲሆን 168/80%/ቱ የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ከታዩ 8 ፋብሪካዎች 6ቱ (በድሬ፣ ባቱ፣ አዲስ አበባ፣ ዋልያ፣ አዋሽ፣ ይርጋለም ጨርቃ ጨርቅ) የሌላቸው መሆኑን ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችና ከአማራ ክልል ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ጽ/ቤት በተገኙና በተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታዎች በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ፤**

223. በህንፃ ደንቡ መሰረት የሚገነባ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረትና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ አገልገሎት ከመስጠቱ በፊት በሚመለከተው አካል ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ በሁሉም ክልልና ከተሞች በሚንስትሮች ምክር ቤት ህንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003 መሰረት በኢንዱስትሪዎች የሚገነባ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረት ሥራው ዲዛይን ሲጸድቅ ጀምሮ እንዲካተት በማድረግና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩን ከአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **በኮሚሽኑ የአካባቢ ብክለት በተመለከተ የወጡ ህጉች ስለመተግበራቸው የተጠናከረ የክትትል ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

224. ኮሚሽኑም ሆነ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለት በተመለከተ የወጡ ህጉች ስለመተግበራቸው የተጠናከረ የክትትል ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

225. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለት በተመለከተ ሁሉንም ተደራሽ ከማድረግና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከመከታተል አንጻር ጠንካራ የሆነ የክትትል ስርዓት መኖሩን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለትን ለመከታተል በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል በተገቢ ሁኔታ ያልተደራጁ በመሆኑ፣
- በፌዴራል ደረጃ ኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጡና ወደ ሥራ የገቡ ከ2800 በላይ ፋብሪካዎች ቢኖሩም ኮሚሽኑ በ2009 ዓ.ም. 20 እና በ2010 ዓ.ም 30 ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ክትትል ያደረገ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል የአካባቢ ጥበቃ በ2010 ዓ.ም በ8 ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ክትትል ያደረገ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ እና በኮምቦልቻ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ በእቅድ ሳይሆን ከማህበረሰብ በሚመጣ ጥቆማ/ቅሬታ መሰረትን ያደረገ ክትትል የሚያካሂድ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በ2010 ዓ.ም. እቅድ መሰረት አድርጎ ክትትል ያደረገባቸው ፋብሪካዎች 10 ብቻ መሆናቸው፣
- በአማራ ክልል በባህርዳር እና በደሴ ከተሞች የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በጽዳትና ውበት ሥር ሆነው ተጠሪነታቸው ለከተማ ልማት በመሆኑ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ጋር በእቅድም ሆነ በሪፖርት የማይገናኙ በመሆኑ በተዋረድ መሰራት ያለባቸው የክትትል ሥራዎች በአግባቡ እንዳይከናወን ማድረጉ፣ በተጨማሪም በባህርዳር ፍሳሽ ላይ ትኩረት በማድረግ ሆቴሎችና ዩኒቨርስቲዎችንም የሚያዩ በመሆኑ ካለው ውስን የሰው ኃይል አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ክትትል አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም ከከተማ ራቅ ብለው የሚገኙ ፋብሪካዎች ወጥ በሆነ መልኩ ለመከታተል የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ ማለትም ኮምቦልቻ፣ ባህርዳር እና ደሴ ከተሞች፣ ደብብ ወሎ ዞን፣ ቱሌሆራ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ተሽከርካሪ አለመኖሩ፣ ሰበታ፣ አዳማ፣ ሞጆ ከተማና ሎሚ ወረዳ የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩን (1 እና 2 ሞተር) ብቻ ያላቸው በመሆኑና፣

- ከከተማ ራቅ ያሉ ፋብሪካዎችን ለመከታተል ያመች ዘንድ ሥራው እታችኛው መዋቅር ድረስ ያልተዘረጋ መሆኑ ለምሳሌ ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ሞጆ እና ሰበታ (ሰበታ ካራና ጀሞ ኮንደሚኒየም ድረስ ሥራው መሰራት ያለበት ቢሆንም) ከተሞች ላይ ብቻ እንጂ መዋቅሩ እስከ ቀበሌ ያለወረደ መሆኑ እንዲሁም በባህርዳር ከ6ቱ ክፍለ ከተማ 2ቱ ላይ በመዋቅር ያልተደራጁ በመሆናቸው የፍሳሽ ማከሚያ ቢኖራቸውም ጊዜ ጠብቀው (አዩኝ አላዩኝ ብለው) የሚለቁ ፋብሪካዎችን በድንገት በመሄድ ለመቆጣጠር እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተል ችግር እንደገጠማቸው በኦዲቱ ወቅት ከየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ በቃለ መጠይቅ ለመረዳት ችለናል፡፡
- በተጨማሪም በክትትል ወቅት መረጃ ለመያዝ የሚያስችል ግብዓቶች ካሜራ፣ ጂ.ፒ.ኤ.ስ፣ የቢሮ መገልገያ ግብዓት የሌላቸው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች (ኮምቦልቻ፣ ሞጆ ከተሞችና ሎሜ ወረዳ) በመኖራቸው የክትትል መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ለመያዝ አለመቻሉ፤
- በኮሚሽኑ እና በአማራ ክልል ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ በካይ የሆኑና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ፍሳሾን መርምሮ በተጨባጭ/በማስረጃነት አቅርቦ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ቤተ-ሙከራ አለመኖሩ፣ በኦሮሚያ ቤተ-ሙከራ ያለ ቢሆንም በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ ቀለል ያሉ ተንቀሳቃሽ የብክለት መለኪያ መሳሪያዎች /አሲዲቲና ቤዚሲቲ ለመለየት የሚያስችሉ..../ መሰሪያዎች አለመኖራቸው፣
- በተጨማሪም ለከተሞች፣ ለዞንና ለወረዳ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ፍቃድ የሚወስዱ ፋብሪካዎች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ በግልባጭ የማይላክላቸው በመሆኑ ሰነዱን መነሻ አድርገው ለመከታተል መቸገራቸው እና የቁጥጥርና የክትትል ሥራው በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሆን ማድረጉን ለየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከተከተለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡

❖ **ፋብሪካዎች በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለማስተካከል እና ችግሮችን ለመፍታት እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤**

226. የኮሚሽኑ ወይም የሚመለከታቸው የክልል/የከተሞች የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

- በኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 ብክለትን አስመልክቶ ከማህበረሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎች የቀረበለት የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰደውን እርምጃ በ90 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ እንዳለበት የሚገለጽ ቢሆንም እርምጃ የማይወሰድ እና ከላይ በሪፖርት ላይ የተገለጹ አብዛኛው ፋብሪካዎች ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውና የብክለት መጠናቸው እየቀነሰ ያልመጣ ቢሆንም ከማስጠንቀቂያ በዘለለ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት እርምጃ አለመወሰዱን ከተከለሱ መረጃዎች/ለፋብሪካዎች በተላከ ደብዳቤ/ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-
- በሞጆና በአዲስ አበባ ከተሞች፣ በደቡብ ወሎ ዞን ተሁለደሬ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ፋብሪካዎች ላይ የማሸግ ሥራ ሲሰሩ በበላይ አካላት (ከየከተሞቹ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ ከክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) ጣልቃ ገብነት በአዲስ አበባ 6 እና በሞጆ 12 ቆዳ ፋብሪካዎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ ማከሚያ እንዲገነቡ በጊዜ የተገደበ የግዴታ ውል እንዲገቡ ተደርጎ የተከፈቱ በመሆኑ ብክለቱ መቀጠሉ፣
- በደሴ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ከህብረተሰቡ በሚቀርብ ቅሬታ መሰረት በተደጋጋሚ ለፋብሪካዎች ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ሲሆን አልፎ አልፎ ወደ ህግ ቢሄዱም ማስተካከያ የማያደርጉ ፋብሪካዎች መኖራቸውን የየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል ለማሳያ ያህል፡-

- ገራዶ የዶሮ ፋብሪካ ቅሬታ ቀርቦበት ክስ ከተመሰረተበት በኋላ የክሱ ውሳኔ ሳይሰጥ በድጋሚ ሌላ ቦታ ላይ የዶሮ ሥጋ ማቀናበሪያ በከተማ መስተዳድር በመሰጠቱ ህዝቡ በራሱ እርምጃ በመውሰድ ድርጅቱን ላይ ጉዳት ማድረሳቸው፣
- የደሴ ከተማ ቄራ ፋብሪካን በተመለከተ ከ40-50 በሬ የሚታረድና ፍሳሹ ሳይታከም እንዳለ ደሙ በቦይ የአካባቢ መንደር መሀል ለመሀል ሰንጥቆ ወደ ወንዝ የሚገባ እና በተጨማሪ በእርዱ ወቅት የሚወጡ ቆሻሻዎችንም(ማለትም የበሬ እግር፣ ሆድ እቃ ወዘተ) ከፋብሪካው 50 ሜትር እርቀት ላይ ባለ ወንዝ ላይ የሚጥል እና በነዋሪው ከፍተኛ ቅሬታ የደረሰ ቢሆንም በከተማ መስተዳደሩ የበፊቱ ፈርሶ እዛው ቦታ ላይ በአለም ባንክ ገንዘብ በዘመናዊ መልክ ቄራ ሊሰራ በመታሰቡ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቱ ከከተማ መስተዳደሩ ጋር ቦታ መቀየር እንዳለበት በመነጋገር የግንባታውን ሥራ ካስቆመ አምስት አመት የሆነው ቢሆንም የሥጋ ማምረቱን የቀጠለና ካለምንም የማከም ሥራ ፍሳሹን የሚለቅ በመሆኑ ብክለቱ የቀጠለ ሲሆን ህዝቡ አሁንም ቅሬታ እያቀረበ እንደሆነ የኦዲት ቡድኑ ቦታው ላይ በመሄድ በመስክ ምልከታና ከአካባቢው ማህረበሰብ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ኮሚሽነሩ ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት መኖሩ እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ማስደረጋቸውን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤**

227. በደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ ላይ የወጡ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጡበትን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ ሊያዘጋጁ እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሊልኩ ይገባል፡፡

228. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 42 ፋብሪካዎች ውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት (በጀት መመደብ፣ ፖሊሲ፣ አሃድ፣ የአካባቢ ባለሙያ መቅጠር፣ የአካባቢ አያያዝ እቅድ በማቀድ ወደ ተግባር መግባት ወዘተ) የዘረጉት 10 (24%) ፋብሪካዎች ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት 32ቱ /76%/ የአካባቢ የአያያዝ ሥርዓት ባለሞያ (የአካባቢ ባለሙያ) የሌላቸው ወይም በከፊል ያላቸው

መሆኑ ከፋብሪካዎች ከተገኙ ማስረጃዎች እና ከኮሚሽኑ የክትትል ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ፋብሪካዎች የደንቡን ድንጋጌዎች እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ የሚገልጽ የአካባቢ የውስጥ ኦዲት አስደርገው ስልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መ/ቤት መረጃ ማቅረባቸውን በተመለከተ በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ታይተዋል፡-
- በናሙና ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ “ISO” ሰርተፊኬት ለማግኘት ኦዲት ከሚያስደርጉ ጥቂት ፋብሪካዎች (ማለትም ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ፣ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ) በስተቀር የተቀሩት ፋብሪካዎች ኦዲት የማያስደርጉ መሆኑ፣ እንዲሁም የአካባቢ ኦዲት የሚያስደርጉትም ቢሆኑ በአማራና ኦሮሚያ ክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤትም ሆነ ለኮሚሽኑ የማይልኩ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በ2010 ዓ.ም. 35 ፋብሪካዎች የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ለማስደረግ ቢያቅድም ከአራት ፋብሪካዎች በስተቀር/ንፋስ ስልክ ቀለም ፋብሪካ፤ ብሄራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ እና ካዲስኮ ቀለም ፋብሪካ፤ ድሬ ቆዳ ፋብሪካ፣/ የተቀሩት የማያስደርጉ ወይም /ለመ/ቤቱ የማይልኩ መሆናቸው፣ በተቀሩት በናሙና በታዩት ከተሞች ፋብሪካዎች ኦዲት የማያስደርጉ ወይም ሥራው ያልተለመደ መሆኑ፣
- በናሙና በታዩት ኮሚሽኑን ጨምሮ በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ፋብሪካዎቹ የአካባቢ ኦዲት አስደርገው እንዲልኩ ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑ፤ በሌላ መልኩ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በራሳቸው ፋብሪካዎቹን የአካባቢ/የክዋኔ ኦዲት እንደማያደርጉ ለየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-ለመጠይቅና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤

229. ኮሚሽኑ ወጥ አደረጃጀት በመፍጠር፣ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ከክልል አካባቢ መ/ቤቶችና እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር ድጋፍ በማድረግና የጋራ እቅድ በማውጣት በቅርበት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፤ ለምሳሌ ከፍቃድ ሰጪ አካላት ጋር (ኢንቨስትመንት ፍቃድ፣ ንግድ ሥራ ፍቃድ፣ የሥራ ፍቃድ) በአካባቢ ጥበቃ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ላይ ፍቃድ ሲሰጡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ሊጠይቁ እና ፋብሪካዎች ሲታገዱ ወይም ሲዘጉ ፍቃዱን ማገድ የሚገባቸው ቢሆንም ሰነዱን የማይጠይቁና የሥራ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም የፍትህ አካላት በአካባቢ ሕግ ተከባሪነት ተሳትፎና ዝግጁነት አነስተኛ መሆኑ፣
- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር የጋራ እቅድ ቢኖርም በእቅድ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑንና በተናጠል የራሳቸውን ድርሻ ለመሥራት የሚጥሩና አፈፃፀማቸውንም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ቢልኩም በተጠናከረ መልኩ በጋራ ችግሮችን በማየትና በመፍታት እየተሰራ አለመሆኑን፣
- በተጨማሪም ኮሚሽኑ ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር በእቅዱ የያዘ ቢሆንም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር ወጥ እና ተናባቢ ያልሆነ አደረጃጀት መኖሩን እና በተወሰኑ ክልሎች በተሟላ ሁኔታ ከክልል እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ባለመውረዱ እቅድና አፈፃፀም ላይ ክፍተት መፍጠሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

❖ **ፋብሪካዎች ያመነጩቱን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድ መረጃ መያዛቸውንና ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን አወጋገድ ዘገባ ማቅረቡን በተመለከተ፤**

230. ደንብ ቁጥር 159/2001 የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ ያመነጨውን በካይ ነገር ያስወገደበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግቦ ሊይዝ እንዲሁም ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡

- ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት በናሙና ከታዩት ISO ሰርተፊኬት ካላቸው ጥቂት ፋብሪካዎች(ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ/ኤጀርሳ)በስተቀር በተቀሩት ፋብሪካዎች ያመነጩትን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግበው አለመያዛቸው በኦዲቱ ወቅት በመስክ ጉብኝት ወቅት ከፋብሪካዎቹ በተሞሉ መጠይቆችና በኮሚሽኑ በተገኙና ከተከለሱ የክትትል ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም በደንቡ መሰረት ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል የሚል ቢሆንም ፋብሪካዎች ላይ የተሰራ ዘገባ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ከኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በቃ-ለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23 በፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኘሮግራም አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

❖ **ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 መሠረት የህግ ማዕቀፎች እንዲወጡ እና ተገባራዊ እንዲሆኑ ማድረጉን በተመለከተ፤**

231. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎችን ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን /ፖሊሲዎች፣ ስታንደርዶች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ ጋይድ

ላይኖች፣ የግምገማ ሰነዶች እና ስትራቴጂዎችን/ እንዲወጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ቢሆንም ግን፡-

- የከተማ ግብርና ዘርፍ የሚመራበት የከተማ ግብርና ፖሊሲ አለመኖሩ፣
- የከተማ ግብርና ልማት ስትራቴጂ ፀድቆ ስራ ላይ አለመዋሉ፤
- ለከተማ ግብርና የሚሆን መሬት ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰጣጥ መመሪያ አለመኖሩ፣
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በ2005 ዓ.ም የወጣ ሲሆን እስከ አሁን ማሻሻያ ሳይደረግለት እየተሰራበት የሚገኝ መሆኑ፣
- በተጨማሪም ዘርፉን እንዲመሩና እንዲያስፈፀሙ ኃላፊነት የተሰጣቸው የክልሎችና ከተማ አስተዳደር አመራሮችና ፈጻሚዎች እየተሠራበት ለሚገኘው ስትራቴጂ ትኩረት ሰጥቶ በወጥነት ከመተግበር አኳያ ውስንነቶች መኖራቸው እና ኤጀንሲውም ወጥነት ባለውና በተሟላ መልኩ ድጋፍና ክትትል ባለማድረጉ፡-

  የተስተዋሉ የሥራ ክፍተቶች ናቸው፡፡

❖ **በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን በተመለከተ፣**

232. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ኃላፊነት በተሰጠው መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩና ሥራ ለሌላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡

- ኤጀንሲው በተለያዩ ምክንያቶች መስራት እየቻሉ ለማይሠሩ ሥራ ለሌላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሮ እራሳቸውን ለማስቻል በሚያደርገው እንቅስቃሴ በዘጠኙ ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች ከ2009-2010 በጀት ዓመት የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በታቀደው ልክ እየተፈፀመ ባለመሆኑ በሀገሪቷ የሥራ አጥ ቁጥር እንዲበራከት አድርጎታል፡፡

❖ **የአንድ ማዕከል አገልግሎት የአሰጣጥ ስርዓትና ስታንዳርድን በተመለከተ፣**

233. በኤጀንሲው በስራቴጂክ ዕቅዱ ላይ በተገለጸው መሰረት በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳሮች የሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎቶችን ለተገልጋዮቻቸው ሁሉን አቀፍ አግልግሎት መስጠት እንዲያስችላቸው የአሠራርና አገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና በስታንዳርዱ መሠረት መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ሁሉም ክልሎችና ከተማ አሰተዳደሮች የሚገኙ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በስው ኃይልና በግብዓት የተሟሉ ባለመሆናቸው በስታንዳርዱ መስረት ለተግልጋዮቻቸው /ስራ ፈላጊዎች/ የተሟላ አገልግሎት እየሰጡ ካለመሆኑም በላይ በሁሉም ከተሞች በሚገኙ የአንድ ማዕክል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽ አለመሆኑ፣ ኤጀንሲውም ችግሩን ለመቅረፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሠራ አለመሆኑ፣

❖ **ለስራ ዕድል ፈጠራ ሥራ የሚውል የመስሪያና የመሸጫ ቦታን በተመለከተ፣**

234. ኤጀንሲው የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ዜጐች አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነው የለማ መሬት በወቅቱና በተፈለገው መጠን የተዘጋጀላቸው መሆኑን፤ እንዲሁም ግንባታቸው በተጠናቀቁ የማምረቻና መሸጫ ሕንጻዎችና ሼዶች ለተጠቃሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊው መሠረተ ልማቶች የተሟላላቸው መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- በአንዳንድ ክልሎች (አማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ) የሚገነባው የመሥሪያና የመሸጫ ሼዶች ከፌደራል ኤጀንሲ በወረደው የስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት አድርገው ባለመገንባታቸው የመሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ለአገልግሎት ምቹ ባለመሆናቸው ለአገልግሎት ሳይውሉ በመፍረስ ላይ መሆናቸው፣

- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እና ለኢንተርፕራይዞች የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች በግንባታ፣ በአቅርቦትና በአጠቃቀም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የክትትል ሥራ ቢሠራም አሁንም ችግሮቹ አለመፈታታቸውን ማሰረጃው የሚያሳይ መሆኑ፣ ለአብነት ያህል፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ አስተዳደሩ በአጠቃላይ መብራት እንዲገባላቸው ከሚያስፈልጋቸው 527 የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች 4(0.008) ብቻ በመሆኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የላቸውም በሚያስብል ደረጃ ላይ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደሩ ውሃ እንዲገባላቸው ከሚያስፈልጋቸው 392 የመሥሪያና መሸጫ ቦታዎች ውስጥ በአንድ ብቻ የገባ በመሆኑ በቀሪዎቹ የውሃ አቅርቦት የላቸውም በሚያስብል ደረጃ ላይ መሆናቸው፣
- በአማራ ክልል ለኢንተርፕራይዞች 1,005 ሼዶች የተዘጋጁ ቢሆንም ሁሉም ሼዶች በመብራት ባለመሟላት ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል በ2009 በጀት ዓመት ተጀምረው በ2010 ሩብ ዓመት የተጠናቀቁ ሼዶች 845 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 87 ሼዶች መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሲሆን ወደ ሥራ ለማስገባት በዋናነት የመሠረተ ልማት ችግር መኖሩ፣ ኤጀንሲውም እነዚህንም ችግሮች ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ለፈቺ አካል በማሳወቅ እንዲፈቱ በጋራ እየሠራ አለመሆኑን፣
- በክልል ከተሞች እና በከተማ አሰተዳደሮች የሚገኑ ነባር ኢንተርፕራይዞች በመስሪያና በመሸጫ ሼዶች የቆይታ ጊዜያቸውን የጨረሱ ኢንተርፕራይዞችን ያለማስወጣትና ለአዲስ ለሚመሠረቱት ኢንተርፕራይዞች ያለማስተላለፍ ችግር መኖሩ፣

❖ **በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ ስለመሰጠቱ እና ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ በተመለከተ፣**

235. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 11፣ 12 በተቀመጠው መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግቶ ሊሠራ ይገባል፡፡

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በ10 ክፍለ ከተሞችና በተመረጡ 35 ወረዳዎች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉ ቤተሰቦችን በአካባቢ ልማት እና ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትና ተጋላጭነትን፣ ለመቀነስ እገዛ የሚያደርግ አደረጃጀት ፈጥሮ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተሰጣቸው የተጠቃሚነት ኮታ መሠረት በሁለቱም ፕሮግራሞች /በአከባቢ ልማትና በቀጥታ ድጋፍ ፕሮግራም/ ምዝገባ ለማካሄድ በታቀደው መሠረት በቀጥታ ድጋፍ ፕሮግራም እና በአካባቢ ልማት ፕሮግራም ከተመዘገቡ 123,918 ውስጥ 19,132(15%) ተጠቃሚ ሲሆኑ 104,786 ዜጐች ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በደቡብ ክልል በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ለማይችሉ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት የተጋለጡ እና ከደህንነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት አኗኗራቸውን በቀጣይነት ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የቀጥታ ድጋፉ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ የተቀመጠው ቁጥርና መጠቀም የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ያለመጣጣም እንዲሁም በልየታ ወቅትም ከነበረው የጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ የሥራ ጉድለቶች መኖራቸው፣
- በአማራ ክልል በደሴ ከተማ በ2009 በጀት ዓመት የተጀመረ ሲሆን ሥራውን በተቀላጠፈ አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የልተዘረጋለትና በአግባቡ የተጠና አደረጃጀት ያልተፈጠረለት በመሆኑ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሠራር ችግሮች መስተዋላቸው፣
- በክልልም ሆነ በከተማ ደረጃ ያለው አደረጃጀት ወጥነት የሌለው በመሆኑ በደሴ ከተማ አሠራርን ተከትሎ ለሚፈጠሩ አደረጃጀቶች ማለትም በክልል የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ምክር ቤት፣ ስትሪንግ ኮሚቴ እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ንኡሳን ኮሚቴዎችን ማቋቋም አለመቻል፣

- የበጀት ዓመቱን ተግባራት በተቀመጠው መርሃ ግብር መሠረት ለማከናወን በፌዴራል የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በኩል በጀት ጸድቆ ለአማራ ክልል መላክ ባለመቻሉ ለሥራዎች መዘግየት ምክንያት መሆኑ፣
- የምግብ ዋስትና ሥራ እንዲከናወን ከአማራ ክልል የደሴ ከተማ የተመረጠ ቢሆንም በጽ/ቤቱ ያለው ባለሙያ የተሟላ ባለመሆኑ ያሉት ሠራተኞች ተረጋግተው እንዳይሠሩ አስተዋጽኦ መፍጠሩ፣
- በደሴ ከተማ ለጽ/ቤቱ ሥራ መሳለጥ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ የቢሮ ግብዓቶች /ጠረንጴዛ፣ ሸልፍ፣ ወንበር፣ ከምፒዩተር፣ ወረቀት…ወዘተ/ ባለመሟላታቸው የምግብ ዋስትና ሥራውን በሚፈለገው አግባብ እየተሠራ አለመሆኑ፣ ለድጋፍና ክትትል የሚያገለግል ተሽከርካሪ የሌለ መሆኑ፣

236. በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ መስራት ለማይችሉ፣ የመስራት አቅም ለሌላቸው፣ በምግብ እጦት ለተጋለጡ ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች ተጠቃሚ ለማደረግ እየሰሩ እንደሆነ ገልጸው ነገር ግን ቀጥታ ድጋፍ ለማድረግ የሚከፈለው ብር 225 በመሆኑ ካለው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ኑሮአቸውን ያሻሽላል ተብሎ የሚታሰብ አለመሆኑ፤ እንዲሁም በአከባቢ ልማት ስራ ለምሳሌ፡ በደረቅ ቆሻሻ ማንሳት፣ በአረንጓዴ ልማት ላይ ሰርተው እራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ረገድ እየሰሩ ቢሆንም የስራ ላይ የሴፍቲ ወይም የደህንነት መሳሪያዎች፣ የመስሪያ እቃዎችን ለመግዛት በጀት ባለመለቀቁ የመዘግየት ሁኔታዎች መኖራቸውን፣ የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲም ሆነ ክልሉ ኤጀንሲዎች ለአስፈጻሚዎች ሥልጠናዎችን በመስጠት የመደገፍ ስራ ቢሰራም ሰልጠና ለመስጠት ሲያቅድ የክልሉን የስልጠና ፍላጎት ጥናት ወይም (ኒድ አሰስመንት ጥናት) ሳይሰራ እና ሳይጠይቅ የሚሰጥ ሥልጠና የተሟላ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑ፣ እና በተሰጠው ስልጠና ላይ ተመስረቶ በስራ ላይ ምን ውጤት እንዳመጣ ወይም አሰገኝ የሚለውን አጥንቶ ለክልሉ በማሳወቅ ሥራዎችን በውጤት እንዲከናወኑ እያደረገ አለመሆኑን፣

237. በተጨማሪም ኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖረት መሠረት የከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቀድሞ ከተመረጡ 11 ከተሞች በተጨማሪ በአዲስ መልክ የከተሞች የምግብ ዋስትና ኘሮግራም

የሚተገበርባቸውን 44 ከተሞች በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ከተሞችን የመለየት ስራ መስራ ታቸውን በ2010 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ቢጠቀስም ኘሮግራሙ በአዲስ መልክ የሚተገበርባቸው በሌሎች ከተሞች ላይ በኘሮግራሙ አተገባበር ዙሪያ የሚያስፈልገውን የበጀት ምንጭ በመንግሥት ደረጃ ለምን ያህል ከተሞች ማስተግበሪያ እንደሚያስፈልግ ተወስኖ ባለመጽደቁ የልየታ ሥራው ብቻ መከናወኑ፣

የክዋኔ ልዩ ኦዲቶች

24 ከጅማ-ቦንጋ-ሚዛን -ዲማ ድረስ በሚያከናውነው የመንገድ ግንባታ ምክንያት በሚዛን አማን ከተማ እና ዲማ ወረዳ በተለቀቀ የመሬት ይዞታና ንብረት የካሳ ክፍያ አፈጻጸምን በተመለከተ ልዩ ኦዲት

238. በሚዛን አማን ህብረት ቀበሌ የመንገድ ግንባታ ክልል ግራና ቀኝ ተነሺ ከሆኑ 22 ግለሰቦች ውስጥ 5ቱ ካሳ ግምት ከተከፈላቸው በኋላ ንብረታቸውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ያላፈረሱ፣ ቀሪዎቹ 17ቱ ሙሉ የንብረት ካሳ ተከፍሏቸው የቤቱን የፊት ለፊት ግድግዳውን ብቻ አፍርሰው በላሚራ ገጥመው የሰሩና ከካሳ ክፍያው በኋላ መንገዱ ይዞታቸውን/ንብረታቸውን ሳይነካ የተጠናቀቀ ሲሆን ይህም ግለሰቦቹ ንብረታቸውን ሳያነሱ ገንዘብም በማግኘት የሁለት ነገር ተጠቃሚ በመደረጋቸው በድምሩ 4,101,563.17 /አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አንድ ሺ አምስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከ17 ሳንቲም/ ብር መንግስት ያለአግባብ ለወጪ እንዲዳረግ መደረጉ፣

239. በዲማ ወረዳ ኮይ ቀበሌ

- የቀበሌው ነዋሪ ሳይሆኑ፣ መንገዱ በሚያልፍበት ቦታ ምንም አይነት ንብረት በስማቸው ሳይኖራቸው፣ በመንገድ ግንባታ ክልል ውስጥ ሳይገባ እንደገባ ተደርጎ ግምት በመገመት እንዲሁም ሊገመትላቸው ከሚገባ ይዞታ/ንብረት በተጨማሪ በሌላ ንብረት ካሳ በማሰራት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው በመደረጉ ብር 2,546,081 /ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ አርባ ስድስት ሺ ሰማንያ አንድ ብር) መንግስት ያለአግባብ ለወጪ እንዲዳረግ መደረጉ፣

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች ቀርበው ሪፖርቱ ለጠየቀው አካል ተልኳል፡፡

25 በግብርና ሚኒስቴር የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ግብዓቶች ግዢ አፈፃፀምን በተመለከተ (ልዩ የክዋኔ ኦዲት)

240. በሚኒስቴር መ/ቤቱና በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ /Ethiosis/ ፕሮጀክት በኩል የአፈር ለምነት ጥናት የተጠና ቢሆንም የተጠናው የአፈር ለምነት ጥናት ለትግራይ፣ ለአማራ፣ ለደቡብ፣ ለድሬዳዋና ለሀረሪ ክልሎች የተሰራጨ ሲሆን በኦሮሚያ፣ በአፋርና በሶማሌ ክልሎች በመጠናት ላይ ያለው የአፈር ለምነት ጥናት ያላለቀና ያልተሰራጨ መሆኑ፣

241. የተለያዩ ሀገራትን ተሞክሮ በመቅሰም የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች ተቋቁመው ወደ ሥራ እንዲገቡ የተደረገው በቀድሞው በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ፋብሪካዎቹ እንዲገነቡ ከተመረጡ ዩኒየኖች ጋር ውይይት ተካሂዶ እንደሆነ እና የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎችን የማቋቋም ሥራው፡-

- የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ይህንን ሥራ ሲያስፈፅም የቆየ መሆኑ፣
- የተመደበው በጀት ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም /AGP/ ለፕሮጀክቱ የተመደበው ጠቅላላ በጀት ብር 174,990,738 ሲሆን
- በተጨማሪም ከሌሎች የልማት አጋር ድርጅቶች ከተገኘ ዕርዳታ ብር 27,575,826 በጀት ለፕሮጀክቱ ተጨማሪ ስራዎች በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በኩል የተመደበ መሆኑን በድምሩ ብር 202,566,564.00 መመደቡን በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የተገለጸ መሆኑ፣

242. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ግብዓቶች ግዢ ለማከናወን ከሚመለከታቸው አካላት ፍላጐት መሰብሰብ ያለበት ቢሆንም ከክልል ግብርና ቢሮዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን አይነትና መጠን የተሰበሰበበት የፍላጎት ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀን 23/11/06 ዓ.ም በቁጥር 65/07-7 ከትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በግብርና ሚኒስቴር ለግብርና ግብዓትና ግብይት ዳይሬክቶሬት የ2006/07 ምርት ዘመን የምርት

ማሳደጊያ ዕቅድ ማሳወቅን በተመለከተ የሚል የተፃፈ ደብዳቤ በስተቀር ከሌሎቹ ክልሎች ለምጥን ማዳበሪያ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ፍላጎት ተብሎ የተሰበሰበ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ፣

243. ለምጥን ማዳበሪያ ግብዓቶች ግዢ የሚሆን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (specification) ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደርግ የሚገባ ሲሆን ስለመዘጋጀቱና በማን እንደተዘጋጀ እንዲገልጹልን በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ቀርቦላቸው፡-

- በግብርና ሚኒስቴር በኩል በኦዲቱ ወቅት ያሉት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክተር እና የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ስፔስፊኬሽኑ በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ መዘጋጀቱንና በወቅቱ ሥራውን ያስጀመረው ኤጀንሲው በመሆኑ ስፔስፊኬሽኑ በኤጀንሲው መዘጋጀቱንና የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ያልተቋቋመ ስለሆነ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ያልነበረው መሆኑን መግለጻቸው፣
- በተጨማሪም የካቲት 12 ቀን 2011 ዓ.ም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በወቅቱ ግዢ የተፈፀመበትን የግብዓቶች ስፔስፊኬሽን ቀሪ ሰነድ ማግኘት እንዳልተቻለ በድጋሚ መግለጻቸው፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በኩል በኦዲቱ ወቅት የኤጀንሲው የአፈር መረጃ ሥርዓት ፕሮጀክት (Ethiosis) ቡድን መሪ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተለያዩ ጊዜያት በግብርና ሚኒስቴር ሲቋቋሙ በነበሩ የባለሙያዎች የቴክኒክ ኮሚቴ በኩል የማዳበሪያ ስፔስፊኬሽኖች ተዘጋጅቷል፤ በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲም በኮሚቴው አባልነት በባለሙያዎች ሲደግፉ ነበር፣ አሁንም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት በዘርፉ ባሉን ባለሙያዎችን ድጋፍ እና ምክረ-ሀሳብ እየሰጡ እንደሚገኙና ከ2009/10 የምርት ዘመን በፊት የተሰሩት ስፔስፊኬሽኖች የተመለከተ መረጃውን በማህደራቸው ውስጥ ለማግኘት እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

244. ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ባለሙያዎች በኮሚቴ አባልነት ሲደግፉ የነበረ መሆኑን ኃላፊዎቹ ቢገልጹም በኮሚቴ አባልነት ሲደግፉ

የነበሩ ባለሙያዎች እነማን እንደሆኑና የተመደቡበትን ደብዳቤዎች/ ማስረጃዎች በኤጀንሲው በኩል ያልቀረበ በመሆኑና በአባልነት እንዲሰሩ የተገለፀላቸው ማስረጃም ያልቀረበ በመሆኑ እነማን በአባልነት እንደሰሩ ለማወቅ አለመቻሉ፣

- የግብርና ሚኒስቴር በ2006 ዓ.ም እና በ2007 ዓ.ም የቀድሞ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ለምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች የሚሆኑ ግብዓቶችን ግዢ እንዲያከናውን የተደረገው ሌሎች ግብዓት አቅራቢዎች ተሳታፊ ሳይደረጉ ቀጥታ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች እንዲገዛ ያደረገ መሆኑን፣

245. በመሆኑም ግዢውን እንዲፈፅም የተጠየቀውና ግዢውን የፈፀመው የቀድሞ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ2006 ዓ.ም እንዲገዙ የተጠየቁ ግብዓቶችን ለመግዛት ለተወዳዳሪዎች የተሸጠው የጨረታ ሰነድ እንዲቀርብ ተጠይቆ፡-

- ለኦዲት የቀረበው የጨረታ ሰነድ ላይ የጨረታ ኮሚቴ አባላት ፊርማ መኖር ሲገባው ምንም ዓይነት ፊርማና የድርጅቱ ማህተም የሌለው መሆኑ፣
- ለግራኑለር ቦሮን የቀረበው የጨረታ ሰነድ ላይ የተገለፀው 25 ኪ.ግ ሲሆን በግብርና ሚኒስቴር የተላከው ስፔስፊኬሽን ላይ ግን 50 ኪ.ግ የሚል መሆኑና
- በ 2007 ዓ.ም ለተወዳዳሪዎች የተሸጠ የጨረታ ሰነድ ላይም አንድ ፓራፍ የተደረገ ፊርማ ያለ ቢሆንም ፓራፉ የተደረገው በማን እንደሆነና የድርጅቱ ማህተም የሌለው መሆኑ፣
- ያራ ስዊዘርላንድ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሰነድ ላይ 6ቱም የጨረታ ኮሚቴ መፈረም ሲገባቸው አራት የኮሚቴ አባላት ብቻ የፈረሙ ቢሆንም እነማን እንደፈረሙ ስማቸው የሌለ መሆኑን፣

246. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቀድሞው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ድርጅት በላከው የምጥን ማዳበሪያ ግብዓቶች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (specification) መሰረት ለምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች የሚሆኑ ግብዓቶች ግዢ በስፔስፊኬሽን መሰረት እንዲከናወን ጥያቄ ቢያቀርብም፡-

- ግብአቶቹ ከውጪ አገር ተገዝተው ወደሀገር ውስጥ ሲገቡ በተቀመጠው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (specification) መሰረት ጥራታቸውና ይዘታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ እየተረጋገጠ ገቢ እንዲሆን ስለመደረጉ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑን፣
- ግብዓቶቹ ከውጪ አገር ተገዝተው በሚገቡበት ጊዜ በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ የሚያሳዩ ማስረጃዎች፣ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረቡ መሆኑን፣

ለማወቅ መቻሉ፣

- ለምጥን ማዳበሪያ ተብለው በ2006 እና በ2007 በጀት አመታት የተገዙ ግብዓቶች ሥራ ላይ ሳይውሉ በኮርፖሬሽኑ (በቀድሞው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት) እና በአምስቱም ዩኒየኖች መጋዘን ውስጥ ተከማችተው እንደሚገኙ መታወቁ፣

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች ቀርበው ሪፖርቱ ለጠየቀው አካል ተልኳል፡፡

26 በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የግዥና ንብረት አስተዳደር በተመለከተ የተከናወነ ልዩ ኦዲት

247. በባለስልጣን መ/ቤቱ የግዥ ሂደት እና ንብረት አያያዝ ላይ፣

- የጨረታ አፈጻጸሙ በሀገር አቀፍ መከናወን ሲኖርበት በአለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወንበት ሁኔታ መኖሩን፣
- ግዥዎች በታቀደላቸው ዕቅድ መሰረት የማይፈፀሙ መሆናቸውን፣
- ግዥዎች ከመፈፀማቸው በፊት የገበያ ጥናት የማይከናወን መሆኑን፣
- የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ላይ ወጥ የሆነ የግዥ ዘዴን የማይጠቀሙ መሆኑን፣
- የፍላጎት መግለጫዎች (Specification) በሚመለከታቸው ስለሚገዛው ዕቃው ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች አለመዘጋጀታቸውን፣

- ግምገማ ለማከናወን የሚያገለግሉት የቴክኒክ መገምገሚያ መስፈርቶች በዝርዝር የማይቀመጡ እና በግልፅነት ለመገምገም የሚያስችል ነጥብ የማይሰጣቸው መሆኑን፣
- የቴክኒክ ግምገማ ሲደረግ ባልተሟላ ማስረጃ ነጥብ የሚሰጥ መሆኑን፣
- ዕቃዎች ገቢ በሚሆኑበት እና በሚገመገሙበት ወቅት በፍላጎት መግለጫው መሰረት አለመሆናቸውን፣
- የቴክኒክ እና የፋይናንሻል ግምገማ ውጤት በአዋጁና መመሪያ ላይ የተጠቀሱት መስፈርቶችን ባላሟላበት ሁኔታ በድምር የመያዝ አሰራር መኖሩን፣
- ንብረቶች ከተገዙ በኋላ የንብረት ገቢ ደረሰኝ በወቅቱ የማይቆረጥላቸው መሆኑን፣
- ንብረቶች በአግባቡ የማይያዙ መሆናቸውና ለታለመላቸው አላማ በወቅቱ የማይውሉ መሆኑን፣
- የግንባታ ስራዎች በተገባላቸው ውል መሰረት በወቅቱ እንዲጠናቀቁ አለማድረግ እንዲሁም ክትትልን ወጥ በሆነ ሁኔታ አለማከናወን፣

በአጠቃላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ የግዥ አፈጻጸም ሂደት የግዥ አዋጁንና መመሪያውን መሰረት በመድረግ የማይከናወኑ አሰራሮች መኖራቸውን እንዲሁም ንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የሚሉ ዋናዋና ግኝቶች ቀርበው ሪፖርቱ ለጠየቀው አካል ተልኳል፡፡

የክትትል ኦዲቶች

ባለፉት ዓመታት በተካሄዱ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን በተመረጡ ስራዎች ላይ የክትትል ኦዲት የተካሄደ ሲሆን፣ በርካታ ነጥቦች ላይ እርምጃ ተወስዶ ተግባራዊ የተደረጉ(በእያንዳንዱ ዝርዝር ሪፖርቶች ውስጥ ተመለክተዋል) መሆኑ አበረታች ቢሆንም፣ተግባራዊ ያልተደረጉ በመኖራቸው ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

27 በፌዴራል የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

248. አገልግሎቱ ካለበት የሰው ሀይል እጥረት የተነሳ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከዘረዘራቸውና በአገልግሎቱ በኩል ግዥ ያቸው ከሚፈፀም የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ያሉ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ከተዘረዘሩት የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ውስጥ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እንዲሁም የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎች ፍላጎት አሰባስቦ ግዥ የማይፈጽም መሆኑ፡፡

249. የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ግዥ እንዳይፈጽሙ የሚል ስርዓት ስለሌለ/ስላልተዘረጋ/ ግዥ አትፈጽሙ የሚል ውሳኔ ማሳለፍ አለመቻሉ፤ በዚህ የተነሳ የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች መኖራቸውና የግዥ ፍላጎታቸውን ለአገልግሎቱ ሳያሳውቁ ግዥ እንደሚፈጽሙ፣ እንዲሁም አገልግሎቱ የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በመኖራቸው ምክንያት የመንግስት መ/ቤቶች የፈለጉትን ዕቃ መጠን በሚፈልጉበት ጊዜ እንደማያገኙና ወደ ፕሮፎርማ ግዥ መግባታቸው፡፡

250. አገልግሎቱ ከ2008-2010 ለሚገዛቸው ዕቃዎች ላይ የዋጋ ማሻሻያ በሚያስፈልግ ጊዜ የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ እንዲቻል የገበያ ጥናት የሚያደርግ ቡድን በ2009 ዓ.ም የተቋቋመ ቢሆንም የገበያ ዋጋ መረጃ ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ባለመገኘቱ ምክንያት የዋጋ ማስተካከያ አለማድረጉ እና አቅራቢዎች የውል ማስከበሪያ ብለው የሚያስይዙትን ገንዘብ በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት የዘረጋ ቢሆንም በውሉ መሰረት ያልፈጸሙ አቅራቢዎች ቢኖሩም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የውል ማስከበሪያውን ገንዘብ አለመውረሱ፡፡

251. አገልግሎቱ ለባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዥ በመፈጸሙ ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም በየጊዜው ጥናት እያካሄደ እንደሆነ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ጥናቱ በገለልተኛ አካል እንዲጠና በወሰነው መሠረት ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጥናቱን እንዲያካሂድ ሃላፊነት ተሰጥቶታል ቢባልም ሀላፊነቱ የተላለፈበት ማስረጃ እና በገለልተኛ ወገን የተጠና ጥናት አለመቅረቡ፡፡

28 በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

252. ኢንስቲትዩቱ ከ2009-2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች አለመሸጋገሩ፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉ

253. የመዳረሻ ገበያ ውስንነት እና በነባር ገበያዎች ውስጥም ያለ ድርሻ አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም የተወሰኑ ገበያዎችና ደንበኞች ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑና ኢንስቲትዩቱ ከውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እና ኢንባሲዎች ጋር የጋራ መግባቢያ ስምምነት ስለመፍጠሩና በጋራ ለዘርፉ አማራጭ ገበያ ዕድል አለመፈጠሩ እና የእንስሳት አቅርቦትን ችግርን ለመፍታት የግል ባለሀብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡና ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ/ራንች/ እንዲያቋቁሙ አለማድረጉ

254. ኢንስቲትዩቱ በስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሀገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን ቀምሮ/አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ እንዳላሰራጨ፤ እንዲሁም ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎች ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሀብትና የመኖ የማምረት

አቅምና ሌሎች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች አለማሰራጨቱ፡

255. በኢንስቲትዩቱ የካቲት 2009 ዓ.ም በተደረገ የደሰሳ ጥናት በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ መሬት ወስደው ወደ ስራ ካልገቡ ኢንዱስትሪዎች መካከል በኦሮሚያ ክልል 19፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 10፣ በአማራ ክልል 42፣ በሀረሪ ክልል 17 እና በደቡብ ክልል 44 ባለሀብቶች መኖራቸው ታውቋል፤ ነገር ግን እነዚህ በጥናት የተለዩት ባለሃብቶች የኢንቨስተመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል እንዲያውቀው የተደረገበት ማስረጃ ክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

29 የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

256. በቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ ለአሁኑ የፌዴራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን የሚመለከቱ ግኝቶች እና የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

257. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤

- በየክልሎች የወጣቶች ተዘዋሪ ብድር ፈንድ በከተሞችና በገጠር ላሉ ለይቶ በመመደብና የተሰራጨውንም ብድር አፈፃፀም በገጠርና በከተማ ለይቶ ከማቅረብ አንፃር በትግራይ፤ በሀረሪ፤ በኦሮሚያና፤ በአማራ ክልል ችግር ያለ መሆኑ
- በፌዴራል ደረጃ ሞዴል የአሰራር መመሪያ በ2005 ዓ/ም በማዘጋጀት ለክልሎች ማውረድ የተቻለ ሲሆን ክልሎችም እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመቃኘት በክልላቸው/ ከተማ አስተዳደራቸው ካቢኔ በማፀደቅ በስራ መመሪያነት

እየተጠቀሙ የሚገኙ ያሉ ሲሆን በአንፃሩ ከመነሻው አሰራሩን ዘርግተው ወደ ስራ ያልገቡ ክልሎች መኖራቸው

- አሰራሩን ዘርግተው አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት ክልሎች በሂደት ያቋረጡ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገለጽ የአሰራር ክፍተት ስለነበር ቤሄራዊ ባንክ በውጭ አማካሪዎች በማስጠናት የመጀመሪያ ረቂቅ ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበት መዳበር የቻለ ቢሆንም መመሪያውን አጽድቆ ወደ ክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች የማሰራጨት ተግባር እስካሁን መፈፀም አለመቻሉ፤
- በአምስቱ የዕድገት ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እንደታየው በአዳማ ከተማ አስ/የ01 ቀበሌ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለስራ ምቹ ባልሆኑ ቦታዎች የተገነቡና መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው ሼዶችና ክለስተሮች ያለስራ መቀመጣቸው፤
- ለአገልግሎት ዘርፍ የተሰሩት ሼዶችና ክላስተሮች አገልግሎት ለመስጠት ሽንት ቤት ስለሌላቸው በጤና ፅ/ቤት እየታሸጉ ኢንተርፐራይዞች መጉላላታቸው፤
- በዱከም ከተማ አስተዳደር የ01 ቀበሌ የአ/ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ መሰረተ ልማት ያልተሟሟላላቸው መሆኑ ፤
- በአሰላ ከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ያልተጣጣመ መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የተገነቡትና በመገንባት ላይ ያሉትም ለስራ ምቹ ያልሆኑና የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው በመሆን፤ 64 ሼዶች በመሰረተ ልማት ችግር ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፤
- የስራ እድል ፈጠራና ለኢንርፕራይዞች ልማት በሚውሉ የመስሪያና መሸጫ ቦታዎች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ጥናት ሰነድ ላይ፤ በ2005 የፀደቀው አደጋን የሚቋቋም አረንጓዴና ተደራሽ የከተሞች ልማት ፖሊሲ ላይ እንደተገለፀው በቂ

መሰረተ ልማት አቅርቦት ያለው መሬት በማዘጋጀትና ከዚህ ውስጥ ቅድሚያ ለጥቃቅንና አነስተና ተቋማት ማምረቻ ቦታ በመለየት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተቋማቱ ማከራየት ቢሆንም በጥናቱ በቀረበ ቃለ መጠይቅ የተሰጠ መልስ እንደሚያመለክተው በመብራት ችግር ወደ ስራ ያልገቡ የማምረቻ ሼዶች በተለያዩ ከተሞች በመኖራቸው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቅድሚያ ለመስጠት እንዲችል በመብራት ኃይል የጋራ እቅድ በማዘጋጀት እና በጋራ ለመገምገም መግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፤

- በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤ በደቡብና፤ በአማራ፤ በሀረሪ፤ በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ከህዳር 18-29/2011 ድረስ የተካሄደ የ100 ቀናት ትግበራ እና የ2011 በጀት አመት ስራዎች አፈፃፀም ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ከመስሪያ ቦታ ድጋፍ ጋር በተያያዘ ትልቁ ማነቆ የመሰረተ ልማት ችግር ሲሆን በታዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የችግሩ ስፋት ቢለያይም በአብዛኞች የተላለፉ ሼዶች የታዩ የመብራት፤ የውሃ፤ የመፀዳጃ ቤት ያለመሟላት ችግር መኖሩ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይም መብራት ባለመሟላቱ እና በትራንስፎርመር ችግር የተጠናቀቁ ሼዶች ለኢንተርፕራይዝ ለማስተላለፍ አለመቻሉ፤
- በመሰረተ ልማት ችግር ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ህንፃዎችና ሼዶች በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት በማሰብ የተሰበሰበ መረጃ ላይ እንደሚያመለክተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ በ2008/2009/2010 ዓ.ም ለቆጣሪ፤ መስመር ዝርጋታ እና ለትራንስፎርመር ማስገቢያ ጠቅላላ 35.304.340.07 ብር ለኢትዮጵያ ለኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተከፈለ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስተጠናቀቀ ድረስ የተገነቡት ህንፃዎችና ሼዶች የኤሌትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤
- በድሬደዋ ከተማ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት የወጣው የገበያ ልማትና ግብይት መመሪያ ተግባር ላይ አለማዋሉ፤

- በተለይ የጨረታ ሰነድ በነፃ ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሰጥ የተቀመጠ ቢሆንም በኤጀንሲ ከሚወጡት ጨረታዎች በስተቀር ሌሎች ተቋማት የጨረታ ሰነድ በሽያጭ ስለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ቅሬታ እያቀረቡ መሆናቸው፤
- ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ከተፈጠረላቸው በኋላ በአቅርቦት፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ ሆኖ ካለመገኘታቸው ጋር ተያይዞ ሆስፒታሎችና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር ያለው የገበያ ትስስር እየተዳከመ መምጣቱ፤
- ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የገበያ እድሎችን ለይቶ በመንግስት ተቋማት በዩኒቨርስቲዎች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ከመፍጠር አንጻር በደቡብ ክልል ሰፊ ክፍተት መኖሩ፤
- በተለያዩ ዘርፎች የገበያ እድሎችን በጥናት በመለየት ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እጥረት መኖሩ፤
- በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣በደቡብና፣ በአማራ፣ በሀረሪ፣ በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የመስክ ምልከታ በተካሄደባቸው ከተሞች የአካባቢ የገበያ አማራጮች እንዲጠቀሙ ከልየታ ጀምሮ እየተሰራ ያለው ስራ በቂ አለመሆን፤
- ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ፕሮጀክት አሳውቀው ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትሥሥር እንዲውል ለማድረግ ፈቃደኝነት አለማሳየታቸው፤
- ከማምረቻና መሸጫ ማዕከላት መመሪያ አተገባበር ጋር ተያይዞ የክራይ መጠን ለኢንተርፕራይዞች በማዕከሉ ውስጥ ቆይታ የሚወሰን ሲሆን በመጀመሪያ አመት

25% በሁለተኛው አመት 50% በሶስተኛው አመት 75% እና በአራተኛው እና በአምስተኛው አመት ሙሉ የክራይ ዋጋ ይከፍላሉ በሚል ቢቀመጥም ይህንን የክራይ አከፋፈል ተከትሎ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የከተማው ገቢዎች ፅ/ቤት ገቢ የመሰብሰብ ስራ ቢሰራም መሰብሰብ ያለበት ኪራይ ሁሉም በአግባቡ መሰብሰቡን በተመለከተ በቂ ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፤
- ለሚዘጋጁ ሼዶችና የገበያ ማዕከላት የአካባቢውን የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ የክራይ ዋጋ ያለተተመነ መሆኑ፤
- ወርሃዊ የክራይ መጠኑ ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ መሆኑ፤
- እንዲሁም በየዓመቱ የሚከፈለው የክራይ መጠን በመመሪያው መሰረት በመጀመሪያው ዓመት 25% በ2ኛ ው ዓመት 50% በሶስተኛው ዓመት 75% በ4ኛው እና በ5ኛው ዓመት የተተመነውን የክራይ ዋጋ ሙሉውን እንዲከፍሉ እና ከ5 ዓመት በኋላ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ የሚደረገው ድጋፍ ክትትል ቀጣይነት የሌለው በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ከመጀመሪያው እስከ 5ኛው የክፍያ ልዩነት ተግባራው እየተደረገ አለመሆኑ፤
- የፌዴራል ከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 ዓ/ም የመጀመሪያ ስድስት ወራት የክልሎች ዕቅድ አፈፃፀም ግብረ መልስ ላይ በአማራ፤ ድሬደዋ፤ ሀረሬ ፤ አፋር ክልሎች ከአሰራር ውጭ የተያዙ የመስሪያና የመሸጫ ሼዶችና ማዕከላት ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች አለመኖራቸው፤
- እንዲሁም እርምጃ የተወሰደባቸው ቢኖሩም በሪፖርት ተካተው እንዲታወቁ አለመደረጉ፤
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ 5 አመት ሆኖ በሚገቡት ውል መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ቢቀመጥም በሁሉም ክልሎች በተሟላ መልኩ ወደ ተግባር አለመገባቱ፤

- ለተከታታይ 5 አመታት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል ተሰጥቷቸው የመመረቂያ መመዘኛ መስፈርት ማሟላት ባለመቻላቸው ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ያልተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት በቀጣይ አይሰጣቸውም ነገር ግን ሌሎች ድጋፎችን እስከ ቀጣይ 2 ዓመት ሊሰጣቸው ይችላል በሚል ቢቀመጥም ይህን ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- ከመስሪያና መሸጫ ክላስተር ማዕከላት ላይ ባለ አፈፃፀም ችግር ምክንያት ነባር ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩም ያልተሸጋገሩም የተሰጣቸውን የማምረቻና የመሸጫ ማዕከል እንደ ርስት በመቁጠር ቦታውን ለመልቀቅ ፍቃደኛ አለመሆን፤
- አመራሩም በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሰረት ስራዎችን መምራት ባለመቻሉ ወደ ስራ ለሚገቡአዲስ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ እጥረት እያጋጠመ ከመሆኑ በተጨማሪ በስራ ፈላጊዎችና በተገልጋዮች የፍትሃዊነት ጥያቄ መነሳቱ፤
- በከተሞች የሚገኙ የከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ (ቢሮዎች) የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ድጋፍ አቅርቦት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች አቅም እያደገና የስራ ስፋት እየጨመረ ሲሄድ በመገምገም ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፈጥሩና ስራቸውን እንዲያስፋፉ በሚል የኢንተርፕራይዙን የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ተለዋጭ የመስሪያ ወይም የመሸጫ ቦታ እንዲሰጥ አለመደረጉ፤

ታውቋል፡፡

30 የፌዴራል አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

258. በቀድሞው የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶች እና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ለአሁኑ የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲን

የሚመለከቱ ግኝቶች እና የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

259. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፤

- ለአስፈፃሚዎች በተፈጠረው ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ በሁሉም ክልሎች በስፋት ወደ ኢንዱስትሪዎች ስለመውረዱ ክትትል በማድረግ ሪፖርት እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ፤
- የሀዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ፤ መክፈል ያልቻሉና ውዝፍ ብድር ያለባቸውን ኢንተርፕራይዞች በዘርፍ፤ባለባቸው የብድር ውዝፍ እዳ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የሚያሳይ የተዘዋዋሪ ብድር መረጃ ያለ ሲሆን፤የመደበኛ ብድር መረጃው የሌለ መሆኑ፤
- በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት የካፒታል እቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ የስራ ማስኬጃ ብድር ያገኙትን ኢንተርፕራይዞች መረጃ ለብቻው ተለይቶ ያልተያዘ መሆኑ፤
- የኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ ድጋፍ የሚሟላው በሁለት መንገድ ሲሆን በጥሬ ገንዘብ በሚቀርብ ብድር (የስራ ማስኬጃ) እና በአይነት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ (የካፒታል እቃ) ነው በዚህም የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ 5012 ማኑፍክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ለስራ ማስኬጃ 5.455.000.000.00 ብድር ለማመቻቸት እቅድ የተያዘ ቢሆንም ብሔራዊ ባንክ የሪፖርት መላኪያ ፎርማቱን ወደ አነስተኛና የብድርና ቁጠባ ተቋም ማውረድ ባለመቻሉ የተሰራጨው የብድር መጠን የማይታወቅ መሆኑ፤
- በኤጀንሲው በሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት በቀረበው የመረጃ ማጠቃለያ ቅፅ መሰረት በተዘጋጀ አጭር ርፖርት ላይ አዲስ ኢንተርፕራይዝና ነባር አንቀሳቃሾች የስራ ማስኬጃ ብድርን በተመለከተ ስራው በዋነኝነት በክልል ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በአበዳሪና በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት በቅንጅት የሚሰራ ሲሆን ለአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ

ማስኬጃ ብድር መስጠትን በተመለከተ በክልሎች ከቀረበ ሪፖርት በመነሳት በ2009 በጀት ዓመት የተሰጠ የስራ ማስኬጃ ብድር መረጃ ከክልሎች ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤

- የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች 7 ቢሊየን ብር ለማመቻቸት እቅድ ተይዞ 338.743.757.13 ብር የተሰራጨ ሲሆን አፈፃፀሙም 4.8% መሆኑ፤
- በ2010 በጀት አመት ለ8000 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 6 ቢሊየን የስራ ማስኬጃ ብድር በአበዳሪ ተቋማት እንዲሰራጭ ክትትል ድጋፍ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ የ3 ክልሎች (ትግራይ፤ሱማሌ እና ድሬደዋ) ብቻ ለ817 አነስተኛና ማካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማስኬጃ ብድር ብር 158.143.568.07 የተሰራጨ ሲሆን፤(የብድር እቅዱን 10.2%) እና በእቅድ ከተያዙት ኢንዱሰትሪዎች ውስጥ ብድር ያገኙት (2.9%) ሲሆን ይህም ከአመታዊ እቅዱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞች ልማት ዳይሬክተር የ2010 አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በበጀት አመቱ ለወጣቶች የተሰራጨው ብድር መጠን ኦሮሚያ፤ አማራ፤ደቡብ፤ ድሬደዋ፤ ጋምቤላ፤ አዲስ አበባና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ውጭ ሌሎች ክልሎች መረጃውን ለይተው ባለመላካቸው አፈፃፀሙ 29 % መሆኑ፤
- የካፒታል ዕቃ ሊዝና ፋይናንስ የ2010 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በፌዴራል ደረጃ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ ብድር የሚያቀርቡ የፋይናንስ ተቋማት ተለይተው ባለመታወቃቸው በጋራ እቅድ አውጥቶ ለመንቀሳቀስ እንቅፋት መሆኑ፤
- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት ለጥቃቅን አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ ቢጠየቁም ለአንድ ኢንተርፕራይዝ ብቻ ብድር ያመቻቹ መሆኑ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በተመለከተ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ መሳሪያውን ዋጋ 20 በመቶ

እንዲቆጥቡ በማድረግ ቀሪውን የካፒታል ዕቃ ተቋሙ በመሸፈንና መሳሪያውን ገዝቶ በመስጠት ኢንዱስትሪዎቹ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ ክፍያውን የሚፈፅሙበት በአይነት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ ሲሆን በዚህም መሰረት በ2009 በጀት አመት ለ2.949 አነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 7 ቢሊየን ማምረቻ መሳሪ እንዲቀርብ ድጋፍ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ 1058 ኢንዱስትሪዎች (የእቅዱን 35.9%) የብር 371.835.094.10 ማምረቻ መሳሪያ (የዕቅዱን 5.3%) የቀረበ መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት ለ8354 አነስተኛ መከከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 8.354.000.000 ማምረቻ መሳሪያ ለማቅረብ ታቅዶ ለ154 አዲስና 779 ነባር በድምሩ ለ933 ኢንዱስትሪዎች (የእቅዱን 11.17%) እና የብር 720.008.035.16 ማምረቻ መሳሪያ (የእቅዱን 8.6%) የቀረበ መሆኑ አፈፃፀሙ ከእቅድ አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ቁጠባን በተመለከተ ይህንን ስራ በዋናነት የሚያከናውኑት ክልሎች ሲሆኑ በሰሩት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለካፒታል እቃ ፋይናንስ ድጋፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቀው 20 በመቶ ቅድመ ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ ሲሆን የስራ ማስኬጃ ብድር ለማግኘት የተቆጠበውን መረጃ የመሰብሰብ ስራ በኤጀንሲው አለመከናወኑ፤
- የኤጀንሲው የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት በቀረበው ሪፖርት ከኤጀንሲው በተጨማሪ ክልል መስተዳድር ፤የከተማ አስተዳደሮች ፤ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወዘተ የሚሳተፉበት የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጀ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የብድር ዋስትና ፈንድ በየክልሎች እንዲቋቋም አለመደረጉ፤
- የብድር ዋስትና ፈንድ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መቋቋሙን በተመለከተ የብድር ዋስትና ፈንድ ለማቋቋም መጀመሪያ ኢንዱስትሪዎች ብድር ማግኘት የልቻሉት ዋስትና ማቅረብ ባለመቻላቸው ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መረሃ ግብር ላይ ቢቀመጥም

የብድር ዋስትና ፈንድ ባለመቋቋሙ ምክንያት ክልሎች የአሰራር መመሪያ ያላዘጋጁ መሆኑ ፤

- በሻሸመኔ ፤ሀዋሳ የስራእድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፅ/ቤት የብድር ዋስትና ፈንድ የአሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል የተባለ ቢሆንም የአሰራር መመሪያ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

- በሀዋሳ፤ በሻሸመኔ ስለብድር ዋስትና ፈንድ አሰራር ላይ ስለፈንዱ (ብድሩ) አጠቃቀም ለቀበሌ አስተዳደር፤ለአንድ ማዕከል ባለሞያዎች እና ለብድርና ቁጠባ ባለሞያዎች ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል ቢባልም ነገር ግን መረጃው በማዕከል የማይገኝ መሆኑ፤

- በሀዋሳ ከተማ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም፤የሃዋሳ ከተማ የስራ እድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርቡ ቢዝነስ ፕላኖች አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ፤

- የካፒታል እቃ ሊዝና ፋይናንስ ዳይሬክተር የ2009 በጀት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተሰራጨው ብድር ለታለመለት አላማ መዋሉን 4 ጊዜ ክትትል ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የብድር መረጃውን ማግኘት ባለመቻሉ የብድር ክትትል ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤

- የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም ኦዲት ለማድረግ በቀረበው የመረጃ ማጠቃለያ ቅፅ መሰረት የተዘጋጀ አጭር ርፖርት ላይ የብድር ተጠቃሚ የሆኑ የአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ብድር ከወሰዱ በኋላ በተዘጋጀው የንግድ እቅድ መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤

- በሻሸመኔ ከተማ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም ለሻሸመኔ ቅርንጫፍ ብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤

- ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የንግድ እቅድ ዝግጅት መሰረት ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ሀዋሳ ከተማ የንግድ ስራ እቅድ የአዋጭነት ጥናት የማይጠና መሆኑ ነገር ግን የቀረበውን ቢዝነስ ፕላን የመገምገም ስራ የሚሰራ መሆኑ ፤ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤት ብድር ከመሰጠቱ በፊት የሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን አዋጭ መሆኑ እንዲጠና ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት መሰረት በነባርና በአዲስ መልክ ሊገነቡ በታሰቡ የክላስተር ማዕከላትና በክላስተር አስተዳደር ስራዎች አዳዲስ አሰራሮች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ለ180 አመራሮችና ባለሞያዎች 2 ጊዜ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ አቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው አለመሰራቱ፤
- በአማራ 6188 ሄክታር ፤በትግራይ 3474 ሄክታር ፤በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች 3068 ሄክታር እና በአዲስ ሄክታር የተዘጋጀ ሲሆን የፕሮቶ ታይፕ ዲዛይንም በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለክልሎች እንዲደርስ የተደረገ ቢሆንም ክልሎች የግንባታ በጀት መድበው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፤
- በአማራ ክልል በተለያዩ ከተሞች የመሬት ዝግጅት በማድረግ 6234.85 ሄክታር መሬት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎበት ከሶስተኛ ወገን ነጻ የተደረገ መሬት መጠን በድምሩ ሲታይ 82.1 ሄክታር ብቻ መሆኑ፤በትግራይ ክልል 3473.85 ሄክታር መሬት ለክላስተር ልማት ቢዘጋጅም ካሳ ተከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ የሆነው 384.98 ሄክታር መሬት ብቻ መሆኑ፡፡
- የ2010 በጀት አመት የዝግጅት ምዕራፍ የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያ የክልል የተደረገ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት እንደተመለከተው የምህንድስና የRTS ጥናቶች ተጨባጭ የመሬቱን ዳታ (መረጃ) ሳይወስዱ ዝም ብለው የአከባቢውን ህብረተሰብ በቃል ጠይቀው ባገኙት መረጃ መሰረት ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት

በአንድ አከባቢ መሆን ያሌለባቸው ምርቶች በአንድ ቦታ እንዲመረቱ መደረጉ፤ለኤክስፖርት ሊሆኑ የሚገባቸውን ምርቶችን ለማምረት አለመቻሉ፤

- ቡልቡላ ላይ የተሰራው ስትራክቸራል ዲዛይን የንፋስ አቅጣጫው የተሳሳተ መሆኑ፤በተጨማሪም ፎቶ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተጨባጭ ነገሮችን የሚያሳይና ያገናዘበ አለመሆኑ፡
- ውኃ የሚወጣበትን ቦታ በድጋሚ በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ እያስጠኑ መሆኑ፤ በጋምቤላና ፤በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው፤ በጋምቤላ ከተማ ለኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከል ግንባታ 250 ሄክታር መዘጋጀት ሲኖርበት 100 ሄክታር ብቻ መዘጋጀቱ እንዲሁም በ13 ወረዳዎች እና በ1 ልዩ ወረዳ መዘጋጀት ያለበት 50 ሄክታር መሬት ያለመዘጋጀቱ፣ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፤በሐረሪ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 መጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት እንደተመለከተው በሶማሌ ክልል ለክላስተር ማዕከላት መዘጋጀት የሚገባው ባለ 50 ፤ባለ 100 እና ባለ 250 ሄክታር መሬት ያልተዘጋጀ መሆኑና ከ 3ኛ ወገን ነፃ አለመደረጉን፤ ለማስጀምር ያክል እንኳን ከክልሉም ሆነ SDG በጀት አለመመደቡ፤
- በሞዴልነት የክላስተር ማዕከላት ፕላን ለሌሎች ክልሎችና ከተሞች አገልግሎት እንዲውሉ ከሚለሙ እና ከሚለዩ መሬቶች ጋር የማጣጣም ስራ እንዲሰራ ክትትል የማድረግ ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ያልተሰራ መሆኑ፤
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተዘጋጀውን ክላስተር ማዕከላት ልማት ፕላን በተመረጡ ከተሞች መተግበር እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ በእቅዱ መሰረት ያልተሰራ መሆኑ፡፡
- የምርት ማሳያና መሸጫ ስታንዳርድ ዲዛይን ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ ላይ ዋናው ስራ የሚካሄድበት በጀት ከአጋር የልማት ድርጅቶች የሚገኝ ቢሆንም የምህድስና አማካሪ ድርጅቶችን ፍላጎት ለማወቅ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ እንዲደርሳቸው በኤጀንሲው በኩል ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣

- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአዲስ መልክ በተዘጋጀው የክላስተር ማዕከላት ፕላን መሰረት ትኩረት በተሰጠባቸው ዘርፎች ለማምረቻነት የሚውሉ 106 ህንፃዎችን በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲገነቡ ድጋፍ ለማድረግ እቅድ የተያዘ ቢሆንም ስራው ያልተሰራ መሆኑ ፤

- በማዕከላት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መጠናቀቅ ባለመቻሉ ነባር የክላስተር ማዕከላት ተረክቦ ተገቢውን መሰረተ ልማት በመሟላት ለኢንዱስትሪያሊስቶች ማሸጋገር ያልተቻለ መሆኑ፤ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችለማምረቻና ለመሸጫ ታስበው የተገነቡ ህንፃዎች በተላከላቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት የተሰበሰበው መረጃ 968 ህንፃዎች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 278 ህንፃዎች መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውና ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው፤

- ታዳጊ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ማዕከላት የገቡ ኢንዱስትሪዎች መረጃ በማደራጀት ረገድ በነባር ማምረቻ ማዕከላት የክልሎች ወጥ የሆነ የአሰራር የባለቤትነት ችግር በመኖሩ መረጃው በአግባቡ ማደራጀት አለመቻሉ፤

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቢሮ የካ ፤ኮልፌ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች በራሳቸው ቅፅ የሚጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤

- በጋንቤላ ክልል የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቆጠራ አለመደረጉ እና ከስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስት ኤጀንሲ ወደ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ አለመተላለፋቸው፣

- ክልሎች የላኩት መረጃ በሚፈለገው ደረጃ ጥራቱን ያልጠበቀና ያልተሟላ በመሆኑ በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤በደቡብና ፤በአማራ ፤በሀረሪ ፤በአዲስ አበባ እንዲሁም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የድጋፍ ክትትል ስራ የተጠቃለለ ሪፖርት ላይ ዝርዝር የኢንተርፕራይዞች መረጃ መሰብሰብያ ቅፅን በተሟላ ሁኔታ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ የታየ ቢሆንም በተለያዩ ቅፆች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በተዘጋጀው ወጥነት ባለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማት መሰረት የማይሰበሰብ መሆኑ፤

- በአፋርና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከጥቅምት 6-13 /2010 በተደረገ ክትትልና ድጋፍ በክልሉ የሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የመለየት ስራ በአሶሳ ከተማ ብቻ ያሉት እንደተለዩና በሌሎች ዞኖች የሚገኙት ያልተለዩ መሆኑ፤ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፤የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የ2010 የመጀመሪያ ዙር የድጋፍና ክትትል ሪፖርት ላይ በሶማሌ ክልል የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር አለመኖሩ፤
- የኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ባለመኖሩ ነባር ሼዶችን ተረክቦ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አለመተላለፉ፤
- በ2009 የመሰረተ ልማትና ክላስተር ዳይሬክተር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በ9 ክልሎችና በ2 ከተማ አስተዳደሮች የተለዩ ህንፃዎች ውስጥ የተገኙ ክፍት የማምረቻ ቦታዎች በእድገት ተኮር ዘርፎች ለተሰማሩ 150 የአነስተኛ መካከለኛ ኢንዱስትሪ አምራቾች በተገቢው ተለይተው ህጋዊነትን በተከተለ መልኩ መተላለፋቸውን ለማረጋገጥ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 77 የአነስተኛ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ክትትል መደረጉ፤
- በሱማሌ ብሂራዊ ክልላዊ መንግስት ፤ የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት እና የድሬደዋ አስተዳደር የተለዩ ነባር ሼዶች ተረክቦና መሰረተ ልማትን አሟልቶ ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተላልፈው እንዲሰጡ አለመደረጉ፤
- በደቡብ ክልል ከአጠቃላዩ የክላስተር ብሎኮች ለአነስተኛ እና ለመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተላለፉት 204 ብሎኮች በህንፃ እና በኢንዱስትሪዎች እድገት ደረጃ ተለይቶ መረጃው እንዲያዝ አለመደረጉ፤
- በ2010 ዓ.ም. 640 ኢግዚብሽንና ባዛር በማዘጋጀት 25600 ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 256.000.000 የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም 211 ኤግዚቪሽንና ባዛር በማጋጀት 7588 ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ በማድረግ የብር 60.622.553 የገበያ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ በተዘጋጀ የኢግዚቪሽን ብዛት 32.9% በተሳታፊ

ኢንተርፕራይዝ በዛት 29.6% በተፈጠረ የገበያ ትስስር የገንዘብ ብዛት 23.6% ሲሆን፤ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤

- በ2010 በጀት አመት አዲስ 100 እና ነባር 395 ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የብር 204.160.559 እና 77.952.283 ኪሎ ግራም ናሙና እንዲያስተዋውቁና በቀጥታም ሆነ ከላኪዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እቅድ የተያዘ መሆኑንና አፈፃፀሙ 300 ነባር እና 206 አዲስ ኢንተርፕራይዝ ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን 208.075.467 ዶላር ዋጋ ያላቸው 19.304.097.30 ኪሎግራም የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ውጤቶች ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የተቻለ ቢሆንም አፈፃፀሙ በምርት ብዛት 25% ብቻ መሆኑ፤
- በየክልሎችና ዞኖች በከተሞች የሚገኙ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሌሎች ክልሎች ዞኖች እና ከተሞች ከሚገኙ ጋር እርስ በእርሳቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የሚያስችል አሰራሮችን በመዘርጋት አራቱን የግብይት ስርዓት ፍራንቻይዚንግ፤አውትግሮይንግ፤አውት ሶርሲንግና ሰብ ኮንትራክቲንግ እንዲጠቀሙ በማድረግ አፈፃፀሙን በአመት አንድ ጊዜ መከታተልና ግብረ መልስ የመስጠት ስራ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በአማራ፤ በትግራይ እና በደቡብ ክልል የተሰራ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ከተማ አስተዳደሮች ስራውን የሚተገብር አካል ባለመኖሩና ያለውም በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ኢንዱስትሪዎቹን ተጠቃሚ ማድረግ አለመቻሉ፤
- ወደ ኢምፐሪዩም የገቡ 95 ኢንዱስትሪዎች 6 ወር ሞልቷቸው ምርታቸውን ያስወጡት ኢንዱስትሪዎች 22 መሆናቸው አፈፃፀሙ 23% መሆኑ፤
- የ95 አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች በኢምፐሪየም ውስጥ ለእይታ በሚመች ቦታና ሁኔታ በመደርደር የብር 4.016.706.75 የምርት ሽያጭ ለማከናወን ታቅዶ የ53 ኢንዱስትሪዎች ምርት የብር 1.092.258.96 ሽያጭ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ በሽያጭ 27% ብቻ መሆኑ፤

- ስትሪንግ ኮሚቴው በተቀመጠለት የውይይት ፕሮግራም መሰረት እየተሰበሰበ አለመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በደቡብ በክልል ደረጃ 23 ተቋማትን ያካተተ በም/ርዕሰ መስተዳድሩ የሚመራ የማኑፋክቸሪንግ ድጋፍ ስቲሪንግ ኮሚቴ የተደራጀ ሲሆን የስቲሪንግ ኮሚቴው የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ሴክተር ተቋማት ለአስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ይሁንና የተዘጋጀውን ዕቅድ የጋራ በማድረግና በማፅደቅ ተፈራርመው ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፤
- በጋንቤላ በክልል ደረጃ 8 አባላት ያሉት የስቲሪንግ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም በስትሪንግ ኮሚቴው መካተት ያለባቸውን ተቋማት በአግባቡ በመለየትና የስትሪንግ ኮሚቴው አባል እንዲሆኑ እቅድ በማውጣትና የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ የዘርፉን የልማት ስራዎችን እየገመገሙአለመሆኑ፤
- በደቡብ ክልል በክልል ደረጃ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፍና የሚከታተል ስቲሪንግ ኮሚቴ አሁን ባለበት ሁኔታ ተደራጅቶ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማስተባበርና ለመደገፍ መቋቋም ያለበት ስትሪንግ ኮሚቴ በየትኛውም እርከን ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- የ2010 የዘጠኝ ወራት የጋራ እቅድ አፈፃፀም ላይ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የጋራ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ለማከናወን አለመቻሉ፣

ታውቋል፡፡

ሀ. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች

ሀ/ የ2010/11 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጐማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዕቅድና ክንውን ማጠቃለያ ሪፖርት

ተ.ቁ	የወኪል መ/ቤቱ ስም	የ2010/11 ዓመታዊ ዕቅድ (በቁጥር)			የ12 ወራት ክንውን ድምር (በቁጥር)			የ12 ወራት ክንውን በመቶኛ (%)
		PBS	ESPES	ድምር	PBS	ESPES	ድምር	
1	ምዕራብ ወኪል	30	6	36	34	2	36	100
2	ምሥራቅ ወኪል	37	1	38	27	2	29	76
3	ደቡብ ወኪል	69	3	72	53	1	54	75
4	ሰሜን ወኪል	54	6	60	52	2	54	90
5	ማዕከላዊ ወኪል	58	-	58	55	3	58	100
ጠ/ድምር		248	16	264	221	10	231	87.5

- በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 264 የ"PBS" እና የ"ESPES" ኦዲቶች የታቀዱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በበጀት ዓመቱ የ231 ኦዲቶች ተከናውኖ ሪፖርቱ ማለትም፡-
  - የ211 ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ሴክተር ቢሮዎች ለየብቻ ተዘርዝሮ፣
  - የክልሎች ዓመታዊ ኦዲት (9) በ2010 በጀት ዓመት የገንዘብ ሚ/ር (1) የ"PBS" ዓመታዊ ኦዲት ተጠቃልሎ፣ በድምሩ 10 ዓመታዊ ኦዲቶች እንዲሁም፣
  - የ10 ክልሎች የ"ESPES" ኦዲቶች
    - የፌደራል መንግስት የፋይናንስ እና በጀት አስተደደር ማኑዋል ማዘገጀቱን ማረጋገጥ
    - የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ም/ቤት የፋይናንስና በጀት ቋሚ ኮሚቴ አባላት በበጀት፣ በወጭ አስተዳደር እና በኦዲት ክትትል ላይ ስልጠና መውሰዳቸውን ማረጋገጥ እና

- የፌዴራል መንግስት ለክልል መንግስታት የሚመደበው በጀት ጭማሪ ማሳየቱን (ፐር ከፒታ) ማረጋገጥ በሚሉ 3 የማረጋገጫ ኦዲቶች ተጠቃልሎ

ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል፡፡

የ2010 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ዓመታዊ ኦዲት ከክልሎች እስከ ገንዘብ ሚ/ር ባሉ ደረጃዎች የተከናወነ ሲሆን ለዚህም፣

- ከስምንት ክልሎች (ከቤኒሻንጉል ክልል በስተቀር) እና ከድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር 55 ኦዲቶች፤ እንዲሁም
- ከፌዴራል የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ተቋማት 5፣

በድምሩ 60 ናሙናዎች ተወስደው ኦዲቶቹን በማከናወን ሪፖርቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ላይ ተጠቃልሎ በወቅቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

- በተጨማሪም በደቡብ ወኪል መ/ቤት የወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል ሀዋሳ በቆሎ ምርምር መለስተኛ ማዕከል የግንባታና ቢሮ ዕድሳት፣ በሰሜን ወኪል መ/ቤት ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የባቲ ዲስትሪክት አገልግሎተት መስጫ ማዕከል የአንድ ገንዘብ ያዥ ሂሳብ፣ በድምሩ 2 ልዩ ኦዲቶች ተከናውነው ሪፖርቶቻቸው ለጠያቂ አካላት ተልከዋል፡፡

? ????? ?

1) የእቅድ ክንውኑ ሲታይ፣
   - ከየወኪል መ/ቤቱ ሁለት ሁለት፣ በአጠቃላይ 10 ኦዲተሮች፣ መጋቢት/2010 ወሩን ሙሉ ሥልጠና ላይ ስለነበሩ፣
   - በደቡብ ወኪል መ/ቤት ከሰኔ 20/2010 ጀምሮ ኦዲተሮች ሂሳብ ለማወራረድ በወኪል መ/ቤቱ ቢሮ ስለነበሩ እንዲሁም በ2011 በጀት ዓመት መጀመሪያ (ሃምሌ ወር/2010) ላይ የሥራ ማስኬጃ በጊዜ ያልተላከላቸው እና ኦዲተሮች የዓመት ዕረፍት ላይ ስለነበሩ፣
   - ከሀምሌ/2010 ጀምሮ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ 12 ኦዲቶች በዕቅድ የተያዘላቸው 2 የደቡብ ወኪል መ/ቤት ኦዲተሮች ከዋናው መ/ቤት ልዩ ኦዲት ወደ ወኪል መ/ቤቱ ስላልተመለሱ እንዲሁም
   - ከጥቅምት/2011 አጋማሽ አከባቢ ጀምሮ ከ5ቱም ወኪል መ/ቤቶች 5 ኦዲተሮች፣ ከ2ቱ የወኪል መ/ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም ከጥር/2011 መጀመሪያ አከባቢ ጀምሮ ከሰሜን

ወኪል መ/ቤት 2 ኦዲተሮች እና የምዕራብ ወኪል መ/ቤት ኃለፊ ለልዩ ኦዲት ወደ ዋናው መ/ቤት በመምጣታቸው፣

የበጀት ዓመቱ ክንውን ከ100% ዝቅ ሊል (87.5% ብቻ ሊሆን) ችሏል፡፡

ለ/ <u>የ2010/11 'PBS' ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት</u>

<u>መግቢያ</u>፣

ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS) እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) ኦዲት ሲሆን፣ የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ፣ የESPES ኦዲት ደግሞ በገንዘብ ሚ/ር በተጠየቀ ጊዜ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት እና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር (PBS III) እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ እየተጠቃለለ የሚላከው ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2010/11 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው

በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃልለው በሚከተለው ሁኔታ ለዓይነት ቀርበዋል፡፡

<u>ጥሬ ገንዘብና ባንክ፤</u>

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግና ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ በተጨማሪም አልፎ አልፎ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በተደረገባቸው መ/ቤቶች በቆጠራውና በጥሬ ገንዘብ ምዝገባ ሚዛን መካከል ልዩነት (አንዱ ከፍ ወይም ዝቅ) የሚታይ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ በካዝና/ሣጥን ያለ ጥሬ ገንዘብ መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (በዴቢት መሆን ሲገባ በክሬዲት) ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ያለና ያልተተካ መሆኑ፣ ከዚህም ካለፉት ዓመታት ዞሮ የመጣ ጉድለት መኖሩ፣
- ከክልል ለወረዳ/ከተማ አስተዳደር ለሚተላለፍ የበጀት ድጎማ አልፎ አልፎ የገቢ ደረሰኝ የማይቆረጥ መሆኑ፣
- ባንክ ገቢ ለተደረገ ገንዘብ ህጋዊ ማስረጃ (ዴቢት አድቫይስ) የሌለ መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ቀሪ ቼክ (Check stub) በፈራሚዎች የማይፈረም ሲሆን የባንክ ሂሳብ ሚዛኑም በአግባቡ የማይሞላበት መሆኑ፣
- ከካዝና (ከሳጥን) በተንጠልጣይ የሚከፈሉ የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች በወቅቱ የማይወራረድ፣ አሊያም ወደ ሂሳብ ክፍል ዞሮ በተሰብሳቢ የማይያዝ መሆኑ እና ለረጅም ጊዜ ተከምሮ የሚቀመጥ መሆኑ፣ እንዲሁም እንዲህ ዓይነት ክፍያዎች አልፎ አልፎ ደጋፊ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ የጥሬ ገንዘብ መዝገብ ምዝገባ በገንዘብ ያገኙ ወቅታዊ አለመደረግ፣
- በካዝና ተቀምጦ ለጥቃቅን ክፍያዎች የሚውለው የገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት (petty cash system) ያልተዘረጋ መሆኑ፣ በፋይናንስ መመሪያ መሠረት ከሣጥን/ካዝና በጥሬ ገንዘብ መከፈል ከሌለበት የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ የሚፈጸም መሆኑ፣

<u>ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ፤</u>

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣ በተለይ በተሰብሳቢ በተያዘው ሂሳብ ውስጥ፡-
    - የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የሚገኝ መሆኑ፣
    - ተሰብሳቢ ሂሳብ እያለባቸው መ/ቤት የለቀቁ ሠራተኞች መኖራቸው፣
- አልፎ አልፎ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ ባልሆነ ሚዛን (ተሰብሳቢ በዴቢት መያዝ ሲገባ በክሬዲት፣ ተከፋይ ደግሞ በክሬዲት መያዝ ሲገባ በዴቢት) የተያዙ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ተቀጽላ ሌጀሮች ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ተከፋይ ሂሣብ ለተከፋዩ ያለ ማስረጃ የሚከፈል መሆኑ፣
- የተወሰኑ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የመነሻ ሰነድ ስለሌላቸው ባለቤቱ የማይታወቅ መሆኑ፣ ከዚህም ውስጥ ለዓመታት ሲንከባለል የመጣ ሂሳብ ያለ መሆኑ፣
- ሥራ ለመሠራቱ ማስረጃ ሳይያያዝ ማስተካከያ ተደርጎ የተመዘገበ የችሮታ ጊዜ ክፍያ መኖሩ፣

<u>ወጪዎች</u>፡

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- አልፎ አልፎ ሠራተኞች ቢሮ ሥራ ላይ ለመሆናቸው በሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ላይ ፈርመው እያለ የውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ በተፈቀደ በጀት ያልተያዙ ወጪዎች ተመዝግበው ሪፖርት የሚደረጉ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ወጪዎች የማይመዘገቡና ሪፖርት የማይደረጉ መሆኑ፣
- በአብዛኛው የውሎ አበል የመስክ ሥራ ከመሠራቱ በፊት ቀጥታ በወጪ የሚመዘገብና ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ፣ በተጨማሪም በድጋሚ እና በብልጫ የተፈጸሙ የውሎ አበል ክፍያዎች መኖራቸው፣
- አልፎ አልፎ የመያዣ ሂሳብ ከግንባታ ክፍያ የማይቀነስ መሆኑ፣

- አንዳንድ ጊዜ የውል ስምምነት የሚያስፈልጋቸው ክፍያዎች ያለ የውል ስምምነት የሚፈጸሙ መሆኑ፣
- የውሎ አበል ፎርምና ተመን (rate) በአግባቡ የማይሞላ መሆኑ፡
- በነዳጅና ቅባት ፍጆታ ላይ ጠንካራ የውስጥ ቁጥርጥር ስርዓት የሌለ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ግዥዎች ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈጸሙ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ወጪዎች ትክክለኛ ባልሆነ የሂሳብ መደብ የሚመዘገቡና ሪፖርት የሚደረጉ መሆኑ፡
- አልፎ አልፎ ክፍያዎች ያለ መጠየቂያ የሚፈጸሙ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ለቋሚ የመንግሥት ሠራተኞች ያለአግባብ የተፈጸሙ የማበረታቻ ክፍያዎች መኖራቸው፣
- ከአንዳንድ ወጪዎች ላይ የቅድሚያ ገቢ ግብር (withholding tax) ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የመ/ቤቱ ያልሆነ ተሽከርካሪ ለተጠቀመበት ነዳጅ ገንዘብ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፣
- በቼክ ለሚፈጸም ክፍያ አልፎ አልፎ ቀሪ ቼክ (check stub) ላይ የተቀባይ ስምና የወጪው ምክንያት የማይጠቀስ መሆኑ፣
- ሠራተኛ ሥራ ከለቀቀ በኋላ ለሠራተኛው የተከፈለ ደመወዝ መኖሩ፣
- የቅድሚያ ክፍያ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ፣

<u>**የሂሳብ ሪፖርት፡**</u>

- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው አካል አለመላካቸው፣
- አልፍ አልፎ የተጣራ ሀብት መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት መሆን ሲገባ በዴቢት) ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ፣

<u>**ንብረት፡**</u>

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች አለመቋቋም፣ በአንዳንዶች ደግሞ የንብረት ምዝገባ መቋረጥ፣
- ለቋሚ ዕቃዎችና የህክምና መገልገያዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

- ለንብረቶች ተገቢው አያያዝ የማይደረግ መሆኑ (ለምሳሌ ተገቢ የንብረት መጋዘን ካለመኖሩ የተነሳ ንብረቶች ባዶ ወለል ላይ ተበታትነው የሚቀመጡ መሆኑ)፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ እና አገልግሎት ከሚሰጡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለሥራ መቀመጣቸው፣
- ዓመታዊ የንብረት፣ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ቆጠራ የማይደረግና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘን መሆኑ፣ አልፎ አልፎ ቆጠራው በተደረገባቸው ደግሞ ቆጠራው ከምዝገባ ሚዛን ጋር አለመመሳከሩ፣
- በአብዘኛዉ መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎች አለመመዝገብ፡
- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በወቅቱ አለመወገድ እና አገልግሎት ከሚሰጡ መድኃኒቶች ተለይተው ለብቻ የማይቀመጡ መሆኑ፣
- በአብዘኛው የተሽከርካሪ ፕሮፋይል እና የባለቤትነት ደብተር ያለመኖር እና አልፎ አልፎ ታርጋ ቁጥር/ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች (በአብዘኛው ሞተር ሳይክሎች) መኖራቸው፣
- አልፎ አልፎ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ሳይለዩ የተመዘገቡ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ንብረት ያለ ትዕዛዝ ከንብረት ክፍል ወጪ የሚደረግ መሆኑ፣
- በአብዘኛው ኦዲት ተደራጊዎች ተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ አለመኖሩ፣
- በአንዳንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ንብረቶች ላልታወቀ አገልግሎት በውሰት በሚል ወጪ የሚደረጉና ለመ/ቤቶቹም ተመላሽ የማይደረጉ መሆኑ፣

<u>የበጀት አጠቃቀም</u>

- ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች የተመደበ በጀት አልፍ አልፎ መሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ወደአልሆኑ ሴክተሮች የሚዛወር መሆኑ፣

<u>የክትትል ኦዲት</u>

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚከድበት ወቅት ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ እና ተጨማሪ ድክመቶች መታየቱ፣

ሌሎች

- በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ ማስረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው የማይቀመጡ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና (በስብሰባ እና በተለያየ ጊዜ) መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣
- ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት
- የኃላፊዎችና የሥራ ሂደት ባለቤት ቶሎ ቶሎ ከቦታቸው መነሳት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ሐ/ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ዓመታዊ የሂሳብ ኦዲት የተሰጠ አስተያየት፣ ትኩራት የሚሹ ጉዳዮች እና በስራ አመራር አንቀጽ ሥር የተገለጹ ዋና ዋና ጉዳዮች

በ'PBS III' ፕሮጀክት 2010 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) ኦዲት ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር የሚል "ነቀፌታ ያለበት" (qualified, Except for) ሲሆን፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እና በስራ አመራር አንቀጽ ሥር ከተገለጹ በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

ትኩራት የሚሹ ጉዳዮች፣

- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሂሳብ በፌዴራል ደረጃ በተጠቃላለው የሂሳብ መግለጫ ውስጥ የታካተተ ቢሆንም በጸጥታ ችግር ምክንያት ሂሳቡን ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣

- ለሀራሪ ክልል ጤና ቢሮ የተመደበ በጀት ብር 437,797.50 ለተለመለት ዓላማ ከመዋል ይልቅ ወደ ሌላ መሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ላልሆነ ሴክተር ቢሮ የተላለፈ መሆኑ፣
- በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል ከጤና ቢሮ ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በባንክ በማስተላለፍ የተከፈለው ብር 399,802.00 ለተጠቃሚው ለመድረሱ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ወይም ሌላ ማረጋገጫ ያልቀረበለት መሆኑ፣ እንዲሁም በክልሉ ም/ቤት የአገር ውስጥ ስልጠና ክፊያ ብር 342,740.49 በሚመለከተው ወጭ አጽዳቂ አከል (ኃላፊ) ያልጸደቀ መሆኑ፣
- 25 የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ሠራተኞች ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ ለአዳማ ሆስፒታል ጤና ኮሌጅ ለተከፈለ ብር 1,000,000.00 የወጪው ደጋፊ ማስረጃ ማለትም ክፊያ የተፈጸመላቸው ሠራተኞች ሥም ዝርዝር እና ገንዘቡ ለኮሌጁ መድረሱን የሚያሳይ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከኮሌጁ ያልቀረበለት መሆኑ፣

<u>በሥራ አመራር ከተገለጹት በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ</u>

- በሁሉም ክልል ወረዳዎች፣ ከተማ እተዳደሮች እና የክልል መሰረታዊ አገልግሎት ሳጪ ሴክተር ቢሮዎች ከፍተኛ መጠን ያለቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ሳይወራረዱ/ ሳይሰበሰቡ/ ለረጅም ጊዜ ተወዝፈው መቀመጣቸው፣
- በሁሉም ክልል በአብዛኛው ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ነዳጅ የሚቀዳለቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ኪሎ ሜትርና ነዳጅ መቆጣጠሪ(ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፣
- በሁሉም ክልል ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና የክልል መሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር ቢሮዎች የግዥ አፈጻጸም መንግስት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት የማይፈጻም መሆኑ፡፡

ልዩ ኦዲት

በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች ትዕዛዝ፣ እንደዚሁ በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 11 /አስራ አንድ/ የል ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ በዚህም ምክንያት በመደበኛው የኦዲት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮብን አልፏል፡፡.

የተከናወኑትም ኦዲቶች፣

ሀ/ በሕጋዊነት ኦዲት-

1. የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ -የሳይበር ታለንት ማነጅሜንት ፕሮግራም
2. አዲስ ቪው ጀንራል ሰርቪስ ኃ/የተ.የግል ማህበር- 2001-2009 ዓመታት ከግብር አከፋፈል ጋር የተያያዘ
3. በገንዘብ ሚኒስቴር- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት፤
4. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት-

   5.1 አለም አቀፍ የስንዴ ግዥን የጨረታ ሂደት በተመለከተ

   5.2 የታብሌት ግዥን በተመለከተ

   5.3 የHP Computer ግዥን በተመለከተ

5. የብረታ ብረት ና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን-

   5.1 የህዳሴ ግድብ የደን ምንጣሮ የአገልግሎት ግዥ በተመለከተ

   5.2 የ114 የመኪና ግዥን የግዥ ሂደት በተመለከተ

6. የጂኦሴንቴቲክስ ኢንዱስትሪያል ወርክስ ኃ.የተ.የግል ማህበር- ከጎልደን ትሬዲንግ ጋር የተደረጉ ግዥዎች ፤ የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትለው ስለመፈጸማቸው፤

7. የወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል ሀዋሳ በቆሎ ምርምር መለስተኛ ማዕከል የግንባታና ቢሮ ዕድሳት፣

8. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የባቲ ዲስትሪክት አገልግሎት መስጫ ማዕከል የአንድ ገንዘብ ያዥ ሂሳብ፣

9. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ- ከፅዳት አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ

10. አንበሳ ባንክ/በፍ/በቤት ትህዛዝ- የአዳማ ልዩ ዞን ከ/ፍርድ ቤት ጠያቂነት በአንበሳ ባንክና በአንድ ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብን ጉድለትን በተመለከተ

11. ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር-- በጅዳ ሳዑዲ አረቢያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ፅ/ቤትና በኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ ማህበራት መካከል ከገንዘብ አስተዳደርና አያያዝ ጋር በተመለከተ

የ2010/2011 ኦዲት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. መግቢያ

የፌዴራልዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የብድርና እርዳታ ሂሣቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ወይም እንደሚያስደርግ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት መ/ቤቱ ኦዲት ከሚያደርጋቸው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሣቦች በሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ያስደርጋል፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መሰረት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለበላይ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች እንዳስፈላጊነቱ ማሳሰቢያ በመስጠት፣ ውጤቱን ከሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2010/2011 ኦዲት ዓመት /ከየካቲት 2010 እስከ ጥር/2011 ዓ.ም/ የኦዲት ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የደረሱን የመንግስት ልማት ድርጅቶችና በመንግስትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንዲደረጉ የተመደቡ 6 ባለበጀትና በከፊል ገቢ የሚሰበስቡ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ፣ እንዲሁም የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርቧል፡፡

2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2010 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ

2.1 <u>የኮርፖሬሽኑ ዓላማ</u>

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲቋቋም፣ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ኮርፖሬሽኑ በስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲመራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በቦርድ አስጸድቆ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

2.2 <u>የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት</u>

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው ክትትል እንዲያደርጉና አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

2.3 <u>የስራ ዕቅድና ክንውን</u>

ኮርፖሬሽኑ በ2010 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛቸውና ያከናወናቸው የሂሳብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

መግለጫ	የ2010 በጀት ዓመት			የ2009 በጀት ዓመት ሲነጻጸር	የ2009 ክንውን በመብለጥ(በማነስ)/
	ዕቅድ	ክንውን	ልዩነት/%	ክንውን	ልዩነት/%
ወጪ የተደረጉ ኦዲት ሪፖርቶች	244	232	(12)/(5%)	239	(7)/(3%)

ከላይ እንደተመለከተው የ2010 ክንውን ሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር በ12 ሪፖርቶች ወይም በ5% የሚያንስ ሲሆን፣ ከ2009 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነጻፀር በ7 ሪፖርቶች (3%) የሚያንስ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለዕቅድ ክንውኑ ልዩነት ዋና ምክንያቱ በቁጥር 28 ረቂቅ ኦዲት ሪፖርቶች ለደንበኞች ተልከው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምላሽ ያልተሰጠባቸው እና ሌሎች 41 ያህሉ በተለያየ ደረጃ በክለሳ ላይ የነበሩ ስራዎች ሲሆን፤ 18 ስራዎች በመካሄድ ላይ የነበሩ በመሆኑ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ወጪ የሆኑት 232(የአንድ መ/ቤት/ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ከአንድ በጀት ዓመት ሂሳብ በላይ ኦዲት የተደረጉት ለየብቻ ተቆጥረው ነው) ሪፖርቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው /Clean opinion/ 148፤ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆኑም ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Except for/ 38 ፤አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው/Disclaimer/ 38፤ ተቀባይነት የሚሳጠ 1 ድርጅት እና አስተያየት የማይሰጥባቸው ኢንተሪም ኦዲቶች 7 ናቸው፡፡

2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ

በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል 149 ሲሆን፣ በ2010 በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ 7 በድምሩ 156 ሰራተኞች ውስጥ በጡረታ የተገለሉ 6 እና በፈቃዳቸውና ልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ 14 በመሆኑ፣ በ2010 በጀት ዓመት መጨረሻ/ሰኔ 30/2010 ዓ.ም/ ላይ 136 ሰራተኞች በስራ ላይ እንደነበሩ ታውቋል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል በስራ መደብና ጾታ ሲተነተን ፕሮፌሽናል /ኦዲተሮች/ 90፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 46 ሲሆኑ፣ በፆታም ሲታይ ወንድ 86 እና ሴት 50 በድምሩ 136 ናቸው ።

2.5 የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ከሆነው የኦዲት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትንና ሀገርቱም በዚህ ሙያ ረገድ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ በመሆኑ፣በእንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው አሶሴሽን

ኦፍ ሰርቲፋይድ አከውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የኮርፖሬሽኑ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ የፈተና ዝግጅት ጊዜ፣ በገንዘብና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና በደመወዝ ጭማሪና በመሳሰሉት ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሰረት 16 ኦዲተሮች የመጀመሪያ ደረጃ/Fundamental stage/፣ 4 ደግሞ በፕሮፌሽናል ደረጃ/ ትምህርቱን በተለያየ ደረጃ በመከታተል ላይ ናቸው።

የኮርፖሬሽኑን ሰራተኞች የሙያ ብቃት ከፍ ለማድረግና የስልጠናውንም ጥራት ለማገዝ ባለው ዓላማ መሰረት የኮርፖሬሽኑ ቤተ መጽሐፍት ለተጠቃሚዎች ዘወትር በስራ ቀናት ክፍት በማድረግ እና እንዳስፈላጊነቱ ከ11፡30 በኋላ ፣ቅዳሜና እሁድ እና በበዕላት ቀናት ክፍት በማድረግና የሚያስፈልጉ መጻሕፍት በማቅረብ በአገልግሎቱ ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

የኦዲት ሙያ ያለቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፣ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሰጠው ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 <u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ</u>

በኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሂሣብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡

በ2010 በጀት ዓመት በእቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፣ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2010 የፋይናንስ እቅድና ክንውን/በብር/

መግለጫ	ገቢ	ወጪ	ያልተጣራ ትርፍ /ከታክስ በፊት/	የተጣራ ትርፍ /ከታክስ በኋላ/
ዕቅድ	38,938,847.00	31,737,765.00	7,201,082.00	5,040,757.00
ክንውን	35,831,029.00	28,566,900.00	7,264,129.00	5,084,890.00
ክንውን፤በመብለጥ (በማነስ)	(3,107,818.00)	3,170,865.00	63,047.00	44,133.00
ልዩነት በመቶኛ/%/	(8)	10	0.9	0.9

የ2010 የእቅድ ክንውን ከ2009 ጋር ሲነጻፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ ብር

የበጀት ዓመት	ገቢ	ወጪ	የተጣራ ትርፍ በመብለጥ(በማነስ)
2010	35,831,029.00	28,566,900.00	5,084,890.00
2009	34,967,369.00	25,952,955.00	6,310,090.00
ልዩነት የ2010 ክንውን በመብለጥ (በማነስ)	863,660.00.00	(2,613,945.00)	(1,225,200.00)
ልዩነት በመቶኛ/%/	2	(10)	(19)

የ2010 ገቢና ወጪ ሂሳብ ከ2009 ጋር ሲነጻፀር ገቢና ወጪው በሰንጠራዡ እንደሚታይ ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል:: የተጣራ ትርፍ ዕቅድ ክንውንም በስትራቴጂክ ዕቅዱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ኮርፖሬሽኑ የሚጠበቅበትን የትርፍ መጠን በመሸፈን ለስትቴጂክ ዕቅዱ ትግበራ ተጨማሪ ትርፍ የተገኘ መሆኑን የሚያመላክት ቢሆንም በ2009 ከተገኘው ትርፍ ጋር ሲነጻጸር በ 19% ያነሰ ነው፡፡

3. የ2010/2011 ኦዲት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከየካቲት1/2010 እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 65 ሲሆኑ፣

በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 170 በድምሩ 235(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡

በነዚህ ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 155 ፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 43 ፣አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 30፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የቀረበባቸው(Adverse) 1 ፣ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 5፣ልዩ ኦዲት 1 በድምሩ 235 ናቸው፡፡ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው መ/ቤቶች 18(አስራ ስምንቱ) የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ፣በዋናው መ/ቤት አንድ ላይ የተጠቀለለውን ብቻ በመውሰድ ግኝቶቻቸው በዚህ ሪፖርት ውስጥ በዝርዝር ተካቷል፡፡

4. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

በ2010/2011 ኦዲት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብለው ወይም የጎላ ችግር ስላለበት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታ እና ከአንድ በጀት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1 <u>አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው ድርጅቶች</u>

አቋም ሊወሰድበት ስላልተቻለ (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት መስጠት ያልተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና የኦዲት አስተያየትም ለመስጠት ያላስቻሉ ዋና ዋና ምክንያቶች/ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

4.1.1 <u>የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ</u>

ሰኔ 30/2006፤2007 እና 2008 ዓ.ም. የተጠናቀቀው የኤጀንሲው የ3 በጀት ዓመት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ የቀረበ ሲሆን፤ የቅርቡን የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ/ በግንባታ ሂደት ላይ ያለ ሂሳብ ውስጥ በጥቅሉ የተካተተው ሂሳብ ብር 10,0376,400.00 ከሁለት ዓመት ባላይ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አላሳየም፡፡ በመሆኑም በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሂሳብ ላይ በቋሚ ንብረት ሂሳብ ብር 581,539,395.00 በዚህ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

ለ/ በክምችት ዕቃዎች፡

- በተጠቃለለው የሀብት ዕዳ ሂሳብ መግለጫ በተመለከተው የክምችት እቃዎች ብር 10,144,537,847.00 ሂሳብ ላይ የተደረሰው በዴቢት ብር 47,419,869.00 እና በክሬዲት ብር 100,461,853.00 ማስተካከያ በማድረግ ነው፡፡ ይህም ማስተካከያ የተደረገበት ምክንያት የሂሳብ ምዝገባው፣ በፒችትሪ ሂሳብ አያያዝ ምዝገባው እና በዓመታዊ ቆጠራ ሂሳብ፤ እንዲሁም የኤጀንሲው የሕክምና መሳሪያዎች/ዕቃዎች መረጃ አስተዳደር ሥርዓት የክምችት መቆጣጠሪያ ምዝገባዎች (Helth Commodities Management Information System-HCMIS) መካከል የነበረውን ልዩነት ለማስታረቅ እንዲሆነ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በሁለቱ የምዝገባ ሥርዓቶች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት በግልጽ የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የተደረገውን ማስተካከያ ተዓማኒነት/እውነተኛነት ለማመንና ለመቀበል አስቸጋሪ በመሆኑ፣ የክምችት እቃዎች ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ (Revolving Drug Fund) እና በጤና ፕሮግራም ሂሳብ ውስጥ የተመለከተው ጊዜው ያለፈበት እና የተበላሸ ክምችት ዕቃዎች በአዲስ አበባ እና ጂማ ቅርንጫፍ ፤ እንዲሁም በዋና መ/ቤት ለሚገኙት የመጠባበቂያ ሂሳብ ያልተያዘለት ሲሆን፤ምን ያህል እንደሆነም ለመወሰን

ባለመቻሉ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ ሂሳብ ተለይተው የተመለከቱ ቢሆንም፣ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው በመሆኑ ምን ያህል መጠባበቂያ ሊያዝለት እንደሚገባ አይታወቅም፡፡ ከዚህም በላይ በጤና ፕሮግራም ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ (ከዓመታዊ ቆጠራ ጋር በመገምገም) አልተደረገለትም፣ በመሆኑም የተያዘው የክምችት ዕቃዎች መጠባበቂያ ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በጉዞ ላይ ያሉ የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ ዕቃዎች ሂሳብ ያልተለመደ ሚዛን (ክሬዲት) ብር 21,882,155.00 እንዴት ሊከሰት እንደቻለ፣በሂሳብ መግለጫዎች ላይም በዚህ መጠን ለምን እንደተገለጸ፣ በቂ ማብራሪያ አልተሰጠም፡፡ ከዚህም በላይ በጉዞ ላይ ያሉ የጤና ፕሮግራም ክምችት ዕቃዎች ብር100,792,756.00 ለረዥም ጊዜ የቆየ ሂሳብ ሲሆን ብር 88,353,477.00 ብቻ መጠባበቂያ የተያዘለት መሆኑ፣
- የክምችት(Stocks) ሂሳብ በዋና መ/ቤት ብር 21,926,020.00 እና በጂማ ቅርንጫፎች ብር 4,680,695.00 የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ስለሆነ፣ የተወገዱ ናቸው በሚል ከሂሳብ ምዝገባ ውጭ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተጠቀሰው መድኃኒት ክምችት ሂሳብ እንዲወገድ ማረጋገጫ የተሰጠበት ሰርትፊኬት ወይም የኮሚቴ ቃለጉባዔ ባለመቅረቡ በትክክል ስለመወገዱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በዚህ(ለ) ስር በተዘረዘሩት ጉዳዮች ምክንያት በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ በክምችት ዕቃዎች ሂሳብ ብር 10,144,537,847.00 እና በአጋር ድርጅቶች ፈንድ ሂሳብ ብር 31,170,156,574.00 ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ፣ እንዲሁም በገቢ ሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የተዘዋዋሪ ፈንድ የተጣራ ገቢ ሂሳብ ብር 529,300,172.00 ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ሐ/ በክምችት እቃዎች ውስጥ ያልተጣራና ለረዥም ጊዜ የቆየ ሂሳብ ከብር 8,956,112,025.00 በላይ ተካቷል፡፡ ይህም ሂሳብ እስከአሁንም እንዲጣራ ስላልተደረገ ትክክለኛ ሚዛን መሆኑንና ድርጅቱም በገንዘብ (በሀብትነት) ሊያገኘው እንደሚችል ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

መ/ በድርጅቱ ቅርንጫፎች መካከል ስለተደረጉ ሂሳብ ልውውጦች (inter-branch accounts)

- በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ ከተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ የተዘዋዋሪ ፈንድ ብር 374,466,353.00 እና የጤና ፕሮግራም ሂሰብ ብር 547,530,762.00 በቅርንጫፎች መካከል የሚታይ የሂሳብ ልዩነት (difference) ሲሆን፣ በመሰረቱ ይህ ሂሳብ ሲጠቃለል ዜሮ ሚዛን ማሳየት ነበረበት፡፡ በመሆኑም ስለልዩነቱ በቂ ማስረጃ እና ማብራሪያ ባለመቅረቡ በቅርንጫፎች መካከል ያለው ሂሳብ በትክክል ስለመገለጹ ለማመን ወይም እርግጠኛ ለመሆን አልተቻለም፡፡
- በዋና መ/ቤት፣ በጂማ፣መቀሌ እና ባህር ዳር ቅርንጫፎች የተያዙትን ለረዥም ጊዜ ለቆዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ለእያንዳንዳቸው የተያዘው መጠባበቂያ ሂሳብ ሲገመገም፣በኦዲተሮቹ አስተያየት መጠባበቂያው በብር435,427,229.00 የሚያንስ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጤና ፕሮግራም ተሰብሳቢ ሂሳብ በድርጅቱ በቆይታ ዕድሜው ያልተተነተነ ሲሆን፣የዋና መ/ቤትና የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር142,211,807.00 መኖሩ ቢታወቅም ምንም ዓይነት መጠባበቂያ ሂሳብ ያልተያዘለት ሂሳብ መኖሩ፣
- ያልተጣሩ ሂሳቦች(Suspense amounting) ብር966,596,978.00 በአብዛኛው በቆጠራ ወቅት የተገኘ የክምችት ዕቃዎች ጉድለት በሰኔ 30/2008 ቆጠራ ጊዜ የታየና ከዚያ በፊት ባሉት ዓመታት በተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ የተያዘ ነው፡፡ይህም ሂሳብ በጥልቀት ተጣርቶ በተገቢው ሂሳብ(Accounts) ውስጥ ማስተካከያ በወቅቱ ሊደረግለት ይገባ ነበር፡፡

በመሆኑም በ(መ) ስር ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ምክንያት የተነሳ በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 8,231,403,029.00 እና የአጋር ድርጅቶች ፈንድ (Donor's fund) ብር31,170,156,574.00 ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ወይም በትክክል ስለመገለጹ ለማመን አስቸጋሪ መሆኑንና በተጣራ ገቢ(Net Incime)

የተመለከተው የተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሳብ ብር 529,300,172.00 ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ሠ/ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚገኘው አንድ የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ ባንክ ሂሳብ በሰኔ 30/2008 ያልተለመደ ሚዛን (በክሬዲት) ብር 260,120,496.00 ያሳያል፡፡ በመሆኑም የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በትክክል ስለመገለጹ ለማመንም ሆነ ስለትክክለኛነቱ ለመግለጽ አልተቻለም፡፡

ረ/ የአጋር ድርጅቶች ፈንድ (Donors Fund) ሂሳብ በጥቅሉ ብር162,606,349.00 በዴቢት፣ ብር41,014,873.00 በክሬዲት ማስተካከያ ኦዲት በተደረገው በጀት ዓመት የተደረገ ቢሆንም፣የሂሳብ ማስተካከያዎቹ በበቂ ማስረጃ ላይ ያልተመሰረቱ በመሆኑ ፣የማስተካከያው አስፈለጊነት ላይ እርግጠኛ ለመሆን አልተቻለም፡፡

ሰ/ በተጠቃለለው የሀብትና እዳ መግለጫ

- ከተመለከቱት ውስጥ ተከፋይ ሂሳቦች ብር 762,427,617.00 የሚጣሩ የክምችት እቃዎች ጉድለት/በመብለጥ ተብለው በሰኔ30/2008 ቆጠራ ወቅትና ከዚያ በፊት የተከሰተ የተከፋይ ሂሳብ እንደሆነ ተመልክቶል፡፡ ሆኖም ይህ ሂሳብ በጥልቀት ተጣርቶ በተገቢው ሂሳብ(Accounts) ውስጥ ማስተካከያ በወቅቱ ሊደረግለት ይገባ ነበር፡፡
- በዋና መ/ቤት፣ እና በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየ ተከፋይ ሂሳብ ብር 1,242,156,826.00 መታየቱ እና ከዚያ ወዲህ ስላልተከፈለ፣ የኤጀንሲው ትክክለኛ እዳ ይሁን/አይሁን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በመሆኑም በ(ሰ) ስር ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ምክንያት የተነሳ በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ብር 3,055,101,791.00 ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ወይም በትክክል ስለመገለጹ ለማመን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

ሸ/ የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ አገልግሎት ገቢ ወደ ጤና ፕሮግራም በሚመዘገብበት ጊዜ በብር94,276,844.00 በስህተት ከፍ ተደርጎ በመያዙ

ምክንያት የተሰብሳቢ ሂሳብ እና የተጣራ ገቢ በዚሁ ያህል ያለአግባብ ከፍ ተደርጎል፡፡

ቀ/ በለፉት ዓመታት በተደረገው ኦዲት የተዘገው ሂሳብ የዚህ ዓመት መነሻ ሂሳቦች መካከል በተሰብሳቢ፤ በተከፋይ በስጦታ እና ፈንድ ሚዛን እንዲሁም በአጋር ድርጅቶች ፈንድ ሂሳብ ከፍተኛ ልዩነት ታይቶል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ሂሳቦች ትክክለኛ ነቸው ብሎ ለመቀበል እና በሂሳቦቹ ላይ እምነት ሊጣልበት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ጉልህ የሆኑ ግድፈቶች ምክንያት ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት አልተቻለም በማለት አቅርበዋል፡፡

ቀደም ባሉት ዓመታት የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር እና ለኤጀንሲው በጉዳዩ ትኩረት ለማስጠት በኦዲተሮቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የተቀሩት 4 በጀት ዓመታት ሂሳብም ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ እንዲቀርብ በቁጥር ቸመ 40/9 በ22/05/2010 እና ቀደም ባሉት ዓመታት በተመሳሳይ ማሳሰቢያ የተሰጠ ሲሆን፤ ሂሳቡን ወቅታዊ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን፤ችግሮቹም የቆዩና በርካታ በመሆናቸው ቀጣይ ባሉት ሂሳቦች ኦዲት ተስተካክለው እንደሚቀርቡ ገልጸው ኤጀንሲው ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት አሁን የሶስት በጀት ዓመት ከ2006 እስከ 2008 ኦዲት ተደርጎ የቀረበ ሲሆን፤ አሁንም የኤጀንሲው ሂሳብ ኦዲት በሁለት ዓመታት ወደኃላ የቀረ ነው፡፡

በመሆኑም ለጉዳዩ አሁንም የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ ለሕብረተሰቡ ጤና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎችን መንግሥት የሚያቀርብበት ዋነኛ መንገድ መሆኑ ታውቆ የኤጀንሲው የፋይናንስ እና መድኃኒት አስተዳደር ሕግን ተከትሎ በግልጽነት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሥርዓት እንዲመራ እንዲደረግ አስፈላጊ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ ወደኃላ የቀሩት ሁለት ዓመታት ሂሳብም በአፋጣኝ ሂሳቡ ተዘግቶ በዚህ ሪፖርት ላይ በተሰጡት ግኝቶች ላይ ተገቢ ማስተካከያዎች ተደርጎ እንዲዘጋጅና ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.1.2 የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት

የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት July 2017 እ.አ.አ የተጠናቀቀው ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ በሂሳቡ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻለ ገልጿል፡፡ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻለቸውም ጉዳዮች፡-

ሀ/ የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሁሉም ገቢዎች በትክክል ስለመመዝገባቸው ማረጋገጫ የሚሆን አይደለም፡፤ አንዳንድ የገቢ ደረሰኞች በዕዳ ተመዝግበው የሚታዩ ሲሆን ተገቢው ማጠራት አልተደረገለትም፤ ከዚህም በላይ ምዝገባዎቹ ከስሕተትና ሳይመዝገቡ ከመቅረት/መዘለል የጸዱ ስለመሆናቸው ቁጥጥር አልተደረገም፡፡ በመሆኑም በትርፍና ኪሳራ መግለጫው የተመለከተው ገቢ ሂሳብ ብር 5,565,513,772.00 ትክክል ስለመሆኑ የሚያሰምን ማረጋገጫ መግኘት አልተቻለም፡፡

ለ/ (1) በሀብትና ዕዳ መግለጫው በቋሚ ንብረት ሂሳብ ሥር ከውጭ ምንዛሪ መዋዠቅ የተነሳ የተጠራቀመው ኪሣራ (Capitalized losses) በግምት ብር 450,000,00.00 መያዙ ከመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎች ያፈነገጠ አሠራር በመሆኑና በሂሳብ መርሆዎቹ መሠረት ኪሣራው በወጪ ሂሳብ ውስጥ መካተት ነበረበት፤ይህም የዓመቱን ትርፍ /Year ended 7 july 2017 Financial Performance/ እና የተጣራ ሀብቱንም በዚሁ ልክ ይቀንሳል/ዝቅ ያደርጋዋል፡፡

(2) የቋሚ ንብረት ፤የተለያዩ ማሽነሪ፤ በሂደት ላይ ያሉ ስራዎች ሂሳብና የመሳሰሉት በርካታ የምዝገባ ስህተቶች የሚታዩበት ሲሆን፤ ሌላ በቂና አሰተማመኝ የኦዲት ማስረጃ ስላልቀረበ በሂደት ያሉ ስራዎችም አሁንም በሂደት ላይ ስለመሆናቸው፤ ማረጋገጥ አለመቻሉ፤ እነዚህ በሂዳት አሉ የተባሉት ስራዎች ቢጠናቀቁ ወደ ቋሚ ንብረትነት በመተላለፍ የእርጅና ተቀናናሽ ሊሰራላቸው ይገባ ነበር፡፡

(3) በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ በግምት ብር 3,600,000,000.00 ቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ (Advance) በተመለከተ በቂና

አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃ ያልቀረበለት፣ ይህም ሂሣብ ከገቢ ሂሣብ ጋር ወይም ከተሰጠ አገልግሎት ጋር የተጣጣ (Off set) ፤ካልሆነም ሊሰበሰብ የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጥ ወይም አጠራጣሪ ሂሣብ ስለመሆኑ፤

(4) በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ ብር 5,080,527,232.00 በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ያልቀረበለትና ለወደፊት ለድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያስገኝ የሚችል ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

(5) ከላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ምክንያት በሀብትና ዕዳ መግለጫ ሂሣቡ የተመለከተው ጠቅላላ የቋሚ ንብረት፤ማሽነሪ እና ሌሎች ዕቃዎች ሂሣብ ብር 33,384,346,957.00 በትክክል የተገለጸ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ሐ/ በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሣብ ውስጥ በግምት ጠቅላላው ብር 700,000,000.00 መሰብሰብ ስለመቻሉ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ያልቀረበለት፣ እንዲሁም በተሰብሳቢ ሂሣብ ውስጥ ያልተለመደ ክሬዲት ሚዛን ብር 1,100,000,00.00 በላይ የሚታይ ነው፡፡ በመሆኑም በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው ጠቅላለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር1,972,739,992.00 ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን/ለማወቅ አልተቻለም፡፡

መ/ በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የረጅም ጊዜ ዕዳ (non-current liability) ብር 3,576,964,271.00 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሊያወጣ የሚገባው(Contrnution by Ethiopian Electric Power) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ይኸው ዕዳ/መዋጮ/ በትክክል የድርጅቱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ሊቀርብ ስላልቻለ፤ እውነተኛ ዕዳ ስለመሆኑ የሚያሳምን ማስረጃ ለኦዲት ስላልቀረበ በትክክል ስለመገለጹ ማወቅ አልተቻለም፤

ሠ/ በሀብትና ዕዳ በረዥም ጊዜ ዕዳዎች ስር ምደባ ያልተደረገላቸው ተሰብሳቢዎች (unallocated collections) በሚል ብር 3,23,959,546.00 የተመለከተ ሲሆን፣ ይህም ሂሣብ ልዩ ልዩ የክሬዲት ሂሣብ ዝውውሮች በገቢ ሊያዙ የሚችሉ ሂሣቦች እስከ 2006 ወደኃላ የሚወስዱ ሂሳቦች ናቸው፤

በመሆኑም ይህ ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ዕዳውም በትክክል ስለመገለፁ የሚያሳምን በቂ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ስለሂሳቡ የኦዲት አስተያየት መሰጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልጿል፡፡ በዚህ በመጋቢት/2011 ዓ.ም ላይ የሂሳቡም ኦዲት በአንድ ዓመት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል ለሚመለከታቸው አካላት እና ለአገልግሎቱ በመ/ቤታችን ለተፃፈ ደብዳቤ ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስዱ በተገለፀው መሠረት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው የተሰጠን ምላሽ ቢኖርም ግኝቶቹ በመጠን ዕየገዘፉ ከመሄደቸው ውጭ በቂ ለውጥ አልታየም፡፡

በመሆኑም አሁንም በቀረበው ኦዲት ሪፖርት መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግና የቀረው የ2018 ሂሳብም ኦዲት ተደርጐ ሪፖርት እንዲቀርብ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

4.1.3 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን (የቀድሞ)

ሰኔ 30/2005 ዓ.ም የተጠናቀቀው የብረታ ብረትና ኢንጅሪንግ ኮርፓሬሽን ዋና መ/ቤት እና በሥሩ ከሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የ20 ሂሳብ መግለጫዎች እና የተጠቃለለ (conciliated accounts) በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፓሬሽን ኦዲት ተደርጎ የተገኘው ውጤት ቀርቧል፡፡

የኮርፓሬሽኑን ዋና መ/ቤት ጨምሮ ኦዲት ከተደረጉት ኢንዱስትሪዎች በአስራ ስምንቱ /በ18 ኢንዱስትሪዎች/ ሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት መስጠት እንዳልተቻለ እና የተጠቃለለውም ሂሳብ መግለጫ ላይ አስተያየት መስጠት አለመቻሉ በኦዲተሮቹ ተገልጿል፡፡ የአሁኑ ሂሳብ ኦዲትም በ5 ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በተመለከተም፡-

- ለኦዲቱ ሥራ እምነት ሲጣልበት የሚችል ለሂሣብ ምዝገባው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በኮርፖሬሽኑ ባለመዘርጋቱ፣ የተመዘገበውን ሂሣብ ለማጣራት ሌላ

አማራጭ የኦዲት ዘዴ ባለመኖሩ የተዘመዘገቡት ሂሣቦች ወይም ሁሉም የሂሣብ እንቅስቃሴዎች የተመዘገቡና ትክክል ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ ከዚህም በላይ ከተጠቃለለው የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ የኮርፖሬሽኑ የውስጥ እርስ በርስ የሂሳብ ልውጦች (Intra-Corporation balances) ከተጠቃለለው ሂሳብ እንደዋዋጡ አልተደረገም፤ ይህም ተቀባይነት ካለው የዓለም አቀፍ ሂሳብ አያየዝ መርሆዎች የፈነገጠ ነው፡፡

- ለኦዲቱ ሥራ እምነት ሲጣልበት የሚችል ለሂሣብ ምዝገባው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ለቋሚ ንብረቶች፤ማሽነሪእና ተቀሳቃሽ ሀብት በኮርፖሬሽኑ ባለመዘርጋቱ፣ በሐብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ሂሣብ ብር 3444359103.00 ትክክለኛነት ለማጣራት ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴ ባለመኖሩ ወይም የሂሣብ ማስተካከያ ያስፈልገው እንደሆነ እና በትክክል የተመዘገበ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው ሂሳብ የማይዳደስ ሀብት (Intangible Asset) ተብሎ ብር 105,135,106.00 እና ለወደፊት የተያዘ ወጪ (Deferred expenditure) ብር 64,030,993.00 በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃ ባለመቅረቡ ከየትኛው ሀብት ጋር ተያያዥ እንደሆነና የተመለከተው ሀብት ትክክል ስለመሆኑ ወይም በአግባቡ ስለመገለፁ ማረጋገጥ ባለመቻሉ እና ከምን እንደመነጨና ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በክምችት ዕቃዎች አያያዝ፣ አመዘጋገብ ላይ በቂና አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ በሀብትና ዕደው መግለጫ ውስጥ የተመለከተው የክምችት ሂሣብ ብር12,771,904,617.00 ትክክል ስለመሆኑ፣ ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴ ባለመገኘቱ፤በሂሣቡ ላይም አስፈላጊ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በተሰብሳቢ ሂሣብ አያያዝና አመዘጋገብ ላይ በቂና አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫ የተመለከተው ብር 5,500,749,769.00 ለበርካታ አመታት የቆዩ፤ በርካታ ሂሳቦቹ ውስጥ ያልተለመደ ሂሳብ ሚዛን(ክሬዲት) የሚያሳዩ ፤በቂ ትንተና ያልተደረገላቸው፤ ይህም ሂሳብ በሙሉ ሊሰበሰብ የሚችል ስለመሆኑ፣ በቂና አስተማመኝ መረጃም

ባለመቅረቡ በሂሣቡም ላይ አስፈላጊ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫው የተመለከተው ብር 50,914,910,840.00 እና ብር 61,058,352,280.00 በተዛማጅ አካላት (Related parties) ሂሣብ የተመለከተ ነው:: ይህ ሂሣብ በኮርፖሬሽኑና፣ በሥሩ ባሉት ኢንዱስትሪዎች መካከል የተደረጉ የሂሣብ ትልልፎችን (Interfund Balances) የሚያመለክትና አንዱ ሌላውን የሚያጣፋ (Cancel out) መሆን ነበረበት፡፡ ሆኖም በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫዎች ላይ ብር 10,143,441,440.00 ልዩነት ለብቻው በተከፋይ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን፤ በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ሊቀርብ፤ ሌላ የኦዲት ዘዴ ለመጠቀም ባለመቻሉ፣የተገለጸው ሂሳብ ትክክለኛነት ለማመን አልተቻለም፡፡
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው ውስጥ ጠቅላላ የተጠራ ሀብት(Equity) ብር3,733,334,183.00 እና ቀድም ባሉት ዓመታት ሂሳቦች ማስተካከያ(prior Years Adjustments) ተብሎ ብር 1,526,402399.00 ተደርጎለት የተደረሰበት ሂሳብ ነው፡፡ ሆኖም ስለማስተካከያ ሂሣቡ በቂና አስተማማኝ ማስረጃም በሆነ ማብራሪያ ሊቀርብ አልቻለም:: በመሆኑም የካፒታል ሂሳብ፤የመጠበበቂያ ሂሳብ፤ እና የተጠራቀመ ትርፍ ጠቅለላ ሐብትን የሚያመለክቱት በትክክል ስለመመዝገባው ለማመንም ሆና ለመውሰድ እና በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለው ተፅዕኖም በግልጽ ለማወቅ አልተቻለም፡፡
- ከተከፋይ የትርፍ ግብር ሂሳብ ላይ የተቀነሰው ብር 229,367,485.00 በቂና አስተማማኝ ማስረጃም በሆነ ማብራሪያ ሊቀርብ አልቻለም:: ከዚህም በላይ የቆየ ታክስ ዕዳ ተከፋይ ሂሳብ በሰኔ 30/2004 እና ሰኔ 30/2005 ሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው መካከል ብር37,437,379.00 ልዩነት የሚታይ ሲሆን፤ ይህንን ልዩነት በተመለከተ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ ወይም ከሂሳብ መግለጫ ማብራሪያ ላይ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ የዓመቱም የትርፍ ግብር ታክስ በትክክል አልተሰላም፤በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ ላይም ተገቢው ማስተካከያ አልተደረገም፡፡ በመሆኑም የትርፍ ግብር፤ የቆየ ታክስ ዕዳ በሐብትና ዕዳ

መግለጫው የተመለከቱት በትክክለኛው መጠን ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻልም፡፡

- ለኦዲቱ ዓለማ እምነት ሊጣልበት የሚችል የውስጥ ቁጥጥር በየኢንዱስትራዎቹ የሽያጭ ሂሣብ ላይ ባለመኖሩ፣ ወይም ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴም ባለመገኘቱ በትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መግለጫው ላይ ለተመለከተው የሽያጭ ሂሣብ 6,517,527,250.00 እና የሽያጭ ጭዎች ሂሳብ ብር5,070,751,363.00 ትክክለኛነት እና በሂሳቦቹም ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በኮርፖሬሽኑ ሊከሰቱ ስለሚችሉ የመጠባበቂያ ዕዳዎች እና ቃል ስለተገባላቸው ጉዳዮች ከስራ አመራሩ መገለጽ ስላለባቸው ጉዳዮች የተሰጠ መረጃ የለም፡፡ ተቀባይነት ባለቸው ዓለም አቀፍ የሂሳብ አያየዝ መርሆዎች መሰረት ይህ መረጃ በሂሳብ መግለጫዎቹ ማብራሪያ ውስጥ ተካቶ ሊቀርብ ይገባል፡፡

ከላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ወሳኝና ጉልህነት የተነሳ፣ የኦዲት አስተያየት ለመስጠትም በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃዎች ባለማቅረባቸው በተጠቃለለው የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ ሪፖርት ላይ አስተያየት መስጠት አልቻልንም በማለት ኦዲተሮች ገልጿል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ለኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ፤ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፤ ለኮርፖሬሽኑ፤ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተገቢው እርምጃ እንድወሰድ በደብዳቤ የገለጽን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከሚዘጋጅበት ቀን ድረስ እርምጃ ስለመወሰዱ ለመ/ቤታችን የደረሰን መረጃ የለም፡፡

4.1.4 <u>የመንግሥት ቤቶች ኮርፖሬሽን</u>

ሰኔ 30/2008 ዓ.ም የተጠናቀቀው የቀድሞ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ/የአሁኑ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን/ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጕ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

- በሀብት ዕዳ መግለጫው በተሰብሳቢነት የተመለከተው በጠቅላላው ብር 326,619,23.00 ለበርካታ ዓመታት የቆየ ሲሆን፤ ከዚህም በተጨማሪ ብር 22,472,069.00 ከሰራተኞችና ሌሎች ተሰብሳቢዎች ለረዥም ጊዜ ሳይሰበሰቡ የቆዩ

ሂሳቦች መኖራቸው፤እነዚህ ሂሳቦች በእውነት ሊሰበሰቡ የሚችሉ ስለመሆናቸው እና ባለዕዳዎቹንም በሕግ አስገድዶ ለማስመለስ ስለመቻሉ ለማመን አስቸጋሪ በመሆኑ፤

- በሀብት ዕዳ መግለጫው በተሰብሳቢነት ከተመለከተው ውስጥ ብር 34,852,689.00 ለተለያዩ ኮንትራክተሮች ቅድሚያ ክፍያ በሚል ለበርካታ ዓመታት የቆየና ወደ ሕንፃ ሂሳብ ያልተካተተ ወይም በግንባታ ሂደት ላይ ወዳለ ሂሳብ ያልዞረ በመሆኑ፤ ወደ ሕንፃ ሂሳብ ገብቶ የእርጅና ተቀናሽ ሊሰላለት የሚገባው ምን ያህሉ እንደሆነ ባለመታወቁ የተጣራ ትርፉን ለወሰን አዳጋች በመሆኑ፣
- በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ላይ የተመለከተው ያልተለመደ ሚዛን (Negative balance) ብር 9,569,559.00 መቼና እንዴት ሊከሰት እንደቻለና በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሚዛን ብር 565,803,260.00 ላይ ለመድረስ ይህው ያልተለመደ ሚዛን ሂሳብ ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠው በመሆኑና ባጠቃላይ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቡ ትክክለኛነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ፣
- በባንክ ሂሰብ ማስታወቂያዎች ላይ የተመለከቱት የተለያዩ ወጪዎች በጠቅላላ ብር 5,265,693.00 እና በጠቅላላ ብር 4,580,138.00 ባንክ ገቢ የሆነ በኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ለምን እንዳልተመለከተ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣እንደዚሁም የተለያዩ ወጪዎች ከብር 312,089.00 በላይ እና ባንክ ገቢ የሆነ ሂሳብ ከብር 1,352,016.00 በላይ በኤጀንሲው ያልተበዘገበ በመሆኑ፤ በሳጥንና ባንክ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ፤ ከሆነም በምን ያህል እንደሆነ ለመገመት አለመቻሉ፤
- ኤጀንሲው በሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ላይ የዘረጋው የውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ፤ሌላ ሊታመንበት የሚቻል አሰራር ባለመኖሩና ይህንን ለማጠራት ሌላ የኦዲት አሰራር/ዘዴ ባለመኖሩ የተመዘገበው ከኪራይ የተሰበሰበ ገቢ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሌሎች ገቢዎች የተካተተውና በሂሳብ መግለጫዎች ማብራሪያ ቁጥር 14 የተመለከተው ብር 40,770,946.00 ከፈረሱ መኖሪያ ቤቶች የተገኘ ካሳ የሚል

ቢሆንም፤ ከዚህ ሂሳብ ውስጥ በጠቅላለው ብር 34,585,081.00 የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ብቻ ስለቀረበለት በቂና አስተማመኝ ደገፍ ሠነድ ያልቀረበለት ነው፡፤ በመሆኑም ይህንን የካሳ ሂሳብ ኤጀንሲው በሙሉ በሙሉ ስለመመዝገቡ እርግጠኛ መሆን አልተቻለም፡፡

በመሆኑም በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የዓለም አቀፍ የሂሳብ አሠራር ደረጃዎች ተከትሎ ስለመዘጋጀታቸው በተጠቀሱት ምክንያቶች በቂና አሳማኝ መረጃ ባለማግኘታቸው አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ መሠረት እነዚህና ሌሎች በሪፖርቱ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ እንዲገለጽልን፤ለኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድና ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጠይቆ በተሰጠ ምላሽ ኮርፖሬሽኑ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት መርዓ-ግብር ማዘጋጀቱንና በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ማስተካከያ ስለወሰደ/በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ ለውሳኔ ስላቀረበ/ በቀጣይ ሪፖርቶች ተመሳሳይ ግኝቶች እንደማይከሰቱ ጠቅሶ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ማስተካከያዎች እንደሚደረጉ ተቅሷል፡፡ የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ ኦዲት በሁለት ዓመት ወደኃላ የቀረ ሲሆን የ2009 በኦዲት ላይ ፤ የ2010 በጀት ዓመትም ኦዲት እንደዲደረግ ረቂቅ የሂሳብ መግለጫዎቹ ለሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደቀረበ ተገልጿል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ሪፖርቱ የተጠቀሱት ችግሮች ተቀርፈው የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ እንዲስተካከልና ወደኃላ የቀረውና ለኦዲት የቀረበው ሂሳብም ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.2 ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው

4.2.1 የግዮን ሆቴሎች ድርጅት

June 30/2017 እ.አ.አ የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሣብ በዘመድሁንና ኩባንያው የተፈቀደለት ኦዲተር ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው ኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

በሀብት ዕዳ መግለጫው የተመለከተው በድምሩ ሀብት ብር 19,956,219.00 እና ዕዳዎች በድምሩ ብር 2,649,453.00 የድርጅቱ ሀብት እና ዕዳ /ግዴታ/ ያልሆነ ሂሣብ የተካተተ በመሆኑ፤ ይህም ከዓለም አቀፍ የሂሣብ ደረጃዎች ያፈነገጠ በመሆኑ ሥራ አመራሩ እናዚህን በሀብትና ዕዳው መግለጫዎች ውስጥ በመካተታቸው በሂሳብ ሪፖርት የተመለከቱት በተጋነነ/ከፍ ባለ መጠን በመሆኑ፡

- የድርጅቱ ስራ አመራር የተለያዩ ደብዳቤዎች ለቀድሞ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር እና ለቀድሞ የኢንዱስትሪ ሚ/ር የተጻጻፈ መሆኑ ቢገለጽም ጉዳዩ ምንም እልባት ስላላገኘ፤

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የሂሣብ መግለጫዎቹ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ዝግጅት ደረጃዎች መሠረት ስላልተዘጋጁ የድርጅቱን ሀብትና ዕዳ የሥራ አፈፃፀም እና የገንዘብ ፍሰት በትክክል አያስዩም በማለት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

መ/ቤታችን ድርጅቱ እና የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱና ማስተካከያ እንዲደረግ በማለት ባለፉት ጊዜያት ለጻፍነው ደብዳቤ ድርጅቱ በሰጠው መልስ ሂሣቦቹ ቀደም ሲል በድርጅቱ ሥር ይተዳደሩ ከነበሩትና አሁን ወደግል ይዞታ የዞሩት ሆቴሎች ሂሣብ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለፅ ማስተካከያ ለመድረግ መርዓ ግብር አዘጋጅቶ የላከ ቢሆንም አሁንም ተገቢው ማስተካከያ አልተደረገም፡፡

በመሆኑም የድርጅቱ ሀብት ወይም ዕዳ ያልሆኑትን ሂሣቦች በማጥራት ከሂሣብ መግለጫዎች ማውጣትና ትክክለኛ የድርጅቱን ገጽታ የሚያሳይ ሂሣብ መግለጫዎች ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

5. ስለመንግስት ልማት ድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ፣ ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

5.1 <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ</u>

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ በመዝገብ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ ሳይይደረግ ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙበት መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለንብረትና ሂሳብ ምዝገባዎች የተለያዩ ሶፍትዌሮችን የሚጠቀሙ መኖራቸውና በአንዱ ሶፍትዌርና በሌላኛው፤ እንዲሁም በቆጠራውና በሶፍትዌሩ ሂሳብ መካከል ከፍተኛ ልዩነት ሲታይ የችግሩ መንስዔ በትክክል ሣይጣራ፤ የፈለጉትን አንዱን ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙ መሆኑ፡
- በአንዳንድ ድርጅቶች በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ ያልተካሄደና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

- አንዳንድ ድርጅቶች በጉዞ ላይ ያለ ንብረት ሂሳብ እና በሂዳት ላይ ያለ ንብረት /ለምሳሌ ግንባታ ሊሆን ይችላል/ በሚል የቆሚ ንብራት ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎቻቸው ላይ የሚያሳዩ ለበርካታ ዓመታት በዚሁ ሂዳት የሚታይ የአንዳንዶቹ እያጨመረ የመሄድ ሁኔታ የሚታይ ሲሆን፤ ስለጉዳዩ በበቂ ማስረጃ የተደገፈና ትክክለኛነቱን በአስተማማኝ የሚያሳይ አለመሆኑ፤

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2 <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ ክምችት እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ ሳያደርጉ ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙ መሆኑ፤

- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሚልተው የማይመዘግቡና የምዝገባ ስህተቶች/ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በጊዜያዊነት/Suspense Account/ የሚይዙ መሆኑ፣

- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም ለምርት ግብዓት ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.3 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋግሩ ተሰብሳቢው እየጨመረና ጊዜው እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ባለዕዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት/ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት በአብዛኛው የማይሳካ መሆኑ፤
- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአሰጣጡ ወይም፤ አፈቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው፣ መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለዕዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡
- በአንዳንድ ድርጅቶች በተዛማጅ አካላት (Related parties) ሂሣብ በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፎች/ በሥሩ ባሉት ኢንዱስትሪዎች መካከል የተደረጉ የሂሣብ ትልልፎችን (Interfund Balances) የሚያመለክትና አንዱ ሌላውን የሚያጣፋ (Cancel out) መሆን የነበረበት፡ በልዩነት ለብቻው በተሰብሳቢ/በተከፋይ እንዲታይ እየተደረገ በቂና አስተማማኝ የማይያዝለት መሆኑ፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ፤ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛ የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

5.4 በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፤ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፤ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣

- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ አንዳንዶቹ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ምንም ማስረጃ የሌላቸው፡ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

5.5 ተከፋይ ሂሳቦች

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም

ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በወቅቱ እንዲከፍሉና ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

5.6 <u>ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉት ቁጥጥር አናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፣ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፣ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፣ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

6. በመንግሥትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በመንግሥትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሲሆን፣ በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠረት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈት እና ለተከፈቱ ሂሳቦችን በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሳብ ማሳወቂያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣
- ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣ የታየ ልዩነትም ሲኖር ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ፤
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽና በወቅቱ እንዲወራረድ አለማድረግ፤
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፤
- የአንዱን በጀት ዓመት ፕሮጀክት ወጪ ሂሳብ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የፕሮጀክት ሂሳብ መዝገብ ያለመቋቋማቸው፣አልፎ አልፎም ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎቹን ለኦዲት አለማቅረብ፣የሂሳብ ማስረጃዎች አያያዝና ፋይል አደራረግ ደካማ መሆን፤
- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠንና በፈፃሚ መ/ቤት ወይም ቅ/ጽ/ቤት ገቢ የሆነው/ የተመዘገበው ሂሳብ መካከል አልፎ አልፎ ልዩነት መኖሩና የተላለፈውም ገንዘብ ስለመድረሱ ማረጋገጫ የማይሰጥ ወይም በደረሰኝ ገቢ እንዲሆን የማይደረግ መሆኑ፣ በፈጻሚ መ/ቤትና ፈንድ አስተላለፊ ድርጅት/መ/ቤት መካከል ወቅታዊ የሂሳብ መረጃ ልውውጥ አለማድረግ፤
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣

- ከፕሮጀክት ሂሳብ ላይ ያለበቂ ምክንያት/የፕሮጀክቱ ባለቤት ይሁንታ ውጭ ለሌላ ተግባር ወጪ ማድረግና ክፍያውም አልፎ አልፎ ከተተመነው በላይ መሆን፡
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ሂሳብ የሚካሄዱ ስብሰባዎች/ወረክሾፕ/ የተሳታፊዎች ዝርዝር የማይያዝ፤ ተሳታፊዎች ከመጡበት መ/ቤት/ድርጅት እንዲሳተፉ የተወከሉ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ የማይያዝና ተሳታፊዎች በተሰተፉበት ጊዜያት የሰዓት መቆጣጠሪያ የማይያዝ/ የማይቀርብ መሆኑንና አልፎ አልፎ ለስልጠናው ቆይተዋል ከተባለው ቀናት በላይ የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ የሚገኝ መሆኑ፤
- ከስልጠናና ወርክሾፕ ፕሮግራሞች ጋር በተያየዘ አስፈለጊ መረጃዎች ማለትም ስልጠናው /ወርክሾ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ፤ የት ቦታ እንደተካሄደ፤ የሚገልጽ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዶች ጋር ያለመያያዝ፤
- በፕሮጀክት ሂሳብ ለተገዙ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ከአቅራቢዎች የሚሰጥ ደረሰኝ በፕሮጀክቱ ስም እንዲዘጋጅ አለማድረግ፤
- በኘሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ንብረቶች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣
- በውስጥ ኦዲተሮች ሊታዩና ሊስተካከሉ የሚችሉ ጥቃቅን ግድፈቶች ጭምር የሚታለፉና የውስጥ ኦዲተሮች የፕሮጀክት ሂሳብን በኦዲታቸው የማይሻፍኑ እና በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት የተደረጉ ግኝቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድና ተመሳሳይ ግኝቶች በተደጋጋሚ የሚታዩ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ ሂሳብ አያያዝ የተመለከቱት ችግሮች እንዲስተካከሉ በየኦዲት ሪፖርቶቹ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን፣የየፕሮጀክቶቹ ፈጻሚዎች ችግሮቹን ሊያስተካክሉትና የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ስለተግባራዊነቱ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።

7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሂያቸው

30.1 <u>የችግሮቹ ምክንያቶች</u>

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- በውስጥ ኦዲተሮች ስራውን በጥልቀት ያለመከታተልና በሚያቀርቡት ግኝቶች ላይም እርምጃ አለመውሰድ፡
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ለሂሳብ ስራው በቂ ትኩረት አለመስጠትና በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

30.2 <u>ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች</u>

የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣ የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ቅልጥፍናና የውጤት ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣ ያስችላል፡፡

በመሆኑም፡

- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት በተሟላ፤ ሁኔታና በእንክብካቤ አመቺ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡና በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርቡ፡

- ለማንኛውም የድርጅቱ ንብረት በማንኛውም ጊዜ ኃላፊና ተጠያቂው ግለሰብ ማን እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅበት ዘዴ እንዲቀየስ፡ለግለሰቦች ተደራራቢ ተግባርና ሃላፊነት በመስጠት ለምዝበራ አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር በተለይ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፤ በንብረትና ገንዘብ አጠባበቅ ረገድ የማያሻማ ግልጽ የሆነ ስራ ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፤
- ከውስጥና፤ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም በኦዲት ሪፖርቶች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

8. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች

በመ/ቤታችን እስከ መጋቢት 30/2010 ዓ.ም ባለው መረጃ መሰረት ከ1 ዓመት በላይ ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ 48 የመንግስት ልማት ድርጅቶችና እንዳሉ ታውቋል፡፡/ ዝርዝራቸው በአባሪ-37 ተመልክቷል/

በመሆኑም እነዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።